በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሂዩማኒቲ

ቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅህኖ፣ በምዕራብ ሸዋ አካባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ተካልኝ ለማ

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሂዩማኒቲ

ቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅህኖ፣ በምዕራብ ሸዋ አካባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

በ 9ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ተካልኝ ለማ

አማካሪ

ዶክተር ሴይመ ከበደ

በተግባራዊ ስነ-ልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማስተማር መርሀ-ግብር የፍልስፍና ዶክተሬት ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2009 ዓ/ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሂዩማኒቲ**

**ቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅህኖ፣ በምዕራብ ሸዋ አካባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት**

**በ**

**ተካልኝ ለማ**

2009 ዓ/ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

የአማካሪ ስም ፊርማ

………………………………… ……………………

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

……………………………………… ………………………

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

………………………………….. ……………………….

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ላደረሰኝ ለእየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማሪያም ምስጋና ይሁን:: ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ሳካሂድ አቅጣጫዎችን በማመላከት፣ ስህተቶቼን በማረምና በማስተካከል ሙያዊ ድጋፋቸውን በመለገስ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ዶ/ር ሴይመ ከበደ የማቀርበው ልባዊ ምስጋና በእጅጉ የላቀ ነው::

ለዚህ ጥናት በተለያየ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለስራዬ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው:: ከነዚህ መካከል:- አቶ ደረጀ አጥናፉ ላደረክልኝ ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍና እገዛ ምስጋናዬ ከልብ ነው:: የሚዛን ቴፒ ዩንቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተጠሪ የነበረው አቶ ውቤ ታደገ ላደረገልኝ የማቴሪያል ድጋፍና ችግሮቼን ስለሸፈነልኝ እመ ብርሀን በህይወቱ ሀሉ ትከተለው:: ዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት፣ ዶ/ር ፍቅሩ ወ/ኪዳን፣ ዶ/ር አማረ ሞላ፣ ዶ/ር ዘውዱ መብሬና አቶ ደጀኔ አካዩ ፅሁፌን አንብባቸው ለሰጣችሁኝ ገንቢ አስተያት ምስጋናዬ ከልብ ነው::        እንዲሁም የሚዛን ቴፒ ዩንቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተጠሪ ወ/ሪት ፀዳለ ታደሰ ላደረግሽልኝ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ምስጋናዬ ይድረስሽ::

ይህን ጥናት ሳካሂድ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር ላደረጉልኝ የኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አዱኛ ጫካ እንዲሁም ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ ስለሺ ተፈራ መምህር ዳምጠው ፍቅሬ፣ የጥናቱን ተተኳሪዎች ያስተማረልኝና በሁሉም መስክ እገዛ ላደረገልኝ መምህር ጎይቶም ካህሳይ፣ መምህርት ድንቅነሽ ወ/ጻዲቅ በጥናቱ ተሳታፊዎች ለነበሩት የኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ “A” እና “F” ክፍል ተማሪዎች ምስጋናዬ የላቀ ነው::

ባሳለፍኩት የትምህርት ጊዜ ሁሌም ከጎኔ ላልተለዩኝና ድጋፍ ላደረጉልኝ ቤተሰቦቼ፣ ባለቤቴ ወ/ሮ በላይነሽ ገመቹ፣ ልጆቼ መአዛና አማኑኤል ተካልኝ፣ ለእናቴ ወ/ሮ ዘለቀች ገቢሶ፣ ለወንድሜ መምህር ታደሰ ለማ፣ እህቴ ሰርካለም ገመቹና ባለቤቷ አቶ ተመስገን አበልቲ፣ አቶ ፀጋዬ ተስፋዬና ባለቤቱ ሀና አስራት  በሞት ለተለየኝ ወንድሜ ጥላሁን ተፈራ ለወንድሜ አያሌው መኮንንና ባለቤቱ ሰናይት ይገዙ  ልባዊ መስጋናዬ ይድረሳችው::በመጨረሻም ይንን ፅሁፍ ለተየበችልኝ ወ/ሮ ሃና ማሞ ምስጋናዬ ይድረሳት::

# ማውጫ

ምስጋና……………………………………………………………………………i
የአባሪዎች ማውጫ ........................................................................................v
የሰንጠረዥ ማውጫ ...................................................................................... vi
አጠቃሎ…………………………………………………………………………..vii
ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ ..................................................................................1
1.1. የጥናቱ ዳራ..................................................................................................1
1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር .......................................................................................15
1.3. የጥናቱ ዓላማዎች...........................................................................................22
1.3.1. ዋነኛ ዓላማ ................................................................................................22
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች..........................................................................................22
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ..............................................................................................22
1.5 የጥናቱ ገደብ ..................................................................................................23
1.6 የጥናቱ አደረጃጀት ..........................................................................................24
ምዕራፍ ሁለት:- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ..........................................................25
2.1 የፅሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች................................................................25
2.1.1. የውጤት ተኮር አቀራረብ.............................................................................26
2.1.1.1 ውስን መፃፍ ..............................................................................................27
2.1.1.2 መር መፃፍ (Guided Writing)...................................................................28
2.1.1.3 ነፃ መፃፍ ..................................................................................................29
2.1.1.4 በውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች ................30
2.1.2 የሂደት ተኮር አቀራረብ..................................................................................31
2.1.2.1 ቅድመ መፃፍ .............................................................................................33
2.1.2.2 ጊዜ መፃፍ ..................................................................................................34
2.1.2.3 ድህረ መፃፍ................................................................................................34
2.1.2.4 በሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች ....................36
2.1.3 የዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ........................................................37
2.1.3.1 የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ገጽታ ...........................................42
2.1.3.2 የተለያዩ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦች..............................................44
2.1.3.3 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታዎች ..........................................................46
2.1.3.4 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ባህሪ.......................................................................49

2.1.3.5 የዘውግ ፅሁፍ አቀራረብ እና ሚና ጫወታ (Gener writing &Role paying)....51
2.1.3.6 በዘውግ ተኮር አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች....52
2.1.4 የሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ....52
2.1.4.1 የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ውሱንነት....54
2.1.4.2 የሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ውስንነት....54
2.1.4.3 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ውስኑነት....55
2.1.4.4 መፃፍን በማስተማር ወቅት የዘውግ እና የሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምረት....57
2.1.5 ትውረታዊ ማዕቀፍ (Theoretical Frame work)....59
2.1.5.1. የመፃፍ ንድፈሀሳቦችና አቀራረቦች....60
2.1.5.1.1. የድርሰት ንድፈ ሀሳብ:-የውጤት ተኮር የመፃፍ ሂደት....60
2.1.5.1.2. የግንዛቤያዊያን ንድፈሀሳብና የሂደት ተኮር ሂደት....61
2.1.5.1.3. የግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ....62
2.1.6 የዘውግና የሂደት ተኮር የመፃፍ ምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር....63
2.1.6.1. ዐውድን መገንባት....65
2.1.6.2. ሞዴል ጽሑፍን መገንባት....66
2.1.6.3. ጽሑፍን በጋራ መገንባት (Collaborative Construction of the text)....66
2.1.6.4. ፅሁፍን በራስ መገንባት....68
2.1.6.5. በጽሁፍ ላይ ፅብረቃ (Reflecting on writin)....70
2.1.7. መፃፍን በማስተማር ረገድ የመምህሩ ሚና....71
2.1.8. መፃፍን የሚደግፉ መልመጃዎች....74
2.1.9. የመፃፍ ትምህርት አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር....76
2.1.10. ለተማሪዎች ፅሁፍ የሚሰጥ ምላሽ....77
2.1.10.1. የመምህር ምገባ መረጃ....78
2.1.10.2 የቢ.ጤ ምገባ መረጃ....80
2.1.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት....82
ምዕራፍ ሶስት:-የአጠናን ዘዴ....87
3.1 የምርምር ንድፍ....87
3.2 የጥናቱ ዓይነት....89
3.2.1. የናሙና አመራረጥ....90
3.1.1.1. የክልልና ዞን ናሙና አመራረጥ....90

3.1.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ....... 90
3.1.1.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ....... 91
3.1.1.4. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ....... 91
3.1.1.5. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ....... 91
3.1.2. የስልጠና መመሪያ (Training Manual) ....... 92
3.1.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ....... 92
3.1.3.1. ቅድመ ትምህርት ፈተና ....... 92
3.1.3.2. ድህረ ትምህርት ፈተና ....... 93
3.1.3.3. የፅሁፍ መጠይቅ ....... 94
3.1.4. የመረጃ አተናተን ....... 94
3.1.4.1. ከቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች ትንተና ....... 95
3.1.4.2. ከተማሪዎች የተገኘ የፅሁፍ መጠይቅ ትንተና ....... 95
ምዕራፍ አራት:-የሙከራ ጥናት ....... 96
4.1 የናሙና አወሳሰድ ....... 96
4.1.1 ተማሪ ....... 96
4.1.2 መምህር ....... 97
4.2 የጊዜ ሰሌዳ ....... 97
4.2.1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ....... 97
4.2.1.1 ፈተና ....... 97
4.2.1.2 የጽሑፍ መጠይቅ ....... 98
4.2.2. መረጃ መተንተን ....... 99
4.2.3. የሙከራ ጥናቱ መረጃ ትንተና ....... 99
4.2.3.1. የፈተና ውጤት ....... 99
4.2.3.2. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና ....... 103
4.2.4. ከሙከራ ጥናቱ የተቀሰሙ ትምህርቶች ....... 107
ምዕራፍ አምስት:-ዋናው ጥናት ....... 110
5.1 የንሞና ዘዴዎች ....... 110
5.1.1 ተማሪ ....... 110
5.1.2 መምህር ....... 110
5.1.3 የጊዜ አጠቃቀም ....... 111
5.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ....... 111
5.1.4.1 ቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች ....... 111
5.1.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ ....... 112
5.1.5 የመረጃ ስብሰባና ትንተና ....... 113

5.1.5.1 የመረጃ ስብሰባ ሂደት ........ 113
5.1.5.2 የመረጃ ትንተና ሂደት ........ 113
5.1.6 የመረጃ ትንተና እና ውይይት ........ 114
5.1.6.1 የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ስለማሻሻሉ ........ 114
5.1.6.2 የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች በተማሪዎች የመፃፍ አመለካከት ላይ ለውጥ አምጥቷል? ........ 121
ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት ........ 131
6.1 የጥናቱ ማጠቃለያ ........ 131
6.1.1 የጥናቱ አካሄድ ........ 131
6.1.2 የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ........ 133
6.1.3 መደምደሚያ ........ 136
6.1.4 የጥናቱ ስነ ትምህርታዊ ፋይዳ ........ 137
6.1.5 የመፍትሔ ሀሳቦችና አስተያየቶች ........ 139
6.1.6 የጥናቱ ውሱንነት ........ 140
6.1.7 ለቀጣይ ጥናቶች አስተያየት ........ 140
ዋቢ ዕሑፎች ........ 143

## የአባሪዎች ማውጫ ገፅ


አባሪ አንድ- የስልጠና መመሪያ ....................................................................156

አባሪ ሁለት- የሂደት ዘውጋዊ ዘዴ አተገባበር..............................................174

አባሪ ሶስት- በሂደት ተኮር የቀረበ የመፃፍ ትምህርት ...............................228

አባሪ አራት- የመፃፍ ቅድመና ድህረ ፈተና ...............................................258

አባሪ አምስት- የፅሁፍ መጠይቅ...................................................................264

አባሪ ስድስት- ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ .......................267

አባሪ ሰባት- ቅድመና ድህረ ፈተና ውጤት መግለጫ ..................................269

አባሪ ስምንት- በቅድመና ድህረ ፈተና ከፍተኛና ዝቅተኛ

ውጤት መግለጫ ...................................................................272

አባሪ ዘጠኝ- የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት መግለጫ .......................................274

አባሪ አስር- የመፃፍ ቅድመና ድህረ ፈተና ..............................................277

አባሪ አስራ አንድ- የፅሁፍ መጠይቅ ..........................................................283

አባሪ አስራ ሁለት- ቅድመና ድህረ ፈተና ውጤት መግለጫ.......................286

አባሪ አስራ ሶስት፡- በቅድመና ድህረ ፈተና ከፍተኛና ዝቅተኛ

ውጤት መግለጫ ...................................................................291

አባሪ አስራ አራት- የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት መግለጫ ..............................292

አባሪ አስራ አምስት- አዋጅ.........................................................................296

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ሰንጠረዥ 1 የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖች የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤት ....................100
ሰንጠረዥ 2- የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት ....................101
ሰንጠረዥ 3 የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ዝቅተኛ ....................102
ሰንጠረዥ 4- ተጠኚዎች በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት ለመፃፍ የነበራቸው አመለካከት .........103
ሰንጠረዥ 5- በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደርጉ በኋላ ለመፃፍ የነበራቸው አመለካከት ....................105
ጠንጠረዥ 6- የሙከራ ቡድኖች የቅድመ እና የድህረ ፈተና ውጤቶች ..115
ሰንጠረዥ 7- የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ወቅት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት ....................116
ሰንጠረዥ 8 - የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖች በቅድመና ድህረ ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት ....................118
ሰንጠረዥ 9- በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች መካከል የpaired t-test ውጤት ....................119
ሠንጠረዥ:- 10 ድርሰት የመፃፍ ልምምዷን በተመለከተ ....................121
ሠንጠረዥ:-11 ድርሰትን በራስ መፃፍና ዕውቀትን በተመለከተ ....................122
ሠንጠረዥ:-12 በድርሰት ውስጥ የሰዋሰው ስህተትና የማንበብ ስሜት ......123
ሠንጠረዥ:-13 በቡድን ስራ መሳተፍና ፅሁፎችን ማንበብ....................123
ሠንጠረዥ:-14 ድርሰት በመፃፍ ወቅት የመምህራን አስተያየት ....................125
ሠንጠረዥ:-15 ስለ መፃፍ ጠቃሚነት ....................126
ሠንጠረዥ 16:- የመፃፍ ተግባራዊ ልምምድ ....................127
ሠንጠረዥ:-17 የጓደኛ አስተያየትና የመምህሩ ድጋፍ....................128
ሠንጠረዥ:-18 በድርሰት ውስጥ ስህተት መፈፀምና ሀሳብ ማደራጀት ......129
ሠንጠረዥ:-19 ድርሰት የመፃፍ ልምምዶችና ሞዴል ድርሰቶች ..............130

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር እና እንዲሁም ተማሪዎች በዚህ ዘዴ ከተለማመዱ በኋላ በመፃፍ ላይ ያላቸው አመለካከት ለውጥ ያሳ እንደሆነ ፈትሿል:: ይህ ጥናት የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸውን የሚያሻሽሉበትን ስልት የተከተለ ነው:: ከዚህ አጠቃላይ ግብ ለመድረስ መጠናዊና ዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ላይ የተመሰረተ ሆኖ ገላጭ የመረጃ አተናተን ስልትን ተግባራዊ አድርጓል:: የጥናቱ ተሳታፊዎች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ሁለት ክፍሎች 9ኛ “A” እና “F” በአጋጣሚ የንሞና ስልት የተመረጡ ሲሆን ከነዚህ ሁለት ክፍሎች አንደኛው በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የተማረው የተማርው ቡድን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በልማዳዊው የማስተማር ዘዴ የተማረው የቁጥጥሩ ቡድን ነው:: ለእያንዳንዱ ቡድን ለአስራሁለት ሳምንታት ትምህርቱ ተሰጥቷል:: ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከመማራቸው በፊትና ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ፈተና ተሰጥቷቸዋል:: እንደዚሁም እነዚህን ሁለት ክፍሎች የሚያሰተምር አንድ መምህር በተመሳሳይ የንሞና ዘዴ ተመርጧል:: ለዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገሉት ቅድመና ድህረ ፈተናዎች ናቸው:: በፈተናዎች የተሰበሰበው መረጃ ሲታይ በቅድመ ፈተና ወቅት የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በ t- ቴስት ቀመር ተሰልቶ በተገኘው ውጤት መሰረት ጉልህ ልዩነት አልታየበትም:: በሌላ በኩል በድህረ ፈተና ወቅት የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት ታይቶበታል:: በተጨማሪም የፅሁፍ መጠይቅ በአጋዥነት በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል:: በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ እንደታየው በአጠቃላይ ድርሰት በመፃፍ ረገድ የሙከራ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊትና ጥናቱ ከተካሄደ በኋላ የጥናቱ ተተኳሪዎች አመለካከት ሲነፃፃፀር የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ፈጥረዋል:: በዚህ ጥናት የታየው ግኝት በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በልማዳዊው ዘዴ ከተማሩት ጋር ሲነፃፀሩ የመፃፍ ችሎታቸው እና ለመፃፍ ክሂል ያላቸው አመለካከት የተሻለ ሆኗል:: በመጨረሻም ቀጣይ ጥናቶች ይኸውም:- አንድ ዓይነት ደረጃ ባላቸው፣ ዝቅተኛ ውጤት ባላቸው እና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ተምህረት አቀራረብ ተግባራዊ ቢሆን ሊመጣ የሚችለው ተፅህኖ ቢመረመር የሚል አስተያየት ቀርቧል::

# ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ስር ለጥናቱ መከናወን አስፈላጊ የሆነው የጥናቱ ዳራ የተካተተበት ነው:: በተመሳሳይ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን አስመልክቶ በጥናትና ምርምር የተገኙ ሀሳቦች፣ የተከሰቱ ለውጦችና የታዩ ዕድገቶች ተገልፆበታል:: በመቀጠልም የዚህ ጥናት አቅራቢ ለዚህ ምርምር ያነሳሱት ምክንያቶች የጥናቱ መነሻ ችግር በሚለው ርዕስ ስር ለጥናቱ መከወን ሰበብ የሆኑ ነጥቦች ተጠቁመዋል:: በሌላ በኩል በጥናቱ ዓላማ ስር ዋና ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ተቃኝተውበታል:: በዚህ ምርምር የታዩ ችግሮች ከተፈቱ በውጤቱ የትኛው አካል እንደሚጠቀም የጥናቱ ጠቀሜታ በሚለው ርዕስ ስር ተብራርቷል:: ከዚህም ሌላ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ ገደብና አደረጃጀት ትኩረት ተሰጥቷቸው የተብራሩበት ክፍል ነው::

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ ተግባቦት ሂደት መሠረታዊ ከሚባሉት አራት ክሂሎች አንዱ መፃፍ ሲሆን በሀሳብ ማስተላለፊያነት የሚያገለግል ነው። ይህን በማጠናከር Tangperpoon (2009) መፃፍ፣ የተለያዩ ጽሑፋዊ ክንውኖች የመጨረሻ ውጤት የሆነ የሀሳብ ማስተላለፊያ እንደሆነ ሲገልጹ፣ Usó-Juan & Martínez-Flor (2006) ደግሞ ጽሑፍ በውሁድ አሀድ (text) አማካኝነት የሚተላለፍ ፈጠራዊ እና ዐውዳዊ የሆነ ተግባቦት መሆኑን ያስረዳሉ። በመሆኑም መፃፍ የድምጽ ወኪል በሆኑ ትዕምርቶችና ምልክቶች አማካኝነት የሚተገበር የመልዕክት ማስተላለፊያ ነው። የመፃፍ ክሂል ከንግግር ክሂል ብዙ ዘግይቶ የመጣ ቢሆንም ለሰው ልጆች የሚሰጠው ጥቅም ከፍ ያለ ሲሆን በዋናነት ዕውቀት የሚቀሰምበትና የሚተላለፍበት፣ ታሪክ የሚመዘገብበትና ከዘመን ወደ ዘመን የሚሸጋገርበት ድልድይ ሆኖ ያገለግላል::

ብዙ ምሁራን ስለመፃፍ ብያኔ የሰጡት ከንግግር ክሂል ጋር በማነፃፀር ነው:: Weigle(2002) የመፃፍ ባህሪ ከንግግር ጋር ሲነፃፀር ቋሚ ጊዜ የሚወስድ፣ ውስብስብና መደበኛነት የሚታይበት መሆኑን ገልፀዋል:: ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው ፅሁፍ ከተፃፈ ከሰዓታት፣ ከቀናት፣ ከወራት፣ ከዓመታት እንዲሁም ከምዕተ ዓመት በኋላ ሊነበብ የሚችል መሆኑን:: በተፃፃሪው ንግግር ግን ከተነገረበት ቅፅበት በአየር ላይ የሚቀር መሆኑን ነው:: ጸሀፊዎች ፅሁፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለማሰብ፣ ለማቀድ፣ ለመከለስና

ለማረም ጊዜ ይፈልጋሉ:: በቋንቋ የመፃፍ ሂደት ውስብስብ ነው:: ምክንያቱም በቀላሉና በግልፅ ለመፃፍ ረጅም አረፍተነገርን፣ ስርዓተነጥቦችንና ሰዋስዋዊ ሂደቶችን የሚከተል መሆኑ ነው::

በሌላ በኩል ስልትና መዋቅር መፃፍን ቀላል በሆነመንገድ እንዲቀርብ ሚያደርጉ ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ ፀሀፊዎች ትክክለኛ ሰዋስውንና የተደራጀ አካሄድን ተከትለው የሚፅፉ ሲሆን በዓረፍተነገርና በአንቀፅ የሚፅፏቸውን ነገሮች ያደራጃሉ:: ከሁሉም በላይ ስህተትን ለማስወገድ የሚጥሩ ሲሆን መደበኛ የሆኑ ቃላትን ለመጠቀም ይሞክራሉ:: በፅሁፍ ጊዜ ጠንካራ ቃላትን የሚጠቀሙ ሲሆን ብዙ ጊዜ ተራ ቃላትን አይጠቀሙም:: በሌላ በኩል ስርዓተነጥቦችን ይኸውም:-ንዑስሠረዝ፣ ጥያቄምልክትና ነጥቦችን በተገቢው ቦታቸው መቀመጥ አለባቸው::

በንግግር ወቅት ተናጋሪው በአብዛኛው መደበኛነትንና የተደራጀ ሁኔታን አይከተልም:: ብዙጊዜ ሙሉ አረፍተነገርና ትክለኛ የሰዋስው ህግጋትን አይከተሉም:: የሚጠቀሙባቸው ቃላት ተራና የተለመዱ ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜ ያለዝግጅትና ግብታዊ በሆነ ሁኔታ ነግግር ያደርጋሉ:: በዚህም የተነሳ ቃላትን መላልሰው የሚደግሙ ከመሆኑ ባሻገር የተነሱበትን ጉዳይ ላያቀርቡ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ንግግር ሲደረግ በመፃፍ ወቅት የማይታዩ ሌሎች ሁኔታዎች ይኸውም:-የፊት ገፅታና የድምፅ ቃና ይታያሉ:: ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መፃፍን መማርም ሆነ ማስተማር ከሌሎች ክሂሎች ጋር ስነፃፀር አስቸጋሪ ተደርጎ ይወሰዳል::

ይሁን እንጂ በተለይ ከንግግር ክሂል ጋር ሲነፃፀር ብዙ ጥቅም የማይሰጥ ወይም ክሂሉን ለማስተማር በጣም አስቸጋሪ ተደርጎ ይወሰድ ነበር (Willson,2003):: ይህ ክሂል ውስብስብና አስቸጋሪ ተደርጎ የሚታይበት ምክንያት ለትምህርትነት የሚቀርበው ፅሁፍ ከቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ከአረፍተ ነገር አሰዳደር፣ ከስርዓተ ነጥብ አገባብ፣ ከይዘት አደረጃጀት እና የሰዋሰው ህግን በተገቢው ቦታ ከመጠቀም ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ነው:: በሌላ በኩል የመፃፍ ክሂል ከባድ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርገው ጉዳይ እንደንግግር ክሂል የአካል እንቅስቃሴ፣ የድምፅ አወጣጥ ደረጃ፣ የፊት ገፅታ መለዋወጥ እና መሰል የመዕክት ማስተላለፊያ አጋሮችን የማይጠቀም መሆኑ ነው (Ur, 1996, Byrne,1990):: እነዚህ ባህሪያቱ ክሂሉን በማስተማር ረገድና ውጤታማነት ላይ የየራሳቸውን ተፅህኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በመፃፍ ክሂል የመጠቀም ችሎታ

እንዲጎለብት ለክሂሉ ትኩረት መስጠት፣ በቂ ልምምድና ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ Norrish (1990) ገልፀዋል:: ከዚህ ሀኔታ መገንዘብ የሚቻለው የመፃፍ ክሂል የውስብስብነት እና የአስቸጋሪነት ባህሪ ቢኖረውም በክሂሉ ተጠቅሞ የሚፈለገው ችሎታ እንዲዳብር ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው እነደሚገባ ነው::

መፃፍ በአንድ በተወሰነ ልማዳዊ ስርዓት በዕይታዊ ትዕምርቶች ሥምረት ቃልን ከቃል፣ ዐረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር፣ አንቀፅን ከአንቀፅ ወዘተ. በማቀናጀት የቋንቋ ስርዓተ አፃፃፍን ተከትሎ አንድ ውስን የሆነ ቅርፅ የሚያስገኝ ተግባር ነው:: በጥቅሉ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ የቋንቋ መሳሪያ ነው (Byrne.1990,14):: እኚህ ምሁር በተጨማሪ እንዳብራሩት መፃፍ በትዕምርቶች የመወከል ሂደት ብቻ ሳይሆን የአዕምሮንና የአካል እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት ይዘትን፣ የአፃፃፍ ስልትን፣ የአወቃቀር ስርዓትን፣ የቃላት ምርጫን፣ የሀሳብ ፍሰትን፣ ወዘተ. ያሉ በርካታ ባህሪያቱን ቅፅበታዊ በሆነ የመፃፍ ሂደት ውስጥ በመጠቀም የሚከናወን የአዕምሮ ስራ መሆኑን ገልፀዋል:: መፃፍ በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተገኘ የዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን፣ ሀሳብ የሚፈልቅበት የክሂል ዘርፍ ከመሆኑም ባሻገር መረጃን ወደ ዕውቀት ለውጦ መልዕክትን ማቀበያ እና በትዕምርቶች ቀርፆ የማቆያ ስልት ነው (Widdowson, 1990:62)::

መፃፍ የቋንቋ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩና እንዲያደራጁ የሚያግዝ ክሂል ነው:: በተጨማሪም የተማሪዎችን የማጠቃለል፣ የመተንተንና አስተያየት የመስጠት ችሎታ የሚያዳብር ክሂል ነው:: ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የመፃፍ ጥቅም በግልፅ የሚያሳየው ውጤታማ የሆነ መፃፍ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊው አካል መሆኑን ነው::

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው፤ መፃፍ በመተላለፊያ ስልቱ በዕይታዊ፣ በአህምሮአዊ እና በአካለዊ ትግበራው፣ አፍላቂ፣ በተግባቦታዊ ባህሪው ርቱዕ መሆኑን ነው:: በተመሳሳይ መፃፍ ትርጉም ያላቸው ዐረፍተ ነገሮችን መሰረት በማድረግ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካይነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር ለአንባቢ የማስተላለፍ ሂደት ነው::

ይሁን እንጂ መፃፍ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች ከፍተኛ ትኩረት እንዲያደርጉ ቢጠበቅም ይህን ክሂል ማስተማር ቀላል አይደለም (Silva,1990)::

በተመሳሳይ እንደ Flower (1990) ጥናት መፃፍ እንደ ሰትራቴጂካዊ ሂደት ሊገለጥ ይችላል::

ይህ ሂደት ከብዙ ነገሮች ይኸውም:- ግንዛቤ፣ ዐውድ፣ ግብና ስትራቴጂ አንፃር ሲታይ ውስብስብና ብዙ የእርስ በርስ ግንኙነት ያለበት ነው:: ከመፃፍ ውስብስብነት ሂደት በመነሳት Reynolds (2005) እንደጠቆሙት በሰዋስው ችሎታና በመፃፍ ልምምድ ላይ የሚታዩ ውስንነቶች በውጤታቸው የተማሪዎችን የመፃፍ ሂደት አስቸጋሪ ያደርጋሉ:: በሌላ በኩል Ramies (1987) እንደገለፁት ተማሪዎች በማንኛውም ርዕስ ላይ እንዲፅፉ ስራዎች ሲሰጣቸው የተለያዩ ስልቶችን ይኸውም:- መንደፍ፣ ማስታወስ፣ መልሶ መላልሶ ማንበብ፣ መከለስና ማረምን የመጠቀም ፍላጎት ያሳያሉ::

መፃፍ የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ተጠቅሞ ሀሳብን በወረቀት ላይ የምናሰፍርበት ሂደት ከመሆኑም ባሻገር፤ መፃፍ ትዕምርቶችን ተጠቅሞ ቃላትን ፣ ዐረፍተነገሮችን፣ አንቀፆችን፣ ወዘተ በቋንቋው ስርዓት አማካይነት አቀናጅቶ የሚያቀርብ ነው (Byrne,1990:1):: መፃፍ የአንድ ቋንቋ ድምፆች ከሚወክሏቸው ምልክቶች ጋር እየተዛመዱ በወረቀት ላይ በማስፈር መልዕክት የሚተላለፍበት ሂደት ነው::

ይሁን እንጂ መፃፍ በቂ ዝግጅትን እና መማርን የሚጠይቅ ነው:: ማንኛውም በአካል እና በአእምሮ ጤነኛ የሆነ ሰው በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር የሚችል ሲሆን ነገር ግን በቋንቋው እንዴት መፃፍ እንዳለበት መማር አለበት (Nunan, 1999: 36):: በሌላ በኩል መፃፍ ጊዜ ተሰጥቶት በተከታታይ ልምምድን የሚጠይቅ የክሂል ዘርፍ መሆኑን Ur (1996:26) and Richards (1990,101) ገልፀዋል:: የምሁራኑን ሀሳብ በማጠናከርም ዓለም (1995:14) የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል::

> መፃፍ ሀሳብን በትክክል ለማስተላለፍ ድምፅን፣ቃላትንና አረፍተነገሮችን በቋንቋ ስርዓት መሰረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበት ነው:: አንባቢም መልዕክቱን በትክክል የሚገነዘበው የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው:: በዚህ መንገድ ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግያስፈልጋል:: ፅሁፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው

በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይበለፅጋል::

በአጠቃላይ መፃፍን አስመልክቶ ከቀረቡ አስተያየቶች መገንዘብ የሚቻለው፤ የመፃፍ ክሂል አካልን እና አዕምሮን በማቀናጀት፣ ድምፆችን በምልክቶች በመወከል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ሂደት መሆኑን ነው:: ከዚህ አንፃር በፅሁፍ የሰፈረን መልዕክት የሚከታተል አንባቢ መልዕክቱን የሚረዳው የቀረበው ፅሁፍ የቋንቋውን ስርዓት እና የአፃፃፍ ህግጋት በሚያሟላ መልኩ በዕይታዊ ምልክቶች አማካይነት ሰፍሮ የተቀመጠ እንደሆነ ነው:: በመሆኑም በፅመፃፍ አማካይነት ሀሳብን ተገቢ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ እንዲቻል ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል::

እንደ Rames (1983:3) አስተያየት "መፃፍ በጊዜ እና በቦታ ሳይገደብ ሰዎችን በዕይታዊ ምልክቶች ከማግባባቱ በተጨማሪ የትምህርት መከታተያ፣ የሀሳብ ማጉያ፣ የዕውቀት መቅሰሚያ ከመሆኑም ባሻገር ሌሎች ጠቀሜታዎች አሉት::" በሌላ በኩል Byrne (1990:16) ባቀረቡት ሀሳብ "የመፃፍ ትምህርት ተማሪዎች ዕውቀትን መዝግበው የሚይዙበት መሳሪያቸው በመሆኑ፣ ፈተናዎች በፅሁፍ ስለሚሰጡ፣ የመፃፍ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል::" በተጨማሪም Brandly (1994,169) and Ur (1996,168) የመፃፍ ትምህርት አስፈላጊነት ከግለሰባዊና ከማህበራዊ ጠቀሜታ አኳያ እንደሚታይ ገልፀው "መፃፍን መማር ለግለሰብ አመለካከትን ለመግለፅ፣ አህምሯዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተፃፉ ሰነዶችን ለመመርመር ሲረዳ፤ ማህበራዊ ጠቀሜታው ደግሞ፣ የስነፅሁፍ ስራዎችንና የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚረዳ ክሂል" መሆኑን አብራርተዋል::

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው የመፃፍ ክሂል የሰው ልጆች ዕውቀት የሚቀስሙበት፣ ዕምነታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ሀሳባቸውንና ዕውቀታቸውን በሆሂያት ውክልና አማካይነት በአካባቢያቸው ወይም በቦታና በጊዜ ከነሱ ርቆ ለሚገኝ ሰው ለማስተላለፍ የሚገለገሉበት ክሂል ነው::

በሌላ በኩል በድሉ (1996፣52) የመፃፍ ክሂል "ጥሩ የመፃፍ ችሎታ የማሰብ ብልሀትን ፣ መላ መምታትን መጠየቅን፣ ግምት መስጠትን፣ መላምት ማረጋገጥንና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲያውቁ ይረዳል "ካሉ በኋላ

አዝወትሮ የሚፅፍ ተማሪ የሚፅፈውን ይዘት እየከለሰ እንደሚመረምር እና እንደሚያደራጅ ጠቁመዋል:: ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው መምህራን የመፃፍ ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያሳድግ አቀራረብ መምረጥ እንዳለባቸው ነው::

በአጠቃላይ የመፃፍ ትምህርት፤ የሀሳብ መፍለቂያ፣ የዕውቀት መቅሰሚያ እና መከታተያ ነው:: ከዚህም ሌላ፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት፣ የግል እና የቡድን ስራዎችን ለመስራትና የተማሩትን እንዳይረሱ፣ በፅሁፍ እንዲያሰፍሩ፣ ያግዛቸዋል:: በተጨማሪም ፈተናዎችን ለመፈተን እና ማስታወሻ ለመያዝ ይጠቀሙበታል:: ከዚህ አነፃር ፅህፈት በየትኛውም የህይወት ገፅታ ውስጥ የመግባባት ፍላጎቶችን በማሟላት እና አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን በማሳደግ ረገድ አስተዋፅኦው እየጎላ የመጣ ሲሆን በቋንቋ መማር ወቅት እንደ ማዳመጥ፣ማንበብና ንግግር ጠቃሚ የክሂል ዘርፍ ነው::

ቀደም ባለው ዘመን በቋንቋ ማስተማር ሂደት የመፃፍ ክሂል በይዘትነት ራሱን ችሎ የሚቀርብ ሳይሆን የሰዋስው ወትርጉም ማስተማሪያ ዐውድ ተደርጎ ይወሰድ ነበር (Richards, 1990:106):: ይሁን እንጅ የሰው ልጅ በቴክኖሎጂና በሳይንስ እየተራቀቀ፣ አዕምሮውና አስተሳሰቡ እያደገና እየበለፀገ በመምጣቱ በአሁኑ ጊዜ መፃፍ ዕድገት እያሳየ የምርምር ዘርፍ እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል::

በዚህ ምክንያት የመፃፍ ክሂል ራሱን የቻለ ዘርፍ እየሆነ መጣ:: በተለይ በ1970ዎቹ መጨረሻ እና በ1980ዎቹ መግቢያ ላይ በሰሜን አሜሪካ እና በሌሎችም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ አገራት በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ እንግሊዘኛ የአፍ መፍቻቸው ያልሆኑ ተማሪዎች ቁጥር በመጨመሩ እና እነዚህ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ጥሩ የመፃፍ ክሂል እንዲኖራቸው ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት መምህራንን ማሰልጠን ተጀመረ:: በስልጠናውም ላይ በመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ላይ ያተኮሩ ትምህርቶች ይዘጋጁ የሚል አስተሳሰብ እየጎላ መጣ (Kroll,1990:262)::

ከዚህ በኋላ በመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ላይ በርካታ ለውጦች የታዩ ሲሆን፣ በውጤቱም የተለያዩ አቀራረቦች እና አመለካከቶች ተከስተዋል:: ይሁን እንጂ የመምህራን የማስተማር ብቃት እና ስልት፤ እንዲሁም የተማሪዎች የመማር

ስልት፤ የተለያየ በመሆኑ የመፃፍ ክሂልን እንዴት እናስተምራለን? ለሚለው ጥያቄ አንድ ወጥ የሆነ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል::

የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች፣ ስነዘዴዎችና አመለካከቶች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የየራሳቸው ስልቶች አሏቸው:: በመስኩ ምሁራን ተደጋግመው የሚጠቀሱና ተቀባይነት ያገኙ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ከሚያገለግሉ አቀራረቦች መካከል በተጠናቀቀ ፅሁፍ ላይ የሚያተኩረው:- ውጤት ተኮር አቀራረብ፣ በፅሁፍ ሂደት ላይ ትኩረት የሚያደርገው እና መፃፍን ዓላማ ያለው እና ድርጊት የሚከናወንበትን ዐውዳዊ አገባብን በመተንተን ትኩረት የሚያደርገው የዘውግ ተኮር አቀረቀረብ መሆናቸውን (Brown, 2001, Atikinson, 2003) ጠቁመዋል::

ውጤት ተኮር አቀራረብ መፃፍን ለማስተማር ጥንታዊ አቀራረብ ተደርጎ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ፣ ተማሪው መምህሩ ከሚያቀርብለት ሞዴል ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንዲፅፍ የሚያደርግ ነው:: የሂደት ተኮር አቀራረብ ሀሳብ በማመንጨት፣ የብጤ እርማት፣ መልሶ መፃፍ እና የመሳሰሉት ብልሃቶች ላይ ትኩረት ሲያደርግ፣ ዘውግ ተኮር አቀራረብ ደግሞ ወደፊት ሊሆኑ የሚችሉ እና በየዕለቱ የሚከሰቱ በተለየ ባህል ውስጥ የሚገኙ ትምህርታዊ እና ስነፅሁፋዊ ሁኔታዎችን ይይዛል::

Burden, Larson and Toonen (2005) እንደገለፁት ቀደም ባሉት ጊዜዎች እስከ 1970 ዎቹ ድረስ መምህራን በመፃፍ ትምህርት ወቅት ትኩረት የሚያደርጉት በመጨረሻው ውጤት ላይ ነው:: ይህ የውጤት ተኮር አቀራረብ ለዐረፍተ ነገር መዋቅር እና ለሰዋስው ትልቅ ግምት የሚሰጥ በመሆኑ በአንፃሩ ለሀሳብ የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ ነበር::

በውጤት ተኮር አቀራረብ መምህሩ ተማሪዎች የሚፅፉበትን ርዕስ ሰጪ እና ምን መፃፍ እንዳለባቸው ወስኖ የተፃፉ ድርሰቶችን ብቸኛ አራሚ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎች በቂ የመፃፍ ልምምድ እንዲያደርጉ አያስችልም:: በማስተማሪያ አቀራረቡ አልፎ አልፎ ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት ደግመው እንዲጽፉ ይደረጋል:: ነገር ግን ይህ የሚደረገው በርካታ የሰዋስው ስህተት ከፈፀሙ፤ እንደ ቅጣት ተቆጥሮ እንጂ የጽሁፍ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ እንዳልነበር ያስረዳሉ (Brakus, 2003)::

ውጤት ተኮር አቀራረብ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ለብዙ ዓመታት ብቸኛ የማስተማሪያ አቀራረብ ሆኖ ቢያገለግልም፣ ስለመፃፍ ቀድሞ የነበረ አስተሳሰብ እያደገ ሲመጣ በደካማ አካሄዶቹ እየተተቸ በሂደት ተኮር አቀራረብ ሊተካ ችሏል:: ሂደት ተኮር አቀራረብም በመፃፍ ክሂል ማስተማሪያነት ማገልገል የጀመረው ከ1970ዎቹ ጀምሮ መሆኑን እና ለውጤት ተኮር አቀራረብ በተቃውሞ የቀረበ አፀፋ ነው (Yan, 2005:76) ይላሉ::

ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንደ ውጤታማ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በተጠናቀቀ የድርሰት ረቂቅ ላይ እንዲሁም በቋንቋ ቅርፅ ላይ ከማተኮር ይልቅ የመፍጠር፣ አዲስ ነገር የመፈለግ፣ ትርጉም የማስፋፋት ሂደት የሚከተል እና በፅሁፍ ሂደት ላይ የሚያተኩር ነው:: ይኸውም ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ ለመፃፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት ተግባር፤ ሀሳብን በማፍለቅ እና በማደራጀት፣ በተደጋጋሚ ረቂቅ መፃፍ ፣ ያረቀቁትን መከለስ፣ መሰረዝ፣ መጨመር፣ መቀነስ እና ደጋግሞ ሀሳብን ማደራጀት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በማረም ሂደቱም የቃላት መረጣ፣ የዓርፍተ ነገር አወቃቀር እና የአፃፃፍ ስርዓትን መከታተል እና መረዳት ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም ባሻገር ተማሪዎች የራሳቸውን ስትራቴጂ እንዲያዳብሩ የማስቻል ሚና አለው (Silva, 1990)::

በተጨማሪም Stanley (2007) እንዳብራሩት ተማሪው የሂደቱ ዋነኛ አካል በመሆኑ ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል:: በጽሁፍ ጊዜ የተማሪው የቀደመ እውቀት እና ፍላጎት ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት የሚያምን ሲሆን፣ አጠቃላይ አቀራረቡ መጨረሻ ላይ ከሚገኘው ውጤት ይልቅ ጽሁፍ ለሚካሄድበት ሂደት ትኩረት ያደርጋል::

ይህ አቀራረብ መፃፍን በማሰተማር ረገድ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣ ሲሆን ለውጡም የተማሪዎችን እና የመምህሩን ሚና በመለየት፣ በአጠቃላይ በመፃፍ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄደው እንቅስቃሴ ሁሉ ተንፀባርቋል:: በክፍል ውስጥ መፃፍን በማስተማር ሂደት በተማሪዎች መካካል የእርስ በርስ መረዳዳት እንዲኖር የሚያበረታታ ሲሆን በተጨማሪም ርዕስ ለመምረጥ፣ ሀሳብ ለመለየት፣ ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ዕድል የሚሰጥ እና ደጋግመው እንዲያቅዱ፣ ሀሳብ እንዲጨምሩ፣ እንዲቀንሱ፣ እንዲያሻሽሉ እንዲሁም መልሰው ማቀናበር እንዲችሉ የማገዝ ሚና አለው (Silva, 1990:15) ::

ሂደት ተኮር አቀራረብ በውጤት ተኮር ድክመት ላይ ተመስረቶ የመጣ ቢሆንም፤ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: ከነዚህም ትችቶች መካከል አንደኛው፣ የሂደት ተኮር አቀራረብ ንድፈ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም፣ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተከታታይነት ያለው ንድፍ፣ ቅድመ መፃፍ እና ክለሳን ማቅረቡና ፅሁፍን ለማህበራዊ ዓላማ በማዋል ረገድ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑና በአንፃሩ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ለማህበራዊ ሀሳብ የሚሰጠው ትኩረት እያደገ በመምጣቱ የተነሳ በሂደት ተኮር አቀራረብ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች እንዲቀርቡበት ምክንያት ሆኗል (Miller, 1984)::

ከዚህም ሌላ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ መፃፍን ለማስተማር ከውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ፤ ሂደት ተኮር የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም፣ ለሁሉም ዐውድ ተስማሚ ሆኖ አልተገኘም:: ለምሳሌ ይህ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የትምህርት ባለሙያዎች አካዳሚያዊ ፅሁፎችን እንዴት እንደሚገመግሙ ስለማያሳይ ለተማሪዎች የተሳሳተ መረጃ ይሰጣል ወዘተ የሚሉ አስተያየቶች ይሰነዘሩበታል (Horwitz, 1986) ::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሂደት ተኮር አቀራረብ ጥልቅ ፍተሻ ተካሂዶበታል:: በዚህ መሰረት ሂደቱ አንዳንድ የማይለዋወጡ የአፃፃፍ ስልቶችን የሚከተል ሆኖ ታይቷል (Badger and White, 2000):: ይህ የአፃፃፍ ሂደት ታላሚን፣ አንባቢያንን እና ይዘትን ግምት ውስጥ ሳያስገባ በተመሳሳይ ሂደት የተሞላ ይመስላል:: ለማህበረሰብና ባህል ትኩረት መስጠት አልቻለም:: ይህ ድክመቱም ለዘውግ ተኮር አቀራረብ መከሰት ምክንያት ሆነ (Atikins, 2003)::

ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የተለያዩ በሁለተኛ ቋንቋ መፃፍን የሚያሳድጉ ስነትምህርታዊ ስልቶች ስራ ላይ ውለዋል:: በ1970ዎቹ በይበልጥ ደግሞ በ1980ዎቹ የቋንቋ ባለሙያዎች የተማሪዎችን የስነልሳን ክሂል በቅድመ መፃፍ ተግባራት ይኸውም:- ለማቀድ፣ ለመንደፍ፣ ለማረም እና ለመከለስ ከፍ ያለ ቦታ በሚሰጠው የሂደት ተኮር አቀራረብ ላይ ትኩረት አድርገው ነበር (Badger and White, 2000; Feez, M ,2002; Muncie, 2002):: ከ1980 እና ከ1990 በኋላ በመፃፍ ላይ ያሉ ንድፈ ሀሳባዊ ፍላጎቶች መፃፍን ዓላማ ያለው ድርጊት እና ትኩረቱም መፃፍ የሚከናወንበትን ዐውዳዊ አገባብን በመተንተን ወደ ሚያተኩረው የዘውግ ተኮር

አቀራረብ ተቀይሯል (Babalola ,2001; Johns, 2003; Matsda, 2003; Zeng, 2005; Hyland, 2007)::

"ዘውግ" ስነፅሁፍን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን በተለየ ባህል ውስጥ በየዕለቱ በሚታዩ ሁኔታዎችና ድግግሞሽ፣ አካዳሚያዊ እና ስነፅሁፋዊ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኝ ነው (Hammoned and Derewianka, 2001):: ብዙ ጊዜ በምዕራባውያን አገራት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ፣ ዘውግ የሚገለፀው ወይም የሚመደበው ለማህበራዊ ዓላማ በሚሰጠው ቅድሚያ ነው::

በተመሳሳይ Badger and White (2000) ገለፃ መሰረት፣ በዘውግ እና ውጤት ተኮር አቀራረቦች መካከል መመሳሰል የሚስተዋል ሲሆን አንዳንዴ የዘውግ ተኮር አቀራረብ፣ የውጤት ተኮር አቀራረብ ቅጥያ ሆኖ ይታያል:: ልክ እንደ ውጤት ተኮር አቀራረብ የዘውግ ተኮር አቀራረብም መፃፍ ስነልሳናዊ ዕይታ መሆኑን ቅድሚያ የሚሰጥ ቢሆንም ይህ አቀራረብ መፃፍ በሚከናወንበት ጊዜ ለማህበራዊ ዐውድ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል:

የዚህ አቀራረብ ማዕከላዊ ነጥብ የመፃፍ ስነትምህርታዊ ፋይዳው ተማሪዎች በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ግልፅ እና ስርዓታዊ በሆነ መንገድ እንዲገልፁ ማስቻል ነው (Hyland, 2003 a):: በሌላ በኩል የዘውግ ተኮር አቀራረብን ተጠቅመን ስራ ላይ የምናውለው ዘዴ ፅሁፎችን እና ለተማሪዎች የታለመውን ማህበራዊ ዐውድ መመርመርን፣ በፅሁፍ ልምምድ ወቅት የሚሰጠውን ምላሽ ማበረታታትን፣ ፅሁፎችን ከተለያዩ ቦታዎች ማስመጣትን በማዕቀፍነት ማካተት ይኖርበታል (Palbn, 2015)::

የዘውግ ተኮር አቀራረብ የመጣው የሂደት ተኮር አቀራረብ ባለበት እጥረት የተነሳ በተሰነዘረበት ትችት ነው:: እንደ Feez (2002) አስተያየት የዘውግ ተኮር አቀራረብ ይህን እጥረት ለማካካስ የመጣ ነው:: በተጨማሪም Paltvidge (2007) እንዳብራሩት በዘውግ ተኮር አቀራረብ የቋንቋ እውቀት ከማህበራዊ አላማ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው እና በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ከሚፈፅመው ሰው ይልቅ በሚያነበው ሰው ላይ ነው::

አብዛኛውን ጊዜ በዘውግ አቀራረብ፣ መፃፍ ዘውግን መሰረት አድርጎ በተማሪው የሚቀርብ ጽሁፍ ነው:: እንደሚታወቀው መማር በመከረጅ የተለያዩ ሞዴሎችን በመመልከት የሚከናወን ነው:: ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ በዘውግ የመፃፍ

ችሎታቸው እንዲጎለብት በዘውግ በቀረቡ የተለያዩ ምሳሌዎች አማካይነት መጋለጥ አለባቸው:: ለተለያዩ ጽሁፎች ተጋላጭ በመሆን ተማሪዎች ዘውግን ስራ ላይ የሚያውሉበትን ክህሎት ያገኛሉ (Balger and White, 2000:155-156):: ማለት ነው::

የዘውግ ተኮር አቀራረብም እንደ ውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: እንደ Caudery (1998:11-13) አስተያየት "የተለየ ዘውግን በግልፅ ለማስተማር መሞከሩና መምህራን ተማሪዎችን ለመረዳት በተገቢው ሁኔታ ላይ አለመገኘታቸውን የገለፁ ሲሆን ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልፁ ብዙም የሚያግዝ አለመሆኑንና መምህሩ በሚያመጣው ተስማሚ ሞዴል በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ ይሆናሉ"::

ሌላው በዘውግ ተኮር ላይ የሚሰነዘረው ትችት ከተለያዩ አንባቢያን ጋር ለመግባባት ምናልባት በቂ የቋንቋ እና የቃላት ችሎታ ላይኖር ይችላል የሚል ሲሆን፣ እንደ Badger and White (2000) አስተያየት የዘውግ ተኮር አቀራረብ እንደ ድክመት የሚቆጠርበት ነጥብ ጽሁፍን ለመፃፍ የሚያስፈልገውን ክህሎት ችላ ማለቱ እና ተማሪዎች በሌላ መስክ ያላቸውን የመፃፍ ችሎታ ግምት ውስጥ የማያስገባ መሆኑ እና የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው መፃፍ በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ የሚተገበር እና የተለየ ዓላማ ነፀብራቅ መሆኑን እንዲሁም ትምህርት ባለን ንቃት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ሁኔታዎችን በመኮረጅ እና በመተንተን ላይ የሚመሰረት መሆኑ ነው::

እንደ Gee (1997) አስተያየት ሂደት ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ በተቃራኒ የቆመ ሲሆን፣ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ደግሞ እየተሻሻለ የሚሄድ ስርዓተ ትምህርትን የሚወክል ተደርጎ ይወሰዳል:: ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት አቀራረቦች የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች የተሻለ አቀራረብ ተደርጎ ይታያል:: የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ማዕከላዊ ነጥብ፣ መፃፍ በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ በዘውግና እና ሂደት ተኮር የሚቀርብ በመሆኑ እያንዳንዱ ፅሁፍ የተለየ ሁኔታን የሚያመለክት አላማ አለው:: መፃፍን ለማስተማር ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴን የመረጠ መምህር አንዳንድ ሁኔታዎችን በመቅዳት፣ ተማሪዎች ዓላማን እና ማህበራዊ ዐውዶችን እንዲረዱ፣ ስለ ሰዋስው፣ ስለቃላት እና መፃፍን የማደራጀት ዕውቀታቸውን ግምት ውስጥ

በማስገባት መልሶ መንደፍና የመሳሰሉትን ሂደቶች እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባዋል::

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሶስት አቀራረቦች ይኸውም:- ውጤት፣ ሂደትና ዘውግ ተኮር አቀራረቦች ላይ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝሮባቸዋል:: ለምሳሌ (Badger and White, 2000; Hyland, 2003; Nordin and Norhisham, 2006):: Badger and White (2000) እንደገለፁጸት በእነዚህ አቀራረቦች ላይ ያለን ክፍተት ለመሙላት ሌላ ስነትምህርታዊ የመፃፍ አቀራረብ ይኸውም ሂደት ተኮርን እና ዘውግ ተኮርን በማቀናጀት የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል:: በሂደት ተኮር አቀራረብ ተደጋጋሚ የመፃፍ ሂደቶች ማለትም ቅድመ መፃፍ፣ ንድፍ፣ ክለሳ እና እርማት ተግባር ላይ የሚውል ሲሆን በዘውግ ተኮር አቀራረብ ደግሞ የተለያዩ ሀሳቦች ማለትም ስለዐውድ ያለ ዕውቀት፣ የፅሁፉ ዓላማ እና የተለያዩ የፅሁፍ ሞዴሎች የሚቀርቡበት ነው:: በተጨማሪም ተማሪዎች የፅሁፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል የተለያዩ ግብዓቶች ይቀርብላቸዋል:: በመሰረቱ ይህ አቀራረብ የሂደት ተኮር ሞዴልና የዘውግ ንድፈ ሀሳብ ቅንጅት ነው (Badger and White, 2000), (Kim and Kim, 2005), (Yan2005, Gao, 2007) ::

በቋንቋ ማስተማሪያ አቀራረቦች ላይ የተደረጉ ጥናቶች የተሻለ ወይም አንድ ወጥ የሆነ የማስተማሪያ አቀራረብ እንደሌለ ያመለክታሉ:: ለምሳሌ McLaughlin (1990) በቋንቋ ማስተማሪያና ንድፈ ሀሳብ ላይ ሳይንሳዊ የሚባል ብቸኛ ትወራም ሆነ ዘዴ አለመኖሩን ገልፀው የተሻለው አቀራረብ ከየዘዴዎቹ የተወጣጡ ጥምር አቀራረቦችን መጠቀም መሆኑን ይመክራሉ:: በተመሳሳይ Harmer (1998) በቋንቋ ማስተማሪያነት የቀረቡ ዘዴዎችን አጢነው ድክመት እንዳለባቸው የተገነዘቡ ሲሆን ይህንን ድክመት ለማሻሻል ከየዘዴዎቹ የተወጣጣ የተሻለና ሚዛናዊ የሆነ የተቀናጀ ዘዴ ንድፈ ሀሳብን አቅርበዋል:: Celce-Murcia, (1991), Ramies (1983,11) ብቸኛና የተሻለ የማስተማሪያ አቀራረብ አለመኖሩን ጠቁመው መምህራን ከየዘዴዎቹ የተሻሉትን አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ሀሳብ አቅርበዋል::

ከፍ ሲል የተጠቀሱት አብነቶች እንደሚያሳዩን በቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ከየዘዴዎቹ ጥሩ የሚባሉትን አቀራረቦች በማቀናጀት ማስተማርን የሚደግፉ ናቸው:: ከዚህ አንፃር ቅንጅታዊ አቀራረብ፤ ዘውግ እና

ሂደት ተኮር አቀራረብን በማቀናጀት የመፃፍ ክሂልን የማስተማር ስልት ይከተላል:: እንደ Rodgers (2001) አተማሪው እንደ ደንበኛ፣ መምህሩ ደግሞ እንደ አማካሪ ይታያሉ፣

- ሰዋስውና ቃላት በዕውነታ ላይ ተመስርተው ይቀርባሉ፣
- በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩ በተከታታይ መፃፍ ወቅት የስነልሳን ችሎታቸው እንዲሻሻል የበለጠ ነፃነት እንደሚኖራቸው እና
- የተለያዩ ተግባራት ለምሳሌ;- በንበት ላይ ማተኮር፣ የሰዋስው ስህተትና አዳዲስ አረፍተ ነገሮችን የመፍጠር ሁኔታ ሊተዋወቁበት ይችላሉ ብለዋል::

መፃፍ ሊኖር ከሚችል የቋንቋ ተጋላጭነት ባሻገር በትምህርት የሚገኝና በልምምድ የሚዳብር ነው(Allwright and Baily 1991) በመፃፍ አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ተግባቦት በዋናነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ የቃልን፣የአረግን፣ የአንቀፅንና የድርሰት አፃፃፍን በየእርከኑ መማር ክሂሉን ለመንገዘብ ጠቃሚ ነው:: በዚህም የተነሳ የመፃፍ ክሂል ከቋንቋ ክሂሎች መካከልትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ሆኗል:: ይህ ክሂል በሀገራችን የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካቶ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ይኸውም:- በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃና እንዲሁም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ሲቀርብ ቆይቷል::

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1944 ዓ/ም በተዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት እንዲሰጥ ተካቶ ነበር:: በሌላ በኩል ይህ ስርዓተ ትምህርት በ1951 ዓ/ም ተሻሽሎ ሲዘጋጅ የትምህርት ዓይነቶች በውስጣቸው ሊይዙ የሚገባቸው ይዘቶች ተካተው ነበር:: በዚህ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከተካተቱ ይዘቶች መካከል ድርሰት አፃፃፍ አንዱ ነበር(ትምህርት ሚንስቴር፣1970):: የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ደረጃ ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች መካከል ተማሪው የቋንቋን ስርዓት ጠብቆ ሀሳቡን በፅሁፍ እንዲገልፅ ማስቻሉ ነው(ተስፋዬ፣1981፣59)::

በመሰረቱ በሀገራችን የመፃፍን ክሂል የማስተማር የረጅም ግዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን በሚጠበቀው ደረጃ ተሳክቶ አይታይም:: በዚህም የተነሳ የሀገራችን

ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ሰጥተዋል:: ከነዚህ መካከል ባየ(1987) ባቀረቡት ሀሳብ በመፃፍ ክሂል ውስጥ የሚታየው ችግር በኢትዮጵያ ብቻ የሚታይ አለመሆኑን አመላክታል:: ይህንን ሀሳብ አስመልክቶ Rechards (1974፣100) በዩኒቨረሲቲ ደረጃ እንኳን ብዙዎቹ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ በተማሩበት መሰረት ጥሩ ፅሁፍ ሲፅፉ አይሰተዋሉም፤ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች ለመፃፍ ፍራቻ የሚታይባቸው መሆኑን ገልፀዋል::

በመፃፍ ክሂል ላይ ለሚታዩ ችግሮች የተለያዩ ምክንያቶችም ቢቀረቡም እነደ Ellis፤1989፤ Rechards 1974 Norish 1983 አስተያየት ለችግሮቹ ዐበይት ምክንያቶች መምህራን የሚከተሉት የማስተማሪያ ስልት የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የትምርት ክፍለጊዜ እጥረት የተማሪዎች ቁጥር መብዛት መሆኑን ገልፀዋል(ተስፋዬ፤1981)

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የሀገራችንን የመፃፍ ክሂል ትምህርት የፈተሹ ጥናቶችን ስናይ የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ችግር ያለበት መሆኑን ይጠቆማሉ:: ከነዚህ ጥናቶች አንዳንዶቹ በሥራ ላይ እየዋሉ ያሉ ዘዴዎች በራሳቸው በተፈለገው ደረጃ የክሂሉን ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ብሎ ለማመን የሚያስቸግር መሆኑን ሲጠቅሱ (ስዩም ከበደ፣ 1988፤ ሰለሞን ዮሀንስ፣ 1991፤ አስቴር ሳሙኤል፣ 1998፤ አለማየሁ፣ 1986)፣ ከፊሎቹ ደግሞ በተግባር ላይ እየዋሉ በሚገኙ ዘዴዎች የተለማመዱ ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ (ክፍሌ፣ 1986):;

ከዚህ በመነሳትም የተሻለ ዘዴ እንዲፈለግ የሚረዳ ጥናት መደረግ እንዳለበት በጥናታቸው ማገባደጃ አስተያየት የሰነዘሩ አሉ (ሰይድ፣ 1993፤ አለማየሁ፣ 1986):: በእነዚህ ሁለት ተመራማሪዎች የቀረቡ ሥራዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረቡ ጥናቶች ሲሆኑ፣ በማጠቃለያቸው ሰይድ፣ (1993) ልማዳዊውን የማስተማር ስነዘዴ ለመለወጥ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ሲገልጹ፣ አለማየሁ (1986) በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር ብዙ መሆን እና የክፍለ ጊዜው አነስተኛነት ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ እና እንዲለማመዱ ለማድረግ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፅሁፍ አርመው በጊዜ ለመመለስ የሚጠቀሙበት ልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ አመቺ እንዳልሆነ

በመግለጽ በማስተማሪያ ዘዴው ላይ ጥናት እንዲካሄድ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

ከዚህም በተጨማሪ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተለያዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ባስተማረባቸው ጊዜያት በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ ችግሮችን በማስተዋሉ እና ይህም ከሚከሰትባቸው አንደኛው እና ዋነኛው የማሰተማሪያ ዘዴው በመሆኑ በዘዴ ፍተሻው ላይ አተኩሯል:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው በመፃፍ ማሰተማሪያ ዘዴነት ያገለግሉ የነበሩ እንደ ውጤት፣ ሂደት እና ዘውግ ተኮር ዘዴዎች የተወሰነ ዕውቀት ለማሰጨበጥ ብቃት ያላቸው ቢሆኑም ድክመት ያለባቸው ናቸው:: በቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች የተሻለ የሚባል አንድ ወጥ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሌለ ያመለክታሉ (McLanghlin,1990):: በአሁኑ ወቅት ይህን ድክመት ለመቅረፍ እና የመፃፍ ክሂልን በተሳካ ሁኔታ ለማሰተማር የተሻለ ዘዴ ሊሆን እንደሚችል በምሁራን የሚነገርለት የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦችን በማቀናጀት መተግበር ነው:: በመሆኑም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ረገድ የዚህን ዘዴ ውጤታማነት ለመፈተሸ አቅዶ ተግብሯል::

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ መፃፍን መማር ለተማሪዎች አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ከመካከላቸው መፃፍን በሚገባ የሚካኑት ጥቂቶች መሆናቸው ይስተዋላል:: ከዚህም የተነሳ በፅሁፍ ሀሳብን መግለጽ ለብዙ ተማሪዎች አስቸጋሪ ሂደት ተደርጎ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በጣም የሚያስጨንቃቸው ነው (Richards, 1990:100):: በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ዐውድ መፃፍን ማሰተማር ከባድ እንደሆነ ይታሰባል:: ነገር ግን ይህ ሁኔታ በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሊከሰት የሚችል ነው (Recards and Nandya, 2002):: በሲንጋፖር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ኮርስ ካጠናቀቁ በኋላ የፅሁፍ ቋንቋን ለአካዳሚያዊ ተግባር ወይም ከህይወታቸው ጋር ለተገናኘ ጉዳይ ሲጠቀሙበት አይታይም (Lin, 2003):: በተመሳሳይ በታይላንድ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች በፅሁፍ ወቅት ችግር ተስተውሎባቸዋል (Foley, 2005)::

የመፃፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ወቅት የሚታዩ ችግሮች ከክሂሉ የውስብስብነት ባህሪ ብቻ የሚከሰቱ ሳይሆኑ ከስነትምህርታዊ ሂደቶች ጋር

በተያያዘ ሊያጋጥሙ ይችላሉ ናቸው:: ከነዚህ ስነትምህርታዊ ሂደቶች መካከል፤ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ አመራረጥ እና ትግበራ፣ የመምህሩ የማስተማሪያ ስልት፣ እንዲሁም የተማሪው የመማር ፍላጎት እና ስትራቴጂ ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት እና የይዘቶች አመራረጥ የመፃፍን ክሂል የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት ይወስኑታል (Silva, 1990)::

የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችግር ስንመለከት ብዙ ተመራማሪዎች እና መምህራን እንደሚሉት የተማሪዎችን ችሎታ የሚያሳድግ የመፃፍ አቀራረብ መኖር እንዳለበት ይስማማሉ:: ከዚህ አንፃር የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እንዲሻሻል ላለፉት አስርት ዓመታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል:: በቀደሙት ጊዜያት የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረቱ ለሰዋስው ትክክለኛነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጥ ለነበረው ውጤት ተኮር አቀራረብ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ የተማሪዎችን ፈጠራና የቋንቋ ክሂል ችላ በማለት የመፃፍ ውጤታማነትን ይለካ የነበረው በሚታየው የፅሁፍ እድገት ሳይሆን በሚገኘው የፈተና ውጤት ነበር::

የውጤት ተኮር አቀራረብ ባለበት ጉድለት የተነሳ ሂደት ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የተሻለ አቀራረብ ተደርጎ ተወስዷል:: ከሂደት ተኮር አንፃር የመፃፍ ሂደት ተመሳሳይ ሲሆን መፃፍ ውስብስብ፣ ተደጋጋሚ እና የፈጠራ ሂደት ነው (Silva, 1990):: በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች በደረጃ እንዲፅፉ ይፈለጋል:: በአጠቃላይ የመጀመሪያው የመፃፍ ሂደት ደረጃ ቅድመ መፃፍ ሲሆን ቀጣዩ መንደፍ እና በመጨረሻም መከለስና ማረም ናቸው:: የሂደት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች የመፃፍን ደረጃዎች እንዲረዱ በመፍቀዱና ለመፃፍ ክሂል አስተዋፅኦ የሚያደርገውን የተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀት እውቅና በመስጠቱ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ነው (Peltridege, 2001)::

ይሁን እንጂ Silva (1990) ባቀረቡት ሀሳብ በሂደት ተኮር አቀራረብ ላይ ድክመት እንዳለና በተለይም ከመፃፍ ዐውድ አንፃር ችግር እንዳለበት ገልፀዋል:: ስለመፃፍ ስንነጋገር ፀሀፊው ስለዐውድ፣ ስለተናጋሪው ማህበረሰብ፣ ስለማህበረሰቡ ባህልና ስለፅሁፉ ማሰብ ይኖርበታል:: ይሁን እንጂ ይህ አቀራረቡ ስለፅሁፍ ዓላማና ዐውድ ብዙ ትኩረት የሚሰጥ አይመስልም:: ከዚህ በተጨማሪ ሂደት ተኮር አቀራረብ የመፃፍ ሂደትን ለሁሉም ፀሀፊዎች አንድ ዓይነት አድርጎ የሚቀበል ሲሆን ፀሀፊውንና የሚፃፈውን ነገር ችላ ይላል (Balger and White, 2000):: ይላሉ::

ከ1980ዎቹ በኋላ የሂደት ተኮር አቀራረብ ባለበት ውሱንነት የተነሳ ዘውግ ተኮር አቀራረብ ተከስቷል:: ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የተለያዩ የፅሁፍ ዓይነቶችን ለተለያዩ የተግባቦት ዓላማዎች መጠቀም እንዳለባቸው በማሳየቱ በሰፊው ተቀባይነት አግኝቷል (Nunan, 1999):: ከዚህም በተጨማሪ ይህ አቀራረቡ ተማሪዎች በማህበራዊ ዐውድ ውሰጥ እንዲፅፉ ዕድል የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር የተለያዩ ፅሁፎችን በተለየ መዋቅር ለፅሁፉ ዕውናዊ ዓላማ እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ነው (Yan, 2005):: ይሁን እንጂ ዘውግ ተኮር አቀራረብ በፅሁፍ ወቅት ሂደትን ችላ በማለቱ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውበታል::

ባለፉት ሃያ ዓመታት መፃፍን በማስተማር ረገድ የትኛው ዘዴ የተሻለ እንደሆነ ለማሳየት ብዙ ውይይቶችና ክርክሮች የተካሄዱ ሲሆን ውጤትና ሂደት ተኮር አቀራረቦች መፃፍን በማስተማር ረገድ ከፍተኛ ተፅህኖ እንደነበራቸው ተስተውሏል:: እንደ Badger and White(2000) አገላለፅ ሂደት ተኮር አቀራረብ በዋናነት በስነልሳን ክሂሎች ይኸውም ማቀድና መንደፍ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ስለስነልሳናዊ ዕውቀት ግን ይኸውም ሰዋሰዋዊ ዕውቀትና ለመፃፍ መዋቅር አነስተኛ ትኩረት የሚሰጥ ነው::

የሂደት ተኮር አቀራረብ የመፃፍ ክሂልን መደበኛ በሆነ ሁኔታ ከመመማር ይልቅ መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ቢማሩ መሻሻል ሊያሳዩ ይችላሉ:: በመሆኑም መምህሩ ተማሪዎች የራሳቸውን ችሎታ እንዲያወጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርባቸዋል:: በሌላ በኩል ሂደት ተኮር አቀራረብ ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ተማሪ ተኮር ነው::

ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር በተደረገው ሽግግር እንደ Zamel (1983) ባሉ የሂደት ተኮር ዘዴ ሀሳብ አራማጆች ላይ የውጤት ተኮር ዘዴ አቀንቃኞችና ሌሎች ተመራማሪዎች ተግዳሮቶች አጋጥመዋቸዋል

በዚህም መሠረት ምሁራን መፃፍን በማስተማር ወቅት የውጤት፣ የሂደትና የዘውግ ተኮር አቀራረቦች እጥረት እንዳለባቸው በመገንዘብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል የዘውግና የሂደት ተኮር አቀራረቦችን አቀናጅቶ የማስተማርን ሀሳብ አቅርበዋል (Balger and White, 2000; Kim and Kim, 2005, Yan; 2005 and Gaon, 2007):: በእነዚህ ምሁራን አመለካከት የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ቅንጅት የተማሪዎችን የፅሁፍ ችሎታ በማሻሻል በኩል

አዎንታዊ ውጤት ያለው ከመሆኑም በላይ በቋንቋ መማር ላይ የተሻለ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል::

መፃፍን በማስተማር ረገድ በስፋት ተቀባይነት ያላቸው ሶስት አቀራረቦች ውጤት፣ ሂደትና ዘውግ ተኮር አቀራረቦች ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ የዘውግና ሂደት ተኮር አቀራረቦችን የማቀናጀት ሀሳብ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል:: Kim (2005) ባቀረቡት አስተያየት መፀፍን ለማስተማር ሂደትና ዘውግ ተኮር አቀራረቦችን በማቀናጀት ተማሪዎችን የመፃፍ ሂደቶችን ቢለማመዱ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ከማደጉም በላይ መፃፍ የሚከናወንበትን ዐውድና ዓላማ የሚረዱበትን ዕውቀት ያገኛሉ:: የBadger and White (200) ጥናት እንዳረጋገጠው እነዚህን ሁለት አቀራረቦች ማቀናጀት የተማሪዎች የመፃፍ ክሂል እንዲሻሻል እገዛ ደርጋል::

ይህን መነሻ በማድረግ በሀገራችን ኢትዮጵያ የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥን ስንመለከት ችግር ያለበት መሆኑን በዘርፉ የተከናወኑ በርካታ ጥናቶች (ለምሳሌ፡- ሰይድ (1993) በዕህፈት ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ማስታወሻ በመያዝ፣ በመወያየት፣ረቂቅ በመፃፍና የብጤ እርማት በማከናወንና መልሶ በመፃፍና በመከለስ ተግባራት ሲሳተፉና በክፍል ውስጥም የመፃፍን ሂደት በተግባር ሲማሩ እንዳልታዩ ገልፅዋል:: አስቴር(1998) መምህራን መፃፍን በማስተማር ዓላማ ተማሪዎችን በማርቀቅ፣ በመከለስና በማረም ሂደት እንዲያልፉ የሚሰጧቸው ድጋፍና የሚያደርጉላቸው ክትትል እንደሌለ ገልፀዋል::ሰለሞን (1991) መምህሩ መፃፍን በሚያስተምረበት ወቅት መምህር ተኮር ዘዴን ስለሚከተል የተማሪዎችን ልምድና ፍላጎት ከግምት ውስጥ እነደማያሰገቡ አመላክተዋል::

እነዚህ አጥኚዎች ባካሄዱቸው ጥናቶች የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች አደረጃጀት ብቁ ሆኖ አለመገኘት፣ የይዘቶች እና ክንውኖች፣ የማስተማሪያ ስነዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ አለመሆኑ፣ የመምህራን መፃፍን የማሰተማር ስነዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ስትራቴጂ የሚያሳድግ አለመሆኑን የገለፁ ሲሆን በጥናቶቻቸው በመፃፍ ትምህርት ላይ ድክመቶች መስተዋላቸውን እንዲሁም የተማሪዎቹ ችሎታ የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱን ጠቁመዋል:: እንዲሁም ክፍሌ (1986) የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታ በሚለው የጥናት

ውጤታቸው ተማሪዎች የሚፈልጉትን ሀሳብ የሚገልፁበት ቃላት የመምረጥ፣ የሰዋስው አገባብ የመጠበቅ እና ሀሳብን አደራጅቶ የመግለፅ ችሎታቸው ደካማ መሆኑን አመልክተዋል::

ከዚህ በተጨማሪ ባየ (1987፣8) በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር በማያያዝ እንደገለፁት፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቋንቋ አገልግሎት እና ስርዓት ተቀናጅቶ የቀረበበት ጊዜ ባለመኖሩ በሒደቱ ያለፉ ተማሪዎች የዕውቀት ባለቤቶች መሆን አልቻሉም:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች የስራ ማመልከቻ ይቅርና ተራ ደብዳቤ በወጉ ለመፃፍ ይቸገራሉ:: ይህን በሚመለከት ተስፋዬ (1986፣9-10) ሲገልጹ፣ "በመፃፍ ትምህርት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በተመለከተ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የመፃፍ ልምምድና የምጋቤ ምላሽ ስራ እየቀረ መጥቷል" በማለት አብራርተዋል::

ከፍ ሲል ከቀረበው ገለፃ መገንዘብ የሚቻለው መምህራን ለመፃፍ ክሂል ትምህርት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የተማሪውን ዳራዊ ዕውቀት፣ ደረጃ፣ ፍላጎት፣ ወዘተ. መሰረት አድርገው የሚዘጋጁበት እና የሚያቀርቡበት ሁኔታ በቂ አለመሆኑን ነው::

የመፃፍ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቀዳሚ ትኩረት ከሚሰጣቸው መሰረታዊ የክሂል ዘርፎች መካከል አንዱ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚታሰበው የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው በሚያስችል ሁኔታ መማር እንዳለባቸው ይታመናል:: ይህን መሰረት በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት እየተሰጠ ባለባቸው በኮሌጅ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በፅሁፍ ሀሳባቸውን የመግለፅ ችግር ያለባቸው እንደሆኑ ስዩም (1988) እና ሀና (2003) ገልፀዋል::

ከዚህ አንፃር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ለሚታዩ ችግሮች ብዙ ተመራማሪዎችና መምህራን ውጤታማ የሆነ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ የሚያሻሽል አቀራረብ እንዲኖር ይፈልጋሉ:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች በድርሰት ፅሁፍ ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ተማሪዎችና መምህራን ብዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

በመፃፍ ክሂል ከተማሪዎች ተከታታይነት ያለው ጥረት፣ በተደጋጋሚ በክሂሉ መገልገልን በመማሪያ ክፍልና ውጪ በቂ ጊዜ ጊዜን መስጠት ይፈልጋል::

የመፃፍ ክሂል አህምሮንና አካልን ማቀናጀት የሚፈልግና ከማሰብ ጋር የተገናኘ ተግባር ሲሆን በአንድ ጊዜም በርካታ መገለጫዎች ይኸውም:- ይዘቱ፣ቅርፁ፣ ዓላማውን ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚጠይቅ ተግባር ነው:: በአንባቢውና በፀሀፊው መካከል በሌሎች እንደሚስተዋለው ዓይነት ፈጣን ምልሽ አይሰጥም:: ፀሀፊው አጋዥ በሆኑ ተግባቦታዊ ስልቶች ይኸውም:- በአካል እንቅስቃሴ፣ በድምፅ ከፍታና ዝቅታ፣ በፊት ገፅታ የማይገለገል በመሆኑ ስነልሳናዊ፣ ስነልቦናዊ ስነአህምሯዊ ችግሮች የሚታዩበት ነው (Byren, 1991:4):: እነዚህ መገለጫዎች ክሂሉን በመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት ላይ ተፅህኖ እንደሚኖራቸው መገመት ይቻላል:: በመፃፍ ክሂል የመጠቀም ችሎታ እንዲሻሻል ለትምህርቱ ተቢውን ትኩረት መስጠትና ተከታታይነት ያለው ልምምድ ማድረግ እነደሚገባ (Norrish: 1990) ገልፀዋል::

ከዚህ አንፃር መምህራን የመፃፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት ሂደቱን በማመቻቸት፣ በመከታተል ተግባቦታዊ ክህሎት እንዲሻሻል የተማሪዎቹን ፅሁፍ ማንበብና በመፃፍ ሂደቱም ተማሪዎቹ እንዲያቅዱ፣እንዲያረቁና እንዲከልሱ ማድረግ ይገባቸዋል (Hedge 1991:11):: በሌላ በኩል Richards (1990:11) እንደገለፁት መምህራን ተማሪዎፈች ጥሩ ፅሁፍ እንዲፅፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተዋጣለትን ዘዴ ለመከተል እነዲችሉ ሂደቶችን ማመቻቸትና ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል::

ተማሪዎች በክሂሉ ተገቢ ዕውቀት አግኝተው ድርሰትን በቅርፅና በይዘቱ የተሟላ ሊያደርግ የሚችለውን የመፃፍ ዘዴዎችን አውቀው እንዲፅፉ መምህራን የተለያዩ የመፃፍ ዘዴዎችን ሲገለገሉ ካሰቡት ግብ ሊደርሱ እንደሚችሉ ይታመናል:: የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ በተካሄዱ ጥናቶች አስቴር (1998) መምህራን መፃፍን በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች በማቀድ፣ በማርቀቅ፣ በመከለስና በማረም ሂደትን እንዲከተሉ በቂ ድጋፍና ክትትል እንደማይደረግላቸው ገልፃለች:: በተጨማሪም ሰይድ (1993) በመፃፍ ትምህርት ወቅት ሳ በመወያየት፣ ማሰታወሻ በመያዝ፣ ረቅቅ በመፃፍና በመከለስ ተግባራት በበቂ ሁኔታ ሲለማመዱ እንዳልታዩ አመላክተዋል:: በተመሳሳይ ሰለሞን (1991) መምህሩ መፃፍን በሚያስተምሩበት ወቅት መምህር ተኮር ዘዴን ስለሚጠቀሙ የተማሪዎቻቸውን ልምድና ፍላጎት ግምት ውስጥ እንደማያስገቡ ገለፀዋል::

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ችግሮች ምክንያቱ በየእርከኖቹ በተዘጋጁ መርሀትምህርቶች ውስጥ ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችሉ ይዘቶች አለመኖራቸው ሳይሆን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉበት ዘዴ ላይ ይኸውም:- በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ ቋንቋውን ለመማር የተመደበው ክፍለጊዜ ማነስ፣ በመምህሩ ላይ የሚያጋጥም የስራ ጫና፣ ድርሰትን የማስተማር ፍላጎት አነስተኛ መሆንና፣ ተማሪዎች ድርሰት እንዲፅፉ አለማበራታትና የፃፉትንም አለማረም መሆኑን አለማየሁ(1986)፣ተስፋዬ (1986)እና ክፍሌ(1986) እንደምክንያት አቅርበዋል::

የዚህ ጥናት አቅራቢ በምዕራብ ሸዋ ዞን በተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ባስተማረባቸው ዓመታት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን እና ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መሄዱን ማጤን ተችሏል:: የችግሩን መንስኤ በመፈተሽ የመፍትኤ ሀሳቦችን መጠቆም አስፈላጊ መሆኑን በማመን በመፃፍ ክሂል ትምህርት ዙሪያ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ድክመት መኖሩን አመላክተዋል:: በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል የተማሪዎችን ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል የተባለው የዘውግ እና ሂደት ተኮር ቅንጅታዊ አቀራረብ የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ማስቻል አለማስቻሉን ማረጋገጥ የሚለው ለጥናቱ እንደአነሳሽ ምክንያት ታይቷል::

ከዚህ በመነሳትም አጥኚው በአሁኑ ወቅት ያለውን የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር በዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በማስተማር ማቃለል ይቻል ይሆንናል ብሎ ያስባል:: በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት የዘውግ እና የሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን በፅሁፍ ሀሳብ የመግለፅ ችሎታ ማሻሻል አለማሻሻሉን ማረጋገጥ ነው:: በዚህም ምክንያት ጥናቱ የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴን ተጠቅሞ ለተወሰነ ጊዜ በማስተማር ዘዴው የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ የሚያሻሽል መሆን አለመሆኑን የመፈተሽ ዓላማ ያለው ሆኖ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ጥረት ይደርጋል::

1. ተማሪዎች በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረጉ በኋላ ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው ይሻሻላል?
2. በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምዱ በኋላ ለመፃፍ ክሂል ያላቸው አመለካከት ለውጥ ያሳይ ይሆን?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎች ያሉት ሲሆን በመቀጠል እንደሚከተለው በተናጠል ቀርበዋል::

### 1.3.1. ዋነኛ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ ሂደተዘውጋዊ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው::

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ዐብይ ዓላማን መነሻ በማድረግ ጥናቱ የሚያተኩርባቸው የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት::

1. ሂደተዘውጋዊ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ያለውን ፋይዳ ይፈትሻል፣
2. ሂደተዘውጋዊ ዘዴን በመጠቀም በተማሪዎች የመፃፍ የትምህርት አመለካከት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ይመረምራል፣

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ሂደተዘውጋዊ ዘዴ ለተማሪዎች የጽሁፍ ክሂል መዳበር አስፈላጊ መሆኑ በጥናቱ ዳራ ላይ ተጠቁሟል:: የዚህ ጥናት ግኝት ዐውድን ተጠቅሞ የተማሪዎችን የመፃፈ ችሎታ ለማሻሻል ጥረት ለሚያደርጉ መምህራንና ተመራማሪዎች ተቀሜታ ይኖረዋል:: ከዚህ አንፃር ይህ ጥናት የተማሪዎችን ድረሰት የመፃፍ ችሎታ ማጎልበት የሚቻልበትን አቀራረብ የሚያጠና በመሆኑ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል::

- የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ክሂል ለማሳደግ ያግዛል::
- ተማሪዎች ለመፃፍ ክሂል አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያግዛል::
- የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ወቅት በተማሪዎች እና በመምህራን መካከል ተገቢ የሆነ መቀራረብ እንዲፈጠር ያግዛል::
- መምህራን የመፃፍ ትምህርት አቀራረባቸውን እንዲያጤኑት ያግዛል::
- በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሂደታዊና ዘውጋዊ ዘዴዎችን እንዴት ማቀናጀት እንደሚቻል ያሳያል::
- ወደፊት የመፃፍ ክሂልን ለማሳደግ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ ሆኖ ያገለግላል::

## 1.5 የጥናቱ ገደብ

የዚህ ጥናት ዓላማ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሂደታዊና ዘውጋዊ ዘዴዎችን በማቀናጀት በማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው:: በዚህ መሰረት ጥናቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይወሰናል::

1- ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 9ኛ "A" እና "F" ክፍሎች ላይ የተገደበ ነው::

2- በምዕራብ ሸዋ ዞን 36 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ: ነገርግን: በዚህ ምርምር ሁሉንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሸፈን በሂደቱም የሚገኙትን መረጃዎች ለመቆጣጠር አዳጋች ስለሚሆን ከሰላሳ ስድስቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በዕጣ ንሞና አወሳሰድ ዘዴ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል:: በስርዓተ ትምህርቱ አደረጃጀት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እርከን የዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎችን ያቀፈ ነው:: ይሁን እነጂ የ10ኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ እርከን ማጠናቀቂያ በመሆኑና በብሄራዊ ፈተና ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ የ9ኛ ክፍል ለዚህ ጥናት ሆን ተብሎ ተመርጧል::

3- በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል የሚማሩ 9 ክፍሎች (section) ሲኖሩ እነዚህን ክፍሎች በሙሉ ከጊዜ፣ ከሰው ኃይልና ገንዘብ አንፃር በመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሳ በጥናቱ ለመሸፈን አዳጋች በመሆኑ በዕጣ ንሞና

ዘዴ 9ኛ"A" እና 9ኛ"F" ክፍሎች የተመረጡ ሲሆን ይህ ጥናት በነዚሁ ክፍሎች ላብቻ ያተኩራል::

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ስድስት ምዕራፎች ይዟል:: የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያውን ክፍል ሲሆን:- የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የቁልፍ ቃላት ብያኔ መግለጫ እና የጥናቱን አደረጃጀት የሚያጠቃልለው ክፍል ነው::

ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ተዛማጅ ፅሁፎች መፃፍን ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር ይኸውም:- የማስተማሪያ ፅሁፎች፣ የትምህርቱ አቀራረብ፣ በመፃፍ ትምህርት ወቅት ከተለያዩ አቀራረቦች አንፃር የመምህሩና የተማሪው ሚና እና ሌሎች ሁኔታዎች በስፋት የተዳሰሱበት ነው:: የተዛማጅ ፅሁፉ ዋነኛ ዓላማ ለዚህ ጥናት ድጋፍ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ ንድፈ ሀሳቦችን ለማግኘት ነው::

ሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ንድፍና ዘዴ የተካተተበት ክፍል ነው:: በዚህ ምዕራፍ ስር ጥናቱ እንዴት እንደተነደፈ፣ በስራ ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡና እንደተነተኑ፣ ወዘተ. የቀረበበት ክፍል ሲሆን፣ አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ በሙከራ ጥናቱ (pilot study) የተሰበሰቡ መረጃዎች የተብራሩበትና የተተነተኑበት፣ እንዲሁም ከሙከራ ጥናቱ የተቀሰሙ ትምርቶች የተጠቃለሉበት ነው::

በምዕራፍ አምስት ስር በምዕራፍ ሶስት ላይ በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በምዕራፍ አንድ ስር ከቀረቡት መሪ ጥያቄዎች ጋር ተገናዝበው መረጃዎቹ ተተንትነው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል:: በመጨረሻው ምዕራፍ ስድስት ስር ማጠቃለያና አስተያየቶች ቀርበውበታል::

# ምዕራፍ ሁለት:- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ስር በፅሁፍ ትምህርት አቀራረቦች ወቅት በዋናነት የሚጠቀሱት:- ወጤት፣ ሂደትና ዘውግ ተኮር አቀራረቦች እንደሆኑና የነዚህ አቀራረቦች ምንነትና

ባህሪያት የተዘረዘረበት ክፍል ነው:: አሁን ባለንበት ዘመን የዘውግና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተቀባይነት እያገኘ ስለመምጣቱ እንዲሁም

ስለባህሪያቱና ምን እንደሚመስል፣ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ እንዴት ሊተገብር እንደሚችል ማብራሪያ ቀርቦበታል::

## 2.1 የፅሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

በጥንታዊ ቋንቋ የማስተማር ሂደት ውስጥ የመፃፍ ክሂል እንደ አንድ ክሂል የሚታይ ሳይሆን ሰዋስውን ለማስተማር የሚያገለግል መሳሪያ ተደርጎ ይወሰድ ነበር (Leki, 1992፣ Richards, 1990):: ይሁን እንጂ ቀስበቀስ በድርሰት ጥናት ላይ የሚድረጉ ምርምሮች እድገት እያሳዩ በመምጣታቸው መፃፍ እንደ አንድ የክሂል ዘርፍ መታየት ደረጃ ላይ በመድረሱ የምርምር ዘርፍ እየሆነ መጥቷል:: ከዚህ አንፃር በእንግሊዝኛ ቋንቋ አፍፊትንም ሆነ ኢአፍፊት ተማሪዎችን የመፃፍ ኪሂልን የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ማገዝ እንዲችሉ በስልጠናቸው ወቅት በመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያተኮሩ ኮርሶች ሊዘጋጁላቸው ይገባል (Kroll,1990:262)::

በተመሳሳይ መልኩ Leki (1992:171) የመፃፍ ክሂል ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ያነበቡትንና ያዳመጡትን ሀሳብ የሚገልፁበት መሳሪያ ሆኖ ስለሚያገለግላቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል በማለት ገልፀዋል:: ከዚህ አንፀር የመፃፍ ክሂል ተማሪዎች የሚማሯቸውን የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች እንደከታተሉ ከማገዙም በላይ ወደፊት ለሚሰማሩባቸው የተለያዩ የሙያ መስኮች ረገድም ጠቃሚ ነው::

መፃፍ መልዕክትን የሚወክሉ ስዕላዊ ምልክቶችን ብቻ የያዘ ሳይሆን አዲስ ግኝትን የመፈለግ እና ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው:: በመሆኑም መፃፍ የፊደልን ቅርፅ ለይቶ ከመፃፍ ጀምሮ አዲስ ሀሳብን በማፍለቅ ቃላትን እና ሀረጋትን አቀናጅቶ ዐረፍተነገር፣ አረፍተነገሮችን አቀናጅቶ አንቀፅን በማዋቀር

ሀሳብን በተደራጀ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ የሚያስችል ሂደታዊ ተግባር ነው (Janet, 2003:345)::

የተለያዩ ምሁራን Ramimes (1983,7), Brown (2000:1), Silva (1990) እንደገለፁት የመፃፍን ክሂል ለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ አቀራረቦች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት አግኝተው በስፋት እየተሰራባቸው ያሉት ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ናቸው ይላሉ:: በሌላ በኩል ካለፉት ሃያ ዓመታት ወዲህ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ስራ ላይ እየዋለ ይገኛል:: እነዚህ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች በዚህ ጥናት ውስጥ የሚነሱ መሰረታዊ ንድፈሀሳቦች በመሆናቸው ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን::

### 2.1.1. የውጤት ተኮር አቀራረብ

መፃፍን በማስተማር ረገድ ውጤት ተኮር አቀራረብ ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም መምህር ተኮር ነው:: በዚህ ዘዴ ተማሪው ሞዴሎችን እንዲቀዳ ይበረታታል (Brakan, 2003; Gabrielatos, 2002):: ይህ ዘዴ በመፃፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ እስከ 1970ዎቹ ድረስ ብቸኛው የማሰተማሪያ ስልት ሆኖ አገልግሏል:: የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ፅሁፎች ምሳሌ ይሆናሉ፣ ጥሩ ተፅፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን አቅርቦ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣ የአፃፃፍ ስልትን ወዘተ ተንትኖ ማሳየት እና ተማሪዎች የተመለከቱትን በፅሁፋቸው እንዲተገብሩ የማድረግ ስልትን የሚከተል ሲሆን ዋነኛው ትኩረቱ የቋንቋውን ሰዋስው ማስተማር ነው (Pica, 1986:6)::

የውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀፆች እና አውዶች መዋቅር እና አደረጃጀት ላይ ነው:: አላማው ትክክለኛ ፅሁፎችን ማፍለቅ ነው:: የውጤት ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያቱን እና መርሆቹን Richards (2002:30-32) እንደሚከተለው ገልፀውታል::

1. የድርሰት አፃፃፍ መመሪያዎችን እና የሰዋስው ህጎችን በተለያዩ የድርሰት አይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱቸው ያደርጋል::

2. የመፃፍ ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን ፅሁፎች መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው:: በተለያዩ የድርሰት አይነቶች ቅርፅ እና አደረጃጀት ላይ ያተኩራል::

3. ትክክለኛ የአረፍተነገር መዋቅር መሰረት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው:: በዚህ የተነሳ የሰዋስው ችሎታ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል::

4. ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲፅፉ እና ስህተት እንዳይሰሩ ለማድረግ ይሞክራል::

5. የእጅ ጽሁፍ፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል ወዘተ እውቀት በትምህርትነት ይቀርባሉ::

በአጠቃላይ የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ድርሰቶችን በማረም እና ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ በመቆጣጠር ላይ ነው:: በዚህ የፅሁፍ ትምህርት አቀራረብ የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ አንቀፆችን መገንባት እና ድርሰቶችን መፃፍ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ የሚደረጉ ልምምዶች፣ የሚመረጡ ሞዴሎች እና የዐረፍተ ነገሮች አመሰራረት የሰዋስው ህግጋትን የተከተሉ ናቸው ::

የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመፃፍ ትምህርት አንድን ድርሰት ለመፃፍ ከሚታለፍበት ሂደት ይልቅ መጨረሻ በሚገኘው ውጤት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: በአጠቃላይ ውጤት ተኮር አቀራረብ ከሂደት ይልቅ ውጤት ላይ ያተኩራል::

እንደ Richards (2001:107), Pincas (1982:14), Raims (1983:7) አገላለፅ በውጤታማ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ:: እነዚህ ተግባራት ውስን መፃፍ (Controlled Writing) ፣ መር መፃፍ (Guided Writing) እና ነፃ መፃፍ (Free Writing) ናቸው::

#### 2.1.1.1 ውስን መፃፍ

ውስን የመፃፍ መልመጃ ትኩረት የሚያደርገው ስህተትን ያለመስራት ወይም በትክክለኛነት ላይ ሲሆን ብዙ ጊዜ መልመጃው ለጀማሪ የመፃፍ ትምህርት ተማሪዎች የሚቀርብ ነው:: ይህ የመፃፍ መልመጃ በአንፃራዊነት ነፃነት ለሚሰጠው መር መፃፍ እንደመሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግላል:: በውስን መፃፍ

መልመጃ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በመከተል ሲሆን ስህተት እንዳይሰሩ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል:: የክንውኑ ዓላማም በአንፃራዊነት ከስህተት የፀዳ አረፍተነገር ወይም አጭር ጽሁፍ መፃፍ ነው::

ውስን የመፃፍ መልመጃ ተማሪዎች የፅሁፍ ቅርፅ እና ይዘት ቀርቦላቸው የሚያከናውኑት በመሆኑ የራሳቸውን ሀሳብ የማፍለቅ ዕድል የላቸውም:: ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ የመምህሩ ጥገኛ ናቸው:: በመሆኑም ስህተት ለመስራትም ሆነ የራሳቸውን ቅርፅ እና ይዘት ለመከተል አጋጣሚው አይኖራቸውም (Raimes, 1983:95-96)::

መፃፍን በመለማመድ ሂደት ተማሪዎች እንዲያስቡ እንዲመራመሩ፣ ሃሳባቸውን በጽሁፍ እንዲያሰፍሩ እና እንዲገልጹ ማበረታታት በትምህርት መርህ አስፈላጊ ነው:: ይሁን እንጂ ውስን የመፃፍ መልመጃ የሚያካትታቸው ተግባራት ማሰብን እና ማፍለቅን የማይጠይቁ ናቸው:: Raimes (1983:117) እንዳቀረቡት በውስን የመፃፍ መልመጃ አማካይነት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው::

- ክፍት ቦታዎችን መሙላት፣
- ሞዴል አረፍተነገሮችን አስመስለው እንዲጽፉ ማለማመድ፣
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን መመስረት፣
- በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማያያዝ አረፍተ ነገርን መመስረት፣
- ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መልሶ መፃፍ እና
- በአንቀፅ ውስጥ የፆታ፣ የቦታ እና የጊዜ ለውጥ በማድረግ እንደገና መፃፍ ናቸው::

#### 2.1.1.2 መር መፃፍ (Guided Writing)

እንደ Pincas (1982:102) አገላለፅ መር የመፃፍ ክሂል መልመጃዎች ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ ሲገልፁ ያጋጥሟቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ችግሮችን ለመቀነስ የሚፈጥሯቸውን ስህተቶች ለማሳነስ የሚያግዙ ተግባራት የሚቀርቡበት ደረጃ ነው:: መር የመፃፍ መልመጃዎች በውስን እና በነፃ የመፃፍ መልመጃዎች መካከል የሚገኝ ሲሆን በናሙናነት የቀረበን ጽሁፍ በአግባቡ በመገንዘብ ቅደም

ተከተሉ ጠብቆ የሚከናወን ነው:: በመር የመፃፍ መልመጃ ተማሪዎች በጅምር የቀረበን አረፍተነገር በራሳቸው ያሟላሉ:: በዚህም የተነሳ ስህተት የሚፈፅሙበት ሁኔታ ከፍ ያለ ይሆናል:: ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው በመር የመፃፍ ክንውን የተሻለ የመፃፍ ነፃነት መኖሩን ነው፡፡ ሆኖም ግን ስህተት በመስራት በኩል ከውስን የመፃፍ መልመጃዎች አንፃር ሲታይ ከፍ ያለ ነው::

በመር የመፃፍ መልመጃዎች ወቅት የሚከናወኑ ተግባራትን Raimes (1983:103) እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል::

1. ዝርዝር መረጃዎችን በመስጠት ሀሳቡን እንዲያስፋፉት ማድረግ፣
2. በሰንጠረዥ የቀረቡ ሀሳቦችን ወደ ጽሁፍ መቀየር፣
3. ያልተጠናቀቁ ታሪኮችን ማጠናቀቅ፣
4. ንድፎችን ተጠቅሞ አንቀፅ መመስረት፣
5. አረፍተ ነገሮችን በማወዳደር በጽሁፍ መግለፅ እና
6. አንድን ፅሁፍ አንብበው የተረዱትን በፅሁፍ መግለፅ ናቸው::

#### 2.1.1.3 ነፃ መፃፍ

እንደ Pincas (1982:110) አገላለፅ በነፃ የመፃፍ መልመጃ ለተማሪዎች ርዕስ ይቀርብላቸዋል ወይም እንዲመርጡ ይደረጋል:: በዚህም የተነሳ በራሳቸው ለመፃፍ ነፃ ናቸው:: በነፃ የመፃፍ መልመጃዎች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር አነስተኛ ነው:: በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በሚመርጡት ወይም በሚቀርብላቸው ርዕሰ ጉዳይ በነፃነት የሚፅፉበት ሲሆን በዚህ የመፃፍ ስራ የመምህሩ ሚና አነስተኛ መሆኑን አክለው ገልፀዋል::የነፃ መፃፍ መለኪያ ምን? እንዴት? ለምን? እና ለማን? ተፃፈ የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ፅሁፍ ቀረበ የሚለውን ሁኔታ ይመለከታል::

### 2.1.1.4 በውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች

በውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተለያዩ ምሁራን ትችት አቅርበውበታል:: በዚህ አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ቀጥለን እንመልከት::

Raimes (1983:17) በሰጡት አስተያየት ውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች እንዴት እና ለምን እንደሚጽፉ ከማሳየት ይልቅ የጽሁፍ ቅርጾችን እና የሰዋስው ህጎችን ተከትለው እንዲጽፉ የሚያደርግ ከመሆኑ ባሻገር የማስተማር ስልቱ በትዕዛዛዊ መመሪያ ላይ የተመሰረተ ነው::

በዚህ አቀራረብ ተማሪው በራሱ ተገፋፍቶ ሀሳቡን በተገቢው መንገድ ለመግለፅ የሚያስችለውን እውቀት አያዳብርም:: ለዚህ ሰበቡ አቀራረቡ ተማሪውን የሚገድብ በትዕዛዝ የተሞላና ተማሪው በራሱ ሀሳብ አመንጭቶ እንዲፅፍ የሚያበረታታ አለመሆኑ ነው:: የመማር ማስተማር ሂደቱ ደረጃዊነት፣ መስመራዊነት እና ትዕዛዛዊነት ይበዛበታል:: ይህ አቀራረብ ለሂደታዊ ፅሁፍ ፣ ለተማሪዎች ዳራዊ እውቀት እና ክህሎት ዋጋ የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ ዋና ትኩረቱ ጽሁፍ ተጠንቶ የሚቀርብበት ውጤት ላይ ነው:: ውጤቱም የሚለካው ከትክክለኛነት አንጻር ነው (Badger and White, 2000:157):: እንደ Zamel (2011:165) አገላለፅ በትክክለኛነት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከሚያጋጥመው ችግር መፃፍን በማጠናቀር ሂደት የተማሪዎችን ተጨባጭ ፍላጎት መፈተሽ እና ያላቸው ልምድ ለማጠናቀሩ ሂደት አጋዥ ነው ወይ የሚለው ይጠቀሳል::

Richards (2001:105), Maray (1980)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጨረሻ የጽሁፍ ውጤት እንጂ የተከተሉትን የአፃፃፍ ሂደት አያመላክትም ሲሉ በተጫማሪም በምሁራን የጥናት ውጤት መሰረት ይህ አቀራረብ ችግር እንዳለበት እና የችግሮቹም መንስኤ አቀራረቡ አንድን ፅሁፍ ለመፃፍ ምን አይነት አካሄድ እንከተል ከሚለው ይልቅ አንድ የመፃፍ ተግባር እንዴት ሆኖ ተጠናቋል በሚለው ላይ ትኩረት ከማድረጉ ባሻገር ለተፃፈ ነገር ትክክለኛነት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል:: በዚህ አቀራረብ ተማሪው የሚያውቀው አረፍተነገርን ከአረፍተነገር እንዴት

ማያያዝ እንዳለበት እና ልዩ ልዩ የጽሁፍ ቅርፆችን እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል ነው:: ይህ አካሄድ ተማሪው በራሱ መንገድ ተጉዞ ሃሳብ አፍልቆ እና አደራጅቶ የራሱን ጽሁፍ እንዴት መፃፍ እንዳለበት አያለማምድም::

በአጠቃላይ የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የመፃፍ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ስህተት እንዳይሰሩ የሚለውን ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ነው:: የመፃፍ ችሎታ የሚያድገው በተደጋጋሚ ልምምድ እንጂ በቅፅበት ባለመሆኑ አቀራረቡ ችግር ይታይበታል:: በመሆኑም መምህራን ይህን አቀራረብ ለብቻው ከመጠቀም መታቀብ ወይም ጠንካራ ጎኑን አጢነው ደካማ ጎኑን ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል::

### 2.1.2 የሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተጀመረው በእንግሊዝና በአሜሪካ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መፃፍን ለማስተማር ሲሆን ባሁኑ ጊዜ በበርካታ ሀገሮች በሁለተኛ እና በውጭ ቋንቋ መፃፍን ለማስተማር እያገለገለ ይገኛል:: አቀራረቡ ከቅርፅ ወይም ትክክለኛነት አንፃር ከማስተማር ይልቅ በአፃፃፍ ሂደት ማተኮር እንደሚገባ ያምናል (Raimes, 1983:10)::

የሂደት ተኮር አቀራረብ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለሰ በፊት ስለሂደት ተኮር አቀራረብ የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሳት ያሰፈልጋል:: ሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ከመጀመሪያው አንስቶ በመፃፍ ወቅት በሚከናወኑት ተግባራት ወይም ወደ ውጤት ለመድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ እንጂ በመጨረሻው ውጤት ላይ አይደለም:: በሂደት ተኮር አቀራረብ የፀሐፊው ትኩረት ፅሁፍን እንዴት እንደሚጀምር መወሰን ላይ ነው (Raimes, 1983:10)::

ሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው የመምህሩ የበላይነት እና ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍጥነት እንዲለማመዱ እና ስለሚጽፉት ድርሰት የአፃፃፍ ሂደት እንዲያስቡ እንጂ ስለቋንቋው የሰዋስው ህግጋት እንዲጨነቁ አይደለም:: ከዚህም ሌላ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንደ ውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በድርሰቱ ረቂቅ እና በቋንቋው ቅርፅ ላይ ከማተኮር ይልቅ አዲስ ነገር የመፈለግ፣ ትርጉም የማስፋት ሂደትን የሚከተል እና በፅሁፍ ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው (Silva, 1990)::

ሂደት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው አካሄድ በሂደት መፃፍን እንዲማሩ እና ከመምህራን ጋርም ተግባብቶ የመስራትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ አሳታፊ ነው:: በዚህም የተነሳ የተማሪው እና የመምህሩ ተሳትፎ በግልፅ የሚታይበት ነው:: በተጨማሪም ተማሪዎች ለመፃፍ በሚፈልጉበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ አዲስ ሀሳብ በማምጣት እና በማደራጀት እንዲፅፉ እድል የሚፈጥር ነው:: ይህ አቀራረብ መፃፍ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየጊዜው እርማት እና ማስተካከያ የሚሰጥበት በመሆኑ ተማሪዎች በሚሰጣቸው አስተያየት መሰረት የማስተካከል ተግባር ያከናውናሉ:: አቀራረቡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች በራሳቸው እንዲሰሩ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ተማሪ ተኮር ነው(Zamel, 2011, Raimes, 1983)::

Zamel (2011) ጽሁፍን በማጠናቀር ሂደት ላይ ፀሀፊዎች እንዴት ይጽፋሉ? ሀሳብ ከየት ይመጣላቸዋል? ሀሳቦቹ እንዴት ይደራጃሉ? እንዴትስ ይሰፋፋሉ? ፀሀፊዎች ምን አይነት አካሄድን ይጠቀማሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስተው ጥናቶች አካሂደዋል:: ጥናቶቹ መሰረት ያደረጉት ፀሀፊዎች እንዴት እንደሚጽፉ፣ ሀሳብ አፍልቀው ፍቺ እንዴት እነደሚፈጥሩ መረጃ መፈለግ ላይ ያተኮሩ ናቸው:: በተጨማሪም እነዚህ ጥናቶች ጽሁፉን በማጠናቀሩ ሂደት ፀሀፊዎችን የሚያሳትፏቸው መሰረታዊ ደንቦች በመሆናቸው በመፃፍ ሂደቱ ላይ ውሳኔ መስጠት እና መምረጥ ያስችላሉ::

መፃፍን የሚያስተምር መምህር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ጣልቃ ገብቶ በመደገፍ ሚናውን ማጎልበት አለበት:: በዚህም የተነሳ የመፃፍ መምህሩ ሀላፊነት የሚወሰነው በተማሪዎቹ የመፃፍ ልምድ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ በቂ ልምድ የሌላቸው ተማሪዎች በቂ ልምድ ካላቸው ተማሪዎች የበለጠ እገዛ ማድረግ እንዳለበት መገንዘብ ይኖርበታል:: በዚህ መሰረት መምህሩ በቂ ልምድ የሌላቸውን ተማሪዎች መፃፍ ሲያስተምር በመጀመሪያው የመፃፍ ተግባር ሙከራ ብቻ የሚሳካ አለመሆኑን ለተማሪዎቹ ማሳሰብ ይገባዋል (Zamel, 1982:195)::

በመፃፍ ትምህርት ወቅት አነስተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የሚያስተምር መምህር የቀደሙ የመፃፍ ስልቶችን በመጠቀም ሀሳቦችን እንዴት እንደሚያመነጩ ወይም እንዴት እንደሚጀምሩ ማስተማር ያለበት ሲሆን፣ በቀጣይ ከመምህሩ የሚጠበቀው ተሳትፎ ሀሳብን በማሳደግ እና በሀሳቡ ውጤቶች

የተለያዩ የፈጠራ ስልቶችን በመማር መጠቀም መቻልን በተመለከተ ያለውን ግንኙነት ማሳየት ነው:: መፃፍን የሚያስተምሩ መምህራን ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተማሪዎችን ተሳትፎ አሳድገው ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ላይ ነው (Zamel, 1982:203)::

በሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች አንድ የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ጽሁፍ ለመፃፍ የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የተግባር ደረጃዎች አሉ (Richards, 2001:108 እና Hedge, 1988:20-23):: እነዚህም፡- ቅድመ መፃፍ፣ ጊዜ እና መፃፍ ድህረ መፃፍ በመባል ይታወቃሉ::

### 2.1.2.1 ቅድመ መፃፍ

እንደ Pianko (1979,7) አገላለፅ ቅድመ መፃፍ (Pre writing) ሁሉም ተግባራት ፀሀፊው የድርሰቱን ርዕስ ካገኘበት ጊዜ አንስቶ የመጀመሪያውን ቃል እስከሚጽፍበት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያጠቃልል ሲሆን ተማሪው መረጃ ለመሰብሰብ አነባቢውን ለመወሰን እና የመጀመሪያ ንድፍን ለማቀድ የሚያከናውናቸውን ተግባራት የሚመለከት ነው: እንደ Richards (2001:109) Hedge (1988:21-22) አገላለጽ በቅደመ መፃፍ ደረጃ ለሚከናወኑ ተግባራት ተማሪዎች ሀሳብ ማመንጨት እንዲችሉ የሚደግፍ እና ስለሚጽፉት ጉዳይ እንዲያስቡ የሚያበረታቱ ናቸው:: በተጨማሪም በቅድመ መፃፍ ደረጃ የጽሁፍን አላማ እና አንባቢን መወሰን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: የአንድ ጽሁፍ ዓላማ የቋንቋ እና የአደረጃጀትን ምርጫ የሚወስን ሲሆን የአንባቢው ቀድሞ መታሰብ ፀሀፊው ምን እና እንዴት መፃፍ እንዳለበት ሀሳብ እንዲያገኝ ያግዘዋል:: በዚህም መሰረት ፅሀፊዎች ሀሳባቸውን ለማሰባሰብ ቅድመ መፃፍን በዋናነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: በቅድመ መፃፍ ደረጃ ሀሳብን ለመሰብሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን /ነፃ መፃፍን ማነቃቃትን ሀሳብ ማሰባሰብን ወዘተ መገልገል ይቻላል::

በአጠቃላይ የቅድመ መፃፍ ደረጃ አንድ ጽሁፍ ለመፃፍ የሚያስችል መረጃ የሚደራጅበት ጊዜ ነው:: ፀሀፊው ፅሁፉን መፃፍ ከመጀመሩ በፊት የሚፅፍበትን ርዕሰ ጉዳይ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች የሚያጣምርበት መንገድ

የርዕሱን ስፋት እና ጥልቀት የአንባቢውን ዳራ በማሰብ የሚያሰላስልበት ደረጃ ነው::

#### 2.1.2.2 ጊዜ መፃፍ

እንደ Richards (2001:109) አገላለፅ በሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ወቅት ይህ ደረጃ ከቅድመ መፃፍ ቀጥሎ የሚመጣ ነው:: ጊዜ መፃፍ ትክክለኛ የመፃፍ ተግባር የሚጀመርበት ከመሆኑም በላይ ተማሪው በቅድመ መፃፍ ደረጃ የሰበሰባቸውን ነጥቦች በረቂቅ መልክ በወረቀት ላይ የሚያሰፍርበት፣ ሀሳቡን ግልፅ በሆነ ቋንቋ የሚጽፍበት እና ለጽሁፉ የራሱን ቅርፅ የሚሰጥበት ደረጃ ነው::

#### 2.1.2.3 ድህረ መፃፍ

እንደ Richards (2001:109) አገላለፅ ደህረ መፃፍ በሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሶስተኛው ደረጃ ነው:: ይህ ደረጃ እንደ ክለሳ ሊወሰድ ይችላል:: በዚህ ደረጃ ፀሀፊው መልዕክትን፣ ቅርፅን እና አንባቢን በድጋሚ የሚያስብበት ከአንባቢው አንፃር የመልዕክትን ግልፅነት እና ትክክለኛነት የሚፈተሽበት እና ጽሁፉን ደጋግሞ በማንበብ ለሚያነበው ሰው ያለውን አመቺነት የሚመለከትበት ጊዜ ነው::

አንድ ጽሁፍ በሚፃፍበት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት በርካታና ዑደታዊ (Cyclical) ናቸው:: ከነዚህ መካከል ማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስ እና መልሶ ማቀድ ለአብነት ይጠቀሳሉ:: በመከለስ ደረጃ ከሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ተፈላጊውን ሀሳብ በተገቢው መንገድ ለአንባቢው መቅረቡን ማጤን፣
- ተፈላጊ ሀሳቦች አለመዘንጋታቸውን ማረጋገጥ፣
- የቃላት አጠቃቃምን ተገቢነት እና ጥንካሬ መፈተሽ፣
- ተገቢ ያልሆኑ ቃላት እና አረፍተ ነገሮች አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- ጽሁፉ ቅደም ተከተል ጠብቆ መደራጀቱን ማረጋገጥ ፣
- በጽሁፉ መካከል ያለውን ትስስር መለየት፣ ተገቢነትን እና ግልፅነትን መፈተሽ እና ማስተካከል፤

የሚሉት ይጠቀሳሉ (Hedge,1988,23 and Richards, 2001:113)::

በመፃፍ ስራ በመጀመሪያ ሙከራ የተዋጣለት ስራ መስራት እንደማይቻል እርግጠኛ መሆን አለብን:: ከዚህም ሌላ አንድ ጥሩ ጽሁፍ ለመፃፍ ሀሳብ ፣ጊዜ እና ትዕግስት ይጠይቃል:: በተጨማሪም ጽሁፍን በምናስተካክልበት ጊዜ በድጋሚ መፈተሽ፣ መፃፍ እና የአርትኦት ተግባር መዘንጋት የለበትም (Richards, 2001:108-109)::

ድህረ መፃፍ፣ በቅድመ እና ጊዜ መፃፍ የተሰበሰቡ ረቂቅ ሀሳቦች ተገቢነት የሚፈትሽበት ደረጃ ነው:: ተማሪው ከዓላማው እና ከአንባቢው አንፃር ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት በተገቢ ሁኔታ መቅረብ አለመቅረቡ የሚረጋገጥበት ደረጃ ነው::

በመሆኑም የቅድመ መፃፍ ተግባራት ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ እንዲሳተፉ እና እንዲመራመሩ የሚያስችላቸውን ቴክኒክ ከማስተዋወቁም ባሻገር  በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ሰለሚጽፉት ድርሰት የተለያዩ ንድፎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቃሉ:: በዚህ መሰረት ከአንባቢው ጋር ከተደረገ ውይይት እና መረጃ ምግባ በኋላ ተማሪዎች ንድፋቸውን መልሰው ይከልሳሉ:: ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳቦች የምንገነዘበው መልሶ መፃፍ እና  ማንበብ የሂደት ተኮር አቀራረብ ፅሁፎች ዋነኛ መለያ ሲሆን ማረም ደግሞ ቀጣይነት ያለው ባለብዙ ፈርጅ ሂደት ነው::

ንድፍ የማውጣት ሂደት የሚከተሉትን ማለትም ሀሳብን ማመንጨት /ቅድመ መፃፍ/ ይዘቱ ላይ ትኩረት በማድረግ የመጀመሪያውን ንድፍ መፃፍ፣ የፀሀፊው ሀሳብ ፍቺ እንዲኖረው ሁለተኛ እና ሶስተኛ ንድፍ ከተቻለም የበለጠ ንድፎችን ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው:: ይህን ሂደት ተኮር ሞዴል የሚከተል የመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ዋነኛው ቁልፍ ተግባር የፅሁፉ ይዘት፣ አለማ እና ተደጋግመው የሚዘጋጁ ንድፎች ናቸው::

ቀጥሎ የሚቀርበው ሰንጠረዥ ከ Tribble (1996) የተወሰደ ሲሆን ድግግሞሽን እና በቅድሚያ ሊተነተን የሚችል የመፃፍ ሂደትን የሚያሳይ ነው::

**የሂደት ተኮር አቀራረብ ቻርት**




Dynamic and unpredictable model of wrting

እንደ የድግግሞሽ ሞዴልነቱ ሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በክለሳ ከአንባያን የሚገኝ ምጋቤ ምላሽ የጽሁፍን ክለሳ የሚያግዝ እና እንደግብዓት ሆኖ የሚያገለግል ነው::

### 2.1.2.4 በሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች

ሂደት ተኮር አቀራረብ እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት መፃፍን ለማስተማር የተሻለ አቀራረብ ሆኖ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም ደካማ ጎን እንዳለው የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረውበታል:: ከአስተያየቶቹ መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት::

የሂደት ተኮር አቀራረብ ለሰዋስው እና መዋቅር አነስተኛ ትኩረት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በፅሁፍ ለሚገኝ የመጨረሻ ውጤት የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው:: መፃፍን በሂደት አቀራረብ የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች በየግላቸው

የራሳቸውን ውስጣዊ ችሎታ እንዲጠቀሙ ከማበረታታቸውም በላይ ትክክለኛነትን ችላ ይላሉ:: በአንፃሩ ውጤት ተኮር አቀራረብ ለትክክለኛነት ከፍ ያለ ቦታ ይሰጣል (Reid, 2001):: ሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሌላው ድክመቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ መፃፍን ተግባራዊ በማድረግ የተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ይዳብራል የሚል አካሄድን መከተሉ ነው (Atikin, 1996: 120)::

ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ መፃፍን በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከተላቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ጫና አላቸው:: ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆች እንዲጽፉ የሚሰጠው ትኩረት በየጊዜው ለሚጽፉት ጽሁፍ በተገቢው ሁኔታ የሚያዘጋጃቸው አይደለም:: በሌላ በኩል ለብጤ እርማት የሚሰጠው ከፍያለ ትኩረት ተማሪዎች ለራሳቸው ችሎታ ያላቸውን ግምት ዝቅ ያደርገዋል:: እንዲሁም በመፃፍ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ጥሩ በሚጽፉት ተማሪዎች ዘንድ ተለይተው እንዲታወቁ ስለሚያደርግ ስነልቦናዊ ጫና ያስከትላል (Horwitz,1986: 445)::

### 2.1.3 የዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ

ባለፉት አስርት ዓመታት ተፈጥሮአዊ አቀራረብ በተለያዩ ቋንቋን የማስተማሪያ ዐውዶች ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል:: ይህ አቀራረብ መሰረት የሚያደርገው ተማሪው በበቂ ሁኔታ ለቋንቋው ከተጋለጠ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እና በአጋጣሚ ቋንቋን ይማራል የሚል ነው (Krashen & Terrel,1983):: መምህራን ተፈጥሮአዊ አቀራረብን ስራ ላይ ሲያውሉ ግብዓቱን ካቀረቡ በኋላ ብዙ ጊዜ ጣልቃ መግባት አይፈልጉም ለዚህ ምክንያቱ ጣልቃ መግባት በትምህርቱ ላይ ችግር ይፈጥራል የሚል ነው:: በዚህ መሰረት በተፈጥሮአዊ አቀራረብ በአብዛኛው ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚደረገው መስተጋብር በተማሪዎች መካከል ነው:: የመምህሩ ሚና የቀረቡ ግብዓቶችን በመቆጣጠር የተገደበ ነው:: በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ቋንቋን በመማር ረገድ ከነሱ ስለሚጠበቀው ነገር ያላቸው ግምት አነስተኛ ነው::

በቅርብ ጊዜያት ይህ ተፈጥሮአዊ አቀራረብ ነቀፌታ ተሰንዝሮበታል:: ለዚህ ምክንያቱ "የማይታይ ስነ ትምህርታዊነትን (Invisible pedagogy) መሰረት ያደረገ መሆኑ ነው:: ብዙ ምሁራን የመማር ማስተማር አቀራረብ "የሚታይ ስነትምህርታዊነት" መሰረት ያደረገ መርህ እንዲኖር ሀሳብ ያቀረቡ ሲሆን ይህ

ሀሳባቸው ተማሪዎች በግልፅ ምን መማር እና መዳሰስ እንዳለባቸው የሚገልፅ እና እንዲሁም በዚህ ግልፅ አቀራረብ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ ከተማሪዎች ጋር የሚቀራረብበትን ስነ ዘዴ እንዲጠቀም የሚያስችለው እና እንዲሁም ተማሪዎች ዕውቀታቸውን እና ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው የሚያስችለው መሆን ይኖርበታል (Bernstein, 1990:73)።

ተማሪዎች ዐውዳዊ እና ስነልሳናዊ ገፅታዎችን በሚገባ በማስተዋል ፅሁፍን ቅርፅ ለማስያዝ እና ለማዋቀር እንዲችሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በትምህርት እና በሌሎች መስኮች የዘውግ አቀራረብን በማስተዋወቅ ረገድ አውስተራሊያ የመጀመሪያዋ ተጠቃሽ ሀገር ናት Macken-Horarik,M (2001)። የዘውግ አቀራረብ "የሚታይ ስነትምህርታዊነት" ሆኖ ቋንቋን ለማስተማር ስራ ላይ ውሏል። የዘውግ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪው ስለ ቋንቋ ግልፅ የሆነ ዕውቀት እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን በመምህሩ እና በተማሪው እንዲሁም በተማሪው እና በተማሪው መካከል ለሚኖረው መስተጋብር ዋጋ ይሰጣል።

በዘውጋዊ አቀራረብ ስራ ላይ የሚውለው ዘዴ መሰረት የሚያደርገው በራሺያው እና በአሜሪካዊው የስነልቡና እና የስነትምህርት ምሁራን Vygotsky, (1934/1978) and Burner, (1986) ስራዎች ላይ ነው። Vygotsky እንዳቀረቡት ሀሳብ በማንኛውም የክሂል ዘርፍ የእያንዳንዱ ተማሪ ዕውቀት ወይም ግንዛቤ ሁለት የዕድገት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው በነፃነት የማከናወን ደረጃ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ የተለያየ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር በሚፈጠር መስተጋብር ችሎታን ማሳያ ደረጃ ነው። በነዚህ በሁለቱ ደረጃዎች መካከል ያለውን ክፍተት Vygotsky "ቅርበት ያለው የእድገት ክልል" (The zone of proximal development) ብለው ይጠሩታል (Feeze and Joyce, 2002: 25-26)።

በ Vygotsky የዕድገት እሳቤ መሰረት የሚያደርገው የመማር ሞዴል ስለቋንቋ መማር ሁለት ሀሳቦችን ያቀርባል።

1. መምህሩ ተማሪው በቋንቋው ምን እንደሚሰራ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ይኸውም ተማሪው በራሱ ብቻ የሚከውን ከሆነ ምንም ዓይነት መሻሻል አያመጣም።

2. መምህሩ ተማሪዎችን የሚደግፍ ከሆነ ያለባቸውን ክፍተት ይሞላል:: እውነተኛ ትምህርት እና መሻሻል ይገኛል ::

ይህ ሞዴል እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ግብዓት ቀርቦላቸው በራሳቸው ችሎታ ብቻ መማራቸው በቂ አለመሆኑን ያሳያል:: Vygotsky ባቀረቡት ሀሳብ ትምህርት በተማሪው እና በመምህሩ ትብብር የሚከናወን ነው:: ይህ ትብብር የሚያሳየው በቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህሩ እና በተማሪው መካከል የሚካሄድ ግንኙነት መኖሩን ነው::

"ዘውግ" ስነፅሁፍን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን ወደፊት ሊሆኑ የሚችሉ እና በየዕለቱ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ በተለየ ባህል ውስጥ የሚገኙ ትምህርታዊ እና ስነፅሁፋዊ ሁኔታዎችን ይይዛል (Hammon and Derewianka, 2003):: በምዕራባዊያን ሀገራት" ዘውግ ወይም የፅሁፍ ዓይነት በንግግር ወይም በፅሁፍ ብዙ ጊዜ የሚገለፀው ወይም የሚመደበው በቀዳሚነት በማህበራዊ ዓላማ ነው :: እንደ Swales (1990) አስተያየት ተመሳሳይ ዓላማ የሚጋሩ ዘውጎች ተመሳሳይ የፅሁፍ ዓይነት ያመለክታሉ ሲሉ Derewianka (2003) ደግሞ ማህበራዊ ዓላማዎችን ቀዳሚ በማድረግ ስድስት ሁኔታዎችን ማለትም:-

1. ታሪክ መንገር (Narrative )፣ ለማዝናናት ታሪክ መንገር፣
2. መዘርዘር (Recount)፣ የሆነውን መንገር፣
3. የመረጃ ዘገባ (Information Report)፣ እውነተኛ መረጃዎችን መስጠት፣
4. መመሪያ (Instruction) ለአንባቢ ወይም ለአድማጭ ምን እነደሚያደርግ መንገር፣
5. ማብራሪያ (Explanation) አንድ ነገር ለምን ወይም እንዴት እንደተከናወነ መንገር፣
6. የማብራሪያ ፅሁፍ (Expository Text) አመለካከትን ማቅረብ ወይም መንገርን ለይተው አቅርበዋል::

እነዚህ ማህበራዊ ዓላማ ያላቸው የዘውግ ፅሁፎች የፅሁፍን ስነልሳናዊ ግብዓት ይኸውም፡-የስነልሳን ደንቦችን፣ ብዙ ጊዜ በሰንጠረዥ የተደገፈ የመዋቅር ቅርፅ

እና ስነልሳናዊ ገፅታን ይወስናሉ:: በተለየ ሁኔታ በሰንጠረዥ የተደገፈ መዋቅር፣ ውሰጣዊ መዋቅር ወይም በመግቢያ መልክ የተደራጀ ፅሁፍ፣ ዋነኛው ፅሁፍ እና ማጠቃለያ እንዲሁም ከስነልሳን አንፃር የተገነቡ የቋንቋ ገፅታዎች ይኸውም፡- ሰዋስው ፣ቃላት፣ አያያዦች ወዘተ ፀሐፊው መረጃዎችን ለመተርጎም ወይም ሀሳብን ወደሚነበብ ፅሁፍ ለመለወጥ መጠቀም አለበት::

የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ስለ ቋንቋ ያለን እውቀት ለተማሪዎች በቀላሉ ወይም ግልፅ በሆነ መንገድ ማቅረብ ላይ ነው:: ዘውግ የሚያመለክተው የጽሁፉን ይዘት እና ቅርፅ ክፍፍል ነው:: በሌላ በኩል ዘውግ እንደ ጽሁፉ ባህሪ ሊገለጽ ይችላል:: እንደ Stan (2000:14) ገለፃ ዘውግ ስርዓታዊ ሂደት ሲሆን በየጊዜው እንደነበሩት ንድፈ ሀሳቦች (Contempory theories) ሁል ጊዜ የሚለዋወጥ ነው:: በመሆኑም የተለያዩ ባህሎችን እና የማህበረሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ወጥነት ባለው መልኩ የሚከናወን ነው:: በዚህ መሰረት ዘውግን ስንተነትነው ዋነኛው እና ማዕከላዊው ነጥብ አላማ ነው:: የተለያዩ ዓይነት ፅሁፎች ወይም ዘውጎች ይኸውም የቅሬታ ደብዳቤ፣ የግብዣ ወረቀት፣ የህግ ዘገባዎች ለተለያየ ዓላማ ይውላሉ:: Swalles (1990: 58) ዘውግን ሲገልጹ ተመሳሳይ ተግባቦታዊ አላማዎችን የሚጋሩ ሰዎች ተግባባቦታዊ ሁነቶች የሚታዩበት ነው::

የዘውግ ተኮር አቀራረብ በ1980ዎቹ የተገኘ ሲሆን በዋናነት ገንቢ በሆነ መልኩ የተለያዩ አላማዎችን ለመረዳት በማህበራዊ አውዶች መፃፍን ስናስተምር መዋቅሮችን እና ስነልሳናዊ ገፅታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን (Yan, 2005:19):: በሌላ በኩል አገባብ፣ መዋቅር፣ አላማ እና ስነልሳናዊ ገፅታዎች እንደ ዘውጋቸው በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ መንፀባረቅ ያለባቸው ሲሆን በዚህ አቀራረብ ለአንባቢው እና ለጽሁፍ አላማ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው (Kim, 2007)::

የተማሪዎች ስነልሳናዊ ገፅታ እና መዋቅራዊ ደንቦች የተለያዩ ዘውጎችን መሰረት አድርገው የሚፈጠሩት ተግባባቦቶች ብዙጊዜ ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ የመፃፍ መምህሩ ተማሪዎችን በመምራት፣ በመደገፍ እና በመረዳት በኩል በተለያዩ ዘውጎች መነሻነት ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል:: የዘውግ ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር ሲነፃፀር ግብዓትን በተመለከተ በመካከላቸው ግልፅ መመሳሰል ይታያል (Badger and White, 2000:155):: ይሁን እንጂ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች የበለጠ

ውጤታማ ሆነው የሚማሩት የተለያዩ ምሳሌዎች እና ፅሁፎች ሲቀርብላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባል::

ከዚህ ቀደም ዘውግ የሚለው ቃል በስነጽሁፍ፣ በስነቃል እና በፊልም ጥናት ላይ ትኩረት ያደርግ የነበረ ሲሆን አሁን ደግሞ በስነልሳን ዘርፍ ላይም ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል:: በሌላ በኩል Swales, (1990) የዘውግን ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል::

1. ዘውግ ከተግባቦታዊ ሁነቶች የሚመደብ ነው:: እንደ Swales (1990) አስተያየት ተግባቦታዊ ሁኔታዎች ቋንቋ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ሚና እንዲጫወት የሚያደርጉ ናቸው:: ተግባቦታዊ ሁነቶች የሚከሰቱበት ሁኔታ ይለያያል:: ይኸውም ተግባቦታዊ አገልግሎት የሚገኝባቸው የተለመዱ ቦታዎች እና አነስተኛ ተግባቦታዊ ሁነቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች መከከል ልዩነት ይታያል:: ተግባቦታዊ ሁነቶች  በንግግር ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ የንግግሩን ሚና እና አካባቢያዊ እንዲሁም ታሪካዊና ባህላዊ ግንኙነቶችንም ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው::

2. ተግባቦታዊ ሁነቶች የተግባቦትን  አላማ የዘውግን ግብ ለማሳካት ያገለግላሉ:: እንደ Swalece (1990:46) አገላለፅ አላማን መለየት ቀላል ጉዳይ አይሆንም:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ተግባቦታዊ አላማዎች ግልፅ ይመስላሉ ይሁን እንጂ በሌላ ዘውግ ለምሳሌ - በጦርነት ወቅት የሚሰጥ ጋዜጣዊ መግለጫ ከአንድ በላይ አላማ ሊኖረው ይችላል:: በዚህ መሰረት አንዳንድ ዘውጎች ከአንድ በላይ ተግባቦታዊ አላማ ሊኖራቸው ይችላል:: ለምሳሌ:- የቴሌቪዥን ማስታወቂያ" የአግባቢነት ሚና፣ አጀንዳ የመቅረፅ እና ለግንኙነት መልካም እይታን ለመፍጠር የሚያግዙ ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላል::

3. የዘውግ ምሳሌዎች መሰረታዊ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል:: ለተግባቦታዊ አላማ የዘውግ አባላትን ማፍራት ብቻ በቂ አይደለም:: የተወሰኑ የዘውግ አባላትን ለመመስረት ተጨማሪ ገፅታዎች ያስፈልጋሉ:: Swales እንዳቀረቡት እነዚህን አቀራረቦች ከተለያዩ ገለፃዎች አንፃር መመልከት ይኖርብናል:: በየዕለቱ በተግባር የሚታዩ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙናል:: ለምሳሌ:- አትክልትና የቤት ዕቃዎችን ተሽከርካሪዎችን ወዘተ ለመግለፅ አስቸጋሪ ሊሆንብን ይችላል::

4. ዘውግ ይዘት፣ ካለበት ሁኔታ እና ከቅርፅ አንፃር ጠቦ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል:: Swales እንዳብራሩት የዘውግ አላማ በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ይህ ተቀባይነት ምክንያታዊነትን ሲያመላክት በተመሳሳይ በስምምነቶች ላይ የሚፈጠሩ እንቅፋቶችን ይቃወማል:: እነዚህ ስምምነቶች ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ ናቸው:: የሳሙና እና ዱቄት ማስታወቂያ በምሳሌነት ብንወስድ የማስታወቂያው አላማ በግልፅ ተቀባይነት ያለው እና የማስታወቂያው ስምምነት ቅርፅ በማስታወቂያው ጣልቃ መግባትን ለመቀነስ ይሞክራል:: ምክንያቱም ስምምነቶች በተጣሱ ቁጥር የዘውግ ተግባቦት አላማም እየቀነሰ ይሄዳል::

5. በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚሰጠው የቃላት ስያሜ ለዘውግ ጠቃሚ ነው:: በዘውግ ውስጥ ያለ የስምምነት እውቀት በጊዜያዊነት ተሳትፎ ከሚያደርጉት ይልቅ ባለሙያ ሆነው በዘውግ ላይ የሚሳተፉ የበለጠ ጠቃሚ ናቸው:: ተማሪው በሚገኝበት ማህበረሰብ የተለያዩ ተግባቦታዊ ሁነቶች ማለትም ገለፃ፣ ንግግር፣ ወርክሾፕ፣ ቲቶሪያል ሴሚናር ወዘተ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው::

#### 2.1.3.1 የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ገጽታ

የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የዘውግ ተኮር አቀራረብ ሁለት የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉት:: የመጀመሪያው ተማሪዎች አንድን የተለየ ዘውግ በተሳካ ሁኔታ በተመሳሳይ መንገድ እንዴት እንደሚጠቀሙበት መነሻ ነጥብ ሆኖ በሚገባ እንዲያስቡ ያግዛቸዋል::በዚህ መሰረት በተገለፀው ዘውገ እና ይህንን ገፅታ ለተማሪዎች ለማቅረብ ውጤታማ የሆነውን የመፃፍ ገጽታ ለመለየት ይሞክራል:: ዘውጎችን መለየት የሚያስገኘውን ስነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ Swales (1990:10) እንደሚከተለው ገልፀውታል::

> የግንዛቤ፣ የንግግር እና የስነልሳን ገፅታዎች ግንኙነት የሚመሰርተው እና ሊያድግ የሚችለው በዘውግ ውስጥ ብቻ ነው:: እንዲሁም ቋንቋ በተሟላ ሁኔታ ስምምነት ላይ የሚደረስበት እና የተግባቦት አላማ እና ደረጃ በቂ በሆነ ሁኔታ ለመመስረት ስነትምህርታዊ ተተግባሪነት በአገልግሎት እና በቅርፅ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያመላክት መሆን አለበት::

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የዘውግ ተኮር አቀራረብ አላማ ለተማሪዎች ስለ መዋቅር እና ንድፍ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ነው:: ይህንን ሁኔታ ግልፅ ለማድረግ ተጠቃሚዎች ተግባቦታዊ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ያለው የስትራቴጂ ደረጃ ተማሪዎች ይህንን ሁኔታ እንዲረዱ የትኛው ስነልሳናዊ ገፅታ እንዳለ ለማሳየት ያግዛል:: በአጠቃላይ የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ አላማ ለተመረጡ መዋቅሮች፣ ስትራቴጂዎች እና ስነልሳናዊ ገፅታዎች ማህበረሰባዊ እና ስነልሳናዊ ገለጻዎችን ማቅረብ ነው (Davies, 1988)::

በሌላ በኩል ዘውግ በተለየ ማህበራዊ አውድ ውስጥ ለተግባቦታዊ ተግባር የተፈጠረ በመሆኑ ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን ሰነ ትምህርታዊ ዘውግ ተማሪዎች መፃፍ ሲማሩ የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ስለቋንቋ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሲኖራቸው ነው የሚለውን አስተሳሰብ መሰረት ያደርጋል (Hyland, 2003a):: በመሆኑም እንደ ዘውግ አቀራረብ በጽሁፍ ላይ የሚደረግ ትንተና ለተማሪዎች የጽሁፍ ተግባር ይጠቅማል:: በዚህ መሰረት ዘውግ የተለያዩ የጽሁፍ ደረጃዎችን ይኸውም የንግድ ውል፣ ገላጭ እና አከራካሪ ጽሁፎችን ያካትታል:: ከዚህ በላይ የቀረቡት አስተያየቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የዘውግን አስፈላጊነት የሚያሳዩ ሲሆኑ ዘውግ ሰዎች በሚገባ የተደራጀውን የፀሀፊውን መልእክት በተለየ መንገድ እንዲረዱ የሚያደርግ ነው:: በመሆኑም ዘውግ የማህበረሰቡን ደንብ 'Social code' በመረዳት ጽሁፉን ለማደራጀት ይኸውም ስለማህበረሰቡ ፍልሰፍና ለመናገር እና መልካም ነገር ለማድረግ ከፍተኛ መሳሪያ ነው:: በአጠቃላይ ሰዎች ዘውግን በተገቢው መንገድ ሲረዱ ከማህበረሰቡ ጋር ያሉበትን ሁኔታ እና ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስማማት ያግዛቸዋል:: በዚህ መሰረት በማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ውጤታማ የዘውግ አቀራረብ ጠቃሚ መሳሪያ ነው::

የዘውግ ተኮር አቀራረብን ተጠቅሞ ተግባቦትን በመፍጠር መፃፍን ለማስተማር የሚያስችሉ የንድፈ ሀሳብ ድጋፎች አሉ:: ተማሪው ለተለያዩ ጽሁፎች መጋለጡ ብቻ ሳይሆን ጽሁፉ የተደራጀበት ሞዴል ያስፈልገዋል:: ከዚህ በኋላ የራሱን ጽሁፍ የሚጽፍ ሲሆን የሚከተሉትን ማለትም ማቀድ፣ መንደፍ፣ መከለስ፣ ማስተካከያ በማቅረብ መዋቅሩ ትክክለኛ የሆነ እና ተገቢነቱም የጽሁፉን አላማ የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል (S.A. MBE, 2010):: ተማሪዎች በመፃፍ

ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ በቋንቋ መማር ሂደታቸው ላይ መፃፍን መማር እንደ አንድ አይነተኛ ጉዳይ አድርገው ማቀድ ይኖርባቸዋል::

ከዚህ በላይ በቀረበው አስተያየት ስለሞዴል አስፈላጊነት ተጠቅሷል በዚህ መሰረት Cope እና Kalantzis (1993:11) መፃፍን ለማስተማር የሚያገለግለውን ሞዴል አቅርበዋል::




Martin's Model of Gener

በአጭሩ የዘውግ ተኮር አቀራረብ መፃፍ ከቋንቋ ዕውቀት ጋር የተገናኘ እና ከማህበራዊ ዓላማ ጋር ቁርኝነት ያለው ነው::

### 2.1.3.2 የተለያዩ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦች

Hyon (1996, 695) Flowrdeus and Swalesን ጠቅሰው እንዳብራሩት የዘውግ አቀራረብን በማቀድ ተማሪዎች ተግባቦታዊ አላማዎችን እና የጽሁፍን ስነልሳናዊ ገፅታ ተገንዝበው ንግግር እንዲያደርጉ ዘውጎችን መለየት ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ባለሙያዎች ለይዘት እና ለማህበራዊ አካባቢ የሰጡት ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ ዘውግ ተማሪዎች የተለያዩ ሁኔታዎችን ለምሳሌ:- እንግሊዝኛን ለትምህርታዊ አላማ፣ በክፍል ውስጥ ለሚደረግ ተግባቦት፣ እንደፈተና መሳሪያ እና የተፃፉ ፅሁፎችን ለማስተማር የሚያገለግል አድርገው ወስደውታል:: በሌላ በኩል አንዳንድ ተመራማሪዎች ዘውግን ስርዓታዊ ስነልሳናዊ አገልግሎት "Systemic functional linguistics" በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ በቋንቋ እና

በአገልግሎቱ መካከል ያለን ግንኙነት የሚያመልከት ነው በማለት ገልፀውታል (Hyon, 1996:696)::

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው በመፃፍ ትምህርት ወቅት የቀረበን ጽሁፍ በቋንቋው የተለየ ገፅታ ላይ ትኩረት በማድረግ መመልከት የሚያስፈልግ መሆኑን ነው::

Hyon, (1996), Halliday (1978)ን በመጥቀስ ሲያብራሩ የአንድ ዘውግ ስነልሳናዊ ገፅታ የማህበራዊ ሁኔታዎችን ድንበር ለማንፀባረቅ ቁልፍ ጉዳይ ነው ብለዋል:: በመሆኑም የቋንቋው ስርዓቶች በተለያዩ ጽሁፎች ውስጥ በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሰንጠረዥ የተደገፈ የዘውግ አቀራረብ ሞዴል አለ:: ይህ አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በይዘቶች በመለየት እና በቋንቋ ምርጫ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ የተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ ለማሻሻል ይሞክራል:: እነዚህ የተለያዩ ዘውጎች በሁለተኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ዋነኛው አካል ሆነው የሚቀመጡ ሲሆን በመርሀ ትምህርት ውስጥ በሁለት ተከፍለው ይቀርባሉ::

ጽሁፋዊ ዘውግ (literary gener) የሰዎችን ልምድ የሚዳስሱ ወይም የሚተረጉሙ ወይም በእውነት ላይ የተመሰረቱ ዘውጎች ናቸው:: በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለተገለፀ እያንዳንዱ ዘውግ ደጋፊ መረጃ ያስፈልጋል:: ደጋፊዎቹ በተለየ የዘውጎች አደረጃጀትና ይዘት በግልፅ እንዲነደፍ ይመራሉ:: በትምህርት ወቅት በተግባር ላይ የሚውሉ ሀሳቦችና የተለመዱ የሰዋስው ህጎች ለእያንዳንዱ ደረጃ ተስማሚ መሆን አለባቸው (Hyland, 2002:96-103)::

አንዳንድ ተመራማሪዎች በማንበብና መፃፍ እና በትምህርታዊ ምርምር ያቋቋሙት ፕሮጀክት መመሪያዊ አቀራረቦችን በመፍጠር ተማሪዎች የተለያዩ የትምህርት ቤት ዘውጎችን ይኸውም ዘገባዎች፣ አካሄዶች፣ ማብራሪያዎች፣ ገለፃዎችን መመሪያዊ አቀራረቦችን በመፍጠር እንዲገነዘቡ ያደረጋል:: ከዚህ ቀደም ሶስት ደረጃዎች ማለትም ሞዴሊንግ ከመፃፍ ጋር ቅርበትን መፍጠር እና በነፃነት ፅሁፍን መገንባትን በማሻሻል አንድ ተጨማሪ ደረጃ በመሰኩ እውቀትን መገንባትን ጨምረዋል::

ይህ ደረጃ አላማው የተማሪዎች ማህበራዊ አካባቢ የሚገኝበት የዘውግ ይዘት ዕውቀትን መገንባት ነው እንደ Byram (2004:234) አገላለፅ አዲሱ ንግግር

የዘውግ ምርምር ስልት ዘውግ ለሚፈጠርበት ማህበራዊ አውድ የተጋነነ ትኩረት ይሰጣል:: የአውስትራሊያው የዘውግ ጥናት ዘውግን ለመተንተን ስነልሳናዊ ዘዴን በሰፊው ተጠቅመዋል Hyon (1996:696), Byram (2004) Medaway (1994)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት ዘውግ ውስብስብ በሆነው ማህበራዊ ባህላዊ ተቋሚዊ ስርዓት ውስጥ በጉልህ ይታያል:: በአጠቃላይ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በተግባቦት ቅርፅ ላይ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ድርጊትንም ይመለከታል::

### 2.1.3.3 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታዎች

በማህበረሰቡ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶች በዘውግ አቀራረብ ላይ ትኩረት ሊደረግ ችሏል:: ዘውግ በማህበረሰቡ ውስጥ በቋንቋ ለመፃፍ ተቀባይነት ያገኘ ነው ብሎ መግለፅ ይቻላል:: Hyland (2003a) እንዳብራሩት ዘውግ በባህል ውስጥ ተቀባይነት ያለው በማንኛውም ተግባር ለምሳሌ ገለፃ፣ የዜና ዘገባ፣ ግጥም እና ትረካ የመሳሰሉት በማህበረሰቡ ውስጥ ዕውን የሚሆኑ ድርጊቶችን ይመለከታል::

ጥሩ የዘውግ ዕውቀት መኖር በመፃፍ ውጤታማ ለመሆን ይረዳል:: ብዙ ጊዜ መፃፍ ዓላማ ያለው፣ በማህበረሰብ እና በባህል ውስጥ የሚተገበር፣ ከዐውድ እና ዓላማ ጋር ግንኙነት ያለው ነው:: ከዚህ ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው የዘውግ ዕውቀት የሚያገለግለው ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ጭምር ነው:: በዚህ መሰረት የአንድን ባህል ዘውግ መማር ስለዚያ ባህል እና ዕድገት እንድንመረምር ያደርገናል (Christine,1987)::

ሌላኛው የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ ለተለያዩ አካዳሚያዊ ሁኔታዎች ያለው አስተዋፅኦ ነው:: ተማሪዎች የተለያዩ ፅንሰሀሳቦችን የፅሁፍ ሞዴሎችን ተገንዝበው የራሳቸውን ተመሳሳይ ፅሁፍ እንዲፅፉ ያደርጋቸዋል::

በወቅቱ በነበረው የውጭ ቋንቋ የማስተማሪያ ስልት ምትክ የዘውግ አቀራረብ በቋንቋ ባለሙያዎች ትኩረት እያገኘ መጣ:: በሂደቱም የዘውግ አቀራረብ አንቀፅን በማጠናቀር ረገድ የተለያዩ የዘውግ ሞዴሎችን በማምጣት የመፃፍ ምድቦችን ማደራጀት እና ልዩ ልዩ አሰራሮችን ስራ ላይ እንዲያውሉ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ሰጥቷቸዋል::

Devit (2003:17) በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የዘውግን ስነትምህርታዊ ፋይዳ እንደሚከተለው አብራርተውታል::

*የዘውግ ስነትምህርታዊነት መምህሩ ትኩረቱን በቀረበው ፅሁፍ ላይ እንዲያደርግ ተማሪዎችም በታለመላቸው ዐውድ እንዲፅፉ ያስችላቸዋል:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባለው ዓለም ውጤታማ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያግዛል:: የዘውግ ንደፈ ሀሳብ እና ምርምር ግለሰቦችን በሁለተኛ ቋንቋ እንዲያሰተምሩ ለማዘጋጀት፣ ለፅሁፍ መማሪያ የሚሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲያዘጋጁ ለመምከር ለትምህርት ባለሙያዎች የተገደበ ሚና ይሰጣል::*

በተጨማሪም Devit (2003) እንዳብራሩት የዘውግተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ መምህሩ ተማሪዎቹ የሚፅፉትን እንዲገምትና ይህ ግምት የተማሪዎቹን ፅሁፍ ሲገመግም ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባት ግንዛቤ ይፈጥርለታል::

ሌላኛው ዘውግ ፅሁፍን የማሳደግ ጠቀሜታ የማህበረሰቡን የቋንቋ ልምምድ ለማጥናት ያግዛል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ Bawarshi (2003:542) እንዳብራሩት "የዘውግ ትንተና ተማሪው የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንደ ለመድረስና የማህበርሰቡ አባላት ምን እንደሚያውቁ እና እንደሚሰሩ በአጠቃላይ የቋንቋ ልምምዳቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስችለዋል::

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው ነገር የዘውግ ትንተና በቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት ከተሰጣቸው ሀሳቦች፣ ዕሴቶች እና እምነቶች ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ከመሆኑም ባሻገር የዘውግ ተኮር አፃፃፍ በቋንቋው እና በቋንቋው ተናጋሪ መካካል የተወሳሰበ እና እርስ በርስ ተደጋጋፊነት ያለው ግንኙነት መኖሩን ያመለክታል::

የመፃፍ ትኩረት፣ ትርጉም፣ ትንተና፣ ክርክር ወዘተ ላይ ሲሆን መጀመሪያ ተማሪዎች ድርሰቱን አጥንተው ከተገነዘቡ በኋላ ሞዴሉን ይከተላሉ:: ከዚህም ባሻገር በዘውግ ውስጥ የተለየ የቋንቋ አጠቃቀምን ተከትለው የራሳቸውን ፅሁፍ ይፅፋሉ (Devit, 2003):: ከዚህ በኋላ ውጤታማ የሆነ ድርሰት ለመፃፍ ተማሪዎች ለራሳቸው ተስማሚ የሆነ ዘውግ እና ራሳቸውን ከተለየ የቋንቋ ዓይነት ወይም ስልት ጋር በማለማመድ በዘውግ ውስጥ በተለየ ሁኔታ የተማሩትን ዓይነት ግምት ውስጥ በማስገባት የራሳቸውን ፅሁፍ ይፅፋሉ:: የዘውግ አቀራረብን በመፃፍ

መማሪያ ክፍል ውስጥ ስራ ላይ ለማዋል የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል Christne (1987):: በዚህ መሰረት ዘውግ በአካዳሚያዊ ዐውድ ውስጥ የተፃፈ፣ የተተነተነ፣ የተቀዳ ሲሆን በስነልሳናዊ ፣ በቃላት እና በፅሁፋዊ ሁኔታው መፈተሽ ያለበት ነው:: በስነልሳን የትንተና ደረጃው የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ገፅታ ከተግባቦታዊ ዓላማው አንፃር መታሰብ አለበት:: በሌላ በኩል የፅሁፍ አወቃቀር ሲተነተን ተማሪዎች ለቋንቋ ምድቦች ማለትም፡-ለቃላት፣ ለዐረፍተነገር፣ ለንግግር እና ለመሳሰሉት ፍቺ የሚሰጠው እንዴት ነው? የሚሉትን ነጥቦች ማሰብ ያስፈልገል::

Kim and Kim (2005) Bhatia (1993)ን ጠቅሰው ባቀረቡት አስተያየት በጽሁፍ ወቅት መደበኛ እና አገልግሎታዊ የቋንቋ ክፍሎችን አንድ ላይ በማስተሳሰር ተማሪዎች ስነልሳናዊ ደንቦች በተለየ የንግግር ወቅት የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲረዱ ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋ:: በዚህ መሰረት ተማሪዎች በዘውግ አቀራረብ የንግግር ይዘትን መዋቅር ሲተነትኑ አንዳንድ የጋራ የሆኑ ደንቦች በእያንዳንዱ ዘውግ ውስጥ መኖሩን ሊለዩ ይችላሉ:: በመሰረቱ እነዚህ ደንቦች ተማሪዎች በሚቀጥለው የትምህርት ጊዜ የሚጠቀሙበትን እውቀት ይፈጥርላቸዋል::

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በአስተሳሰባቸው ተለዋዋጭ እንዲሆኑ በማገዝ በኋላ ላይ ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚያደራጁ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ደጋፊዎች እንደጠቆሙት የዘውግ ተኮር አቀራረብ ከፍ ባለ ደረጃ ካሉት ይልቅ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ጀማሪዎች እና በመካከለኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የበለጠ ጠቃሚ ነው:: በዚህ የተነሳ ተማሪዎች በመፃፍ ተግባራቸው ወቅት የሚያጋጥማቸው ጭንቀት የሚቀንስ ቢሆንም ሰዎች አዲስ ነገር ሲማሩ በጋራ የሚያሳስቧቸው ነገሮች እንደ ማመሳከሪያ ወይም እንደምሳሌ ለመውሰድ ምክንያት ይፈልጋሉ::

ዘውግ ሁልጊዜ የተለያዩ ነገሮችን ደምዖችን፣ ስልቶችን፣ የንግግር ገለፃዎችን እና አመለካከቶችን በማጣመር የሚያቀርብ ነው:: በመሆኑም የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ለተለያዩ ዘውጎች እንዲጋለጡ በማድረግ በዘውግ አቀራረብ ተጠቅመው የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል:: በዚህም የተነሳ የዘውግ አቀራረብ በዘውግ መሰረታዊ አስተሳሰብ እውን እንዲሆን በመጨረሻው ደረጃ ተማሪዎች በዘውግ ውስጥ የሚገኘውን አቀራረብ እንዲገነዘቡት እና እንዲገለገሉበት ማስቻል አለበት (Hingugen, 2006)::

Hyland, (2007:10-11) የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን ጠቀሜታ እንደሚከተለው አቅርበውታል፤

- ግልፅ (explicit)- የመፃፍ ክሂል መለማመድ ለማመቻቸት በትምህርትነት የሚቀርበውን ነገር ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፤
- ፍላጎትን ያማከለ (Needs Based)- የጽሁፍ አላማ እና ይዘት መነሻው የተማሪዎች ፍላጎት መሆን አለበት፤
- ሀላፊነት መስጠት (Empowering)- በደንቦች እና በጽሁፍ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ልዩነት የሚያሳዩ ነገሮችን ማቅረብ
- ደጋፊ (Supportive)- የተማሪዎችን የመማር እና የፈጠራ ችሎታ ለማሳደግ ለመምህሩ ትልቁን ሚና መስጠት፤
- ጥልቀት (critical)- ለተማሪዎች መረጃዎችን በማቅረብ ንግግሮችን እንዲገነዘቡ እና በጥልቀት እንዲመለከቷቸው ማድረግ፤
- ንቃትን ከፍ ማድረግ (conciousners raiting)- ስለጽሁፍ እና ተማሪዎች በጽህፈት ጊዜ በራሳቸው እንዲተማመኑ ለመምከር  የመምህሩን ንቃት ከፍ ማድረግ::

### 2.1.3.4 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ባህሪ

የዘውግ ተኮር የመፃፍ አቀራረብ ቋንቋን ለማስተማር በመጀመሪያ ብቅ ያለው በአውስትራሊያ በማህበረሰቡ ውስጥ ከተነጠሉ ቡድኖች ጋር ለመስራት በማሰብ ነው (Feez, 2002:24):: በተደጋጋሚ የተለየ ቦታ የማይሰጣቸው ተማሪዎች ከተለያዩ ዘውጎች ጋር መላመድ ያለባቸው ሲሆን ከዘውግ ጽሁፎች ጋር እንዲላመዱ ለማድረግ ሲታሰብ ስለስነልሳን እና ስለማህበረሰቡ ደንቦች በቂ ግንዛቤ የሌላቸው ተማሪዎች ተከስተዋል:: በመሆኑም መፃፍን በዘውግ ማስተማሪያ ክፍል ውስጥ ጠንካራ በሆኑ ስርዓቶች መምህሩን ሞዴል በማድረግ ተማሪዎች የተለያየ ዘውግ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ታይቷል:: ይሁን እንጂ የመጨረሻው አላማ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲጽፉ ማስቻል ነው:: በዚህ መሰረት በተከታታይ በዘውግ ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ የመፃፍ ሂደት ከሞዴል ወደ ቁጥጥር የሚደረግበት የጽሁፍ ልምምድ እና በመጨረሻም ራስን ችሎ ወደመፃፍ የሚያመራ ነው (Hyland, 2007):: ከዚህ በላይ የቀረበውን የመፃፍ

ሂደት ባህሪ ተደጋጋሚ ሞዴል፣ ፅሁፍን በጋራ መገንባትን እና በግል ጽሑፍን ማደራጀትን የሚያመለክት ነው::




Hyland's gener based writing process. (Hyland, K. 2007:21)

በሞዴሊንግ ደረጃ መምህሩ እና ተማሪው ስለጽሁፍ መዋቅር ዐውድ እና ቋንቋ ውይይት ከማካሄዳቸውም በላይ ጽሁፍን በጋራ ያጠናቅራሉ:: በግል የመፃፍ ደረጃ ተማሪዎች የግላቸውን ጽሁፍ ሲጽፉ በመምህር እና ተማሪ ውይይት ደረጃ ጽሁፉን ለማጠናቀቅ የመልሶ ክለሳ እና የአርትኦት ስራ ይከናወናል (Hyland, 2004:21)::

እያንዳንዱን ደረጃ ከሚያሳዩት ሀሳቦች እንደተመለከትነው እነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች የዘውግ ተኮር የመፃፍ ሂደትን ተፈጥሮሃዊ ስርዓት የሚያመለክቱ ሲሆን ተማሪዎች በሌሎች ድጋፍ በነፃነት ራስን ችሎ ወደ መፃፍ ለውጥ መድረሳቸው ነው:: ሌላኛው የዘውግ ተኮር የመፃፍ ሂደት ጠቃሚ ባህሪ በሂደቱ የእያንዳንዱ ደረጃ ተለዋዋጭነት ነው:: ከዚህ አንፃር ተማሪው እና መምህሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወዳለፈው ደረጃ መመለስ የሚችሉ ሲሆን በተጨማሪም ከታለመው ዘውግ ጋር ሲለማመዱ እና በቂ እውቀት ሲኖራቸው ያለፈውን

የሞዴል ደረጃ በመተው የሚቀጥለውን ደረጃ መጀመር ይችላሉ (Hyland, 2007: 129)::

#### 2.1.3.5 የዘውግ ፅሁፍ አቀራረብ እና ሚና ጫወታ (Gener writing &Role paying)

የተማሪዎቻቸውን ሚና በመገመት አንፃር መፃፍን በሚያስተምሩ መምህራን መካከል ልዩነት ይታይባቸዋል:: ከዚህ አንፃር ልምድ ያላቸው ፀሀፊዎች የዘውግ ፅሁፍ ሁል ጊዜ ሚና ጫወታ (Role paying ) እንዳለው የሚገነዘቡ ሲሆን በሌላ በኩል አነስተኛ ልምድ ያላቸው ፀሀፊዎች ግን ትኩረት የሚያደረጉት ስለራሳቸው ገለፃ በመሰጠት እና በቀጥታ ስለድርሰቱ ፍንጭ በመስጠት ላይ ነው:: ይህንን ሁኔታ Simpson (1997) ባቀረቡት ምሳሌ በስነፅሁፍ ኮርስ ላይ ተማሪው በአንድ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ በመስማማት ወይም ባለመስማማት ድርሰት እንዲፅፉ ይደረጋል:: የተፃፈውን ድርሰት ፍንጭ በሚሰጥ ሁኔታ ስንተረጉመው አለመስማማትን መርጠው የሚፅፉ ጀማሪዎች አለመስማማታቸውን በመግለፅ ወይም በርዕሱ ዙሪያ የራሳቸው ሀሳብ በመገንባት ይጀምራሉ:: በተመሳሳይ መስማማትን የመረጡ ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ በጥልቀት ሳያስቡ እስማማለው የሚለውን አገላለፅ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ከዚህ አስተያየት መገንዘብ የሚቻለው አነስተኛ ልምድ ያላቸው ፀሀፊዎች ርዕሱን ከተለያየ አቅጣጫ ለማጤን እንደማይሞክሩ ነው::

Bawarishi (2003) እንዳመለከቱት በመፃፍ ወቅት ተማሪዎች ሚና እንዲኖራቸው እና የሚሰማቸውን ነገር ለመግለፅ እንዲችሉ ተገቢ ልምምድ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: በሌላ አባባል በዘውግ ፅሁፍ ውስጥ ውጤታማ የሆነ ምላሽ እንዲኖር ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያመነጩ እና ይህንን ያመነጩትን ሀሳብ በተለያየ መንገድ ማቅረብ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል:: በዚህ መሰረት ሚና ጫወታ በዘውግ ፅሑፍ ውስጥ ለመተርጎም ለመተንተን እና ሀሳብን ከራስ አመለካከት አንፃር ለመግለፅ ሰፋ ያለ ዕውቀት ይጠይቃል:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ለምሳሌ ተማሪዎች ሚና እንዲጫወቱ ፅሁፉ ፍንጭ እንዲሰጥ አስፈላጊ ይሆናል:: በመጨረሻም የቀረበው ፅሁፍ በተማሪዎቹ በራሳቸው እንደተፃፈ የሚያሳምን መሆን ይኖርበታል::

### 2.1.3.6 በዘውግ ተኮር አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች

እንደ ሌሎች አቀራረቦች የዘውግ ተኮር አቀራረብም ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: እንደ Caudery (1998:11-13) አስተያየት የተለየ ዘውግን በግልፅ ለማስተማር መሞከሩና መምህራን ተማሪዎችን ለመረዳት በተገቢው ሁኔታ ላይ አለመገኘታቸውን የገለፁ ሲሆን እንዲሁም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልፁ ብዙም የሚያግዝ አለመሆኑን ወይም መምህሩ በሚያመጣው ተስማሚ ሞዴል በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ ይሆናሉ:

በዘውግ ተኮር ላይ ሌላው የሚሰነዘረው ትችት ከተለያዩ አንባያን ጋር ለመግባባት ምናልባት በቂ የቋንቋ እና የቃላት ችሎታ ላይኖራቸው ይችላል የሚል ሲሆን እንደ Badger and White (2000) አስተያየት የዘውግ ተኮር አቀራረብ እንደድክመት የሚቆጠርበት ነጥብ ጽሁፍን ለመፃፍ የሚያስፈልገውን ክህሎት ችላ ማለቱ እና ተማሪዎች በሌላ መስክ ያላቸውን የመፃፍ ችሎታ ግምት ውስጥ የማያስገባ መሆኑ ነው::

በአጠቃላይ የዘውግ ተኮር አቀራረብ በዋነኛነት ከሚተችባቸው ነገሮች መካከል በአብዛኛው ተማሪዎችን ተቀባይ አድርጎ መቀጠሩ ሲሆን በሌላ በኩል የዘውግ ተኮር አቀራረብ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው መፃፍ በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ የሚተገበር እና የተለየ ዓላማ ነፀብራቅ መሆኑን እንዲሁም ትምህርት ባለን ንቃት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ሁኔታዎችን በመኮረጅ እና በመተንተን ላይ የሚመሰረት መሆኑ ነው:

### 2.1.4 የሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ

የሂደተዘወጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ቅንጅት ነው:: የሂደት ተኮር አቀራረብ በመፃፍ ውስጥ የሚከተሉት አራት ደረጃዎች ማለትም 1. ቅድመ መፃፍ 2. መንደፍ 3. ክለሳ እና 4. የአርትኦት ስራዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይህ አቀራረብ ለክለሳ እና ከሌሎች ለሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ተማሪዎች ብዙ ንድፎችን እንዲጽፉ ያደርጋል:: የሂደት ተኮር አቀራረብ ጠቃሚ ገፅታው በጽሑፍ ጊዜ ተማሪዎች ከርዕሱና ከይዘቱ ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት የሚፈጥረው ትርጉም እና በጽሑፍ ጊዜ ስለሚከተሉት ሂደት በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረው ትርጉም ነው::

በሌላ በኩል የሂደት ተኮር አቀራረብ በመፃፍ ወቅት ተማሪዎች የሚከተሏቸውን ሂደቶች ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ እና ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ይዘው የሚመጡት ጽሑፍ ለመፃፍ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዳለው የሚቀበል በመሆኑ በሰፊው ተቀባይነት አግኝቶ ስራ ላይ ውሏል::

እንደ Yan (2005:20) አስተያየት የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሶስት ደረጃዎች ማለትም 1. ታላሚው ዘውግ ለተማሪዎች በሞዴልነት መቅረቡን 2. ጽሐፍ በመምህሩ እና በመምህሩ ቢጋራ መገንባቱ እና 3. እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ጽሑፍ መፃፍ እንዳለበት ይቀበላል:: በተጨማሪም ወጥ የሆኑ ዕሑፎችን በማስተዋወቅ ተማሪዎችን በማሳተፍ በጽሑፍ ሂደት አግባብነት እንዲኖር ያግዛል::

Hyland, (2003b) ዋና ዋና የዘውግ እና የሂደት ተኮር አቀራረቦችን መርህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አጠቃለው አቅረበዋቸዋል::

| ባህሪይ | ሂደት | ዘውግ |
|---|---|---|
| ዋና ሃሳብ | መፃፍ የማሰብ ሂደት ነው<br>በፅህፈት ያተኩራል | መፃፍ ማህበራዊ ድርጊት ነው<br>በመጨረሻው ውጤት ላይ ያተኩራል |
| የማስተማር ትኩረት | በፈጠራ ፅሁፍ ያተኩራል<br>ሀሳብ እንዴት እንደሚፈጠር እና እንደሚያድግ | አንባቢዎች በሚጠብቁት እና በውጤቱ ላይ ያተኩራል<br>ማህበራዊ ዓላማን ውጤታማ በሆነ መንገድ መግለፅ |
| ጥቅሙ | የመፃፍ ሂደት የሚያሳይ ነው<br>ለማስተማር መሰሰረታዊ ነገሮችን ያዘጋጃል | ዐውድን በግልፅያሳያል<br>ለአንባቢው እና ለዓላማ ፅሁፍን ዐውዳዊ ያደርጋል |
| ጉዳቱ | የአፍ መፍቻና ሁለተኛ ቋንቋን ተመሳሳይ አድርጎ ይወስዳል<br>የሁለተኛ ቋንቋ ችግሮችን ችላ ይላል<br>ለውጤት አነስተኛ ቦታ ይሰጣል<br>ሁሉም መፃፍ ተመሳሳይ ሂደት የሚከተል ነው | የመፃፍን ትምህርት ከውጤት አንፃር ያያል<br>ለፅሁፍ ውጤት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል<br>የፅሁፍ ክሂሎችን ችላ ይላል |

(Hyland, 2003b:24)

ሂደት ተኮር አቀራረብ መፃፍን እንደግንዛቤ ተግባር የሚቆጥር ሲሆን በፀሐፊውና በፅሁፉ ሂደት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: የዚህ አቀራረብ ዓላማው የፀሀፊዎችን

ሀሳብ መገንዘብና መግለፅ እንዲሁም የፅሁፍ ክሂልን ማሳደግ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው:: በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ስለመፃፍ ሂደት ግልፅ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል:: ነገርግን በፅሁፍ ወቅት ስራ ላይ ያለውን መደበኛ የቋንቋ ስርዓት ለመጠቀም ክፍተት ይታይበታል:: በሌላ በኩል የዘውግ አቀራረብ መፃፍን ማህበራዊ ድርጊት አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን በክፍል ውስጥ አቀራረቡ ማህበራዊ ዓላማን ለማሳካት በዐውድና በቋቋን ገፅታ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ግልፅ የሆነ የቋንቋ ተፅታዎችን ለማህበራዊ አገባብ እንዲጠቀሙበት ያስችላል::ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ ለፅሁፍ ውጤት ከፍተኛ ውጤት የሚሰጥና ለፅሁፍ ክሂልና ሂደት የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ ነው::

### 2.1.4.1 የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ውሑንነት

የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ ተማሪዎች በተለየ ዘውግ ተደጋጋሚ ሂደቶችን ቅድመ መፃፍ፣ ንድፍ፣ ክለሳ እና አርትኦትን ሲጠቀሙ በአላማ እና ቅርፅ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲያጤኑት ዕድል ይፈጥራል:: በሌላ በኩል የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች መፃፍን ከየራሳቸው እይታ አንፃር ስለሚመለከቱት ሁለቱም አቀራረቦች መፃፍን በማስተማር አኳያ ተፎካካሪ ንድፈ ሀሳቦች እንዷላቸው የሚታሰብ ሲሆን እያንዳንዱ አቀራረብ ሌላኛውን አቀራረብ ከራሱ እይታ አንፃር ትችቶችን ይሰነዝሩበታል::

### 2.1.4.2 የሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ውስንነት

እንደ Hyland (2003a) አስተያየት የዘውግ ተኮር አቀራረበ ለሂደት ተኮር አቀራረብ ተፃራሪ በመሆን መፃፍን ለማስተማር የተፈጠረ አቀራረብ ነው:: የሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረቱ በግለሰብ የግንዛቤ ጽሁፍ ላይ ተመስርቶ የጽሁፍን ክሂል ማሳደግ ሲሆን ይህ አቀራረብ በዘውግ ንድፈ ሀሳብ ተከታዮች ዘንድ የፍቺን ማህበራዊነት ግምት ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ ትችት ይሰነዝሩበታል::

በሌላ በኩል Johns (1997) ባቀረቡት አስተያየት የሂደት ተኮር አቀራረብን መሰረት ያደረገ ጽሑፍ በክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ግምት ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ ውስኑነት አለበት ብለዋል:: በሳቸው አስተያየት ማህበራዊ ሁኔታ በጥንቃቄ ታየቶ የፅሑፉን ሁኔታ ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል:: ነገር ግን የሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው የአንባቢውን

እና የማህበረሰቡን ሚና ችላ በማለት የግለሰቡ የጽሑፍ እድገትና አላማ ላይ ያደርጋል::

በተመሳሳይ Hyland (2005) ባቀረቡት ሀሳብ ይህ አቀራረብ መፃፍን ኢ-አገባባዊ አድርጎ በመቁጠር ፀሀፊው በግሉ የሚሰማውን ትርጉም ለመግለፅ የቆመ አድርጎ ይቆጥራል:: ከዘውግ ተኮር እይታ አንፃር ፀሀፊዎች ፅሁፍ የሚጽፉት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ብቻ ሳይሆን በተለያየ ማህበራዊ ዐውድ ውስጥ የተለያዩ አላማዎችን ለማሳካት የተለያዩ ጽሑፎችን ይፅፋሉ:: እነዚህ ማህበራዊ ዐውዶች ፀሐፊው ለተጠቀመበት ቃላት ፍቺ ለመስጠት ወሳኝ ነገሮች ናቸው::

ሂደት ተኮር አቀራረብ በመፃፍ ወቅት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚሄድ ሂደት ነው Ramanathna and Kapalan (1986):: በዚህ አቀራረብ ዕይታ የመፃፍ ክሂል በዝምታ መስማማት፣ ደመናፍሳዊ ሂደት እና የፅሑፍ ቅርፆችን በግልፅ ለማስተማር ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎች እነዚህን ሁኔታዎች እንዲገለገሉ የሚገፉፉ በመሆኑ እንደ ደካማ ነጥብ ታይቶበታል::

ከዚህም ሌላ የሂደት ተኮር አቀራረብ በግለሰቦች መነቃቃት እና ራስን በመግለፅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ በክፍል ውስጥ የመምህራን ሚና እየቀነሰ መጥቷል:: ከዚህ አንፃር በመፃፍ ወቅት ተማሪዎች ስለጽሁፍ ሂደት ግንዛቤያቸው ከፍ እንዲል በራሳቸው ማስተዋል የደረሱበትን አጠቃቀም እንዲረዱት የመምህሩ ጣልቃ ገብነት ቀንሷል (Hyland, 2004,8):: በዚህ ወቅት የመምህሩ ሚና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይሆናል::

ከማህበራዊ ዕይታ አንፃር የፅሑፍ ቅርፅ እና የቃላት ምርጫ ከዐውድ ጋር የተገናኙ ናቸው (Hyland, 2003:,21):: በጽሑፍ ወቅት ለተማሪዎች ነፃነት መስጠት ርዕቱነትን የሚያበረታታ ቢሆንም በመፃፍ ዐውድ ለሰዋስው እና ቅርፅ ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው አያደርግም:: በሌላ በኩል (Swales,1990:220) አስተያየት ራስን መግለፅ እና በራስ መተማመንን ማሳደግ ጠቃሚ ቢሆንም መፃፍን ለመለማመድ በቂ አይደለም::

### 2.1.4.3 የዘውግ ተኮር አቀራረብ ውስኑነት

የዘውግ ተኮር አቀራረብ ክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: ከዚህ አንፃር የዘውግ ተኮር አቀራረብ ነቃፊዎች የዘውግ

አቀራረብ የፀሐፊዎችን ፈጠራ እና ራስን የመግለፅ ሁኔታዎች የሚያደናቅፍ ነው በማለት ይተቹታል (Hyland, 2004)::

በሌላ በኩል የዘውግ ስነትምህርታዊነት  አስተሳሰብ በተማሪዎች ከሚደረግ ሙከራ ይልቅ ትምህርት ለቋንቋ ባለን ግልፅ ግንዛቤ መታየት ይኖርበታል:: ከዚህ አንፃር መምህራን ተማሪዎቻቸው ጽሑፍን እንዲያገናዝቡ ዕድሉን ማመቻቸት ይኖርባቸዋል:: ይህ ሁኔታ ተማሪዎች ጽሁፍ እንዴት ትርጉም ሊሰጥ እንደሚችል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛል::

ይሁን እንጂ የዘውግ ተኮር አቀራረብ መፃፍን በግልፅ በማስተማሩ የተለያዩ ትችቶች ተሰንዝረውበታል:: ከተሰነዘሩበት ትችቶች መካከል የሂደት ተኮር አቀራረብ ደጋፊዎች እንደሚስማሙበት ዘውግ በግልፅ ማስተማር ወቅት መሰረታዊ ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ ገደብ በማበጀት የፀሀፊዎችን ፈጠራ ከመከላከሉም በላይ ዘውግ ፍቺ ከሚሰጥበት መንገድ ይልቅ እንደ እቅድ /ንድፍ/ ሊታሰብ ይችላል (Hyland,2003a)::

ከዚህም ሌላ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን መፃፍ በምናስተምርበት ወቅት የዘውግ ተኮር አቀራረብ ስራ ላይ ሲውል ያላቸውን ፍርሃት ገልፀዋል:: በዘውግ ተኮር አቀራረብ ፅሁፍን ስናስተምር ፅሁፍን ከምንፅፍበት ትኩረት አንፃር ልናየው እንችላለን:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች በራሳቸው ከመማር ይልቅ ተማሪዎች በትክክል ለምን እንደሚጽፉ እንዲነገራቸው ስለሚጠብቁ አቀራረቡ ፈጠራን አያበረታታም በሚል እንደስጋት ይቆጠራል::

የዘውግ ተኮር አቀራረብ ፈጠራን የሚገደብ ሁኔታ ያለው እና በአንዳንድ ፀሀፊ ላይ ቦታ እንደሚወስን ነው:: በሌላ በኩል አንድ ፀሀፊ ጽሁፍ ማህበራዊ አላማን ከግብ ለማድረስ ነው ብሎ ካሰበ ለምሳሌ የስጦታ ካርድ፣ የላብራቶሪ ሪፖርት የስራ ማመልከቻ በመሳሰሉ ዐውዶች የተወሰኑ አካሄዶች ይተገበራሉ:: ፀሐፊዎች ምን እና እንዴት እንደሚሰሩ ከመንገር ይልቅ የዘውግ አቀራረብ የቋንቋ ምርጫዎችን በማድረግ ራስን መግለጽን በማበረታታት ፀሐፊዎች በተለየ ማህበራዊ ፀውድ ውስጥ ስላለው ተግባቦት እና ማህበራዊ ውጤት ቦታ ይሰጣል::

### 2.1.4.4 መፃፍን በማስተማር ወቅት የዘውግ እና የሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምረት

መፃፍ በባህሪው ውስብስብ ተግባር ነው:: እንደ Hyland, (2003a:23) አስተያየት መፃፍ የማህበራዊ ግንዛቤ ድርጊት ነው:: በመሆኑም ፀሀፊዎች ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት ስለ ዐውድ እና አንባቢ የተወሰነ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል::

በተመሳሳይ Trribble (1996:103) ባቀረቡት ሀሳብ የፀሐፊው ፍላጎት እንዴት መፃፍ እንዳበት ብቻ ሳይሆን በዐውድ ውስጥ ምን መፃፍ እንዳበት ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ከዚህም ሌላ ሰዎች በተስተካከለ ሁኔታ የመፃፍ ችሎታቸው እነዲያድግ ሁለት ጠቃሚ ሀሳቦችን አቅርበዋል::

1. ፀሐፊው በድርሰት ፅሑፍ ውስጥ ሲሳተፍ ተገቢውን ሂደት ለማሟላት ያለው የችሎታ መጠን እና
2. በተለየ የተግባቦት ሂደት አውድ እና ይዘት የዘውግ ጽሁፍ ላይ የሚኖራቸውን ተፅህኖ ለመረዳት የፀሐፊውን ችሎታ መጠን ግምት ውስጥ መግባት አለበት::

ሁለቱም አቀራረቦች ማለትም ሂደት እና ዘውግ ተኮር አቀራረቦች ባለባቸው ጉድለት የተነሳ የተለያዩ ትችቶች የተሰነዘሩባቸው ሲሆን እያንዳንዱ አቀራረብ መፃፍን ከተለየ ዕይታ አንፃር እንደሚቃኙት ግልፅ ነው:: በተመሳሳይ መልኩ Badger and White (2000) ባቀረቡት አስተያየት የነዚህ ሁለት አቀራረቦች ልዩነት በክፍል ውስጥ የሚደረገውን ልምምድ ባልተፈለገ አቅጣጫ በመምራት ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ:: ምክንያቱም ውጤት፣ ሂደት እና ቦታ ከአውድ፣ ከአገልግሎት እና ዳራ አንጻር በቅርብ የተሳሰሩ እና ግንኙነት ያላቸው ናቸው:: ከዚህ አንፃር የሂደት እና የዘውግ ተኮር አቀራረቦች ጥምረት አንዱ የአንዱን ክፍተት ለመሙላት የቆመ አድርጎ መውሰድ ይቻላል::

በሌላ በኩል የዘውግ ስነትምህርታዊነት መሰረት የሚያደርገው ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሚደረግ ሂደት ከሚማሩ ይልቅ በአውድ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀምን በግልፅ በማሳየት ማስተማር የተሻለ ነው የሚል ሲሆን ይህ ማለት ግን የሂደት ተኮር አቀራረብን መተካት ማለት እንዳልሆነም ገልፀዋል Hyland (2004:21) ይህንን ሀሳብ Swales (1990) ሲያጠናክሩ “ድርሰትን ስንፅፍ ቅድመ

መፃፍን እና የፈጠራ ሀሳብን ማሳደግን ልምምድን ማበረታታት እና ስለራሳቸው ጽሁፍ ያላቸው ግንዛቤ ይኸውም የንድፍን ጠቃሚነት እና በርዕስ መረጣ ወቅት የግልሰብን ፍላጎት መጠበቅን ችላ ማለት ብልህነት አይደለም“ ብለዋል::

ይሁን እንጂ በሂደት ተኮር አቀራረብ ወቅት ተማሪዎች የሚያገኙት በራስ መተማመን እና የክህሎት መጨመር ጠቃሚ መሆኑን Swales (1990) ገልፀዋል:: ነገርግን እነዚህ ሁኔታዎች ብቻ የዘውግ አቀራረብን ለመማር በቂ አለመሆናቸውንም አክለው ገልፀዋል:: በሌላ በኩል ባቀረቡት ሀሳብ የዘውግ ልምምድ ለፀሀፊው ውስጣዊ ሂደት እና ውጫዊ ሁኔታ እኩል ግምት የሚሰጥ ነው::

የዘውግ ስነትምህርታዊነት የተማሪዎችን የመፃፍ ችግር ለማቃለል ሰዋስው አስፈላጊ መሆኑን ከማብራራት ይልቅ በመፃፍ ትምህርት ሂደት ከመጀመሪያው አንስቶ ተማሪዎች አውድን መሰረት አድርገው ተገቢ የሆነ ጽሁፍ እንዲፅፉ ስለስነልሳናዊ ገፅታ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: አንዳንድ መምህራን ማቀድ፣ ንድፍ እና አርትኦት ጠቃሚ ነገሮች መሆናቸውን አይቀበሉም:: ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች በተለየ አውድ ውስጥ አላማን ለማሳካት እና ጽሁፍን ለመፃፍ ለብቻቸው በቂ አይደሉም Hyland (2004:21)::

የተለያዩ ምሁራን Badger and White (2000), Hyland (2004) Trribble (1996) የመፃፍን ክሂል ለማስተማር የዘውግ እና ሂት ተኮር አቀራረቦችን የማቀናጀት ሀሳብ አቅርበዋል:: Badger and White (2000) በሰጡት አስተያየት የሁለቱ አቀራረቦች ጥምረት አንዱ የአንዱን ክፍተት ለመሙላት ያገለግላል ብለዋል:: ከዚህ ሁኔታ የምንገነዘበው የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች መፃፍን በማስተማር ረገድ በተናጠል ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሁለቱ አቀራረቦች ቅንጅት አስፈላጊ መሆኑን ነው::

እንደ Hyland (2005) አስተያየት በመፃፍ ልምምድ ወቅት የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ውህደት ተማሪዎች የጽሁፍ ፈጠራ ሂደት፣ የጽሁፍ አላማ እና ይህንን በትክክለኛ ሁኔታ መግለፅ እና በዐውድ የትኛው ድርሰት እንደሚፃፍ እና እንደሚነበብ እንዲሁም ትርጉም እንደሚሰጥ ለመገንዘብ ይረዳል::

በተመሳሳይ በተለያዩ ሀገራት የቋንቋ መምህራን ላይ በተደረገ ቅኝት Kay and Dudey-Evan (1998) የነዚህ ሁለት አቀራረቦች ውህደት ተቀባይነትን

አግኝቷል:: በአጠቃላይ የሂደት ተኮር አቀራረብ ከዘውግ ተኮር አቀራረብ ጋር ሲቀናጅ ስለዘውግ ውጤት ያለን እውቀት ዕቅድ፣ ንጽፍ፣ ክለሳ እና የአርትኦትን ስራ አንድ ላይ በማምጣት እና የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል እድል በመፍጠር የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ያስችላል::

### 2.1.5 ትውረታዊ ማዕቀፍ (Theoretical Frame work)

ከዚህ ቀደም የተነሱ ነጥቦችን መሰረት ስናደርግ መፃፍን የምንማረውና የምናደረጀው መፃፍን እንደግንዛቤና እንደማህበራዊ ድርጊት ስንቆጥረው ፀሐፊዎች ፅሁፍ የሚፅፉት የራሳቸውን ሀሳብ ለመግለፅ ወይም ፍቺ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን በተለየ አውድ ውስጥ ማህበራዊ ዓላማን ለማሳካት ነው:: ፀሐፊ ሊገልፅ የፈለገውን ፍቺ እና ሀሳባቸው በተለየ ማህበራዊ አውድ ውስጥ ወደ ጽሁፍ እንዲሸጋገር ውስብስቡን የመፃፍ ሂደት ማከናወን ይገባል::

ጽሁፍን ለመፃፍ ፀሐፊው የመንደፍ፣ የማርቀቅ እና የመከለስ ችሎታ ኖሮት የድርሰቱን ፈጠራዊነት እና ተደጋጋሚ ባህሪያቱን በመገንዘብ የማርቀቅ እና የመከለስ የቋንቋ አጠቃቀምና ይዘቱን መከለስ የማደራጀት እንቅስቃሴዎችን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል:: በተወሳሰበ ሂደት ድርሰት ሲፃፍ ሊገልፅ የተፈለገው ፍቺ መፈተሻና በጽሁፍ ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ በተፈለገው ማህበራዊ ዐውድ እንዲተላለፍ ከአንባቢው ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር መሆን አለበት::

በተመሳሳይ ጽሑፍ ለመፃፍ ፀሐፊው የመንደፍ፣ የማርቀቅ እና የመከለስ ችሎታ ኖሮት ፈጠራዊነት ፣ማደራጀት እና ሀሳብ መከለስ ፣ሀሳብን በጽሁፍ ለማስተላለፍ፣ ጽሑፍን ከቋንቋ ይዘት እና አጠቃቀም አንፃር ማጤን ይገባል::

በተጨማሪም ፀሀፊ ፅሑፍ የሚፅፈው የተለየ ማህበራዊ አላማን ለማሳካት መሆኑን በግልፅ መረዳት አለበት:: ፅሁፍ በተለይ ቅርፅ ሰዋስው እና መዋቅር የሚፈጠረው በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ ከሌሎች ተሳታፊዎች ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር ነው:: በመሆኑም ፀሀፊ ስለ ስነለሳናዊ ገፅታ ማህበራዊ አውድ ማህበራዊ አላማ የፀሀፊውን እና የአካባቢውን ሚና ግልፅ እውቀት ሊኖረው ይገባል::

ፀሀፊ በጽሁፍ አውድ የቋንቋው ገፅታ ግልፅ እውቀት እንዲኖር መምህር ለሁሉም ተማሪዎች በፅሁፍ ሂደት ተፅህኖ ስለሚያሳድረው ማህበራዊ ሁኔታ ተመሳሳይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል::

በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ፅሁፍ ስለሚፈጠርበት ሁኔታ መናገር እና መተንተን እንዲሁም በመዋቅር፣ ሰዋስው እና የቃላት ምርጫ ግልፅ ማብራሪያ መስጠት አለባቸው:: ከዚህም ሌላ መምህራን በመፃፍ ወቅት ተማሪዎች በተለየ አውድ እንዲያደራጁ እና ቅድመ መፃፍ ተግባራትን እንዲያሳድጉ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን ተማሪዎችም ጽሁፍ በተለያየ አውድ እንደሚጻፍ ሊያስቡበት ይገባል::

### 2.1.5.1. የመፃፍ ንድፈሀሳቦችና አቀራረቦች

ዋነኞቹ የመፃፍ ንድፈ ሀሳቦች ከማጠናቀር ግንዛቤና ከማህበራዊ ግንባታዊያን ዕይታ አንፃር ይመደባሉ:: በሌላበኩል እነዚህ ንድፈሀሳቦች ዋና ዋና ለሆኑት የፅሁፍ አቀራረቦች ውጤት፣ ሂደት፣ ዘውግና ሂደተዘውጋዊ መሰረት ናቸው::እነዚህ የመፃፍ ንድፈሀሳቦች ጥርቅም ባህር የሆነው ክፍል የ Arsitotil,Piaget,Vygotsky እና ሌሎች ባለሙያዎችን ስራ መሰረት ያደርጋሉ:: ይህም በሂደት በመፃፍ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ያሳያሉ::

መፃፍን በማስተማር ላይ ያለ አመለካከት የውጭ ቋንቋን በማስተማሩ ዘርፍ ትኩረት በሚሰጥና የሚደረግ ለውጥ ነፀብራቅ ነው:: በትምህርቱ ላይ የሚደረገው ትኩረት በተማሪ፣መምህራንና መርሃትምህርት መካከል በሚያደርጉት ዝንባሌ የተለያየ ነው::ይሁን እንጂ በተለያዩ ዝንባሌዎች የተነሳ የተለያዩ ዝንባሌዎች ብቅ አሉ:: ይሁን እንጂ ሁሉም መፃፍን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሰዎችን የመማር ስልት ግንዛቤያቸውን፣ውጤታማነታቸውን፣ ማህበራዊ ዳራቸውንና ዕውቀትን መሰረት ያደርጋሉ::

#### 2.1.5.1.1. የድርሰት ንድፈ ሀሳብ:-የውጤት ተኮር የመፃፍ ሂደት

የድርሰት ወይም የውጤት ተኮር አፃፍፍ ንድፈሀሳብ በመፃፍ ረገድ የተለያዩ የድርሰት ጥናቶች ድምር ውጤት ነው:: Till(1960) እነደገለፁት እሰከ 1960ዎቹ ድረስ ፅህፈት የግለሰቦች ጥራት ውጤት ተደርጎ ይታይ የነበረና እንደ ጥሩ የመፃፍ ሞዴል ተደርጎ ይወሰድ የነበረውን የ Arstotilን ሞዴል መሰረት ያደረገ

ነበር:: የድርሰት ንድፈሀሳብ በተለያዩ ዕይታዎች አሁን ያለበት የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሷል::

#### 2.1.5.1.2. የግንዛቤያዊያን ንድፈሀሳብና የሂደት ተኮር ሂደት

የድርሰት ንድፈሀሳብ መፃፍን ለማስተማር በሚካሄድበት መንገድ ላይ ውሱንነት ይፈጠርበታል ተብሎ ይታሰባል:: በ Braddoc,Liyod እና Schoer(1963) በተደረጉ ጥናቶች የመፃፍ ችሎታቸውን በመረዳት በኩል እና ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ላይ ጉድለት መኖሩን አሳይተዋል:: እንደዚህ ጥናት መፃፍ ከውጤት ይልቅ ሂደት መሆኑን ተቁመዋል:: Berlin(1984) እንዳስገነዘቡት መፃፍ ከሁለት ትላልቅ አቀራረቦች ጥልቀት ያለውና ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ነው::

የመጀመሪያው ጥለቀት ያለው አቀራረብ የፈጠራ ተነሳሽነትን ውጤት መሰረት ያደረገ መሆኑ ይታመናል:: ገውም ትኩረት የሚያደርገውም መፃፍ ግላዊ ተማሪዎች ፍላጎታቸውን የሚያመለክቱበትና የሚገልፁበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: በተማሪዎች የሚፃፈው ፅሁፍ የትኩረት አቅጣቻቸው ምን እንደሆነ ለሚቀርብ ጥያቄ ፍንጭ የሚሰጥ ነው:: በአጠቃላይ የተማሪዎች የህይወት ልምድ መገለጫ ሊሆን ይችላል:: በሌላ አባባል ጥልቀት ያለው ፅሁፍ የታላሚውን ቋንቋ ስነልሳናዊ ሂደት ላይ ከማተኮር ይልቅ ላለፈው ሁኔታ ትኩረት ይሰጣል::

ሁለተኛው አቀራረብ የግንዛቤያዊያን የመፃፍ አቀራረብ ሲሆን በማሰብ ምክንያት ማስታወስና ምናብ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይህም በታላሚው ቋንቋ አህምሯዊና ሂደታዊ ግንዛቤ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የስነልቦና ውጤት ተደርጎ ይታሰባል:: በዚህም ምክንያት ቋንቋ የሰውን ልጅ ባህሪ ለመግለፅና ለመረዳት የሚያገለግል መሳሪያ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል:: ይህ ሂደት በ1960ዎቹና በ20ኛው ክፍለዘመን ማብቂያ ላይ ዕድገት እያሳየ የመጣ ነበር:: ይሁንእንጂ መፃፍ የተለያዩ ችግሮችን ለማቃል የሚያገለግል ሀሳባዊ የሆነ ሂደት ነው ማለት ይቻላል:: በግንዛቤያዊያን አቀራረብ የመፃፍ ዓላማ ተማሪዎች የተዋጣላቸው ፀሀፊዎች እንዲሆኑና እንዲሁም መፃፍ መማርና ሀሳብን ለመግለፅ የሚያገለግል መሆኑን እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው::

የግንዛቤያዊያን ስነልቦና የዕድገት ዘርፍ በ Dart Mouth ኮሌጅ አንግሎ-አሜሪካዊያንን የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለማስተማር ሴሚናር በቀረበበት ወቅት መፃፍንለመረዳትና ለማስተማር የቀረበውን የግንዛቤዊያንን ሂደታዊ አቀራረብ

ውጤት ተደርጎ ተወስዷል:: እነዚህ የታዩት አካሄዶች የግንዛቤያዊያንና የማህበራዊ አቀራረቦች ከግንዛቤያዊያን ስነልቦና የተወሰዱ ናቸው:: የግንዛቤያዊያን አቀራረብ በግለሰቦች የመፃፍ ሂደት ላይ ትኩረት ሲያደርግ የማህበራዊ አቀራረብ ደግሞ መፃፍን ለመማር በሚደረጉ አብሮ የመስራት ትብብሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል::

የግንዛቤያዊያን ስነልቦና በዋነኞቹ ንድፈሀሳቢያዊያን Jean Piajet እና Lev Vygotsky ስራዎች እየዳበረ የመጣ ነው:: Piajet (1967) ቋንቋ የማሰብ መሳሪያ መሆኑ ላይ ትኩረት ይሰጣል:: በሌላ በኩል Vygotsky (1962:1978) በቋንቋና ማህበረሰብ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ትኩረት ከማድረጉም በላይ ዕውቀት በቋንቋ አማካይነት ከማህበረሰቡ ወደ ግለሰብ መምጣቱ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይሁንእንጂ የግንዛቤያዊያን ሂደታዊ ንድፈሀሳብ መፃፍን ለማከናወን በሚያስፈልጉ ሂደቶች ይኸውም:- መንደፍ፣መከለስና አርትኦት ተፅዕኖ ስር ይውላል::

የግንዛቤያዊያን ንድፈሀሳብ ዋነኛ መለያው በአህምሮ ውስጥ ስለሚካሄደው ሂደት አዎንታዊ አስተሳሰብበመያዙ ነው:: በተጨማሪም በተማሪዎች ዘንድ ያለ ልዩነት ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለውን ሙከራዊ ሞዴልን በማቅረብ ስነትምህርታዊ አጠቃላይነትን የሚያበረታታ ነው:: በመፃፍ ሂደት ዋነኛው የግንዛቤያዊያን ንድፈሀሳብ ጭብጥ በሀሳብና በቋንቋ መካከል ያለው የእርስበርስ ግንኙነት ነው:: Piajet እና Vygotsky መፃፍን በመማር ማስተማር ወቅት ግለሰባዊና ትብብራዊ ሂደቶች ስራ ላይ እንዲውሉ አስተያየት አቅርበዋል::

የመፃፍ ሂደት በ Flower and Hayes(1981) የግንዛቤያዊያን ሞዴል ይኸውም ስነፅሁፍ በሂደታዊ አቀራረብ ከግንዛቤያዊያን እይታ አንፃር እንዲሆን ተፅዕኖ አሳርፈዋል:: ከዚህ አንፃር የመፃፍ ሂደት መፃፍ በሚተነቀርበት ጊዜ የልዩልዩ ሀሳቦች ቅንጅት ነው (Flower and Hayes 1983:366):: በነዚህ ሁለት ሙሁራን አስተያየት መፃፍ መንደፍ፣ መከለስና መንደፍ በጥምረት ስራ ላይ የሚውሉበት ሂደት መሆኑን የሚጠቁም ነው::

### 2.1.5.1.3. የግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ

የስነትምህርት ሙህራን የበለጠ ውጤታማ በሆነው የመፃፍ ዘዴ ላይ ክርክሮችን እያካሄዱ ይገኛሉ:: በመማር ንድፈሀሳብ መማር በልምድ የሚገኝ አህምሮን ልክ

እንደ ባዶ ወረቀት አድርጎ የሚወስደው የግንባታዊያን ንደፈሀሳብ በዚህ ረገድ የክርክሩ ሂደት አንደኛው አካል ነው:: በዚህ አዲስ ዝንባሌ Piajet መማር የተማሪዎች ድርጊትና ባካባቢያቸው ላለው ሁኔታ መጋለጣቸው መሆኑን አጢኗል (Byernes,2001):: የግንባታዊያን ንደፈሀሳብ የውጭ ቋንቋዎችን ስንማር ባለን የቀድሞ ዕወቀት መሰረትነት አድስ ዕውቀት የምንገነባበት ነው የሚለውን ጭብጥ ግምት ውስጥ ያስገባል:: በሌላ በኩል ግንባታዊያን እንግሊዘኛን እንደውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች አዲሱ መረጃ ቀድሞ ያላቸውን ዕውቀት በመተቀም ትርጓሜ ይሰጡታል( Pirie and Kierer,1992)::

የግንባታዊያን ንድፈ ሀሳብ እንግሊዘኛን እነደውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ያለውን ልምዳቸውን መሰረት ያደርጋሉ:: በከፊል ያላቸውን ግንዛቤ መሰረት በማድረግ ከጊዜ ወደጊዜ ባላቸው ግንዛቤና ለቋንቋውው መጋለጣቸው ትክክለኛነት እየገነቡ ይሄዳሉ (Byrnes,2001):: ይህ ንድፈሀሳብ የግለሰቦችን መማርና በሚያሳዩት የተለያየ የዕድገት ደረጃዎች ሊከሰት ያችላል::

### 2.1.6 የዘውግና የሂደት ተኮር የመፃፍ ምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር

የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር አተገባበር መሰረታዊ መርህ ተማሪዎች መፃፍ የግንዛቤ እና ማህበራዊ ድርጊት መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል:: ከዚህም ሌላ ስለዘውግ ያላቸው እውቀትና ጽሑፍ የሚከናወንበትን ሂደት ግምት ውስጥ መግባት አለበት::

የዘውግ- ሂደት ተኮር የማስተማር ሞዴልን በክፍል ውስጥ ስራ ላይ የሚውልበት አቀራረብ የFeez and Joce’s (1998) የመማር ማስተማር ውህደት ከአምስት ደረጃዎች ማለትም አውድን መገንባት፣ ጽሁፍን በጋራ መገንባት፣ ጽሑፍን በግል መጻፍ፣ ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሑፎች ማገናኘት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው:: ይህ የመፃፍ ሞዴል መሰረት የሚያደርገው በመማር ማስተማር ሂደት ዘውግን መሰረት ከሚያደርገው የአውስተራሊያው የዘውግ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለማስተማር መሰረት ከሚያደርገው መርህ ነው::

ይህ መፃፍን የማስተማር አቀራረብ መሰረት የሚያደርገው የ vygotsky Zone of Proximal development እና የ Bruner (1986) ስራዎች ላይ ነው:: መምህሩ

ትምህርቱ ሲጀመር ጀምሮ ጠንካራ ድጋፍ ማድረግ ያለበት ሲሆን ይህ ሁኔታ በኋላ ላይ ተማሪዎቹ መሻሻል እያሳዩ ሲሄዱ እየቀነሰ ይሄዳል::

በተጨማሪም የዘውግ እና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምር ትግበራ ተማሪዎች ከሚጽፉት ታላሚው ዘውግ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው (White and Arndt's, 1991):: ይህ ሁኔታ ተማሪዎች የጽሁፍን ውስብስብነትና ተደጋጋሚነት እንዲገነዘቡና ጽሁፍን ሲያጠናቅሩ ስለዘውግ ያላቸውን እውቀት እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል:: የዚህ መፃፍን ለማስተማር አቀራረብ ማዕቀፍ በዋናነት መሰረት የሚያደርገው የFeez እና Jogce's (1998) የጽሁፍ ሞዴልን ነው::

ይህ የመፃፍን ውስብስብነት የሚያንፀባርቀው ሞዴል የክፍል ውስጥ ተግባራትን ለማደራጀት መመሪያዎችን ያቀርባል:: በአጠቃላይ የWhite and Arndt's (1991) የዘውግ ሂደት ተኮር ሞዴል የስነትምህርታዊነት ማዕቀፍ አላማ ስለታላሚው ዘውግ በማህበራዊ አውድ እና ስነልሳናዊ ገፅታው ግልፅ ማብራሪያ መስጠት እና የዘውግ እውቀት ውስብስብ ከሆነው መፃፍ ጋር ማቀናጀትን ማሳየት ነው::

**የዘውግ- ሂደት ተኮር አቀራረብ ማስተማሪያ ሞዴል**




Feez and Joyee's (1998)

የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል በአምስት ደረጃዎች ማለትም ጽሑፍን መገንባት፣ የጽሁፍን ሞዴል መተንተን፣ ጽሑፍን በጋራ መገንባት እና በጽሑፍ ላይ ጽብረቃ መስጠትን ያካተተ ነው:: ይህ ሞዴል ተማሪዎች የዘውግን ውስብስብ እይታ እንዲያሳድጉና በጽሑፍ ወቅት እንዲጠቀሙበት የማድረግ አላማ አለው:: በሌላ በኩል ይህ ሞዴል እንደሁኔታው ተለዋዋጭ በሆነ ሁኔታ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን መምህሩ በማንኛውም አስፈላጊ ጊዜ እገዛ ሊያደርግ ይችላል::

በእንዳንዱ ደረጃ የተማሪዎች ትኩረት የተለያየ ቢሆንም ነገር ግን አንዱ ከአንዱ ይኸውም የጽሑፍ ማህበራዊ አውድ፣ ይዘት፣ የጽሁፍ አደረጃጀት፣ የጽሁፍ ስነልሳናዊ ገፅታ፣ ዘውግን ከሂደት ጋር በማጣመር የተያያዙና ግንኙነት ያላቸው ናቸው:: ቀጥለን አንድ በአንድ እንመልከታቸው::

### 2.1.6.1. ዐውድን መገንባት

ዐውድን በምንገነባበት ደረጃ የአራቱ ተላውጦዎች ማዕቀፍ ማለትም (Gener, Field, tenor and mode) በአውስትራሊያ የዘውግ ትምህርት ቤት በማህበራዊ አውድ ውስጥ ታላሚው ዘውግ ይኸውም የታላሚው ጽሁፍ ማህበራዊ አላማ፣ ታላሚው ጽሁፍ ሲፃፍ ማህበራዊ ተግባሩ፣ በተግባቦታዊ ተሳትፎ የተሳታፊዎች ግንኙነት እና ተግባቦት የሚገኝበትን ሁኔታ መመርመር ለተማሪዎች እንደመመሪያ ያገለግላል::

ለተማሪዎች ዐውድን መገንባት በጣም አስፈላጊው ደረጃ ሲሆን መምህራን ለትምህርቱ ጠንካራ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በዚህ ደረጃ ጠቃሚው መርህ ተማሪዎች ጽሑፍ ከማህበራዊ አውድ እንደሚገኝ እና በድርጊቱ ውስጥ ማህበራዊ ግንኙነትን እንደሚያካትት እንደገነዘቡት ማድረግ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች የዘውግን አላማ ለመረዳት በተፈጠረው ግንኙነት ዐውድን መረደታቸው አስፈላጊ ነገር ነው (Cllaghan 1993:181) በዚህ ደረጃ በቋንቋ አገልግሎት እና በዐውድ ውስጥ ፍቺ እንዴት እንደሚፈጠር ትኩረት ይደረጋል (Feez, 2002, Hyland, 2004)::

በዚህ ደረጃ በክፍል ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል በአውዱ ላይ ውይይት እንዲደረግ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ማቅረብ፣ ስለፅሁፍ

በስዕል መግለፅ፣ እንግዳ ተናጋሪዎችን መጋበዝ እና የመሳሰሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ (Hyland, 2004:130-131)::

#### 2.1.6.2. ሞዴል ጽሑፍን መገንባት

በዚህ የሞዴል ጽሑፍ ትንተና ደረጃ መምህሩ ያለውን ግንኙነት በጠንካራ ሁኔታ ይመራል:: በዚህ የሞዴል ጽሑፍ ታላሚው ዘውግ በአውዱ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: (Feez, 2002:66):: መምህሩ እና ተማሪው ስለጽሁፉ አደረጃጀት፣ ሰዋስዋዊ ገጽታው በተለየ አውድ ውስጥ የጽሑፍን አገልግሎት በተመለከተ እና የቃላት ምርጫ ላይ መነጋገር አለባቸው::

Hyland (2004) ባቀረቡት ሀሳብ ትንተናው ከታች ወደ ላይ ከሚሆን ይልቅ ጽሁፍ ሙሉ በሙሉ ቢሆን ይሻላል ብለዋል:: ከተለየ አንባቢና መልእክት ጋር አለማን ለማሳየት ጽሁፍ እንዴት እንደተደራጀ ግምት ውስጥ መግባት አለበት:: በመሆኑም ሁሉም የጽሁፍ አካል የተግባቦትን አላማ ለማሳካት እንዴት መፃፍ እንዳለበት ለምሳሌ አንቀፅ እና አረፍተነገር እንዴት እንደሚደራጅ፣ እንደሚዋቀሩና በስርዓት እንደሚፃፉ መገንዘብ ያስፈልጋል:: በሌላ በከል መምህራን ለተማሪዎች በአረፍተነገር ውስጥ ሰዋስውን በግልፅ እንዲጠቀሙ ማሳየት ያለባቸው ሲሆን ይህም ለተማሪዎቹ ጠቃሚ ነው (Hyland, 2004)::

በሞዴል ጽሑፍ ትንተና ወቅት በመዋቅር ላይ መነጋገር፣ በሰዋስው፣ ከማህበራዊ አላማ ጋር በተገናኘ ልምምድ ማድረግ ጠቃሚ የክፍል ውስጥ ተግባራት ናቸው (Pallridse, 2001)::

#### 2.1.6.3. ጽሑፍን በጋራ መገንባት (Collaborative Construction of the text)

በዚህ ደረጃ መምህሩ ሚናውን በመቀነስ ሁኔታዎችን ወደማመቻቸት ይሄዳል (Hyland 2004,134):: ተማሪዎች በማርቀቅና በማዘጋጀት ደረጃዎች ላይ እያሉ በግልፅ መነጋገር እና በፍቺ ላይ መስማማት እንዲኖር መደገፍ ያስፈልጋል:: በጽሑፋቸው ላይ ቁጥጥር ለማድረግና አጠቃላይ የሆነ የዘውግ ምሳሌ እንዲሰጡ በአነስተኛ ቡድኖች እንዲደራጁ ይደረጋል:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች በጽሁፍ አደረጃጀት ላይ ችግር ካለባቸው ወደቀደመው ደረጃ ስለአውድና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ዳግመኛ ሊመለከቱት ይችላሉ:: (Callaghan, 1993)::

የዚህ ደረጃ ጠቃሚ ገፅታው መምህር የጽሑፍ ሂደት የሆኑትን ሀሳብ እና ተማሪዎች ጽሑፍ በሚያጠናቅሩበት ጊዜ የዐውድ የዘውግ እና በጽሑፍ ሂደት እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ መሆኑ ነው:: ተማሪዎች ካለፉት ደረጃዎች ያገኙትን የዘውግ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ተከታታይ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የመፃፍ ሂደት እንዴት እንደሆነና የጽሁፍ ክሂላቸው እንዲዳብር በጽሑፋቸው ይዘት ጽሑፍ፣ መንደፍ እና መከለሰን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል:: (Hyland, 2004):: በክፍል ውስጥ ጽሑፍን በጋራ የመገንባት ተግባር በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ሊከናወን ይችላል::

### 1. በአገባቡ ላይ መነጋገር

ተማሪዎች በሚፃፈው ጽሁፍ አገባብ ላይ ንግግር ማድረግ ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ጽሁፍ የሚገነባበት ሁኔታ አላማው የፀሀፊው እና የአንባቢውን ሚና መለየት ይኖርበታል:: ይህ አይነቱ ጽሁፋዊ ገፅታ ለማህበራዊ ሁኔታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መለየት አለበት::

### 2. ይዘትን ማሳደግ

ተማሪዎችን የሚያነቃቃቁ ስልቶችን ተጠቅሞ የሚቀርቡ ጽሁፎች ይዘትን ያጎለብታሉ:: በዚህ መሰረት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማስቀረት ተገቢነት ያላቸውን ይዘቶች ለማሳደግ ስለአውድ ያላቸው እውቀትና በአውድ ላይ ለመነጋገር እንደ ማዕቀፍ መጠቀም አለባቸው::

### 3. ጽሑፍን ማደራጀት

በዚህ ተግባር ተማሪዎች ያገኙትን ሀሳብ ያደራጃሉ:: ከዚህ አንፃር መዋቅርን መሰረት አድርገው ጽሁፍ ስለሚፈጠርበት የቋንቋ ገፅታ ይነጋገራሉ::

### 4. ራስን በመገምገም ንድፍን መከለስ

ተማሪዎች የንድፍን ይዘትና አደረጃጀት በዐወዱ ውስጥ ዓላማውን ማሳካቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ግምገማ ያካሂዳሉ::

5. **ንድፍ ማዘጋጀት**

በቅድመ መፃፍ ተግባራት ወቅት የተፃፈወን ንድፍ መሰረት በማድረግ የፅሁፍን ንድፍ ያዘጋጃሉ::

6. **ራስን መገምገምና ንድፍን መከለስ**

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ራሳቸውን መገምገምና ፅሁፍን የመከለስ ተግባር ያከናውናሉ::

7. **የብጤ ግምገማ**

ተማሪዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ በተማሩት የዘውግ ዕውቀት አማካይነት የፅሁፍን ውጤታማነት ይገመግማሉ:: በዚህ መሰረት መምህራን ተማሪዎች ንድፍን ለመገምገም የሚያስችል መመሪያ ያዘጋጃሉ:: ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው ጋር ንድፋቸውን በመለዋወጥ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የቢጤዎቻቸውን ንድፍ አርመው ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ:: ከዚህ በኋላ ሁለቱም በጋራ በንድፎቻቸው ላይ ይነጋገራሉ:: መምህሩም በውይይቱ በመሳተፍ ተጨማሪ አስተያየት ሊሰጥ ይችላል::

8. **ከቢጤ በተሰጠ አስተያየት ንድፍን መከለስ**

በንድፍ ላይ ከቢጤ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ተማሪዎች ከውይይትና ከምጋቤ ምላሽ በመነሳት ንድፋቸውን ይከልሳሉ::

### 2.1.6.4. ፅሁፍን በራስ መገንባት

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን እና የፅሁፍ ክሂላቸውን ተጠቅመው ዐውድን በመመርመር የራሳቸውን ፅሁፍ በግላቸው ይፅፋሉ:: ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ቢጤዎቻቸውን እና መምህራንን ሀሳብ መጠየቅ ይችላሉ:: እንዲሁም ባለፈው ፅሁፍን በጋራ የመገንባት ደረጃ የአገባብ ዕውቀት፣ የዘውግ እና ሂደት ጥምረትን የመጠቀም ልምድ የራሳቸውን ፅሁፍ በነፃነት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል::

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በየግላቸው የመፃፍን ተግባር የሚያከናውኑ ከመሆኑም በላይ የዘውግን ዕውቀት ማቀናጀታቸውን ለማረጋገጥ መምህሩ የተለያዩ ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያበረታታቸዋል:: ተማሪዎች

ግላዊ የፅሁፍ ተግባር እንዲያከናውኑ ከተነገራቸው በኋላ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ይመከራሉ::

1. **የይዘት ትንተና**

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የጽሁፉን አገባብ እንዲተነትኑት የሚጠየቁ ሲሆን ፅሁፍ የተፃፈበት ሁኔታና ዓላማውን እንዲለዩ ይጠበቃሉ:: የፅሀፊዎችነ እና የአንባቢን ሚና የተፃፈው የፅሁፍ ዓይነት እና ማህበራዊ ሁኔታ ለመፃፍ ገፅታ ያበረከተው አሰተዋፅኦ ይታያል::

2. **ይዘትን ማሳደግ**

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የፅሁፍ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉና መነሳሳት እንዲፈጥሩ ይበረታታሉ:: ከዚህም ሌላ የማይፈለጉ መረጃዎችን በመተው ተፈላጊ ይዘቶችን እንዲያሳድጉ የማህበራዊ ዕውቀትን እንደመመሪያ እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ::

3. **ፅሁፍን ማደራጀት**

ተማሪዎች ያገኟቸውን ሀሳቦች የሚያደራጁ ሲሆን ታላሚውን ዘውግ መሰረት በማድረግ ንድፍ ያዘጋጃሉ:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዝርዝር መረጃዎች ሀሳባቸውን የበለጠ ማሳደግ ወይም የማይፈለጉ መረጃዎቸን ማስወገድ ይችላሉ::

4. **ራስን መገምገምና ረቂቅን መከለስ**

ተማሪዎች ይዘት እና አደረጃጀት የጽሁፍን ማህበራዊ ዓላማ የሚያሳኩ መሆናቸው ከመምህራቸው በተሰጣቸው መገምገሚያ አማካይነት ፅሁፋቸውን ይገመግማሉ::

5. **ንድፍ መፃፍ**

የቅድመ መፃፍ ተግባራትን መሰረት አድርገው ንድፍ ያዘጋጃሉ::

6. **ራስን መገምግምና ንድፉን መከለስ**

ተማሪዎች ራስን መገምግምና የዘውግን ዕውቀት እንደመመሪያ ተጠቅመው ከፃፏቸው ፅሁፎች የይዘት ምርጫ በማድረግ ሰዋስውና ቃላት በማህበራዊ ዐውድ

ውስጥ ዓላማቸውን አስተካክለዋል? የሚለውን ሀሳብ ሊያጤኑት ይገባል:: ራስን የመገምገሚያ መስፈርት በመምህሩ ሊዘጋጅ ይገባል::

7. **የብጤ ግምገማ**

ተማሪዎች አስተያየት ለመቀበል ከቢጤዎቻቸው ጋር ንድፋቸውን ይለዋወጣሉ :: በመቀጠልም ፀሀፊውና ቢጤው በንድፉ ላይ ለመነጋገር ይገናኛሉ:: ተማሪዎች ለግምገማው መስፈረት የሚሆነው በአገባብ እና በፀሀፊው ገፅታ የዘውግን ዕውቀት መሰረት እንደሚያደርግ ተማሪዎችን ማስታወስ ያስፈልጋል::

8. **የቢጤ አስተያየትን መሰረት ያደረገ የንድፍ ክለሳ**

ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ ካገኙ በኋላ በተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ አማካይነት ንድፋቸውን ይከልሳሉ:: በመቀጠልም ተማሪዎች የመጨረሻውን ንድፍ ከመጀመሪያው ንድፍና የማነቃቂያ ማስታወሻቸውን ለመምህራቸው ያቀርባሉ::

9. **ለንድፉ የመምህሩ ምላሽ**

መምህሩ ንድፉ ከማህበራዊ አውድ አንፃር ተገቢ በሆነ ሁኔታ ተፅፏል? ዓላማው መሳካቱን ለማረጋገጥ በተማሪዎቹ ንድፍ ላይ ምልክት በማድረግ አሰተያየት ያቀርባል:: አስተያየት የመስጫ መስፈርት መሰረት የሚያደርገው መምህሩ በንድፍ ላይ የሚሰጠው አስተያየት ነው::

10.**ከመምሩ በሚሰጠው ምላሽ ንድፍን መከለስ**

ተማሪዎች ከመምህሩ ባገኙት ምላሽ እና አስተያየት ንድፋቸውን ይከልሳሉ::

#### 2.1.6.5. **በጽሁፍ ላይ ፅብረቃ** (Reflecting on writin)

ተማሪዎች ንድፍ ፅፌው ከጨረሱ በኋላ በፃፉት ፅሁፍ ላይ ፅብረቃ እንዲያደረጉ ይጠበቃል:: ይህ ሁኔታ የፅሁፍን አገባብ፣ ማህበራዊ ዐውድ ላይ የሚያሳርፈውን ተፅህኖ እንዲገነዘቡ ያግዛል:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በአገባብ ላይ ያለን ተመሳሳይነትና ሌሎች ያጠኗቸውን ፅሁፎች እንዲያጤኑት ያበረታታል:: በፅብረቃ አማካይነት በተግባር ላይ ባለው ፅሁፍ ላይ ተፅህኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ሁኔታዎች እና ተግባራትን ለማጠናቀቅ ስለሚከተሉት ስልት በፅብረቃ እንዲገልፁ ይበረታታሉ (Johans, 1997:134) ::

በአጠቃላይ በፅሁፎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲያጤኑት ይህም በፅሁፍ ውስጥ የታለመውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ዕድል ይፈጥርላቸዋል::

### 2.1.7. መፃፍን በማስተማር ረገድ የመምህሩ ሚና

ከመፃፍ ትምህርት የሚጠበቀው አጠቃላይ ግቡ ተማሪዎች መፃፍን በማህበራዊነት፣ በትምህርታዊነት፣ በሙያ እና በህይወት ገጠመኞቻቸው ውስጥ በአግባቡ እንዲገለገሉበት ማድረግ ነው:: እነዚህን ክህሎቶች ተማሪዎች በተገቢው መንገድ እንዲያጎለብቷቸው የመምህሩ ሚና ከፍ ያለ ነው (Hedge, 1988:8 )::

Hedge (1988:8) መምህራን በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንደሚከተለው አቅረበዋቸዋል::

- በመፃፍ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያፈልቁ ማገዝ ፣
- የጽሁፍ ሞዴል ማቅረብ እና ጥሩ የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው ማበረታታት፣
- እቅድ እንዲያወጡ ማገዝ፣
- በክፍል ውስጥ ተስማሚ ሁኔታዎችን መፍጠር እና
- ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የፅሁፍ መልመጃዎችን ማቅረብ ናቸው::

Raimes (1983:12-22) መምህራን መፃፍን በሚያስተምሩበት ጊዜ ለራሳቸው ማቅረብ የሚገባቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል::

1. ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በተገቢ መንገድ እንዲማሩ መፃፍ እንዴት ያግዛቸዋል?
2. አመቺ የሆነ ርዕስ እንዴት ማገኘት እችላለሁ?
3. ተማሪዎች የሚጽፉት ነገር ትርጉም እንዲኖረው እንዴት ማገዝ እችላለሁ?
4. ተማሪዎች የፃፉትን የሚያነበው ማነው?
5. ተማሪዎች ፅሑፋቸውን እንዲጽፉ ምን ያህል ጊዜ መስጠት አለበት?

6. ተማሪዎች የሚፈጥሩትን ስህተት በተመለከተ ምን ማድረግ አለብኝ? የሚሉ ናቸው::

በሌላ በኩል Richards (2000:111) መፃፍን አስመልክቶ መምህሩ ሊያከናውን የሚገባውን ተግባር እንደሚከተለው ገልፀውታል::

- የመፃፍ ሂደትን ያስተምራል::
- የመፃፍ ተግባራት ግልፅ እና ቀላል ሆነው እንዲቀርቡ ያደርጋል::
- የመፃፍን ውጤት ይተነትናል ይገመግማል::
- መልመጃዎችን በተገቢ መንገድ ያደራጃል::
- የተማሪዎችን የአጭር እና የረጅም ጊዜ ግብ ያዘጋጃል:: የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች በግል እና በቡድን እንዲከናወኑ እና መጠኑም እንዲጠበቅ ያደርጋል::
- ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙበት ያግዛል::
- የሆሂያትን አጣጣል፣ የስርዓተ ነጥቦችንና የአንቀፆችን አደረጃጀት ወዘተ. ያስተምራል::
- የመፃፍ ህጎችን እና መርሆችን ያስተምራል::

በአጠቃላይ መምህሩ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማመቻቸቱም በላይ ተማሪዎች ወደ ተሻለ የመፃፍ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ልምዱን የሚያካፍል ሲሆን የተሻለ አቀራረብ እንዲኖር ውይይቶችን ያካሂዳል::

በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት በሚቀርብበት ክፍል ውስጥ የመምህሩ ሚና ምን መሆን አለበት? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስለዘውግ አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት:: ዘውግን በመተንተን በፅሁፍ ውስጥ የሚገኘውን ፍንጭ በመጠቀም የተደበቀውን ነገር ለመረዳት ያስችላል:: ይህም መምህራን ተማሪዎች ዘውግ አስፈላጊ፣ ቀላል እና ፍቺያቸው ቀጥተኛ ከሆኑ ቃላት ብቻ የተገነቡ እንዳልሆነ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል:: መምህራን ግልፅ ያልሆኑ የዘውግ ፅሁፎችን ሀሳብ በመገመት ተማሪዎቹ ግልፅ እንዲሆንላቸው አስፈላጊ ነገሮችን ሊያመላክተቷቸው ይችላሉ::

ዋነኛው የዘውግ ትንተና አስተዋፅኦ የተማሪዎችን የማሰብ ችሎታ ከፍ ከማድረጉም በላይ ስሜት ያላቸው ሀሳቦችን እና ዕይታዎችን እንዲያፈልቁ ያስችላቸዋል (Bawarishi, 2003):: ለምሳሌ መምህራን የተለያዩ ቃላትን ይኸውም ተወያዩ፣ ተንትኑ፣ሀሳብ አቅርቡ ወይም አወዳድሩ እና አነፃፅሩ የመሳሰሉትን ቃላት ለመግለፅ አንዳንድ ገላጭ ዓረፍተ ነገሮችን ሊያቀርቡላቸው ይችላሉ::

በተመሳሳይ በዘውግ ፅሁፍ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ትኩረት ለመሳብ የተለመዱ የሚመስሉ ነገር ግን በዘውግ ውስጥ የተለየ ትኩረት ያላቸውን ቃላት ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ለምሳሌ በዘውግ በሚሰጥ ስራ የተለየ ህግ ወይም እንቅስቃሴ ለማህበረሰቡ አትራፊ ይሆናል የሚል ቢሆን በመጀመሪያ አትራፊ የሚለው ቃል መገለፅ አለበት ነገርግን ተማሪዎች በራሳቸው ስለአስፈላጊነቱ ግንዛቤው ላይኖራቸው ይችላል:: ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ለተሰጣቸው የዘውግ ፅሁፍ ስራ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ለመርዳት መምህራን ተማሪዎቻቸውን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊጠይቋቸው ይችላሉ ::

- ይህ የዘውግ ፅሁፍ ለምን ዓላማ ነው የሚያገለግለው?
- የዚህ የዘውግ ፅሁፍ ገፅታ ምንድን ነው?
- ይህ የተለየ የዘውግ ገፅታ እንዴት ዓላማውን ይደግፋል?
- ይህ የዘውግ ፅሁፍ የቀረበው ለማን ነው?
- የዘውግ ፅሁፍ ሲፃፍ ግምት ውስጥ ያስገባው ምንድን ነው?
- ይህ የዘውግ ፅሁፍ ማንን ያገለግላል? (Bawarishi,2003:14)::

በተጨማሪም Bawarishi (2003) እንዳብራሩት እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ተማሪዎች ዘውግን የቋንቋው ተናጋሪ ባለበት ማለትም:- በማህበረሰቡ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚነሳ እና ተቀባይነት ያለውን ጉዳይ የተለየ ዓላማን ለማሳካት ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎች የበለጠ ከተለማመዱት ዘውግ ጋር እነዚህን የዘውግ ፅሁፎች ማነፃፀር ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ ድርሰት ከማስታወቂያ ጋር ሲነፃፀር ተማሪዎችን የሚያሳስበው ፊች ይኸውም ርዕሱን ማብራራት፣ ለትንተና ዐውድ መፍጠር፣ ትንተናውን በማስረዳት እና በተጠይቃዊነት በመደገፍ እንዲገነዘቡት ያሰፈልጋል::

እንደ Conners (1997) አስተያየት መምህሩ የዘውግ ፅሁፍን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲያቅድ በሚና ጫወታ ወቅት በሁለቱም ማለትም ገፀባህሪን በመሳል እና አንባቢውን በመሳብ ረገድ ጠቃሚነት ላይ መወያየት ያስፈልጋል:: ፅሁፍ በባህላዊ ዐውድ ውስጥ ሲተገበር ሌሎች ሁኔታዎችን ማለትም የድምፅ ቃና፣ቅርፅ እና ስልትን ለመወሰን ልዩ ሚና ይኖርዋል:: በአጠቃላይ የዘውግ ተኮር አቀራረብ መምህራን የበለጠ ግንዛቤ እና ዓላማ ፈጥረው አስፈላጊውን ማብራሪያ እና የሚጠበቀውን ነገር አከናውነው በሁኔታዎች፣ ዐውድ እና መነቃቃት ውስጥ የራሳቸውን ዘውግ ማደራጀት ይችላሉ::

የዘውግ አቀራረብ መፃፍን በማስተማር ረገድ ደካማ ጎን ተደርጎ የሚታሰበው ፅሁፍን ለመፃፍ የሚያስፈልገውን ክሂል ችላ ማለቱ እና አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎችን መረጃ የሚቀበሉ አድርጎ መቁጠሩ ነው:: ይሁን እንጂ መፃፍ በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ የሚተገበር እና የተለየ ዓላማ ነፀብራቅ ነው:: በመሆኑም መማር የተለያዩ ግንዛቤዎችን ፈጥሮ በመቅዳት እና በመተንተን መፃፍን መማር ይቻላል:: ሌላኛው የዚህ አቀራረብ ደካማ ጎን ብዙ ጊዜ ተማሪዎች የፅሁፍ ሞዴል የሚቀርብላቸው መሆኑ ሲሆን ይህ ደግሞ ነፃ ሆነው የራሳቸውን ፅሁፍ ለማሻሻል ያስቸግራቸዋል::

### 2.1.8. መፃፍን የሚደግፉ መልመጃዎች

እንደ Ur (1996, 164) አገላለፅ መፃፍን ለማስተማር መልመጃዎችን በምንመርጥበት እና በምናዘጋጅበት ጊዜ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ተስማሚ የሆኑት ይዘቶች የትኞቹ ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ማግኘት ይገባል ብዙ ጊዜ የመፃፍ ክሂልን ለማለማመድ ተብለው በማስተማሪያ መስሪያዎች ውስጥ የሚካተቱ መልመጃዎች ውጤታማ አይደሉም :: በተጨማሪም መፃፍን ለማለማመድ የሚዘጋጁ መልመጃዎች የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት እንደሚገባቸው ጠቁመዋል::

- መልመጃዎች የሚያነሳሱ፣ አስደሳች እና ማራኪ መሆኑን ተማሪዎች ተገንዝበውታል?
- የሚዘጋጁት መልመጃዎች የተማሪዎችን ደረጃ ያገናዘቡ ናቸው?
- የተማሪዎችን ፍላጎት ያከብራል?

- መልመጃዎች በግልፅ እና በቀጥታ ይቀርባሉ?
- መልመጃዎች በምን መልኩ መቅረብ አለባቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ከመልመጃው ዝግጅት በፊት ምላሽ ሊያገኙ ይገባል::

ከዚህም ሌላ Ur (1996:163-164) መፃፍን በመማር ማስተማር ሂደት መልመጃዎችን በ3 አይነት መንገድ እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል::

1. **መፃፍን እንደመሳሪያ**

ብዙ ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መፃፍ ጥቅም ላይ የሚውለው የቋንቋ ይዘቶችን ለማቅረብ እንጂ ራሱን መፃፍን ለማስተማር አይደለም:: ተማሪዎች አዳምጠው ወይም አንብበው ስለተረዱት ነገር ምላሽ ሲጽፉ የቀረቡ ፈተናዎችን ሲሰሩ ሁሉም ተግባራት መፃፍን እንደመሳሪያ ተጠቀሙበት እንጂ በቀጥታ መፃፍን ለማለማመድ አልዋሉም:: በዚህ የተነሳ መፃፍ ሌሎች የቋንቋ ይዘቶችን ለማስተማሪያነት እና ለመከታተያነት ጥቅም ላይ ሲውል እንደመሳሪያ አገልግሏል ይባላል::

2. **መፃፍን እንደግብ**

መፃፍ እንደግብ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ አብይ አላማው መፃፍን እንደክህሎት መለማመድ ነው:: በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የተወሰነ የአፃፃፍ ቅርፆችን /የእጅ መፃፍን የቃላት አፃፃፍንና ስርዓተ ነጥብን/ በቃል ወይም በአረፍተ ነገር ደረጃ ሲማሩ በከፍተኛ የመፃፍ ደረጃ ትኩረታቸው በይዘትና በአወቃቀር ላይ ነው:: በዚህ ደረጃ የተማሪዎች ተግባር የሚገለፀው በታላሚው ቋንቋ ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ የጽሁፋቸውን አላማ እንዲዘረዝሩና ተደራሲያቸውን እንዲወስኑ በማድረግ ነው::

3. **መፃፍን እንደመሳሪያና እንደግብ**

በዚህ የክንውን አይነት አላማ ያለውን ወጥ የመፃፍ ትምህርት ከሌላው የክሂል ትምህርት ይዘት ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ነው:: የመፃፍን ልምምድ የተሻለ ለማድረግ ከሌሎች የክሂል ዘርፎች ጋር አደራጅቶ ማቅረብ ተገቢ ነው:: በቅድሚያ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደመሆኑ መጠን በሌሎች የክሂል ዘርፎች አማካይነት ሊጠናከር ይችላል::

### 2.1.9. የመፃፍ ትምህርት አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር

ከዚህ ቀደም ውጤት፣ ሂደት እና ዘውግ ተኮር አቀራረቦችን ትኩረት አድርገን ተመልክተናቸዋል:: እያንዳንዱ አቀራረብ የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት:: ሂደት ተኮር አቀራረብ ፈጠራ የሚያነሳውን የመፃፍ ሂደት ችላ የሚል እና ብዙ ጊዜ ተቀባይነት ያለው መሳሪያ እና ትኩረት የሚያደርገው በመጨረሻው ውጤት ላይ ነው:: እንደዚህ አይነቱ አቀራረብ መርሀ ትምህርት ሲነደፍ፣ የትምህርትን ሂደት ለመቆጣጠር ስህተትን እና ፈተናዎችን ለመገምገም ይጠቅማል::

በሌላ በኩል ሂደት ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ በተፃራሪ በመፃፍ ፈጠራዊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይሁን እንጂ መፃፍ ድርጊቶችን እንደመቅዳት ቀላል አይደደለም:: ነገር ግን ሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ሲያቀዱ የበለጠ የማብራራት፣ የመከለስ እና በተለያየ ደረጃ ማረምን የሚያጠቃል ሲሆን አንባቢው እና የጽሁፍ አላማ የበለጠ ጠቃሚ ሲሆኑ የጽሁፉ የተግባቦት ሀይል ዋነኛው አንቀሳቃሽ ነው:: ይሁን እንጂ የክፍል ውስጥ ተግባራት ግልፅነት የሚጎድላቸው እና ተማሪዎች መፃፍን በተለያየ ደረጃ ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል:: የሂደት ተኮር ዋነኛው ችግር የማህበረሰቡን ጽሁፍ በመተውና የጸሀፊዎችን ፅሁፍ ከማህበረሰቡ አንፃር የሚመለከትበትን ሁኔታ ችላ በማለት የግለሰብን የመፃፍ ችሎታ በማሳደግ ላይ ያተኩራል::

በአንፃሩ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ሀሳብ ወይም ንድፍ ከመሆን ባለፈ ገላጭ መሆኑ ጠቀሜታ አለው:: ዘውግን በመግለፅ እና በመተንተን ዘውግ እንዴት እንደሚገነባ እና ወደተማሪዎቹ እንደሚተላለፍ በግልፅ ያሳያል:: በዚህ መሰረት ተማሪዎች በንግግር ተግባቦት ተቀባይነት ያለውን በዘውግ ምሳሌ የተገኙትን እውቀቶች ይጋራሉ::

የእያንዳንዱ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሁለት ጠቃሚ ነገሮችን ማለትም ተማሪውን እና የክፍል ውስጥ ልምምድን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል:: ማንኛውም መርሃ ትምህርት እና የማስተማር ዘዴ ሲመረጥ ከተማሪው ፍላጎትና የቀደመ ታሪክ ይኸውም የቀደመ የተማሪዎች የትምህርት ታሪክ፣ ፍላጎት እና ግብ ጋር የተገናኘ መሆን ይኖርበታል:: ዝርዝር እና የተለዩ ፍላጎቶችን ለመለየት የዘውግ ተኮር አቀራረብ አቅም አለው::

ቀላል እና ውጤታማ የሆኑ ሞዴሎችን ወደ ተማሪዎች ማሸጋገር ቀላል ጉዳይ አይደለም:: እንደ Swales (1990) አገላለፅ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልምምድ ሲደረግባቸው ጥሩ ፅሁፎች እንዴት በትክክል እንደሚሰሩ እርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው:: የገላጭነት ሀይል እና አንዳንድ የመመሪያ መለኪያዎች ተመጣጣኝነት መኖር አለበት::

አገባብ፣ መዋቅር፣ አላማ እና ስነልሳናዊ ገፅታዎች እንደ ዘውጋቸው በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ መንፀባረቅ ያለባቸው ሲሆን ተማሪዎች የራሳቸውን ድርሰት ሲፅፉ ይህንን ሁኔታ መገመት አለባቸው (Harwood,2005:3):: እንደ Kin (2007) አስተያየት በዘውግ አቀራረብ ለአንባቢው እና ለፅሁፉ ትኩረት መስጠት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: በሌላ በኩል Kim (2005) እንደገለፁት የዘውግ አቀራረብ እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስናስተምር እንደ ድጋፍ ሰጪ ሆኖ ያገለግላል::

የተማሪዎችን ስነልሳናዊ ገፅታ እና መዋቅራዊ ደንቦች የተለያዩ ዘውጎችን መሰረት አድርገው የሚፈጥሩት ተግባቦቶች ብዙ ጊዜ ውስንነት አለባቸው በመሆኑም የመፃፍ መምህሩ ተማሪዎችን በመምራት ፣በመደገፍ እና በመረዳት በኩል በተለያዩ ዘውጎች መነሻነት ክህሎቶቻቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛል:: ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር ሲነፃፀር ግብዓትን በተመለከተ በመካከላቸው መመሳሰል ይታያል (Badgen and White, 2000:155):: ይሁን እንጂ በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ ሆነው የሚማሩት የተለያዩ ምሳሌዎች እና ፅሁፎች ሲቀርብላቸው ነው::

### 2.1.10. ለተማሪዎች ፅሁፍ የሚሰጥ ምላሽ

መፃፍ በዘውግ አቀራረብ ዓላማ ያለው ተግባር እና አንባቢው እንዲያነበው የሚታቀድ ነው:: በመሆኑም ፀሀፊ ስለአንባቢው እና አንባቢው ጽሁፍን እንዴት ተገንዝቦ ምላሽ እንደሚሰጥ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ፀሐፊው የአንባቢውን ምላሽ ካጤነ ከማህበረሰቡ ምን እንደሚጠበቅ በማወቅ የመፃፍን ማህበራዊ አላማ ለማሳካት ይሞክራል (Hyland, 2003a:177):: በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህሩ እና ተማሪዎች ለሌላኛው ተማሪ ፅሁፍ የታለሙ አንባቢያን ሊሆኑ ይችላሉ:: በአንፃሩ ምላሻቸው ጽሁፍ እንዲከለስ እና የመፃፍ ችሎታ እንዲያድግ ዕድል ይፈጥራል::

ምጋቤ ምላሽ በተለያየ የመመዘኛ ዘዴዎች አማካይነት መምህራን በልምምድ ሂደት ላይ የሚሰጡት ውጤት፣ ለጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ ፣ተማሪዎች ለሰሩት ስራ የሚሰጣቸው አስተያየትን ያጠቃልላል (Grami, 2005:126)::_እንደ Hyland, (2003a) አገላለፅ 3 አይነት ምገባ መረጃዎች አሉ:: እነሱም ፡- የመምህሩ፣ የመምህሩና የተማሪው ውይይት እና የብጤ ምገባ መረጃዎች ናቸው:: ለዚህ ጽሁፍ አስፈላጊ የሆኑት የመምህር እና የቢጤ ምገባ መረጃዎች በስፋት ተዳሰዋል::

### 2.1.10.1. የመምህር ምገባ መረጃ

መምህሩ ምገባ መረጃ ሲሰጥ የመፃፍን አላማ ግምት ውስጥ በማስገባት በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት እና ምን አይነት ምገባ መረጃ እንደሚሰጥ ማቀድ አለበት (Grami , 2005:126)::

የዘውግ ተኮር ጽሁፍ ግብ በዘውግ እውቀት እና በማህበረሰቡ ደንቦች ላይ በመመስረት መፃፍን ማጠናቀር ነው:: በመሆኑም ምገባ መረጃ የምንሰጥበት ጊዜ ተለዋዋጭ በመሆኑ በመፃፍ  ሂደት ደረጃዎች ሁሉ ሊገኝ ይችላል:: ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ንድፍ የሚሰጥ ምገባ መረጃ ቀጣዩን ንድፍ የበለጠ ሊያሻሽል ይችላል( Hyland, 2003a:179)::

ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው ተማሪዎች የራሳቸውን ጽሁፍ ሲጽፉ የሚሰጣቸው ምገባ መረጃ መፃፍን  ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳለው ነው:: ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ በምን አይነት ምገባ መረጃ ላይ ማተኮር እንዳለብን እና የትኛው ምገባ መረጃ ስራ ላይ መዋል እንዳለበት መወሰን ነው:: እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በሁለተኛ ቋንቋ የመፃፍ  ትምህርት ወቅት ጠቃሚዎች ናቸው:: ምክንያቱም ተማሪዎች በሚሰጣቸው አስተያየት መሰረት ጽሁፋቸውን እንዲያሻሽሉ እና በመፃፍ  ላይ ያላቸውን አመለካከት ከፍ እንዲያደርጉ ያግዛል::

በሁለተኛ ቋንቋ መፃፍን ስናስተምር ይዘት በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም መፃፍ  ያለይዘት እና ሀሳብ ማደራጀት አይከናወንም:: በመሆኑም ምገባ መረጃ ሲሰጥ እንደ ቋንቋ መምህር ሰዋስው እና ቃላት ላይ ትኩረት ከማድረግ እንደ መፃፍ መምህር ራስን መቁጠር ይገባል:: በሌላ በኩል በሰዋስዋዊ ቅርፆች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሲደረግ የተማሪዎችን ሀሳብ የማፍለቅ ችሎታ ይታገዳል (Zamel, 2012:86, Dana Ferris, 2012)::

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በባህል አማካይነት መፃፍን ሲማሩ የመምህሩ ሚና አቅጣጫ ማሳየት ይሆናል:: ተማሪዎች ጽሁፋቸው በተገቢው ሁኔታ ተነቦ በሰዋስዋዊ ስህተቶቻቸው አስተያየት ከተሰጣቸው ደስተኛ ሊሆኑ ይችላሉ (Hyland, 2003a:256):: በዚህ ሁኔታ መምህሩ ለተማሪዎቹ የሚሰጣቸው አስተያየቶች ጽሁፋቸውን በተመለከተ መሆን የለበትም:: መምህሩ የተማሪዎቹን ጻራዊ ፍላጎት እና ተማሪዎቹ እርሰ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት:: በመሆኑም መምህሩ ምገባ መረጃን ተማሪዎቹ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ እና ሁኔታ ማቅረብ አለበት::

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ መፃፍን የሚማሩት ለወደፊት የህይወት አላማቸው ሊረዳቸው የሚችል የጽሁፍ ችሎታ ለማግኘት ነው:: በመሆኑም አንባቢው ይህን የጽሁፍ ሁኔታ የሚሳካበትን አላማ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት:: ተማሪዎች ወደፊት ለስራ ወይም አካዳሚያዊ ሁኔታ ሊጽፉ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ የወደፊቱ የጽሁፋቸው አንባቢዎች ሰዋስዋዊ ስህተቶቻቸውን ላይታገሱ ይችላሉ:: በመሆኑም በሰዋስዋዊ ቅርፆች እና ስህተት የተነሳ በስራቸው ላይ አሉታዊ ውጤት ሊያሳድርባቸው ይችላል:: በተመሳሳይ በአካዳሚያዊ ሁኔታም ሰዋስዋዊ ስህተት መስራት አሉታዊ ውጤት ያስከትላል (Hyland, 2003a:181):: በመሆኑም ምገባ መረጃ ተማሪዎች ስለሰዋስዋዊ ቅርጾች እንዲያስቡ ዕድል የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል::

ከዚህም በተጨማሪም ስሜት እና ሃሳብ በቋንቋ ይገለፃሉ:: ይህ ማለት ፍቺ በተመረጡ ተገቢ ቅርፆች አማካይነት የሚቀርብ ሲሆን ሁል ጊዜ ቅርፅ ፍችን ለመፍጠር የሚጠበቅ ነገር አይደለም:: ነገር ግን ፍቺን ለመግለፅ ዋነኛው ግብዓት ሊሆን ይችላል:: በመሰረቱ ቅርፅና ፍቺ በእውነተኛው የህይወት ተግባቦት የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸው:: በተመሳሳይ ይህ ሁኔታ ለጽሁፍ በምንሰጠው ምላሽም ይንፀባረቃል (Hyland, 2003a:184-185):: መምህሩ ለተማሪዎቹ የሚሰጠው ምገባ መረጃ በድርሰቱ ሀሳብ እና አደረጃጀት ላይ ብቻ መገደብ የለበትም:: በአንፃሩ በሰዋስዋዊ ስህተቶች ላይም ምገባ መረጃ በመስጠት ተማሪዎች የስነልሳን እውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ይኖርበታል::

በመሆኑም ለተማሪዎች ጽሁፍ ምገባ መረጃ ሲሰጥ ይዘት እና ቅርፅ መጣመር አለባቸው:: Ferris (2012) በመምህራን የጽሁፍ ምገባ መረጃ ላይ ባደረጉት

ቅኝት ተማሪዎች በሁለቱም ማለትም በሰዋስው እና ይዘት ላይ አስተያየት ሲሰጣቸው ደስተኞች መሆናቸውን ገልፀዋል::

ይሁን እንጂ ቅርፅ እና ይዘት በምገባ መረጃ ወቅት የጎላ ጠቀሜታ ቢኖራቸውም መምህሩ እነሱ ላይ ትኩረት አድርጎ ስህተቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋ ስለማይችል ሁሉንም ስህተቶች ከመከታተል መምህሩ በጽሁፍ ላይ የተሳሳተ ግምት እንዲመጣ በሚያደርጉ ስህተቶች ላይ ማተኮር አለበት:: በዘውግ ተኮር ጽሁፍ በቅርፅ ላይ የሚያተኩሩ ምገባ ምላሾች አላማ የሚያደርጉት በወቅታዊ የጽሁፍ አይነት ነው:: በመሆኑም መምህሩ ትኩረቱን በጽሑፉ ግልፅነት ላይ ጣልቃ የሚገቡ ስህተቶችን በማመልከት ላይ መሆን ይኖርበታል (Hyland, 2003a:186)::

#### 2.1.10.2 የቢጤ ምገባ መረጃ

የብጤ ምገባ መረጃ መሰረት የሚያደርገው ቋንቋን መማር የሚቻለው በማህበራዊ መስተጋብር ነው የሚለውን አስተሳሰብ ነው (Feez, 2002: 24):: ተማሪዎች በሚያበረታታ ሁኔታ ከአንባቢያን በሚያገኙት ምላሽ ላይ ውይይት ማካሄድ ይችላሉ:: በዚህ ሂደት የአንባቢን ስሜት የመረዳት ችሎታቸውን ያሳድጋሉ:: በመሆኑም የብጤ ምገባ መረጃ በሁለተኛ ቋንቋ የመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የተለመደ ተግባር ሆኗል:: ይሁን እንጂ ምገባ መረጃ ጠቃሚ ቢሆንም መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ቁጥር መብዛት የተነሳ ከጊዜ አንፃር ምገባ መረጃን ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆንበት የብጤ ምገባ መረጃ እንዲኖር ያደርጋል:: ይሁን እንጂ የብጤ ምገባ መረጃ አውንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶች ይኖሩታል::

ዋነኛው የብጤ ምገባ መረጃ አዎንታዊ ውጤት የተማሪዎችን የንባብ ስሜት ከፍ በማድረግ የተሻሉ ፀሀፊዎች እንዲሆኑ ማስቻሉ ነው:: ምክንያቱም የብጤ ምገባ መረጃ ጥሩ ግብዓት ሆኖ ተማሪዎች የጓደኞቻቸውን ድርሰት ከአንባቢ አንፃር በማየት የንባብ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል:: ከዚህ አንፃር አንባቢዎች ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚረዱት እና በድርሰቱ ውስጥ ምን እንደሚፈልጉ ግንዛቤ ያገኛሉ:: ይህ የግንዛቤ መፈጠር ፀሀፊዎች ጽሁፈታቸውን እንዲያሻሽሉ እና ምን ማድረግ እንደለባቸው ድርሰታቸውን እንደፀሀፊ እንዲከልሱ ያደርጋቸዋል (Hyland, 2003a:198):: ተማሪዎች እርስ በርስ አስተያየት

ሲሰጣጡ ንቁ ተሳትፎ ስለሚያደርጉ የመምህሩ ስራ ከመቀነሱም በላይ የተማሪዎችን እርስ በርስ የመደጋገፍን ሁኔታ ያሳድጋል::

አሉታዊ ውጤቱን ስንመለከት ተማሪዎች ከተሰባሰቡበት ባህል አንፃር ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተስማሚ ላይሆን ይችላል (Hyland, 2003a: 42):: ከዚህ አንፃር የባህል ብዙሐነት ባለበት ሁኔታ ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቻቸውን ጽሁፍ ጥሩ ወይም ጥሩ አይደለም የሚል አስተያየት ከመስጠት ይቆጠባሉ:: ከዚህም ሌላ በብጤ ምገባ መረጃ በሚሰጠው አስተያየት ላለመስማማት ያንገራግራሉ:: በተጨማሪም አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ ከቢጤዎቻቸው ጋር ላለመጋጨት ራሳቸውን ይቆጣጠራሉ:: ይህ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰውን ቅር የማሰኘት ተግባር ትህትና እንደጎደለው ሰው ስለሚያስቆጥር የቡድን ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል በተማሪዎች የሚሰጠው የብጤ ምገባ መረጃ ጥንቃቄ የበዛበት ይሆናል:: (Carson and Nelson, 2012)::

ተማሪዎች በብጤዎቻቸው ጽሁፍ ላይ ችግሮችን ላያስተውሉ ይችላሉ:: ምክንያቱም በቋንቋው ብቃት ላይ ከሚስተዋልባቸው ችግር ባሻገር የአደረጃጀቱን ስርዓት ይኸውም መፃፍን ተጠይቃዊ የማድረግ ችግር ይስተዋልባቸዋል:: በብጤ ምገባ መረጃ ወቅት የሚሰጡት አስተያየቶች በተማሪዎቹ ውስን የቋንቋ ችሎታ ላይ መሰረት አድርገው በሰዋስዋዊ ስህተቶች እና በቋንቋ ችሎታቸው ላይ ያጠነጠነ ከሆነ የምገባ መረጃ ውጤት ይቀንሳል::

ከዚህም ሌላ የብጤ ምገባ መረጃ አሉታዊ ሁኔታ ያለው ሲሆን ከመምህሩ ምገባ መረጃ የተለየ ዓላማ እና ውጤት አለው:: በመሆኑም ተገቢ የሆነ የምገባ መረጃን ስራ ላይ ማዋል ጠቃሚ ነው:: Hyland (2003a) እንደገለፁት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሀሳብ ካላቸው ውጤታማ ምገባ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ::

Reid (2001) እንዳመለከቱት የብጤ ምላሽን የተመለከተ ስልጠና ቢሰጥ ተማሪዎች የተሻለ አስተያየት ሰጪ እንዲሆኑ ያደርጋል ያሉ ሲሆን በተጨማሪም ባቀረቡት አስተያየት ተማሪዎች በራሳቸው ጽሁፍ ላይ ማስታወሻ መያዝ እንዳለባቸው እና ከዚህ በኋላ ማስታወሻዎቻቸውን ማገናዘቢያ እንዲሆናቸው እርስ በርስ በመለዋወጥ የተሻለ ምገባ መረጃ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል::

### 2.1.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ በመፃፍ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ጥናቶች ተካሂደዋል:: በዚህ ስር ለማመላከት የተፈለገው ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት የተካሄዱ ጥናቶች ከርዕሳቸው ከአላማቸውና ከአጠናን ዘዴያቸው አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ መንገድ ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ማመላከት ነው::

ክፍሌ ሀብተማሪያም (1986) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ፅሁፍ ባቀረቡት ጥናት የሁለተኛ ደረጃ በተለይም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ጉዳይን ቃኝተዋል:: በጥናታቸው የተገኘው ውጤት ጥናቱ ያሳተፋቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር እንዳለባቸው ጠቁመዋል:: በመሆኑም ተማሪዎች ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት በትክክል የመግለፅ ፣ቃላት የመምረጥ፣ ሰዋስዋዊ አገባብን የመጠበቅ፣ በስርዓተነጥቦች በተገቢ ሁኔታ የመጠቀም፣ ዐረፍተነገርን በተገቢ ሁኔታ አዋቅሮ የመፃፍ እና ሀሳብን አቀነባብሮ የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያመላከቱ ሲሆን በጥናቱ ለተደረሰበት ውጤት ምክንያት ከሆኑ ነገሮች መካከል የመማሪያ መፃህፍቱ አቀራረብ እና የትምህርቱ አሰጣጥ ዋነኛ ነጥቦች መሆናቸውን ገልፀዋል::

ማረው ዓለሙ (1987) “በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት” በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል::በጥናታቸው ማጠቃለያ ላይ የደረሱበት ድምዳሜ በግል ከሚፃፉ ድርሰቶች ይልቅ በቡድን የሚፃፉ ድርሰቶች የተሻሉ መሆናቸው፣ በጥሩ ድርሰት እና በቡድን ስራ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን እና የቡድን ስራ ለድርሰት ፅሁፍ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል::

ስዩም ከበደ (1988) “ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለ9ኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት” በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት ሂደታዊ የመፃፍ አቀራረብን ተጠቅሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መፃፍን በማስተማር ክሂሉን ለማሳደግ ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን ጠቁመዋል ዘዴው ጠንካራ ጎን እንዳለው ቢታመንም ትምህርት የሚቀርብበት ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነ ተማሪዎችን፣ ለመረዳት ለመፃፍ ፈተና ለማዘጋጀት እና ለአካዳሚያዊ የመፃፍ ክንውኖች ተማሪዎቹን ብቁ በማድረግ ረገድ በኩል ድክመት እንዳለው ጥናቶች ስለሚያመላክቱ እና

ተማሪዎች በመፃፍ ሂደቱ ደጋግመው በመፃፍ መፃፍን ይማራሉ በሚለው ትወራ ውጤት ለማየት ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ በአማርኛ ድርሰት ማስተማር በኩል ያለውን ችግር ያቃልላል ማለት አያስደፍርም::

ሰለሞን ዮሀንስ (1991) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ድግሪ መሙያ "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል:: የደረሱበት ውጤትም በመምህራን የማስተማር ዘዴ እና በተማሪዎች የመጻፍ ስትራቴጂ መካከል ክፍተት መኖር መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸውን በመፃፍ ሰትራቴጂ የሚያሳድግላቸው አለመሆኑን ጠቅሰዋል::

አስቴር ሳሙኤል(1998) "የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ " በሚል ርዕስ በአራት የአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቤቶች ጥናት ያካሄዱ ሲሆን የጥናታቸው ውጤት የሚያመለክተው መምህራን መፃፍን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ በማፃፍ ሳይሆን በአብዛኛው ስነልሳናዊ ዕውቀቶችን ለማስጨበጥ ትኩረት በመስጠት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል::

ዕጌ ታደሰ (1992) "ለመፃፍ ክሂል የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል?" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ መስተዳድር ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተኛው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መፃህፍት ላይ የይዘት ግምገማ አካሂደዋል:: በጥናታቸው ማጠቃለያ የደረሱበት ጥናቱ በተካሄደባቸው ክፍሎች የመፃፍ ክሂል ይዘቶችን አስመልክቶ የቀረበው የተለጣጣቂነት መስፈርት በተገቢ መንገድ ስራ ላይ አለመዋሉን እና ለትምህርቱ የተመረጡት ይዘቶች የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥኑ አለመሆናቸውን በምክንያትነት አቅርበዋል::

ተመስገን ፈቀደ (2001) "የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማሰተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ" በሚል ርዕስ ግምገማ አካሂደዋል:: የጥናቱ ዓላማ በሀዲያ ዞን በሾኔ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማሰተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ግንኙነት በመፈተሽ የመምህራን የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎችን የድርሰት መፃፍ ብልሀት መመርመር ነው::

በጥናቱ የተገኘው ውጤት በመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ እና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ጠቁመዋል::

ሶፊያ ሙሀመድ (2002) "በዳሞት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ድርሰትን ለማስተማር ሂደት ተኮር የማስተማር ስልት ያለውን ተግባራዊነት መፈተሸ" ላይ ግምገማ አካሂደዋል:: የጥናቱ ዓላማ የሂደት ተኮር የድርሰት ትምህርት አቀራረብ ያለውን ተግባራዊነት መፈተሽ ነው:: በጥናቱ የተገኘው ውጤት ሂደት ተኮር የድርሰት ትምህርት አቀራረብን በማወቅ እና በአግባቡ ተጠቅሞ የማስተማር ክንውን የሚካሄድበት አለመሆኑን እና የመምህራን ትኩረት ለተማሪዎች ስነልሳናዊ ዕውቀትን ለማስጨበጥ የታለመ በቃላት እና ዐረጋት ፍቺ እና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ እንጂ እነዚህን ስነልሳናዊ ዕውቀቶች ተጠቅመው ሀሳባቸውን በፅሁፍ መግለፅ የሚችሉበት የማስተማሪያ ዘዴ አለመሆኑን ጠቁመዋል::

ሰይድ ይመር (1993) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ትምህርት ይዘቶች ክንውኖች የማስተማሪያ ስነዘዴ ትግበራ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል:: የጥናቱ ዓላማ የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የተመረጡት ይዘቶች ለማስተማር መምህራን የሚገለገሉባቸውን ስነዘዴዎች እና አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ እና የተማሪዎቹን ችሎታ ማጤን ነው:: በጥናቱ የተገኘው ውጤት በመፃፍ ትምህርት ወቅት የሚቀርቡት ይዘቶች መልመጃዎች እና የስነዘዴዎች ትግበራ መፃፍን የሚያለማምዱት ለመፃፍ ክሂል መዳበር አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆኑን ጠቁመዋል:: በዚህ ጥናት የቀረበው መፍትሄ ልማዳዊውን የማስተማር ስነዘዴ ለመለወጥ ትኩረት መስጠት እና ለመምህራን ስልጠና መስጠትን ነው::

አስቻለው ቦጋለ (2000) "በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍተሻ" በሚል ርዕስ በሶስት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን አካሂደዋል:: በደረሱበት መደምደሚያ መምህራን የመፃፍ ትምህርትን እንደሌሎቹ የቋንቋ ትምህርቶች ትኩረት ሰጥተው አለማቅረባቸው የመፃፍ ትምህርት በክፍል ውስጥ ተገቢውን አቀራረብ አለመከተሉ እና መምህራን ክሂሉን በማስተማር ረገድ የግንዛቤ እጥረት እንደታየባቸው ጠቁመዋል::

አንለይ አዳነ (2000) “ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የመፃፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ፍተሻ” በሚል ርዕስ በአማራ ክልል በአራት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት አካሂደዋል:: በደረሱበት ድምዳሜ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ መፃፍን ለማስተማር የቀረቡት ተግባራት በአብዛኛው የጥብቅ እና መር መፃፍ አቀራረብ የተለያዩ መሆናቸው የመምህሩ መመሪያዎች በአግባቡ አለመዘጋጀታቸው መምህራን በተገቢ መንገድ ክሂሉን አለማለማመዳቸው የሚሰጡው ምጋቤ ምላሽ አነስተኛ መሆኑ በክፍል ውስጥ ዝቅተኛ የተማሪዎች ተሳትፎ መታየቱን ጠቁመዋል::

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናታዊ ስራዎች የመፃፍ ክሂል ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች፣የማስተማር ስነዘዴ ትግበራ፣ የመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ እና ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ባለው ተግባራዊነት ላይ በመመስረት የቀረቡ ናቸው:: ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ያላቸው አጠቃላይ ዝምድና ማዕከላዊ ነጥባቸው ከመፃፍ ክሂል ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው:: በዚህም ምክንያት በክለሳ ድርሳናት ውስጥ የሚቀርቡበት አንዳንድ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ሊኖረቸው ይችላል ተብሎ ይታሰባል:: ይህ ጥናት በዋናነት ከነዚህ ጥናቶች የሚለየው ከትኩረት አቅጣጫው፣ ከአጠናን ስልቱ አንፃር ሰፊ ልዩነት አለው:: በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ፣የተተኳሪ መጠን ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የጥናቱ ዘመን እና ዓላማ ከቀደምት ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል:: ይህ ጥናት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የዘውግ-ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን የሚሞክር ከመሆኑም በተጨማሪ ከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከትኩረት አቅጣጫ እና ከሙከራዊነቱ አንፃር ከቀደምት ጥናቶቹ ይለያል::

Kongpetch (2006) የዘውግ ተኮር አቀራረብን ተጠቅመው በታይላንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ጥናት አካሂደዋል:: በጥናታቸው እንደጠቆሙት የታይላንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሲፅፉ ለተለያዩ አላማዎች መጋለጥ አለባቸው:: ለምሳሌ ለክፍል ስራዎች ራሳቸውን ችለው ለሚያካሂዱቸው ፕሮጀክቶች ፅሁፋቸውን አቅርበዋል:: ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን አደራጅተው ተገቢውን ጽሁፍ ተጠቅመው የመፃፍ ችግር ተስተውሎባቸዋል:: በጥናቱ የታየው

ጉዳይ የዘውግ ተኮር አቀራረብ በታይላንድ የትምህርት አውድ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ፈትሿል::

Burns (2001) አንድ ተከታታይ የሆነ የክፍል ውስጥ አካሂድን የተከተለ በከፍተኛ ደረጃ ዘውግ ተኮር የሆነ ጥናት አካሂደዋል:: አላማውም ከተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ እንዴት እንደሚጽፉ የሚያሳይ ነው:: ጥናቱ ተማሪዎች እንዴት የስራ ደብዳቤ መፃፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ሞክሯል:: በውጤቱም የዘውግ አቀራረብ ውጤታማነት ታይቷል:: በዘውግ እና በስነ ልሳን መዋቅር ላይ ትኩረት በማድረግ ተማሪዎች የቋንቋ ገፅታዎችን እንዴት እንደሚገለገሉበት ይዘቶች እንዴት እንደሚደራጁ ግልፅ ሀሳብ እንዴት እንደሚያገኙ ፍተሻ አካሂደዋል::

Henry and Roseberry (1998) አጭር የጎብኚዎችን የእንግሊዝኛ የመረጃ ጽሁፉን በመጠቀም ጥናት አካሂደዋል:: በዚህ ጥናት የተካፈሉ ተማሪዎች በሁለት የተከፈሉ ሲሆን በተመሳሳይ የጽሁፍ ተግባር አንደኛው የዘውግ አቀራረብን የተከተለ ሲሆን ሌላኛው የዘውግ አቀራረብ የማይከተል ነው:: ተሳታፊዎቹ ፈተና የወሰዱ ሲሆን የዘውግ ተኮር አቀራረብ የተከተሉት ካልተከሉት የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል::

መረጃው እንደሚያመለክተው የመዋቅሩ ይዘት እውቀት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲያደራጁ ማለትም በሁለቱም በኩል የተግባቦት ዓለማቸውን ለማሳካትና በሚገባ የተደራጀ ጽሁፍ እንዲጽፉ አግዟቸዋል:: ተማሪዎች የንግግርንና የስነልሳን ገጽታዎችን የመገንዘባቸው ሁኔታ በዘውግ ተኮር አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

# ምዕራፍ ሶስት:-የአጠናን ዘዴ

በምዕራፍ ሶስት ስር የምረምሩ ንድፍ እንዴት እንደተዘጋጀ፣ የጥናቱ ዓይነት ምን እንደሆነ እና እንዴት ሊመረጥ እንደቻለ፣ የተመረጠው የጥናት ዓይነት እንዴት ተግባራዊ እንደተደረገ በዝርዝር ተመልክቷል:: በመቀጠል ተመራማሪው ጥናቱን ለማካሄድ የተገለገለባቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ይኸውም:- ቅድመና ድህረ ፈተናዎች እንዲሁም የፅሁፍ መጠይቅ ለምን ሊመረጡ እነደቻሉ ማብራሪያ ቀርቦበታል:: በተጨማሪም ለዚህ ምርምር በመረጃ ሰጪነት የተመረጡ ተጠኚዎች እነ ማን እንደሆኑና እንዴት እንደተመረጡ የተቃኘበት ክፍል ነው::

## 3.1 የምርምር ንድፍ

በማህበራዊ ሁኔታዎች ከተለያዩ ፅነሰሀሳቦችና ትርጓሜዎች በትምህርት ላይ የታዩ ንድፈሀሳባዊ ጥያቄዎችን ስናነሳየምርምር መሳሪያዎችን የምንመርጥባቸው መስፈርቶችን ለመወሰንና ንደፈሀሳቦችንና የምርምር ችግሮችን ለመረዳት የተለያዩ ምሳሌ የሚሆኑን ዕውነታዎችን እናገኛለን:: ትክክለኛውን የምርምር ስልት መምረጥ በምርምሩ አካሄድ ወሳኝና በኋላም የምርምሩን አቅጣጫ ለመወሰን በጣም ወሳኝ ነገር ነው:: እንደሚታወቀው ተመራማሪው እንድ ጊዜ የምርምሩን ሰልት ከወሰነ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለመተርጎም የምርምሩን መሳሪያዎች ለመወሰን ቀላል ይሆንለታል Norman and Yuvona(1994)::

በዓለም ላይ በተለያዩ ምሁራን የተነደፉ የምርምር አካሄዶች የሚታዩ ሲሆን በዋናነት ፖዘቲቪስትና አንቲፖዘቲቪስት ይጠቀሳሉ:: ፖዘቲቪዝም ምልከታና ምክንያት መሰረታዊ ነገሮች መሆናቸውን ይቀበላሉ:: እንደነዚህ አመለካከት ዕውነተኛ ዕውቀት የሚመነጨው በሙከራና በምልከታ ከስሜታችን በሚገኝ ልምድ ነው::ከዚህም ሌላ የፖዘቲቪስት አመለካከት በሃያኛው መቶ ክፍለዘመን በትምህርት ላይ የሚካሄዱ ምርምሮች ላይ ተፅዕኖ አሳርፏል:: በተፃራሪው የግለሰቦችን ተፈጥሮ በማጤን በኩል ባለበት ክፍተት ተቃውሞ ተሰንዝሮበታል:: ይህ አመለካከት የሰዎች ባህሪ በውጫዊው አካባቢ ተፅዕኖ ስር ያለና አዝጋሚ ነው ብሎ ያስባል Cohn and Robis (2000)::

ሁለተኛው አመለካከት አንቲፖዘቲቪዚም ማህበራዊ ሁኔታ የግለሰቦች እይታና አመለካከት በአካባቢያችን በሚታዩ የተለያዩ ክስተቶች የሚታይ ዕድገት ነው::

በመሆኑም በዚህ አመለካከት ዕውቀት በውጫዊ ሁኔታ የሚገኝ ሳይሆን በግለሰቡ ልምምድ የሚመጣ ነው። እንደ Denzin and Lincoln(2000) አስተያየት አንቲፖዘቲቪዚም እውነታ ተደጋጋሚና ውስብስብ ነው። ይህ ማለት እያንዳንዱ ክስተት የተለያዩ ትርጓሜዎች ሊኖሩት ይችላሉ። እነደዚህ አስተሳሰብ የክስተቶች ማረጋገጫ ክስተቶችን የምንረዳበት ደረጃ በሚመረመሩ ክስተቶች ላይ ትኩረት ከማድረግ በተለያዩ አካላት በሚፈጠሩ ግንኙነቶች ላይ ማተኮር ይሻላል።

እነዚህን ሁለት አመለካከቶች ስንፈትሻቸው የፖዘቲቪስት አመለካከት ከሰዎች ባህሪ አንፃር ማህበራዊ ሁኔታዎች ተጨባጭ፣ የሚለኩ፣የሚተነበዩና ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ ናቸው። በሌላ በኩል አንቲፖዘቲቪዚም ክስተቶችን መረዳትና መተርጎም ከሂደት ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ትርጉም ለመስጠት ያስችላል ከዚህ በላይ የተነጋገርንባቸው አመለካከቶች በሳይንሳዊ ምርምሮች ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ያሳርፋሉ። ለምሳሌ ፖዘቲቪዚም ለአሃዛዊ ምርምር ይኸውም በፅሁፍ መጠይቅ፣በሙከራና በፈተና ለሚገኙ መረጃዎች ትኩረት ይሰጣል። በሌላ በኩል አንቲፖዘቲቪዚም ማህበራዊ ክስተቶችን ለመመርመር ከዓይነታዊ ትንተና ጋር ግንኑነት ካላቸው ለግለሰብ የሚደረግ ቃለመጠይቅ፣ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅና ግለሰባዊ ግንኙነቶች ወዘተ ትኩረት ያደርጋል።

ይህንን ምርምር ለማካሔድ የሙከራ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። የሙከራ ንድፍ ተመራማሪው መላምቶችን ለመፈተሽና በተለዋዋጮች መካከል ያለውን ግኑኝነት በመመርመር ተቀባይነት ያለው መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ያስችለዋል (Best and Khan, 1993:146)። በዚህ ምርምር ፀሀፊው የኳይዚ ሙከራዊ ንድፍን ተግባራዊ አድርጓል። የኳይዚ ሙከራዊ ንድፍ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ክትትሉ መቼ እና በነማን ላይ መካሄድ እንዳለበት ለመቆጣጠር ያስችላል። ነገርግን የሙከራና የቁጥጥሩ ቡድን አባላትን በአጋጣሚ መመደብ ይገባል። በመቀጠል የምርምሩ ንድፍን የሚያሳይ ቻርት ቀርቧል።

*የምርምር ንድፍ*




## 3.2 የጥናቱ ዓይነት

ይህ ጥናት በዋናነት መጠናዊ የምርምር ዘዴን (Quantitave Method) ሲከተል በአጋዥነት አይነታዊ የጥናት ዘዴ (Qualitative Method) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ገላጭ የመረጃ አተናተን ስልትን የተከተለ ይሆናል:: Burges, (1989,4) Sleber, (1975)ን ዋቢ ጠቅሰው እንዳብራሩት መጠናዊ እና አይነታዊ የምርምር ዘዴዎችን በጣምራ ማካሄድ እንደሚቻል ጠቁመዋል:: ይህ በአንድ ቡድን ጥናት ቅድመና ድህረ ፈተናዎች ተግባር ላይ ሲውሉ በአንድ አዲስ የማስተማሪያ ዘዴ አማካይነት በተጠኚዎች ላይ ለውጥ መገኘት አለመገኘቱን ለመለየት የሚያስችል ዘዴ እንደሆነ ገልፀዋል (Koul, 1996,460)::

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ጠቀሜታ እንዳለው ማረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል:: በመሆኑም ይህንን አላማ ለማሳካት ሙከራዊ (experimental) የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል::

የናሙናዎችን የባህሪ ልዩነት ለመፈተሽ እንዲቻል የቡድኖችን ባህሪ የማወዳደሪያ ስታስቲካዊ ዘዴ (Between- group design) ጥቅም ላይ ውሏል:: ከዚህ በተጨማሪ ለጥናቱ ግብዓት ይሆን ዘንድ ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተገምግመዋል::

### 3.2.1. የናሙና አመራረጥ

Frankel and Wallen (1990:68) ናሙና ተመራማሪው የሚፈልጋቸው ቡድኖች ሲሆኑ እነዚህን ናሙናዎች በመገልገል በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ እንዲደርስ ያስችሉታል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ Frankel and Wallen (2011:91) በምርምር ውስጥ ናሙና መረጃ የሚያስገኙ ቡድኖች ናቸው በማለት ገልፀዋል:: በሌላ በኩል Best and kahn (1993:13) ናሙና ከአጠቃላዩ ቁጥር በአነስተኛና ወካይ በሆነ ቁጥር የሚመረጥ ን ብለዋል:: በዚህ ጥናት ተመራማሪው አሳማኝ ሆነ የናሙና አወሳሰድ ስልትን ተከትሏል:: እነደCreswell(2012:145) አስተያየት በዚህ የናሙና አወሳሰድ ተመራማሪው ተሳታፊዎችን ይመርጣል:: ምክንያቱም ናሙናዎቹ ፈቃደኛ ሆነው በጥናቱ ይሳተፋሉ::

#### 3.1.1.1. የክልልና ዞን ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢ ከጥናቱ አላማ አንፃር ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴን (Purposeful or judgmental) በመጠቀም በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው የምዕራብ ሸዋ ዞን ተመርጧል:: ለዚህ ምክንያቱ አጥኚው በተጠቀሰው አካባቢ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስተምር በነበረበት ወቅት  በመፃፍ  ክሂል ላይ ችግር በማስተዋሉ ለጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበት ወካይ ናሙና በዓይነትና በመጠን ለማግኘት የሚያስችል እና ይህንን ጥናት ለማድረግ ከመምህራንና ከአካባቢው አስተዳደር የሚፈለገው ድጋፍ እንደሚገኝ በመተማመን ነው::

#### 3.1.1.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከሚገኙ 36 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ትምህርት ቤት ለመምረጥ ስራ ላይ የዋለው መንገድ በመጀመሪያ የትምህርት ቤቶቹን ስም በፊደል ተራ ቅደም ተከተል መዘርዘር ነው:: ከዚያም Franked and Wallen (1993:496-4979) ያቀረቡትን የዕጣ ቁጥር

በመጠቀም እንዲለዩ ተደርጓል:: በዚህ መሰረት በዞኑ ካሉት 36 ትምህርት ቤቶች የኢጃጂ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሙከራ ጥናቱ፣ የኤጀሬ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ለዋናው ጥናት ተመርጠዋል::

### 3.1.1.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: የክፍል ደረጃው የተመረጠው ሆን ተብሎ ነው:: ይኸውም በስርዓተ ትምህርቱ አደረጃጀት በሁለተኛ ደረጃ ከሚገኙ ሁለት የክፍል ደረጃዎች ማለትም 9ኛና 10ኛ ክፍሎች 9ኛ ክፍል አንዱ ሲሆን ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ነው ተብሎ በመታሰቡ ክፍሉ ሊመረጥ ችሏል:: በሌላ በኩል 10ኛ ክፍል ሁለተኛ ደረጃው ማብቂያ በመሆኑና የትምህርቱ አሰጣጥም ተማሪዎቹን ለሀገር አቀፍ ፈተና በማዘጋጀት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ይህ ክፍል ለጥናቱ አልተመረጠም::

### 3.1.1.4. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በምዕራብ ሸዋ ዞን ከሚገኙ 36 ሁለተኛ ደረጃ ትምህት ቤቶች ውስጥ በቀላል የንሞና አወሳሰድ ዘዴ የኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሙከራ ጥናቱ የተመረጠ ሲሆን በዚሁ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ 16 ክፍሎች መካከል በዕጣ የንሞና አወሳሰድ 9A ክፍል ለሙከራ ቡድን 9D ክፍል ደግሞ ለቁጥጥር ቡድኑ ተመርጠዋል:: ለዋናው ጥናት በዚሁ ዞን የሚገኘው የኢጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተመሳሳይ ቀላል ንሞና አወሳሰድ ዘዴ የተመረጠ ሲሆን በ9ኛ ክፍል ውስጥ ካሉ ዘጠኝ ምድቦች ክፍሎች መካከል 9ኛA ክፍል ለቁጥጥር ቡድኑ እንዲሁም 9ኛ F ክፍል ደግሞ ለሙከራው ቡድን በተመሳሳይ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል::

### 3.1.1.5. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ከተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍሎችን ከሚያስተምሩ መምህራን በንሞና ዕጣ አወሳሰድ አንድ መምህር ተመርጦ የሙከራውን እና የቁጥጥሩን ቡድኖች እንዲያስተምር ተደርጓል:: ጥናቱን ለማካሄድ የተመረጠው መምህር የሙከራ ቡድኑን በአዲሱ መንገድ እንዲያሰተምር ሲደረግ፣ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በነባሩ መንገድ እንዲያስተምር

ተደርጓል:: በአዲሱ መንገድ ለማስተማር ይረዳው ዘንደ በተዘጋጀው የስልጠና መመሪያ ስልጠና ወስዷል::

### 3.1.2. የስልጠና መመሪያ (Training Manual)

የዚህ የስልጠና ማኑአል ዓላማ መምህሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን በዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ መፃፍን ሲያስተምር ስለዚህ አቀራረብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማስቻል ሀሳቦችን አጋርቷል:: መምህሩ በተመራማሪው የተሰጠውን ስለጠና በተገቢ ሁኔታ በመከታተሉ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀረረብን ለመተግበር ችሏል::

ይህ የስልጠና ማኑአል ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች አሉት:: የመጀመሪያው ክፍል መግቢያውን የተመለከተ ሲሆን በዚህ ርዕስ ስር ለሰልጣኙ የስልጠናው ስምምነት ፎርም አጠቃላይ የስልጠናው ሂደት እና ለስልጠናው የተመደበው ጊዜ ተጠቃሏል::

በሁለተኛው ምዕራፍ ስለዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ንድፈ ሀሳብ የቀረበ ሲሆን ይህም ለሰልጣኝ መምህሩ ትምህርቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ስለዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እውቀት እንዲያገኝ አግዞታል:: በመጨረሻው ምዕራፍ መምህሩ በሙከራው ትምህርት ወቅት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ነገሮች ተጠቃለዋል::

### 3.1.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ የሚያገለግሉ መረጃዎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም ከቅድመና ድህረ ፈተናዎች፣ ለተማሪዎች ከተደረገ ከፅሁፍ መጠይቅ ልዩ ልዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል::

#### 3.1.3.1. ቅድመ ትምህርት ፈተና

የሙከራውና የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የሙከራ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የጽሁፍ ችሎታቸውን ዳራ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መገንዘቡ ለጥናቱ ጠቃሚ ነው:: በመሆኑም የተማሪዎቹን የጽሁፍ ችሎታቸውን የሚለካ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተዘገጅቷል:: የፈተናውን ጥራትና ተገቢነት ለማረጋገጥ

አማካሪውና ሌሎች የቋንቋ ባለሙያዎች እንዲገመግሙት ተደረጎ በተሰጠው ማሻሻያ መሰረት ተስተካክሏል:: የቁጥጥሩና እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ትምህርቱን ከመለማመዳቸው በፊት ይህ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸው ያመጡት ውጤት በስታትስቲካዊ ዘዴ አማካዩና ልዩነቱ ወጥቷል::

### 3.1.3.2. ድህረ ትምህርት ፈተና

ከህድረ ትምህርት ፈተናው ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ እንዲቻል የፈተናውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል ቅድመና ደህረ ፈተናዎች አንድ ዓይነት ይዘት እንዲኖራቸው ተደርጓል:: በመሆኑም ፈተናዎቹ በጥያቄ ቁጥር፣ ብዛት፣ አቀራረብ በይዘትና በአወቃቀራቸው አንድ ዓይነት እንዲሆን ተደርጓል:: ቡድኖቹ በተለያየ ሁኔታ በየግላቸው የተዘጋጀላቸውን ትምህርት በአጥኚው ስልጠና በተሰጠው በትምህርት ቤቱ አንድ መምህር ትምህርቱ ተሰጥቷል:: ቡድኖቹ ከትምህርቱ በኋላ በትምህርት አቀራረብ ልዩነት ምክንያት የችሎታ ልዩነታቸውን የሚለካ ድህረ ትምህርት የጽሁፍ ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቶ:: ፈተናውን በአማካሪው እና በቋንቋ ባለሙያ መምህራን በሰጡት አስተያየት መሰረት ታርሟል::

ድህረ ትምህርት ፈተናውን ለሙከራ እና ለቁጥጥሩ ቡድኖች በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ በአጥኚወና በሁለት የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተሰጥቷል:: በዚህ መንገድ ተማሪዎቹ የመፃፍ ጥያቄዎቹን በተገቢው መንገድ መግለፃቸውን እና በጥያቄዎቹ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች በሚገባ መገንዘባቸውን በሚሰጧቸው ምላሾች መሰረት ታርሟል::

የሁለቱም ክፍሎች የቅድመና ድህረ ትምህርት የፈተና ወረቀቶች በወቅቱ በፈታኞች ተሰብስቧል:: የውጤቱን አሰጣጥና የአስተራረሙን ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል በትምህርት ቤቱ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአጥኚወ ታርሟል:: ለአራሚዎቹ Heaton (1988:146) ከይዘት ከአደረጃጀት ከቋንቋ አጠቃቀም ከቃላት አመራረጥ እና ከስርዓተ አፃፃፍ አኳያ የተዘጋጀ የማረሚያ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል::

የአስተራረም ሂደቱም ከፈተና ወረቀቱ ላይ የተማሪዎች ስም ሳይፃፍ ኮድ ተሰጥቶታል:: በዚህ መሰረት የአንድ ተማሪ የመልስ ወረቀት በሶስት ኮፒ ተባዝቶ ለሶስቱ አራሚዎች ተሰጥቷል:: ሶስቱ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት

ውጤት ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ የተማሪው ውጤት ተደርጎ ተወሰዷል::

#### 3.1.3.3. የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቁ የቀረበው በሙከራ ጥናቱ የዘውግ ሂደት ተኮር አቀረቀረብን ለተከታተሉት ተማሪዎች ነው:: ዓላማውም ተማሪዎቹ በዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ በመፃፍ ትምህርት አመለካከታቸው ላይ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን ለማወቅ ነው:: በዚህ መሰረት የጥናቱ ትኩረት ለሆነው የመፃፍ ክሂል ተማሪዎች ለጥናቱ ከሚያስፈልገው የመረጃ ዓይነት አኳያ የተለያዩ ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅቷል:: የሚቀርቡት ጥያቄዎች በሶስት ዋና ክፍሎች ተከፋፍለዋል :: በዚህ መሰረት ክፍል አንድ የፅሁፋዊ መጠይቁን ዓላማ እና የመጠይቁን አሞላል የሚጠቁም መመሪያ የያዘ መግቢያ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የተማሪዎቹን ዳራ የሚመለከት ነው:: ክፍል ሶስት ደግሞ የጥናቱ ዋነኛ መረጃዎች ይኸውም ከምርምሩ ዓላማ ጋር ግኑኝነት ያላቸው አማራጭ መልሶችን የያዙ “ዝግ ጥያቄዎች” (Close- questions) ናቸው:: የፅሁፍ መጠይቁ ስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አማካሪዬ እና ሁለት የቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደረጓል:: አስተያየቱን መሰረት በማድረግ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት ለተጠኚዎቹ ቀርቧል:: በመጨረሻም ለተማሪዎቹ አስፈላጊው ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል::

### 3.1.4. የመረጃ አተናተን

ይህ ጥናት በዋናነት መጠናዊ የመረጃ ትንተና ዘዴን (Quantitative data analysis method) የሚጠቀም ሲሆን በደጋፊነት አይነታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴን (qualitative data analysis method) ተጠቅሟል:: በዚህ መሰረት በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎችና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

### 3.1.4.1. ከቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች ትንተና

የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት /የቁጥጥሩና የሙከራ/ ቡድኖች በተመደቡት በአዲሱ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እና በቀደመው የመፃፍ ትምህርት መማርና መለማመድ ከመጀመሪያቸው በፊት የነበራቸውን ችሎታ በአቀራረቡ ከተማሩና ከተለማመዱ በኋላ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለማሳየት የሚያስቸሉ ናቸው:: ውጤቱን በመመርመር አቀራረቡ ውጤታማ መሆን አለመሆን አስተያየት ተሰጥቶበታል:: በዚህ መሰረት ክፍሎች በአጋጣሚ የንሞና ዕጣ ተመርጠው  የቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲወሰዱ ተደርጓል ::

ከዚህ ጥናት ላይ የቀረቡት የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ውጤታማነት የሚታወቀው በቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት ሲታይና ጉልህ ልዩነቱን ያመጣው የድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት ከፍ ብሎ መገኘት ከሆነ ይህ ጉልህ ልዩነት በ t- ቴስት ቀመር ቀርቧል::

### 3.1.4.2. ከተማሪዎች የተገኘ የፅሁፍ መጠይቅ ትንተና

ፅሁፋዊ መጠይቁ የቀረበው ለተማሪዎች ሲሆን ጥያቄዎቹ ዝግ በመሆናቸው የአተናተን ስልቱም ይህንኑ ተከትሏል;; በዚህ መሰረት አማራጭ መልሶች በያዙ ጥያቄዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተመሳስሎነታቸው መሰረት በሰንጠረዥ መልክ  በቁጥርና በመቶኛ በመጠቆም በመጠናዊ የመረጃ ትንተና ተደርጓል::

**የምርምር ስነምግባራዊ መርሆችን መጠበቅን በተመለከተ**

የምርምር ተግባር ከፍተኛ ትዕግስት፣ ጥንቃቄና ታማኝነት የሚጠይቅ ስራ ነው:: ከዚህ አንፃር በጥናቱ ውስጥ በዋቢነት ያገለገሉትን ስራዎች በትክክል ከመግለፅ ጀምሮ በመረጃ አሰባሰብና አያያዝ ሂደት እንዲሁም በመረጃ ትንተና ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ተጨባጭ፣ ሚዛናዊና ነባራዊ ሁነቶችን ለማቅረብ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጓል:: በመጨረሻ የተማሪዎችም ሆነ የመምህራን ግላዊ መረጃዎች በጥንቃቄ ተይዟል:: በጥናቱ ትንተና ጊዜም ከመረጃ ሰጪዎች ፈቃድ ውጭ ማንነታቸው በግልፅ አልተጠቆምም::

# ምዕራፍ አራት:-የሙከራ ጥናት

የሙከራ ጥናት የሚደረገው ዋናው ጥናት ከመካሄዱ አስቀድሞ በአነስተኛ መጠን የጥናቱን ማካሄጃ መሳሪያዎች እና አካሄዱን ለመፈተሽ ነው:: Yin(1994) የሙከራ ጥናትን ተቀሜታ አስመልክተው በሰነዘሩት አስተያየት ጥናት አድራጊው መረጃ የመሰብሰብ ዕቅዱን ግልፅአድርጎ ማሳየትና የምርምሩን የአሰራር ማዕቀፍ በዋና ጥናቱ ላይ አጉልቶ እንዲያሳይ ያግዘዋል:: በዚህ መሰረት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመወሰን ትክክለኛነታቸው (validity) እና አስተማማኝነታቸው reliability ይፈተሻል:: ከዚህም ሌላ የሙከራ ቡድኑን መምህር ለማሰልጠን የተዘጋጀው የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የስልጠና መምሪያ በትግበራው ወቅት በምልከታ እና መምህሩ በሚሰጠው ምላሽ ይፈተሻል:: በዚህ መንገድ በሙከራ ጥናቱ የተገኘው ውጤት ዘዴውን በመከለስ የዋናውን ጥናት አካሄድ ለማጥራትና እና በስልጠና መምሪያው ላይ አስፈላጊ ማሻሻያዎች በማድረግ ለመገልገል አስችሏል::

ከዚህም በተጨማሪ የሙከራ ጥናቱ ተካሂዶ የምርምሩን ጥያቄዎች ለመመለስ በቅድመና ድህረ ፈተናዎችና የፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል:: የሙከራ ጥናቱ ውጤት በዋናው የምርምር ስራ ላይ ምን ምን ሊጨመር እንደሚገባው ከማሳየቱም ባሻገር ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ ተቃሚ ሀሳቦች ተገኝተዋል::

## 4.1 የናሙና አወሳሰድ

### 4.1.1 ተማሪ

በኢጃጂ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር ወንድ 556 ሴት 543 በድምሩ 1099 ነው:: ይህ መረጃ የተገኘው ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ነው:: የምድብ ብዛታቸው 16 ነው:: ሁሉም ምድቦች በአንድ ፈረቃ የሚማሩ መሆናቸው ተረጋግጧል:: በመሆኑም ካሉት 16 ምድቦች ውስጥ ሁለት ምድቦች የንሞና ዘዴ በመጠቀም ሁለት ክፍሎች ለቁጥጥር እና ለሙከራ ጥናቱ ተመርጠዋል:: በእያንዳንዱ ምድብ ያለው የተማሪ ቁጥር ተቀራራቢ ነው:: በአንድ ምድብ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ቁጥር ከ55-60

ይደርሳል:: ይህንንም የተማሪዎቹን የስም መጥሪያ ሰነድ በማየት ተረጋግጧል:: በተጨማሪም ለጥናቱ ከተመረጡት ሁለት ምድቦች 110 ተማሪዎችን ለሙከራው ጥናት መለየት ያለባቸው በቅድመ ፈተናው ሊሆን ስለሚገባ ፈተናው ለ 110 ተማርዎች ተሰጥቷል:: በፈተናው ውጤት መሰረት ተቀራራቢ ውጤት ያላቸው 50 ተማሪዎች ተመርጠዋል:: እነዚህ ተማሪዎች እያንዳዳቸው 25 ተማሪዎች ባሏቸው ሁለት ምድቦች ተከፍለው አንደኛው የቁጥጥር እና ሁለተኛው የሙከራ ቡድን ሆነው የማስተማሩ ስራ ተከናውኗል::

### 4.1.2 መምህር

በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ሲኖሩ በዕጣ የንሞና አወሳሰድ ዘዴ አንደኛዋ መምህርት ትምህርቱን እንድትሰጥ ተወስዳለች:: የተመረጠችው መምህርት ሁለቱን ቡድኖች ማለትም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖችን ያስተማረች ሲሆን የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር እንዲያግዛት መፃፍን በዘውግ ተኮር አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችል ስልጠና በምርምር አድራጊው ተሰጥቷታል:: የስልጠናው ጊዜና ቦታ ለመምህሯ በሚያመች ሁኔታ ተከናውኗል:: በዚህም መሰረት በየቀኑ ለሁለት ሰዓታት በአጠቃላይ ስልጠናው ለስምንት ሰዓታት ተሰጥቷል::

## 4.2 የጊዜ ሰሌዳ

በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መደበኛው ክፍለ ጊዜ በ40 ደቂቃ የተከፋፈለ ነው:: ይሁን እንጂ ለሙከራ ጥናቱ በተቃራኒ ፈረቃ ለአንድ ሰዓት የሚሰጥ ነው:: ከዚህ ጊዜ ካነሰ ለምርምሩ የሚሆን በቂ መረጃ ለመሰብሰብ አዳጋች ይሆናል:: በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ በሳምንት ለሁለት ቀናት አንድ አንድ ሰዓት በጠቅላላው ከየካቲት 26- ሚያዚያ 12 2007 ዓ.ም ለ6 ሳምንታት ይኸውም ለ12 ሰዓታት ትምህርቱን ተከታትለዋል::

### 4.2.1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

#### 4.2.1.1 ፈተና

በዚህ የሙከራ ጥናት የቅድመ እና ድህረ ጽሁፍ ፈተናዎች ተሰጥተዋል:: ቅድመ ፈተናው የሚያገለግለው ጥናቱ ከመካሄዱ አስቀድሞ በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ተመሳሳይ ውጤት መኖር አለመኖሩን ለማየት ነው::

ይህም ከተመሳሳይ ደረጃ በመነሳት አንደኛው በዘውግና ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ እና ሌላኛው በልማዳዊው መንገድ ልምምድ ካደረጉ በኋላ በመካከላቸው የተከሰተ ለውጥ ወይም ጉልህ የሆነ የችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመረዳት አግዟል:: በዚህም መሰረት በምርምር አድራጊው እና በሁለቱ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተመረጡት ክፍሎች ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል:: እርማቱም በእነዚሁ መምህራን ከተከናወነ በኋላ በውጤቱ መሰረት ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠው በዕጣ በመለየት 9ኛ "A"ክፍል ተጠኚ እና 9ኛ "D" የቁጥጥር ቡድን ተደርገው የሙከራ ስራው ተከናውኗል::

የድህረ ጽሁፍ ትምህርት ፈተና አላማው ለስድስት ሳምንታት ይኸውም ለአስራ ሁለት ሰዓታት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያላቸውን ልዩነት ለመፈተሽ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የድህረ ፅሁፍ ፈተናውን ሂደት ምርምር አድራጊው እና ሁለቱ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታትለውታል::

የቅድመ እና ድህረ ፅሁፍ ፈተናዎች እርማት የተደረገው ሁሉን አቀፍ የድርሰት እርማት (Holstic Approach) ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከቋንቋ አጠቃቀም ከስርዓተ ነጥብ አንፃር የተከናወነ ነው::

#### 4.2.1.2 የጽሑፍ መጠይቅ

በዚህ የሙከራ ጥናት የተከናወነው የጽሁፍ መጠይቅ አላማ የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አመለካከት ላይ ያመጣውን ውጤት ለመፈተሽ ታስቦ ተካሂዷል::

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በLikert scale ስልት የተዘጋጁ 20 የአመለካከት ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ ተጠኚዎቹ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልሶቻቸውን በትክክል እንዲሰጡ በመገምገሚያው ላይ ያለውን "ለመወሰን ያስቸግረኛል" የሚለው ምላሽ ወጥቶ መልሶቹ ወደ አራት ተስተካክለዋል:: ዓላማውም የፅሁፍ መጠይቁ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ጥናቱ ከመካሄዱ አስቀድሞ እና ጥናቱ ከተካሄደ በኋላ ስለድርሰት ጽሁፍ ያላቸውን አመለካከት ለመለየት የቀረበ ነው::

በዚህም መሰረት የተዘጋጀው መጠይቅ ለ25 የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ተሰጥቶ የተገኘውም ውጤት በስታስቲካዊ መንገድ ተሰልቶ ቀርቧል::

### 4.2.2. መረጃ መተንተን

መረጃዎች በቅድመ እና ድህረ የፅሁፍ ፈተና ተሰብስበው ለትንተና እና ለውይይት እንዲያመቹ ሆነው ተተናቅረዋል:: በዚህ መሰረት የተሰበሰቡት መረጃዎች አማካይ (x)፣ the degree of Freedom (d/f) የአማካይ ልዩነት (የ t-ዋጋ) ፣ (የp- ዋጋ) ጠቃሚነት በየቡድኖቹ መካከል ተነፃፅሯል::

በቁጥጥሩ እና በሙከራ ቡድኖቹ መካከል በቅድመ እና ድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ያለው ጉልህ ልዩነት በ0.05 ደረጃ መሆኑ ኢ-ጥገኛ የንሞና ቲ-ቴስት (Independent sample t- test)ን ተግባራዊ በማድረግ በጽሁፍ ተፈትሿል:: መጠይቁ በ (Likert Scale) የተሰበሰቡ መረጃዎች በስታትስቲካዊ ዘዴ ተተንትነዋል::

### 4.2.3. የሙከራ ጥናቱ መረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በመጀመሪያ የቁጥጥሩ እና የሙከራ ቡድኖቹ የወሰዱቸው የቅድመ እና ድህረ የፅሁፍ ፈተና ውጤቶች ተፈትሸዋል:: በዚህ መሰረት በዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረገው የሙከራ ቡድን እና በተለመደው መንገድ መፃፍን ከተማረው የቁጥጥር ቡድን የትኛው? ቡድን የተሻለ ውጤት እንዳመጣ ፈትሿል::  በተመሳሳይ የጽሑፍ መጠይቁም ምላሽ ተብራርቷል:: በሙከራ ጥናቱ የተከናወነው የጽሑፍ መጠይቅ አላማው  የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከመማራቸው አስቀድሞ እና በአዲሱ አቀራረብ ከተማሩ በኋላ ስለ ጽሑፍ ያላቸውን አመለካከት ያጤነ ሲሆን ከሙከራ ጥናቱ የተገኘው ውጤት ማጠቃለያ እና ከዚህ የሙከራ ጥናት የተቀሰመው ትምህርት ተዳሷል::

#### 4.2.3.1. የፈተና ውጤት

በዚህ የሙከራ ጥናት የተሰጡት የቅድመ እና ድህረ የጽሁፍ ፈተናዎች ተጠኚዎች በዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ  ከመለማመዳቸው በፊት የነበራቸውን ችሎታ እና በዚህ ዘዴ መፃፍን ከተለማመዱ በኋላ ያመጡትን ውጤት በማነፃፀር ውጤታቸው መሻሻል  ማሳየት አለማሳየቱን

ለማረጋገጥ የረዳ ነው:: በፈተናዎቹ የተገኘውን ውጤት በመፈተሽ የዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ጠቃሚ መሆኑን ያመለከተው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል::

**ሰንጠረዥ 1 የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖች የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤት**

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | d/f | T-Value | P-Value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | X | SD | SE | N | X | SD | SE | | | |
| ቅድመ ፈተና | 25 | 50.92 | 8.89 | 1.78 | 25 | 51.17 | 7.41 | 1.48 | 49 | -.105 | 0.917 |
| ድህረ ፈተና | 25 | 52.09 | 7.47 | 1.49 | 25 | 61.63 | 7.95 | 1.59 | 49 | -4.375 | 0.367 |

ይህ ሰንጠረዥ የተራኪ ድርሰት አፃፃፍን በሚመለከት ከትምህርት በኋላ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል በቅድመ እና በድህረ የጽሁፍ ፈተና ውጤት ላይ የተከሰተ ጉልህ ልዩነት መኖር አመኖርን ለማረጋገጥ የሚያስችል የኢ-ጥገኛ ንሞና ቲ-ቴስት (independent sample t- test) ፍተሻ ውጤት ያሳይ ነው::

የቅድመ ጽሑፍ ትምህርት ፈተና አላማው የሙከራ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የሁለቱ ቡድኖችን ተመሳሳይነትን ለመመልከት ነው:: በዚህ መሰረት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች አማካይ ውጤት እንደ  የአቀማመጣቸው ቅደም ተከተል 50.92 እና 52.09 ነው:: ይሁን እንጂ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም ለማለት የ t-ዋጋ ውጤት ማመሳከር ያስፈልጋል:: በመሆኑም በዚህ ሰንጠረዥ የ t-ዋጋ -.105 (d/f 49) እና የ P-ዋጋ 0.917 ነው:: ይኸውም ከአልፋ ቫልዩ (alpha value) (0.05) ይበልጣል ማለት ነው:: ይህ ስሌት የሚያመለክተው በቅድመ ፈተና ወቅት በቁጥጥር ቡድኑ እና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው::

በሌላ በኩል በዚሁ ሰንጠረዥ በድህረ ፈተና ወቅት በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድኖቹ መካከል የተራኪ ድርሰት አፃፃፍ ውጤት ተነፃፅሯል:: ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 51.17 ሲሆን የሙከራ

ቡድኑ ደግሞ 61.63 ነው:: የ t-ዋጋ ስሌታቸው -.4.375 (d/F 49) ሲሆን የ P-ዋጋ ደግሞ 0.367 ነው:: ይህ ውጤት ከ0.05 ያነሰ ነው:: በመሆኑም ውጤት በስታትስትካዊ ስሌት መሰረት በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው:: ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተለማመዱ በኋላ ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ነው::

**ሰንጠረዥ 2- የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት**

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | d/f | T-Value | P-Value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | X | SD | SE | N | X | SD | SE | | | |
| ቅድመ ፈተና | 8 | 59.43 | 2.22 | .78 | 8 | 58.33 | 3.55 | 1.18 | 15 | -9.358 | 0.078 |
| ድህረ ፈተና | 8 | 60.82 | 4.19 | 1.48 | 8 | 70.95 | 1.83 | .65 | 15 | -,6.267 | 0.000 |

ሰንጠረዥ ሁለት የሚያሳየው በተራኪ ድርሰት ጽሑፍ ወቅት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ እና በድህረ ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት ንፅፅር ነው::

በቅድመ ፈተና ወቅት በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 59.45 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 60.82 ነው:: በመሆኑም በዚህ ሰንጠረዥ የ t-ዋጋ -9.358 (d/f 15) እና የp ዋጋ ደግሞ0.078 ነው፡፡ ይህም ከ0.05 የበለጠ ነው:: ውጤቱ የሚያመለክተው በቅድመ ፈተና ወቅት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በስታትስትካዊ ስሌት መሰረት ጉልህ ልዩነት ያልታየበት መሆኑን ነው:: በዚህ መሰረት በቅድመ ፈተናው ወቅት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ችሎታ ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋግጧል::

በሌላ በኩል በዚህ ሰንጠረዥ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በድህረ ፈተና ውጤት ከፍተኛ ውጤት ባስመዘገቡት የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት ታይቷል:: ከዚህ አንፃር የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 60.82 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 70.95 ነው:: በተመሳሳይ የሁለቱ ቡድኖች t-ዋጋ-.6.267 (d/f15) ሲሆን የp-ዋጋ ደግሞ 0.000 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው:: ይህ ሁኔታ የሚጠቁመን ተራኪ ድርሰት በሚፃፍበት ወቅት ከፍተኛ ውጤት ባስመዘገቡት በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድኖቹ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መታየቱን ነው:: በዚህ መሰረት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት እና በዚሁ ምክንያት በሁለቱ ምድቦች መካከል ልዩነት መከሰቱ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ለጀነር ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ከተጋለጡ በኋላ ነው:: ይህም አዲሱ አቀራረብ የተሻለ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል መሆኑን እንገነዘባለን::

**ሰንጠረዥ 3 የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት**

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | d/f | T-Value | P-Value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | X | SD | SE | N | X | SD | SE | | | |
| ቅድመ ፈተና | 17 | 46.91 | 7.94 | 1.92 | 17 | 47.80 | 6.30 | 1.53 | 30 | -.361 | 0.078 |
| ድህረ ፈተና | 17 | 47.97 | 4.45 | 1.08 | 17 | 57.24 | 5.40 | 1.31 | 30 | -5.443 | 0.000 |

ሰንጠረዥ ሶስት በተራኪ ድርሰት ጽሑፍ ወቅት በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን የሚያነፃፅር ነው::

በቅድመ ፈተና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ቡድኖች አማካይ ውጤት፣ የቁጥጥር ቡድኑ 46.91 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 47.91 ነው:: በአንፃሩ የ t-ዋጋ -.361 (d/f 30) ሲሆን የ p- ዋጋ ደግሞ 0.078 ነው:: ይህም ከሚጠበቀው ዋጋ /0.05/ የበለጠ ነው:: ከዚህ አንፃር ውጤቱ የሚጠቁመው በቅድመ የፅሁፍ ፈተና ወቅት በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው::

በሌላ በኩል በዚሁ ሰንጠረዥ በድህረ ፈተና ወቅት የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 47.97 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 57.84 ነው:: የt-ዋጋ -5.443 (d/f30) ሲሆን የp-ዋጋ ደግሞ .000 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው:: ይህ የሚያመለክተው በድህረ የፅሁፍ ፈተና ወቅተ በሙከራ ቡድኑ ውስጥ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች የተሻለ መሆኑን ነው::

### 4.2.3.2. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና

ይህ የጽሁፍ መጠይቅ ተጠኚዎቹ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ ተራኪ ድርሰት መፃፍ ከመለማማዳቸው በፊት እና ልምምዱን ካደረጉ በኋላ ያላቸውን አመለካከት ለማጤን የተከናወነ ሲሆን በ /Likert scale/ ስልት የቀረቡ 20 የአመለካከት ጥያቄዎችን ይዟል:: ከነዚህ ጥያቄዎች መካከል የመጀመሪያዎቹ አስሩ ጥያቄዎች ተጠኚዎች በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከመለማመዳቸው በፊት ለድርሰት የነበራቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑ እና ልምምዱን ካደረጉ በኋላ ግን አዎንታዊ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ተስተውሏል:

**ሰንጠረዥ 4- ተጠኚዎች በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት ለመፃፍ የነበራቸው አመለካከት**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | 2 | 1 | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | ከዚህ ቀደም በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ድርሰት በመፃፍ እለማመድ ነበር:: | 4 | 3 | 7 | 28% | 14 | 4 | 18 | 72% |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ድርሰት ስፅፍ በነፃነት በራስ መፃፍን አለማምደውኛል:: | 8 | 1 | 9 | 36% | 12 | 4 | 16 | 64% |
| 3 | በቡድን ስራ ወቅት በመፃፍ ስራ ላይ የሚያሳትፉኝን ተግባራት መቀበል ያስደስተኛል:: | 5 | 5 | 10 | 40% | 7 | 8 | 15 | 60% |
| | መምህራን ድርሰቴን አርመው ይሰጡኝ | 2 | 8 | 10 | 40% | 8 | 8 | 16 | 60% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የነበረው አስተያየት በየጊዜው ሙከራዎችን | | | | | | | | |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍትን መጽሔቶችን እና ጋዜጦችን በተደጋጋሚ ማንበብ እወዳለሁ:: | 4 | 3 | 7 | 36% | 2 | 1 | 3 | 64% |
| | | - | 5 | 5 | 20% | 8 | 13 | 21 | 80% |
| 6 | ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቴ ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችለኝን በቂ እውቀት አግኝቼአለሁ:: | - | - | - | - | 14 | | 11 | 100% |
| 7 | ድርሰት ለመፃፍ የተፈጥሮ ስጦታ ያስፈልጋል ብዬ ስለማስብ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አልነበረኝም:: | 6 | 4 | 10 | 40% | 6 | 9 | 15 | 60% |
| 8 | ድርሰት ስፅፍ ፅሁፌ የሰዋስወ ስህተት ስለሚበዛበት ድርሰት ፃፍ ባልባል ደስ ይለኛል | 4 | 11 | 15 | 60% | 5 | 5 | 10 | 40% |
| 9 | ከዚህ ቀደም በክፍል ጓደኞቼ ፊት የፃፍኩትን ድርሰት ሳነብ ጥሩ ስሜት አይሰማኝም:: | - | 25 | 25 | 100% | - | - | - | - |
| 10 | ከዚህ በፊት ድርሰት እጽፍ የነበረው የጽሑፍ ችሎታዬን የማሻሻል ፍላጎት ኖሮኝ ሳይሆን በመምህሬ ስለምታዘዝ እና ለማገኘው ውጤት ስል ነበር:: | - | 17 | 17 | 68% | 3 | 5 | 8 | 32% |

በሠንጠረዥ አራት በተራ ቁጥር “1” በክፍል ውስጥ እና ውጪ የመፃፍ ልምምድ ያደርጉ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ (28%) ማለትም 7 ተማሪዎች አዎነታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 18 ተማሪዎች ማለትም (72%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ እንደ ቅደም ተከተላቸው (28%) እና (72%) ነው:: ከዚህ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ለመፃፍ መሻሻል ጉልህ ድርሻ ለሚኖረው ልምምድ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ነው::

“ይማሩበት የነበረው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በራስ መፃፍን የሚያበረታታ ነበር” ለሚለው በተራ ቁጥር “2” ለቀረበው ጥያቄ 8 ተማሪዎች (32 %)አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 17 ተማሪዎች (68%) ግን አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በተራ ቁጥር ስድስት ላይ ከዚህ ቀደም በነበሩበት ክፍል

ድርሰትን ለመፃፍ የሚያስችል እውቀት ማግኘታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል::

በተመሳሳይ "ድርሰት ልዩ ተሰጥኦ ይጠይቃል" ለሚለው ጥያቄ (40%) አውንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ (60%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ይህ የሚያሳው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ስለድርሰት ፅሁፍ ያላቸው አመለካከት በተለይ ልምምድ ማድረግ እና በነፃነት መፃፍን በተመለከተ አሉታዊ አመለካከት እንደነበራቸው ለማየት ተችሏል::

ንባብ እና መፃፍ የማይነጣጠሉ ተግባራት ሲሆኑ ይህንን አስመልክቶ በተራ ቁጥር "5" የተለያዩ ጋዜጦችን እና መፅሄቶችን ያነቡ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ (40%) ወይም 10 የጥናቱ ተተኳሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት (60%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ይህ የሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችን ለማንበብ ያላቸው ፍላጎት አበረታች አለመሆኑን ነው::

በአጠቃላይ በሠንጠረዥ አምስት ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ስለድርሰት ፅሁፍ ልምምድ ማድረግና የራስን ድርሰት ለመፃፍ እንዲሁም በመፃፍ ወቅት በቡድን ተግባር ለመሳተፍ የነበራቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ነው::

**ሰንጠረዥ 5- በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደርጉ በኋላ ለመፃፍ የነበራቸው አመለካከት**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመቶኛ |
| 11 | በዘውግ ተኮር አቀራረበ ድርሰት የመፃፍ ልምምድ በማድረጌ የመፃፍ ፍላጎቴ ተነሳስቷል:: | 2 | 20 | 22 | 88% | 1 | 2 | 3 | 12% |
| 12 | በክፍል ውስጥ የተነበቡልኝ ሞዴል ድርሰቶች ተራኪ ድርሰተ ለመፃፍ ጠቅመውኛል:: | 4 | 18 | 22 | 88% | 2 | 1 | 3 | 12% |
| 13 | የፃፍኩትን ድርሰት ጓደኞቼ አንብበው የሚሰጡኝ አስተያየት የተሻለ እንድጽፍ አነሳስቶኛል:: | 2 | 21 | 23 | 92% | 1 | 1 | 2 | 8% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | በዘውግ ሂደት ተኮር አቀራረብ ተራኪ ድርሰት ስጽፍ መምህሬ | 1 | 19 | 20 | | 3 | 2 | 5 | 20% |
| 15 | የፃፍኩትን ድርሰት ደጋግሜ ሳነብ ስህተቶችን አገኝበታለሁ:: | 3 | 13 | 16 | 64% | 4 | 5 | 9 | 36% |
| 16 | በፅሁፍ ሀሳብን ማቀናበር ሀሳቤን እንዲደራጁ ጠቅሞኛል:: | 2 | 15 | 17 | 68% | 5 | 3 | 8 | 32% |
| 17 | መፃፍ ለወደፊቱ ህይወቴ ጠቃሚ ነው:: | 3 | 18 | 21 | 84% | 3 | 1 | 4 | 16% |
| 18 | ስሜትን ለመግለፅ መፃፍ ጠቃሚ መንገድ ነው:: | 18 | 3 | 21 | 84% | 3 | 1 | 4 | 16% |
| 19 | የተለያዩ የመፃፍ ተግባራትን /አንቀፅ ደብዳቤ ድርሰት መፃፍ/ ማከናወን ያስደስተኛል:: | 2 | 8 | 10 | 40% | 13 | 2 | 15 | 60% |
| 20 | በትምህርት ቤት ብዙ የመፃፍ ልምምድ ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: | 1 | 22 | 23 | 92% | 1 | 1 | 2 | 8% |

ከፍ ሲል የቀረበው ሠንጠረዥ አምስት ተጠኚዎች በዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተራኪ ድርሰትን መፃፍ ከተለማመዱ በኋላ ስለ መፃፍ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚለውን ለማወቅ በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ11-20) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው::

ተማሪዎች በመፃፍ ወቅት ተገቢ የሆነ ድጋፍ ካገኙ ለድርሰት አዎንታዊ አመለካከት እንደሚኖራቸው Caval Cant, (1993) ገልፀዋል:: በዚህ የፅሁፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር “11” ላይ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር አቀረረብ ድርሰት የመፃፍ ልምምድ በማድረግህ ስለመፃፍ ያለህ አመለካከት ተሻሽሏል? ለሚለው ጥያቄ (88%) ይኸውም 22 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ መስጠታቸው፣ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑን ይጠቁማል::

በተጨማሪም በሰንጠረዥ ተራ ቁጥር "12" ላይ "በክፍል ውስጥ የቀረቡ ሞዴል ድርሰቶች ተራኪ ድርሰት ለመፃፍ ጠቅመውኛል" ለሚለው ጥያቄ (12%) ወይም 3 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ (88%) ወይም 22 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህ የሚጠቁመን ተማሪዎችን በሚስብ መልኩ የተለያዩ ሞዴል ድርሰቶች በመጠቀም፣ በተማሪዎች መካከል እንዲሁም በመምህሩና በተማሪው መካከል ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር ተጠኚዎች ለተራኪ ድርሰት ፅሁፍ አውንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል ማለት ነው::

በሰንጠረዥ ተራ ቁጥር "13" " የፃፍኩትን ድርሰት ጓደኞቼ አንብበው የሚሰጡኝ አስተያየት የተሻለ እንድጽፍ አነሳስቶኛል":: ለሚለው ጥያቄ ሁለት መላሾች (8%) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት ሃያ ሶስት መላሾች (92%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በሌላ በኩል በሰንጠረዥ ተራ ቁጥር "20" "በትምህርት ቤት ብዙ የመፃፍ ልምምድ ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ":: ለሚለው ጥያቄ ሁለት ተማሪዎች ማለትም (8%) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ ሃያ ሶስት ወይም (92%) መላሾች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከነዚህ ምላሾች መገንዘብ የሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ የጽሁፍ ልምምድ ካደረጉ የሚፅፉትን ድርሰት ለሌሎች ለማሳየትና አስተያየት ለመቀበል እንደሚገፋፉ ነው::

በአጠቃላይ የጥናቱ ተተኳሪዎች፣ ተራኪ ድርሰት ሲፅፉ ከአቻዎቻቸው እና ከመምህራቸው የሚያገኙትን ድጋፍ እና አስተያየት ይፈልጉታል:: በክፍል ውስጥ ሞዴል ፅሁፎች መቅረባቸው ድርሰቶቻቸውን ደጋግሞ በማንበብ እርማት ለማድረግ መፈለጋቸው ለመፃፍ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው ያሳያል::

### 4.2.4. ከሙከራ ጥናቱ የተቀሰሙ ትምህርቶች

የሙከራ ጥናቱ የሚያመለክተው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ የምርምሩ ጥያቄዎችን መሰረት የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው:: በዚህም መሰረት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለዋናው ጥናት አስተማማኝ እና ትክክለኛ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ መሆናቸው ተረጋግጧል ::

1. በቅድመ እና ድህረ የጽሁፍ ፈተናዎች ላይ ተጠኚዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ የተፈቀደላቸውጊዜ አንድ ሰዓት ነው:: ይሁን እንጅ ይህ ጊዜ ለሙከራና

ለቁጥጥሩ ቡድኖች በቂ አለመሆኑን ተመራማሪው አስተውሏል:: በተለይም ተራኪ ድርሰት ሲጽፉ በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው በዋናው ጥናት ላይ አስራ አምስት ደቂቃ በመጨመር አንድ ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ እንዲሆን መደረግ ተደርጓል::

2. በ Likert scale የቀረበላቸውን የጽሁፍ መጠይቅ በተመራማሪው በተሰጣቸቸው ገለፃ /x / ምልክት አድርገው የሞሉ ቢሆንም አንዳንድ ተማሪዎች የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ የሰጧቸው ምላሾች የተሟላ ማብራሪያ እና ገለፃ ሊሰጣቸው እንደሚገባ አሳይቷ::

3. ከቀረቡት የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች መካከል በተራ ቁጥር 19 የቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ በሚያስገኝ መልኩ እንደገና ተስተካክሎ መፃፍ እንዳለበት ግንዛቤ ተወስዷል::

4. የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር እንዲያገለግል ስለዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ለ 8 ሰዓታት በተመራማሪው ስልጠና ቢሰጥም ስልጠናው በተግባር የተደገፈ መሆን እንዳለበት ትምህርት ተቀስሟል:: በዚህ መሰረት በዋናው ጥናት የተወሰኑ ተማሪዎችን በመምረጥ በተግባር የተደገፉ ስልጠና ለመምህሩ ተሰጥቷል::

## ማጠቃለያ

የሙከራ ጥናቱ ዋነኛ አላማ የዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከልማዳዊው የመፃፍ ማስተማሪያ ጋር ሲነጻጸር የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ማሻሻሉን መመርመር ነው:: ይህንንም የሙከራ ጥናት ለማከናወን መረጃዎች በቅድመ እና ድህረ  የፅሁፍ ፈተናዎች እና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል::

የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከልማዳዊ የመፃፍ ትምህርት ጋር ያለውን ውጤታማነት ለመመርመር ቅድመ እና ድህረ የጽሁፍ ፈተና ተገባር ላይ ውሏል:: የቅድመ ጽሁፍ ፈተና ውጤት እንዳመለከተው በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ተመሳሳይ ችሎታ መኖሩን አሳይቷል:: ይሁን እንጂ የሙከራ ቡድኑ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረጉ በኋላ በተሰጠው ድህረ የጽሁፍ ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል:: ከዚህ በተጨማሪ የሙከራ ቡድኑ በድህረ የጽሁፍ ፈተና ከሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ተማሪዎች የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል::

የሙከራ ቡድኑን በተመለከተ በLikert scale የተሰበሰበው መረጃ የሚጠቁመው ሙከራው ከተካሄደ በኋላ ለመፃፍ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ማሳደራቸውን ነው:: ይህ አዎንታዊ አመለካከት ሊፈጠር የቻለው ተጠኚዎቹ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ ካደረጉ በኋላ ነው::

በአጠቃላይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን ከመለማመዳቸው በፊት ስለመፃፍ አሉታዊ አመለካከት እንደነበራቸው የታየ  ሲሆን በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተራኪ ድርሰትን መፃፍ ከተለማመዱ በኋላ አዎንታዊ አመለካከት ማሳየታቸው ታይቷል:: በአጠቃላይ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በሙከራ ክፍሉ ውስጥ በመተግበር እና በፅሁፍ መጠይቅ መረጃዎችን በመሰብሰብ የተጠኚዎችን አዎንታዊ አመለካከት ለማጤን ተችሏል::

# ምዕራፍ አምስት:-ዋናው ጥናት

ይህ ክፍል የንሞና ዘዴዎችን የተማሪዎች እና መምህር መረጣ እንዲሁም ጥናቱን ለማካሄድ በተመረጡ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ማለትም በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎችና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው በተገኙ ውጤቶች ዙሪያ ማብራሪያና ትንተና የቀረበበት ነው:: በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ የሚያመለክት ክፍል ነው::

## 5.1 የንሞና ዘዴዎች

### 5.1.1 ተማሪ

በምዕራብ ሸዋ ዞን ከሚገኙ 36 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀላል የንሞና ዘዴ ለዋናው ጥናት ተመርጧል:: በኢጀሬ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር ወንድ 265 ሴት 249 በድምሩ 514 ናቸው:: የምድብ ብዛታቸው 9 ሲሆን ሁሉም ምድቦች በአንድ ፈረቃ የሚማሩ ናቸው:: በመሆኑም ካሉት 9 ምድቦች ውስጥ ሁለት ምድቦች ቀላል የንሞና ዘዴ በመጠቀም፣ ተማሪዎቹ ለቁጥጥር እና ለሙከራ ጥናቱ ተመርጠዋል:: በተመሳሳይ የንሞና አወሳሰድ ዘዴ 9ኛA እና 9ኛF ክፍሎች ለጥናቱ የተመረጡ ሲሆን ከላይ በተገለፀው መንገድ 9ኛA ክፍል ለቁጥጥር ቡድኑ እና 9ኛF ክፍል ደግሞ ለሙከራ ጥናቱ ተመርጠዋል::

### 5.1.2 መምህር

በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሉ:: ከነዚህ መካከል አንድ መምህር ለዚህ ጥናት የተመረጠ ሲሆን ሁለቱንም ቡድኖች ማለትም የቁጥጥሩን ቡድን በልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ አስተምሯል::

ለዚህ ጥናት የተመረጠው መምህር የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር ይረዳው ዘንድ ስለሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በንድፈ ሀሳብና በተግባር ልምምድ የተደገፈ ስልጠና በቀን ለሁለት ሰዓታት በአጠቃላይ የስምንት ሰዓታት

ስልጠና ተሰጥቶታል:: ስልጠናው ትኩረት ያደረገው አዲሱን አቀራረብ በሚመለከት በንድፈ ሀሳብና በተግባር ልምምድ ላይ ነው:: ተመራማሪው ለመምህሩ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብን ሞዴል ካስተዋወቀ በኋላ እንዴት ተግባር ላይ እንደሚያውል የሚያስችለው ስልጠና ተሰጥቶታል:: ከዚህም በተጨማሪ መምህሩ ትምህርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ ለማመሳከሪያነት ይረዳው ዘንድ የስልጠና መመሪያ ተሰጥቶታል (ይህንን በአባሪ 1 ይመለከቷል)::

ለጥናቱ የተመረጠው መምህር የስልጠና መመሪያውን መሰረት የሙከራ አድርጎ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች በዘውግ ሂደት ተኮር አቀራረብ ያስተማረ ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑን ግን በልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ አስተምሯል::

በአጠቃላይ የተመረጠው መምህር የሙከራ ቡድኑን ሲያስተምር በተሰጠው ስልጠና መሰረት አቀራረቡን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ አድረጓል::

### 5.1.3 የጊዜ አጠቃቀም

የኤጀሬ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ ነው:: ይሁን እንጂ በጥናቱ ወቅት ለአንድ ክፍለ ጊዜ የሚሰጠው ጊዜ ከፍ ያለ መሆን አለበት:: በጥናቱ ወቅት ከፍ ያለ ጊዜ የሚያስፈልግበት ምክንያት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን ስራ ላይ ለማዋል በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስቦ ነው::

ከዚህ አንፃር የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በሳምንት ለሁለት ቀናት በየእለቱ ለአንድ ሰዓት ከጥቅምት 25/02/2008 እስከ የካቲት 04/2008 ዓ.ም ድረስ ለ12 ሳምንታት የትምህርቱ ሂደት ተካሂዷል:: ጥናቱ ቴስቶችን እና ፈተናዎችን ጨምሮ ለ32 ሰዓታት ተከናውኗል::

### 5.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ዋናውን ጥናት ለማከናወን እንዲያገለግሉ ታስበው ቅድመና ድህረ ፈተናዎች እና የጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል::

#### 5.1.4.1 ቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች

ከዚህ ቀደም እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ መሻሻል ማምጣት

አለማምጣቱን መመርመር ነው:: በዚህ ጥናት በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች የተመዘገቡ ውጤቶች በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ያለውን የውጤት ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማወቅ የረዳ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው::

የቅድመ ትምህርት ፈተና ዓላማ ሙከራው ከመካሄዱ በፊት በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ ነው:: በሌላ አባባል የቅድመ ፈተና አላማ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት መመርመር ነው:: ይህ የቅድመ ትምህርት ፈተና ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት የተከናወነ ሲሆን ሂደቱም በትምህርት ቤቱ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በተመራማሪው ጥቅምት 25/2008 ዓ.ም በተመደበለት አንድ ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ ተከናውኗል::

በሌላ በኩል ጥናቱ ከተከናወነ በኋላ በ06/06/2008 ዓ.ም የድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች ተሰጥቷል:: ይህ ፈተና የሙከራ ጥናቱ የተካሄደባቸው ተማሪዎች በዘውግ- ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መፃፍን የማስተማር አቀራረብ በመማራቸው በድርሰት የመፃፍ ክሂላቸው ላይ የታዩ መሻሻሎችን ለመፈተሽ የረዳ ነው:: የድህረ ትመህርት ፈተናው በትምህርት ቤቱ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በተመራማሪው ተሰጥቷል::

#### 5.1.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቁ የቀረበው በሙከራ ጥናቱ በአዲሱ አቀራረብ ይኸውም በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ ድርሰት የመፃፍ ትመህርትን ለተከታተሉና ልምምድ ላደረጉ ተማሪዎች ነው:: የመጠይቁ አላማም ተማሪዎቹ በዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ በመፃፍ ትምህርት አመለካከታቸው ላይ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን ያጤነ ነው::

በዚህ መሰረት የጥናቱ ትኩረት ለሆነው የመፃፍ ክሂል ተማሪዎች ለጥናቱ ከሚያስፈልገው የመረጃ አይነት አኳያ የተለያዩ ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅቷል:: የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ አላማና የመጠይቁን አሞላል የሚጠቁም መመሪያ የያዘው መግቢያው ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ

የተማሪዎችን ዳራ በተመለከተ ነው:: ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ ከጥናቱ አላማ እና መላምት ጋር ግንኙነት ያላቸው አማራጭ መልሶችን የያዙ ዝግ ጥያቄዎች /Closed questions / ናቸው::

የፅሁፍ መጠይቁ በአብዛኛው የተዘጋጀው በLikert ስኬል መሰረት ሲሆን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ቀርበውበታል:: የፅሁፍ መጠይቁ ከ Robert Sommer and Barbara Sommer (1980, 138-139 and 151) የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና ስለቶች ሀሳብ በመውሰድ የጥናቱን የዓላማ ጥያቄዎች ሊመልስ በሚችል መልኩ የቀረበ ሲሆን ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት አማካሪው እና ሁለት የቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል:: አስተያየቱን መሰረት በማድረግ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት ለተጠኚዎቹ ቀርቧል:: በመጨረሻም ለተማሪዎቹ አስፈላጊው ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ መጠይቁን ሞልተዋል::

### 5.1.5 የመረጃ ስብሰባና ትንተና

#### 5.1.5.1 የመረጃ ስብሰባ ሂደት

የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በቅድመ ፈተና ውጤታቸው መሠረት በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ በተመሳሳይ የችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ለመለየት አስችሏል፡፡ ከዚህ በኋላ ትምህርቱ ለሶስት ወራት ተካሂዷል:: ጥናቱ በመካሄድ ላይ እያለ ከጽሁፍ መጠይቅ እና እንዲሁም በመጨረሻው ከድህረ ትምህርት ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል:: የድህረ ትምህርት ፈተናው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ድርሰት በመፃፍ ረገድ የችሎታ ልዩነት መታየት አለመታየቱን ለመመርመር ረድቷል::

#### 5.1.5.2 የመረጃ ትንተና ሂደት

በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ለትንተና እና ለውይይት በሚሆን መልኩ ተጠናቅረዋል:: ከዚህ አንፃር የመረጃዎች አማካይ /x/ the degree of freedom(d/f) የአማካይ ልዩነት(t-value) እና ጉልህ ልዩነት /p-value/ ለእያንዳንዱ ቡድን ስራ ላይ ውሏል:: በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖቹ መካከል በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች ጉልህ ልዩነት መኖሩን ለመለየት በ0.05 ደረጃ

ይኸውም (Independent t-test) ስራ ላይ ውሏል:: በተመሳሳይ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአይነታዊ ዘዴዎች ተተንትነው ቀርበዋል::

### 5.1.6 የመረጃ ትንተና እና ውይይት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ውይይት ቀርቧል:: መጀመሪያ የቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች ውጤቶች የቀረቡ ሲሆን፣ በመቀጠልም ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች የተነተኑ ሲሆን በመጨረሻም ከተገኙ ውጤቶች ማጠቃለያ ቀርቧል::

**የምርምሩ አላማ 1**

#### 5.1.6.1 የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ስለማሻሻሉ

በሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩት ይልቅ ድርሰት በመጻፍ ረገድ የተሻለ ውጤት አሳይተዋል:: ይህ አላማ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ቀርቧል:: መጀመሪያ በድርሰት አጻጻፍ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች መካከል በቅድመና ድህረ ፈተናዎች የታዩ ልዩነቶች ውይይት ተደርገውባቸዋል:: ቀጥሎ በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል የታዩ ልዩነቶች ተነፃፅረዋል:: ለዚህ አላማ የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤቶች ጥቅም ላይ ውለዋል::

በፈተናዎቹ አማካይነት የተገኙት ውጤቶች በአኀዛዊ ስልት ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን በሁለቱ ቡድኖቹ መካከል የታየውን ልዩነት ለማነፃፀር የኢ.ጥገኛ ንሞና ቴስት (Independent sample t-test) ስራ ላይ ውሏል::

## ጠንጠረዥ 6- የሙከራ ቡድኖች የቅድመ እና የድህረ ፈተና ውጤቶች

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | No | X | SD | SE | No | X | SD | SE | D/F | t-value | P-value |
| ቅድመ ፈተና | 45 | 50.094 | 5.4873 | 0.81808 | 45 | 50.1558 | 6.777969 | 1.01066 | 88 | 0.047 | 0.962 |
| ድህረ ፈተና | 45 | 50.3698 | 5.4380 | 0.81065 | 45 | 58.709 | 8.0764111 | 1.20386 | 88 | 5.745 | .000 |

በሠንጠረዥ ስድሰት ላይ የኢ-ጥገኛ ንሞና ቲ- ቴስት /Independent sample t-test/ ያገለገለው በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች መካከል ያለውን የአማካይ ዋጋ ልዩነት ለማመልከት ነው::

የቅድመ ፈተናው አማካይ ውጤት ለቁጥጥር ቡድኑ 50.094 ሲሆን ለሙከራ ቡድኑ ደግሞ 50.1558 ነው:: ይህ የሚያመለክተው በቅድመ ፈተና ወቅት ሁለቱ ቡድኖች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ሲሆን ሁለቱ ቡድኖች ባስመዘገቡት የድርሰት ጽሁፍ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በ ቲ- ስሌታዊ ዋጋ /t-calculated value/ ተመሳክሯል::

በዚሁ መሰረት የሁለቱ ቡድኖች የቲ- ዋጋ በቅድመ ፈተና ወቅት 0.047 /d/f 88/ ሲሆን የP- ዋጋ ደግሞ 0.962 ነው:: ይህም ከሚታሰበው የአልፋ ዋጋ /0.05/ የበለጠ ነው:: ይህ የሚያመለክተው የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ ፈተና ወቅት በፃፉት ድርሰት ውስጥ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው:: በሌላ አባባል ሁለቱ ቡድኖች ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት የቅድመ ፈተና ውጤታቸው ተመሳሳይ መሆኑን ነው::

በሌላ በኩል በሰንጠረዥ ሰባት በድህረ ፈተና ወቅት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖቹ ተማሪዎች መካከል በድርሰት ጽሑፍ ውጤታቸው መካከል ያለው አማካይ ልዩነት የቁጥጥሩ ቡድን አማካይ ውጤት 50.3698 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 58.709 ነው::

ከዚህም ሌላ የቲ- ዋጋ 5.745 /d/f 88 / እና / የ P ዋጋ ደግሞ .000 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው:: በመሆኑም መረጃው የሚያመለክተው በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ጥናቱ ከተካሄደ በኋላ በአማካይ ውጤታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው:: ይህም ድርሰት በመፃፍ ረገድ በዘውግ- ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሩት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በልማዳዊው አቀራረብ ከተማሩት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው::

በአጠቃላይ በቅድመ ፈተና ወቅት በሠንጠረዥ ስድስት ላይ የታየው የቁጥጥሩ እና የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች አማካይ ውጤት በt- ቴስት ቀመር ተሰልቶ በተገኘው ውጤት መሰረት ጉልህ ልዩነት አልታየበትም:: በሌላ በኩል በድህረ ፈተና ወቅት የቁጥጥሩ እና የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎቹ አማካይ ውጤት በt- ቴስት ቀመር ተሰልቶ በተገኘው ውጤት መሰረት ጉልህ ልዩነት ታይቶበታል:: ከዚህ አንፃር ሙከራው ከተካሄደ በኋላ በድርሰት አፃፃፍ የሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር ከፍያለ ውጤት አስመስዝግበዋል ማለት ነው:: ይህም አዲሱ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ውጤታማ መሆኑን የሚያመላክት ነው::

## ሰንጠረዥ 7- የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ወቅት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | No | X | SD | SE | No | X | SD | SE | D/F | t-value | P-value |
| ቅድመ ፈተና | 10 | 57.8970 | 1.24765 | 0.39454 | 10 | 59.3010 | 1.78618 | 0.56486 | 18 | 2.038 | 0.057 |
| ድህረ ፈተና | 10 | 57.9320 | 1.18448 | 0.37457 | 10 | 69.7300 | 1.69159 | 0.53493 | 18 | 18.066 | 0.000 |

ሰንጠረዥ ሰባት የሚያመለክተው ድርሰት በመፃፍ ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችን ውጤቶች ያነፃፅራል:: ለዚህ መረጃ የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤዎች ጥቅም ላይ ውለዋል::

በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት በአማካይ 57.8970 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 59.3010 ነው:: በቅድመ ፈተናው ውጤት የሁለቱ ቡድኖች ውጤት ሲነፃፀር የአንዱ ከሌላው ተቀራራቢ ነው:: ይህ የተገኘው ውጤት በ t-value ሲረጋገጥ 2.038 /d/f 18 / እና የp-value ዋጋ 0.0057 ነው:: ይህም ከ0.05 የበለጠ ነው ማለት ነው::

በቅድመ ፈተና ወቅት የተገኘው ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን የሚያመላክት ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

በዚህ ሰንጠረዥ እንደተገለፀው በድህረ ፈተናው ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የቁጥጥር ቡድኑ 57.9320 አማካይ ውጤት ያገኙ ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ 69.7300 ነው:: ይህ የሚያሳየው ሁለቱ ቡድኖች በድህረ ፈተና ወቅት የተለያየ ውጤት እንዳላቸው ሲሆን የt-value 18.066 / d/f 18/ እና የp ዋጋ 0.00 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው::

ከዚህ በላይ የታየው ውጤት የሚያመለክተው በስታትስቲካዊ ስሌት መሰረት በድህረ ጽህፈት ትምህርት ፈተና ወቅት ከፍተኛ ውጤት ባስመዘገቡ የቁጥጥሩ እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለው ውጤት መመዝገቡን ነው:: በአጠቃላይ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አንፃር ሲታይ የተሻለ እንደሆነ መረዳት ተችሏል:: ይህም መፃፍን በአዲሱ የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ማስተማር በልማዳዊው ዘዴ ከማስተማር ይልቅ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን ያሳያል::

ሰንጠረዥ 8 - የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖች በቅድመና ድህረ ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ውጤት

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | No | X | SD | SE | No | X | SD | SE | D/F | t-value | P-value |
| ቅድመ ፈተና | 10 | 43.365 | 2.7899 | 0.8822 | 10 | 42.133 | 1.9064 | 0.6028 | 18 | 4.153 | 0.264 |
| ድህረ ፈተና | 10 | 43.466 | 2.8344 | 0.8963 | 10 | 48.464 | 1.1782 | 0.3726 | 18 | 5.149 | 0.000 |

በሰንጠረዥ ስምንት ላይ ንፅፅሩ የተካሄደው በመፃፍ ፈተና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት ባስመዘገቡት የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ነው::

በስታትስትካዊ ስሌት የተደረሰበት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡት የቅድመ ፈተና አማካይ ውጤት የቁጥጥር ቡድኑ 43.365 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 42.133 መሆኑ ተስተውሏል:: በዚሁ ፈተና የቲ- ዋጋ 4.153 /d/f18 / እና የp ዋጋ ደግሞ 0.264 ነው:: ይህም ከ0.05 የበለጠ ነው:: ይህ ውጤት የሚያመለክተው በቅድመ ፈተና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የቁጥጥሩና የሙከራ ቡድኑ ተማሪች ውጤት  ሲነፃፀር ጉልህ ልዩነት ያልታየበት መሆኑ ነው ::

በሌላ በኩል በድህረ ትግበራ ፈተና ወቅት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 43.466 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ 48.466 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው:: ይህ ስሌት ሙከራው ከተካሄደ በኋላ በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ዝቅተኛ ውጤት ባስመዘገቡ ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው::

የጥናቱ መርሃ ግብር ከተካሄደ በኋላ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር በጽህፈት ፈተና ወቅት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል:: ይህ የሚያሳየው የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አተገባበር ድርሰት በመፃፍ ሂደት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ውጤት የተመዘገበበት መሆኑን ነው::

በአጠቃላይ ድርሰት በመፃፍ ረገድ በቅድመ ትግበራው ፈተና ውጤት መሠረት ተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በተለያየ የማስተማር ዘዴ ተመሳሳይ ይዘትን ለተወሰነ ጊዜ ከተማሩ በኋላ በተሰጣቸው የድህረ ጽህፈት ትምህርት ፈተና ውጤት ተለያይተዋል:: በዚሁ መሠረት ድርሰት በመፃፍ ረገድ ትምህርቱን ሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን የተከታተሉ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በልማዳዊው መንገድ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ይልቅ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸው ተረጋግጧል:: ይህም ግኝት ‹‹የድርሰት ክሂልን በሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ማስተማር የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ያሳያል::

ከዚህም ሌላ በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ያለውን ውጤት ለመመልከት /paired t-test /ፔይርድ ቲ ቴስት/ ስራ ላይ ውሏል:: ቀጥሎ በሚቀርበው ሰንጠረዥ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ እና ድህረ ፈተና ባስመዘገቡት ውጤት እና እንዲሁም የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች በሁለቱም ፈተናዎች ያስመዘገቡት ውጤት ተነፃፅሯል:: በዚህ መሰረት በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ተነፃፅረዋል::

ሰንጠረዥ 9- በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድን ተማሪዎች መካከል የ paired t-test ውጤት

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | | | | የሙከራ ቡድን | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | No | X | SD | SE | No | X | SD | SE | D/F | t-value | P-value |
| የሙከራ | 45 | 50.1704 | 6.7944 | 1.0129 | 45 | 58.7087 | 8.0764 | 1.204 | 44 | 17.278 | 0.000 |
| የቁጥጥር | 45 | 50.0056 | 5.3596 | 0.79897 | 45 | 50.3698 | 5.438 | 0.8106 | 44 | 1.253 | 0.135 |

ሰንጠረዥ ዘጠኝ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች መካከል በቅድመ እና ድህረ ፈተናዎች የተመዘገቡ ውጤቶችን በንፅፅር የሚያሳይ ነው::

በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል ያለው የ paired t-test ትንተና አማካይ የቅድመና ድህረ ፈተና ውጤት 50.1704 እና 58.7087 ነው:: በተመሳሳይ በዚሁ ቡድን የt ዋጋ 17.278 d/f 44 እና የ pዋጋ 0.000 ነው:: ይህም ከ0.05 ያነሰ ነው:: ይህ ስታትስቲካዊ ስሌት የሚያመለክተው በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል በቅድመና ድህረ የድርሰት ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው::: በሌላ በኩል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ አኳያ ለዘውግ- ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተጋለጡ በኋላ በድርሰት ፈተና ረገድ የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል::

በዚሁ ሰንጠረዥ በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በቅድመ ፈተና ወቅት 50.0056 ሲሆን በድህረ ፈተና ደግሞ 50.3698 ነው:: ይህ የሚያሳየው በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በቅድመ እና ድህረ ፈተና ወቅት ያስመዘገቡት ውጤት ተመሳሳይ መሆኑን ነው:: የt ዋጋ 1.523 /d/f 44/ እና የpዋጋ 0.135 ነው:: ይህም ከ0.05 የሚበልጥ በመሆኑ ሰንጠረዡን የሚያጠናክር ነው:: የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመና በድህረ ፈተናዎቻቸው መካከል በስታትስቲካዊ ስሌት መሰረት ጉልህ ልዩነት አልታባቸውም:: ከዚህ አንፃር ልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ አመቺ አለመሆኑን ነው::

በአጠቃላይ በቅድመ እና ድህረ ፈተና ወቅት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ የቁጥጥሩ እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ሲነፃፀር በቅድመ ፈተና ወቅት ጉልህ ልዩነት ያልታየበት ሲሆን በድህረ ፈተና ወቅት በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ላይ ለውጥ ታይቷል:: በቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ላይ ግን ጉልህ ልዩነት አልተመዘገበም:: ይህም አዲሱ አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችል ጉልህ ፋይዳ ያለው መሆኑን ያሳያል::

**የምርምሩ አላማ 2**

### 5.1.6.2 የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች በተማሪዎች የመፃፍ አመለካከት ላይ ለውጥ አምጥቷል?

በዋናነት ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃ የተሰበሰበው ለምርምሩ አላማ ሁለት "የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች በተማሪዎች የመፃፍ አመለካከት ላይ ለውጥ አምጥቷል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ነው:: መረጃው የተሰበሰበው በ Likert scale ስልት ከቀረቡ ሃያ የአመለካከት ጥያቄዎች ሲሆን ተጠኚዎቹ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሾችን እንዲሰጡ ወደ ገለልተኛነት የሚያመራው መገምገሚያ ተቀንሶ ወደአራት ዝቅ ተደርጓል:: የመጀመሪያዎቹ አስር ጥያቄዎች ተጠኚዎች በዘውግ-ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ድርሰት መፃፍን ከመለማመዳቸው በፊት ለድርሰት የነበራቸውን አመለካከት የሚዳስሱ ሲሆን የተቀሩት አስር ጥያቄዎች ደግሞ ከልምምዱ በኋላ የታየውን ለውጥ የሚመለከቱ ናቸው::

ሠንጠረዥ:- 10 ድርሰት የመፃፍ ልምምደን በተመለከተ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 1 | ከዚህ ቀደም በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ድርሰት በመፃፍ እለማመድ ነበር:: | 12 | 0 | 12 | 27% | 24 | 9 | 33 | 73% |
| 2 | ድርሰት ለመፃፍ የተፈጥሮ ስጦታ ያስፈልጋል ብዬ ስለማስብ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አልነበረኝም:: | 8 | 14 | 12 | 31 | 19 | 12 | 33 | 73% |

"ስር በተራ ቁጥር "1" በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ የመፃፍ ልምምድ ያደረጉ እንደነበር" ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ (73%) ማለትም 33 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 12 ተማሪዎች ይኸውም (27%0 አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህንን ሀሳብ በሚያጠናክር ሁኔታ ልምምድ

ድርሰት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ጠቃሚ መሆኑን Hedge, (1992) ገልፀውታል:: ከዚህ አንፃር ከተጠኚዎች ከተገኘው ምላሽ መረዳት የተቻለው በከዚህ ቀደም የፅህፈት ትምህርታቸው ወቅት በቂ የድርሰት ልምምድ ያላላደረጉ መሆኑን ነው::

በተመሳሳይ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ (67%) ማለትም 31 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን የተቀሩት (34%) ማለትም 14 ተማሪዎች ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የተፈጥሮ ችሎታ ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ ያነሱ ሲሆን ለፅህፈት ልምምድ የነበራቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: Ede (1992) ጥሩ ድርሰት እንዴት እንደሚፃፍ ዘዴውን ካለመማር የተነሳ ድርሰት ለመፃፍ ልዩ ተሰጥኦ ሊኖር ይገባል የሚል አመለካከት ተማሪዎች እነደሚያሳድሩ ያቀረቡትን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው::

**ሠንጠረዥ:-11 ድርሰትን በራስ መፃፍና ዕውቀትን በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ድርሰት ስፅፍ በነፃነት በራሰ መፃፍን አለማምደውኛል:: | 4 | 8 | 12 | 27% | 21 | 12 | 33 | 74% |
| 4 | ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቴ ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችል በቂ ዕውቀት አግኝቼአለሁ:: | - | 8 | 8 | 18% | 14 | 23 | 37 | 82% |

በሠንጠረዥ" 11 " በተራቁጥር " 3 "ስር "የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ድርሰት ሲፅፉ በነፃነትና በራስ መፃፍን አለማምደዋቸው እንደነበር" ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ (74%) ማለትም 33 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 12 ተማሪዎች ማለትም (27%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራቁጥር "4" ለቀረበው ጥያቄ (82%) ይኸውም 37

ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 12 ተማሪዎች ማለትም (27 %) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ::

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ድርሰት ይፅፉ በነበረበት ጊዜ በራሳቸው ተማምነው በነፃነት የመፃፍ ሂደትን ያላዳበሩ ከመሆናቸውም በላይ ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችል በቂ ችሎታ እንዳልነበራቸው ነው::

ሠንጠረዥ:-12 በድርሰት ውስጥ የሰዋሰው ስህተትና የማንበብ ስሜት

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 5 | ድርሰት ስፅፍ ፅሁፌ የሰዋስው ስህተት ስለሚበዛበት ድርሰት ፃፍ ባልባል ደስ ይለኛል:: | 2 | 8 | 10 | 22% | 22 | 13 | 35 | 82% |
| 6 | ከዚህ ቀደም በክፍል ጓደኞቼ ፊት የፃፍኩትን ድርሰት ሳነብ ጥሩ ስሜት አይሰማኝም:: | - | 8 | 8 | 18% | 23 | 14 | 37 | 82% |

በሠንጠረዥ 12 ተራ ቁጥር "5 " ላይ "ድርሰት ስፅፍ የሰዋስው ስህተት ስለሚበዛበት ድርሰት ፃፍ ባልባል ደስ ይለኛል" ለሚለው ጥያቄ (66%) ይኸውም 29 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 16 ተማሪዎች ማለትም (45%) ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 27 ተማሪዎች (67%) አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ (33%) ይኸውም 15 ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:

ሠንጠረዥ:-13 በቡድን ስራ መሳተፍና ፅሁፎችን ማንበብ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 7 | በቡድን ስራ ወቅት በመፃፍ ስራ ላይ የሚያሳትፉኝን ተግባራት መቀበል ያስደስተኛል:: | 8 | 17 | 15 | 34% | 16 | 14 | 30 | 67% |
| 8 | በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍትን መጽሔቶችን እና ጋዜጦችን በተደጋጋሚ ማንበብ እወዳለሁ:: | 6 | 10 | 16 | 35% | 10 | 19 | 29 | 66% |

በሰንጠረዥ 13 ተራቁጥር 1 ላይ የቀረበው ጥያቄ ትኩረት ያደረገው በመፃፍ ወቅት በቡድን ስራ ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሆነ ለመረዳት ነው:: ከዚህ አንፃር በተሰበሰበው መረጃ (24%) ማለትም 11 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 31 ተማሪዎች ደግሞ (76%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ንባብና መፃፍ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን Brown (1994)፣Hedge (1990) ገልፀዋል:: ከዚህ አንፃር በተራቁጥር 8 ላይ ለቀረበው ጥያቄ "በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍትን፣ መጽሔቶችን እና ጋዜጦችን በተደጋጋሚ ማንበብ እወዳለሁ" ለሚለው ጥያቄ 35 ተማሪዎች 78% አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 10 ተማሪዎች ይኸውም 22% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ከዚህ አንፃር ከተጠኚዎቹ የተገኘው ምላሽ የሚጠቁመው ተማሪዎቹ ለድርሰት ልምምድ የነበራቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ነው::

ከተሰጠው ምላሽ መረዳት የተቻለው በቡድን ስራና ንባብ ላይ የነበራቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ነው:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች አንቀፅ ወይም ድርሰት ለመፃፍ ሲነሱ በቡድን ሆነው ሀሳብ ቢቀያየሩ የተሻለ ይሆናል:: በሌላ አባባል ተማሪዎች የተሰጣቸውን ፅሁፍ አስቀድመው ከመፃፋቸው በፊት በተለያዩ ተግባራት ቢሳተፉ ይህ ሁኔታ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ለመወያየትና ሀሳባቸውን ለሌሎች ለማካፈል ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ በኋላ ላይ የአንቀፅ ወይም የድርሰት ፅሁፍን በየግላቸው እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል:: ሌላኛው በቡድን የመሳተፍ ጥቅሙ በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ የሚፈጥር መሆኑ ነው:: ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቡድን ውይይት ወቅት እንዲያነቡ፣ መረጃዎችን እንዲያሰባስቡና ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ያበረታታቸዋል:: ይህን በማድረግ የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ ይቻላል::

ሠንጠረዥ:-14 ድርሰት በመፃፍ ወቅት የመምህራን አስተያየት

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 9 | መምህራን ድርሰቴን አርመው ይሰጡኝ የነበረው አስተያየት በየጊዜው ሙከራዎችን እንዳደርግ የሚገፋፋኝ ነበር:: | 5 | 10 | 15 | 33% | 13 | 17 | 30 | 67% |
| 10 | ከዚህ በፊት ድርሰት እጽፍ የነበረው የጽሑፍ ችሎታዬን የማሻሻል ፍላጎት ኖሮኝ ሳይሆን በመምህሬ ስለምታዘዝ እና ለማገኘው ውጤት ስል ነበር:: | 6 | 7 | 13 | 29% | 18 | 14 | 32 | 71% |

በሰንጠረዥ 14 ተራ ቁጥር 9 ላይ የቀረበው ጥያቄ ትኩረት ያደረገው መምህራን ድርሰትን አርመው የሚሰጡት አስተያየት ድርሰት እንዲፅፉ የሚገፋፋቸው እንደሆነ ለመረዳት ነው:: ከዚህ አንፃር በተሰበሰበው መረጃ (33%) ማለትም 15 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 30 ተማሪዎች (71%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል::በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራቁጥር 10 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 32 ተማሪዎች (71%) አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 29 ተማሪዎች (29%) ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል::

ከቀረበው ሠንጠረዥ መገንዘብ የሚቻለው ድርሰትን በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎችና በመምራን መካከል የነበረውግንጡነት ተማሪዎች ድርሰት እንዲፅፉ የሚያበረታታ አልነበረም::በተጨማሪም ተማሪዎች ድርሰት ይፅፉ የነበረው በመምህራቸው የሚሰጣቸውን ተግባር ለማከናወንና የሚያገኙትን ውጤት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ነው::

ሠንጠረዥ:-15 ስለ መፃፍ ጠቃሚነት

| ተ/ ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 11 | መፃፍ ለወደፊቱ ህይወቴ ጠቃሚ ነው:: | 5 | 34 | 39 | 87% | 4 | 2 | 6 | 13% |
| 12 | ስሜትን ለመግለፅ ፅህፈት ጠቃሚ መንገድ ነው:: | 6 | 30 | 36 | 80% | 5 | 4 | 9 | 20% |

በሠንጠረዥ 15 ተራ ቁጥር አስራ አንድ ላይ “መፃፍ ለወደፊቱ ህይወቴ ጠቃሚ ነው” ለሚለው መጠይቅ 8 ተማሪዎች ማለትም (18%) አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን በሌላ በኩል 37 ተማሪዎች ማለትም (82%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ከዚህ ሠንጠረዥ መገንዘብ የሚቻለው አብዛኛው ተማሪ ከሙከራ ትምህርቱ በኋላ ስለመፃፍ ጠቃሚነት አዎንታዊ አስተያየት እንዳላቸው ነው::

በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 12 ላይ “ስሜትን ለመግፅ መፃፍ ጠቃሚ መንገድ ነው” ለሚለው ጥያቄ 37 ተማሪዎች ማለትም (82 %) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ነገርግን ስምንት ተማሪዎች ማለትም (17%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:

በቀረበው ሠንጠረዥ መገንዘብ የሚቻለው መፃፍ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው ነው::ሰዎች መፃፍ በሚገባ ሲረዱ ሀሳባቸውን በነፃነት የሚገልፁበት ሁኔታ የሚፈጠርላቸው በመሆኑ መፃፍ እነደ አንድ ጠቃሚ የቋንቋ ክሂል አድርጎ መውሰድ ይቻላል:

ሠንጠረዥ 16:- የመፃፍ ተግባራዊ ልምምድ

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 13 | የተለያዩ የመፃፍ ተግባራትን /እንቀፅ ደብዳቤ ድርሰት መፃፍ/ ማከናወን ያስደስተኛል:: | 6 | 27 | 33 | 73% | 6 | 6 | 12 | 26% |
| 14 | በትምህርት ቤት ብዙ የመፃፍ ልምምድ ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: | 12 | 20 | 32 | 71% | 8 | 5 | 13 | 29% |

በሠንጠረዥ 16 ተራቁጥር አስራአንድ ላይ የተለያዩ የመፃፍ ተግባራትን /እንቀፅ፣ደብዳቤ፣ ድርሰት መፃፍ /ማከናወን ያስደስተኛል በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ 27 ተማሪዎች ይኸውም (82% )አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን በአንፃሩ 8 ተማሪዎች ደግሞ (18%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 14 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 41 ተማሪዎች (91%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 4 ተማሪዎች ደግሞ (9%) ደግሞ አሉታዊ ምለሽ ሰጥተዋል:

በሠንጠረዥ ሃያ በተራ ቁጥር 15 ላይ "የፃፍኩትን ድርሰት ጓደኞቼ አንብበው የሚሰጡኝ አስተያየት የተሻለ እንድፅፍ አነሳስቶኛል" ለሚለው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (73%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 13 ተማሪዎች (26%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በአቻ አስተያየት በኩል ጠንካራ ወይም ደካማ ጎንን ለይተው የማሳየት ችግር መኖሩ ክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ ተስተውሏል:: ይሁን እንጂ Harmer, (1996, 244) ባቀረቡት አስተያየት በቢጤ አስተያየት አሰጣጥ ረገድ የትክክለኛነት ጉዳይ የመምህራን ስጋት መሆኑን ጠቅሰው ትክክለኛነት ብቸኛ የመማር ሂደትን መገምገሚያ እንዳልሆነና ይልቁንም ተማሪዎች ሂደቱን ተቀብለው ተሳትፎ ካደረጉ ትክክለኛነት በሂደት ሊሻሻል ይችላል የሚለውን ሀሳባቸውን የሚያጠናክር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 16 ላይ የቀረበው ጥያቄ የመምህሩን ድጋፍ አስፈላጊነት ለማረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ሲሆን 32 ተማሪዎች ማለትም (71%)

አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 13 ተማሪዎች ማለትም (29%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህ Hillocks, (1986,165 ) በድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የመምህሩ ምላሽ አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም Mangelsdorf, (1992) ተማሪዎች የመምህራቸውን ድጋፍ እንደሚሹ የገለፁት ሀሳብ ትክክል መሆኑን ያሳያል::

ሠንጠረዥ:-17 የጓደኛ አስተያየትና የመምህሩ ድጋፍ

| ተ/ ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 15 | የፃፍኩትን ድርሰት ጓደኞቼ አንብበው የሚሰጡኝ አስተያየት የተሻለ እንድፅፍ አድርጎኛል:: | 13 | 20 | 33 | 73% | 7 | 5 | 12 | 27% |
| 16 | በዘውግ ሂደት ተኮር አቀራረብ ተራኪ ድርሰት ስጽፍ መምህሬ የሚያደርጉልኝን ድጋፍ ወድጄዋለሁ:: | 23 | 14 | 37 | 73% | 5 | 3 | 8 | 27% |

በሠንጠረዥ 17 በተራ ቁጥር 15 ላይ “የፃፍኩትን ድርሰት ጓደኞቼ አንብበው የሚሰጡኝ አስተያየት የተሻለ እንድፅፍ አነሳስቶኛል” ለሚለው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (73%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 13 ተማሪዎች (26%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በአቻ አስተያየት በኩል ጠንካራ ወይም ደካማ ጎንን ለይተው የማሳየት ችግር መኖሩ ክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ ተስተውሏል:: ይሁን እንጂ Harmer, (1996, 244) ባቀረቡት አስተያየት በቢጤ አስተያየት አሰጣጥ ረገድ የትክክለኛነት ጉዳይ የመምህራን ስጋት መሆኑን ጠቅሰው ትክክለኛነት ብቸኛ የመማር ሂደትን መገምገሚያ እንዳልሆነና ይልቁንም ተማሪዎች ሂደቱን ተቀብለው ተሳትፎ ካደረጉ ትክክለኛነት በሂደት ሊሻሻል ይችላል የሚለውን ሀሳባቸውን የሚያጠናክር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 16 ላይ የቀረበው ጥያቄ የመምህሩን ድጋፍ አስፈላጊነት ለማረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ሲሆን 32 ተማሪዎች ማለትም (71%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 13 ተማሪዎች ማለትም (29%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: ይህ Hillocks, (1986,165) በድጋፍ አሰጣጥ ረገድ የመምህሩ ምላሽ አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም Mangelsdorf, (1992) ተማሪዎች የመምህራቸውን ድጋፍ እንደሚሹ የገለፁት ሀሳብ ትክክል መሆኑን ያሳያል::

ሠንጠረዥ:-18 በድርሰት ውስጥ ስህተት መፈፀምና ሀሳብ ማደራጀት

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 17 | የፃፍኩትን ድርሰት ደጋግሜ ሳነብ ስህተቶችን አገኝበታለሁ:: | 10 | 27 | 37 | 82% | 3 | 5 | 8 | 18% |
| 18 | በፅሁፍ ሀሳብን ማቀናበር ሀሳቤን እንዳደራጅ ጠቅሞኛል:: | 10 | 27 | 37 | 82% | 6 | 2 | 8 | 18 |

በሠንጠረዥ 18 ተራ ቁጥር 17 ላይ "የፃፍኩትን ድርሰት ደጋግሜ ሳነብ ስህተቶች አገኝበታለሁ" ለሚለው ጥያቄ (73%) ማለትም 33 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ (27%)ማለትም 12 ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: በተመሳሳይ በዚሁ ሠንጠረዥ በተራቁጥር 18 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 35 ተማሪዎች ማለትም (78%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 10 ተማሪዎች ማለትም (22%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል::

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ፅሁፋቸውን ደጋግመው ባነበቡ ቁጥር ስህቶቻቸውን የማየት አጋጣሚ ይሰፋላቸዋል:: ይህ ሁኔታ የተፈጠሩ ስህተቶችን አርመው የተስተካከለ ድርሰት የመፃፍ ሂደቶችን ይፈጥራል:: በሌላ በኩል በሂደዘውጋዊ አቀራረብ መማራቸው ሀሳባቸውን በተሸለ ሁኔታ እንዲያደራጁና እነዲያቀነቀብሩ አግዟቸዋል::

ሠንጠረዥ:-19 ድርሰት የመፃፍ ልምምዶችና ሞዴል ድርሰቶች

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | በአዎንታዊ መልስ የሰጡ | | | | በአሉታዊ መልስ የሰጡ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ድምር | በመቶኛ | | | ድምር | በመተኛ |
| 19 | በዘውግ-ሂደት ተኮር አቀራረበ ድርሰት የመፃፍ ልምምድ በማድረጌ የመፃፍ ፍላጎቴ ተነሳስቷል:: | 12 | 24 | 36 | 82% | 6 | 3 | 9 | 18% |
| 20 | በክፍል ውስጥ የተነበቡልኝ ሞዴል ድርሰቶች ድርሰት ለመፃፍ ጠቅመውኛል:: | 10 | 31 | 41 | 91% | - | 4 | 4 | 9% |

በሠንጠረዥ 19 በተራ ቁጥር 19 ላይ "በዘውግ-ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ በማድረጋቸው የመፃፍ ፍላጎታቸው ተነሳስቶ እንደሆነ" ለቀረበላቸው ጥያቄ (87%) ማለትም 39 ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን የቀሩት 9 ተማሪዎች ማለትም (20%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል:: የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሙከራው ከተከናወነ በኋላ በዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር አቀራረብ አስፈላጊነት ላይ አዎንታዊ አመለካካት እንዳሳደሩ መረዳት ይቻላል:: ተማሪዎች በመፃፍ ሂደታቸው በቂ ልምምድ ካደረጉ፣ ለድርሰት ፅሁፍ አዎንታዊ አመለካከት እንደሚኖራቸው Cohn እና Cavalcanti, (1993) የገለፁትን የሚያጠናክር ነው::

በተመሳሳይ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 20 ላይ "በክፍል ውስጥ የተነበቡላቸው ሞዴል ድርሰቶች ድርሰት ለመፃፍ  ጠቅሟቸው እንደሆነ" ለቀረበላቸው ጥያቄ (80%) ይኸውም 36 ተማረዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 9 ተማሪዎች (20%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል :: ከዚህ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው የተለያዩ ሞዴል ፅሁፎችን በማምጣት ተማሪዎቹ እንዲለማመዱት በማድረግና በልምምዱ ወቅትም በተማሪዎችና በመምህሩ እንዲሁም በተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና መረጃ ምገባ የመሰጣጣት ባህልን በማዳበር ድርሰት በመፃፍ ረገድ በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ አመለካት ማሳደር ይቻላል ::ለመፃፍ ክንውን የሚሆኑ ሞዴል ድርሰቶችን በክፍል ውስጥ ማቅረብ ተማሪዎች ጥሩ መፃፍ ምን አይነት እንደሆነ እንዲያጤኑ የሚያግዝ መሆኑን Kroll, (1990) and Hillocks, (1986) የገለፁትን የሚያረጋግጥ ነው::

# ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት

ይህ ክፍል የጥናቱ ማጠቃለያ የሚቀርብበት ነው፡፡ በመሆኑም በቀደመው ክፍል በዝርዝር የቀረበው የጥናቱ ግኝት ተጨምቆ ማጠቃለያ በሚለው ስር የቀረበ ሲሆን፣ በቀጣዩ ክፍል አዲሱ አቀራረብ ለመፃፍ ክሂልም ሆነ ለቋንቋው ትምህርት በአጠቃላይ የሚሰጠው ጥቅም ሥነትምህርታዊ ፋይዳ በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ስር ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም ለዘዴው ተግባራዊነት መሟላት እንደሚገባቸው የታመነባቸው ነጥቦች በአስተያየት መልክ ተዘርዝረዋል፡፡

## 6.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

ሂደተዘውጋዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ የማሳደግ ሁኔታ የሚፈጥር የበለጠ ተማሪ ተኮር አቀራረብ ነው:: ይህ ዘዴ ተማሪዎች በዓላማና ቅርፅ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲገነዘቡና በተለየ ሁኔታ ዘውግን ለቅድመ መፃፍ፣ንድፍ፣ ክለሳና አርትኦትን ለመፃፍ ተግባር እንዲጠቀሙ የሚፈቅድ ነው::

ጥናቱ ሲካሄድ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች ለማነቃቃት የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ስልቶችና አካሄዶች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ በሌላ በኩል የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎችን በልማዳዊው የማስተማር ስልት በማስተማር ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ለዚህ ጥናት ግብዓት የሆኑ መረጃዎች በቅድመ፣ በሂደትና መጨረሻ ላይ ተሰብስበዋል፡፡ ከተጠኚዎቹ የተሰበሰቡት መረጃዎች በ independ እና Paired Sample t-test አማካይነት በኃዛዊ እና መጠናዊ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በዚህ ክፍል ዋና ዋና አካሄዶች እና ግኝቶች ቀርበዋል፡፡

### 6.1.1 የጥናቱ አካሄድ

የዚህ ጥናት ዓላማ የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ይልቅ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የተሻለ አስተዋፅዖ ይኖረው ወይም አይኖረው እንደሆነ ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተመራማሪው ሁለት የምርምር ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ የጥናቱን አካሄድ በሚከተለው ንድፍ መሠረት አከናውኗል፡፡

1. የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በመጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መፈተሽ፤

2. የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በመጠቀም በተማሪዎች የመፃፍ ትምህርት አመለካከት ላይ ሊያመጡ የሚችለውን ለውጥ መመርመር፤

በጥናቱ ዙሪያ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራማሪው በሁለት ደረጃዎች የተከፈሉ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ የሙከራ ጥናት ሲሆን ሁለተኛው ዋናው ጥናት ነው፡፡ የሙከራ ጥናቱ ዓላማ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት እና አስተማማኝነት መፈተሽ እና መሳሪያዎቹ ተፈላጊውን መረጃ እንዴት እንዳስገኙ በማጤን ለዋናው ጥናት በሥራ ላይ ለማዋል የሚቻልበትን የተሻለ ስልት መቀየስ ነው፡፡

ጥናቱን ለማከናወን በቀላል የንሞና ዘዴ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም ኢጃጁና ኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመረጡ ሲሆን፣ የኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሙከራ ጥናቱ እንዲሁም የኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዋናው ጥናት ተመርጠዋል፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ ክፍል ሁለት ሁለት ክፍሎች ማለትም አንደኛው ክፍል ለቁጥጥር እና ሁለተኛው ደግሞ ለሙከራ ቡድኑ የተወሰዱ ሲሆን ለሙከራ ጥናቱ ለእያንዳንዱ ቡድን ሃያ አምስት ተማሪዎች ለዋናው ጥናት ደግሞ ለእያንዳንዱ ቡድን አርባ አምስት ተማሪዎች ተወስደዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በልማዳዊው የመፃፍ ማስተማሪያ ስልት እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የአንድ ሰዓት ርዝማኔ ያለው ሆኖ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ኖሮት የሙከራው ጥናት ለስድስት ሳምንት እንዲሁም የዋናው ጥናት ለአሥራ ሁለት ሳምንት ተከናውኗል፡፡

መምህሩ በሂደተዘውጋዊ ዘዴ ሲያስተምር ችግር እንዳይገጥመው የአተገባበር መርሆዎችን ተገንዝቦ ለመተግበር የሚያስችለው የስልጠና እቅድና ለዚሁ የሚረዳ የስልጠና መምሪያ (Manual training) በተመራማሪው ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መሰረትም በሙከራ እና በዋናው ጥናት ትምህርቱን እንዲያስተምሩ የተመረጡት መምህራን የጥናቱን ተተኳሪዎች ለማስተማር ይረዳቸው ዘንድ ስለሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ተሰጥቶቸዋል፡፡

### 6.1.2 የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

በጥናቱ ዙሪያ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራማሪው ሁለት የምርምር ዓላማዎችን ነድፏል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ከ9ኛ ክፍል ሁለት ምድቦች (Sections) ተመርጠው አንደኛው የሙከራ እና ሁለተኛው የቁጥጥር ቡድን እንዲሆኑ ተደርገው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ሂደት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን ከተጠኚዎቹ የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ አስችለዋል፡፡ ከነዚህ መካከል የመጀመሪያውና ዋነኛው የቅድመ ትግበራ እና የድኅረ ትግበራ ፈተና ውጤት ንፅፅር ነው፡፡ በመሆኑም የሁለቱ ምድብ ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ ትግበራ ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሙከራ ቡድኑ በሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ አቀራረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ በልማዳዊው የፅህፍት ትምህርት አቀራረብ የአሥራ ሁለት ሳምንታት የመፃፍ ክሂል ትምህርት እንዲከታተሉ ተደርገው በመጨረሻ የድኅረ ትግበራ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

ቀሪው ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን በዚሁ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠናዊና በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል፡፡ በዚህ መሰረት የቅድመ እና ድህረ ትግበራ ፈተና ውጤቶች በመጠናዊ ስልት ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን ለንፅፅሩ Independent እና Paired Sample t-test ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በዓይነታዊ ስልት ተተንትነዋል፡፡ አጠቃላይ የጥናቱ ግኝትም በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡

**የምርምሩ አላማ 1**

የመጀመሪያው የምርምሩ አላማ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ልምምድ ካደረጉ በኋላ ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው ይሻሻል ይሆን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ነው፡፡

ይህን የምርምር አላማ መሠረት በማድረግ የተገኘው መረጃ በሶስት መንገድ ተቃኝቷል፡፡ በመጀመሪያ ልምምድ ከመደረጉ በፊትና ከልምምዱ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የመፃፍ ችሎታ ልዩነት ጉልህነት ያለው መሆን አለመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው በሁለቱ ቡድኖች ዝቅተኛ ውጤት ባስመዘገቡ ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ማየትና የመጨረሻው በነዚሁ ሁለት ቡድኖች ከፍተኛ ውጤት

ባላቸው ተማሪዎች መካከል የተከሰተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተደረገ የቅድመ እና ድህረ ትግበራ ፈተናዎች ውጤት ንፅፅር ነው፡፡

1. የቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤቶች እንደሚያመለክቱት የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ ከልማዳዊ የማስተማር ስልት አንፃር የተሻለ ውጤታማ ነው፡፡ በመሆኑም የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችግር ለማቃለል አማራጭ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሆኖ ሊታሰብ ይችላል፡፡

2. በሁለቱ ምድቦች ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን በንፅፅር ስንመለከትም ድርሰት በመጻፍ ረገድ ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች አንጻር ሲታዩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የተሻሉ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል አንፃር ከልማዳዊው የመፃፍ ማስተማር ዘዴ ይልቅ ውጤታማ መሆኑን እናጤናለን፡

3. በተመሳሳይ ሁኔታ በሁለቱ ቡድኖች ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችም እንደሚያሳየው በሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በልማዳዊው ስልት ከተከታተሉት ይልቅ የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህም አዲሱ አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን ከማረጋገጡም በላይ በሙከራ ቡድኑ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ተማሪዎች የድርሰት ትምህርትን በሂደተ ዘውጋዊ  የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ መማርን የወደዱት መሆኑን ያሳያል፡፡

4. በጥምር t-test የተካሄደው የውጤት ትንተና የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ይልቅ በድህረ ፈተናው የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች በድህረ ፈተናው ወጤት ንፅፅር ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል፡፡ ይህም የሂደተ ዘውጋዊ  የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የምርምሩ ዓላማ 2**

ሁለተኛው የምርምሩ ዓላማ በሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ከልምምዱ በኋላ ለመፃፍ ክሂል ያላቸውን አመለካከት መመርመር ነው፡፡

በዚህ የምርምር ዓላማ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ ረገድ ያላቸው አመለካከት ተመዝኗል፡፡ ለዚህ የምርምር ዓላማ እንዲረዳ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊትና ጥናቱ ከተካሄደ በኋላ ስላላቸው አመለካከት ለመረዳት ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ ለመረጃ ትንተና ይረዳ ዘንድ የመቶኛ ስሌት ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ የምርምር ዓላማ ዙሪያ የሚከተለው ግኝት ተስተውለዋል፡፡

1. የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በመተግበሩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ ረገድ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓል:: ከዚህምሌላ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ለመማር እንዲነሳሱና በራስ የመተማመን ፍላጎታቸው ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ እንዲሁም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በግልፅ እንዲወያዩ፣እንዲጠያየቁና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አግዟቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ይህ አቀራረብ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰት ስለመፃፍ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡

2. ተማሪዎች እርስ በርስና ከመምህር ጋር የፈጠሩት ግንኙነት በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎችም በዚህ አቀራረብ ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ ይህ አቀራረብ የመጀመሪያቸው መሆኑንና በዚህ አቀራረብ መማር ከጀመሩ ወዲህ ድርሰት የመፃፍ ፍላጎታቸው እንደተነሳሳ በጽሑፍ መጠይቅ ምላሻቸው አስረድተዋል፡፡

3. በልምምድ ወቅት የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ጠቃሚ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎች የተሟላ የመማር ልምድ ለመፍጠር፣ በመፃፍ ትምህርት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት ውጤቶች እንዳመለከቱት የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከመፃፍ ትምህርት አንፃር ሁሉን ችግር የሚፈታ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች መፃፍን በመማር ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ሆኖ ታይቷል፡፡ ከዚህም ሌላ ተማሪዎች

እርስ በርስ ሀሳብን እንዲለዋወጡ፣ እውቀታቸውን እንዲያካፍሉ፣ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ፍላጎት ላላቸው መምህራን የተለያዩ አጋጣሚዎችን የሚፈጥር መሆኑ ታይቷል፡፡

### 6.1.3 መደምደሚያ

ይህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበው የመፃፍ ትምህርት በተማሪዎቹ የመፃፍ ክሂል መሻሻል ላይ አዎንታዊ ተጽህኖ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል::

ከዚህ አንጻር ይህ ምርምር የሚከተለውን ማጠቃለያ አቅርቧል፡፡

1. ይህ ጥናት የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ አንጻር የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ከማሳደግ አኳያ የተሻለ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

2. የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ድረሰት በመጻፍ ረገድ የተለያዩ ሞዴል ፅሑፎችን በማምጣት ተማሪዎች እንዲለማመዱ በማድረግና በልምምዱ ወቅት በተማሪዎችና በተማሪዎች እንዲሁም በተማሪዎችና በመምህሩ መካከል የመረዳዳትና መረጃ የመለዋወጥ ሂደትን በማጠናከር በተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ አመለካከት ላይ አዎንታዊ ለውጥ መፍጠሩን ለማጤን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይም ድርሰት በመፃፍ ረገድ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የነበራቸው አሉታዊ አመለካከት ጥናቱ ከተከናወነ በኋላ ወደ አዎንታዊነት የተቀየረ መሆኑ ታይቷል፡፡

3. ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ለማን? እና ለምን? እንደሚጽፉ በማሰብ፣ በማቀድ፣ በማርቀቅ፣ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እና በመወያየት ተደጋጋሚ ልምምድ ስለሚያደርጉ የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ መተግበሩ ተስተውሏል፡፡

4. የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በክፍል ውስጥ በመተግበር ረገድ የጊዜ እጥረት፣ የተማሪዎች የመፃፍ ዳራ፣ የባህል ተጽህኖ፣ የመማሪያ ክፍሎች ስፋነትና የውይይትና የመተጋገዝ እጥረት ትምህርቱን በመተግበር ረገድ እንደችግር የታዩ ነጥቦች ናቸው፡፡

5. የዘውግ ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲያግዝ የቀረበው የማስተማሪያ ጽሑፍ አዲሱን የማስተማሪያ ዘዴ ለመተግበር የሚያስችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማቃለል የሚከተሉት ሁኔታዎች ይኸውም፡- ተማሪዎች ተከታታይነት ባለው ሁኔታ እንዲፅፉ ማነቃቃትና ከተለያዩ ዘውጎች ጋር እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታይቷል፡፡

### 6.1.4 የጥናቱ ስነ ትምህርታዊ ፋይዳ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል የሚያስችል ፋይዳ ያለው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለዚህም በተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ለሚገኙ ሁለት ምድብ ተማሪዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው የመፃፍ ትምህርት ለሙከራ ቡድኑ በሂደተ ዘውጋዊ ተኮር ዘዴ እና ለቁጥጥር ቡድኑ በልማዳዊው መንገድ ለተወሰነ ጊዜ ተሰጥቶ በታየው ውጤት መሠረት ትምህርቱን በአዲሱ ዘዴ የተከታተሉ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ውጤቱ የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የሚከተሉት ስነ ትምህርታዊ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑን አሳይቷል፡፡

1. የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ዋነኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ታላሚውን ቋንቋ በስፋት እንዲጠቀሙ፣ በጋራ እንዲሠሩ፣ እርስ በርስ እንዲተራረሙና ሀሳብ እንዲለዋወጡ ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር በተለይ የመፃፍ ክሂልና በአጠቃላይም የታላሚው ቋንቋ የተግባቦት ችሎታቸው እንዲዳብር ያደርጋል፡፡

2. በጥናቱ ወቅት እንደታየው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን ተግባር በፍላጎትን በንቃት ያከናውኑት ነበር፡፡ የሚሰጣቸውን እርማትና ማስተካከያ ለመቀበልና ለመተግበር ያላቸው ፍላጎት የተሻለ ነበር፡፡ ተስፋ ሳይቆርጡ የተሻለ ሠርተው ለመገኘት ጥረት አድርገዋል፡፡ በመሆኑም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግ ችግራቸውን በራሳቸው መፍታት እንሚችሉ የሚያሳያቸው ስለሆነ ትምህርቱን በፍላጎት እንዲከታተሉ እና የሚሰጧቸውን ተግባራት በራሳቸው ተነሳሽነት ጭምር እንዲሠሩ ስለሚያደርግ ጥሩ የመማር ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

3. ከድኅረ ትግበራ ፈተናው ውጤት ማየት እንደተቻለው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ይልቅ የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ ተማሪዎች ከትግበራ

በኋላ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽም ስለመጻፍ ክሂል ያላቸው አመለካከት ከአሉታዊነት ወደ አዎንታዊነት የተለወጠ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም አቀራረቡ የሚኖራቸውን የተሳሳተ አመካከት ወደ ትክክለኛው እንዲቀይሩ እና በትምህርቱ ሂደት የበኩላቸውን ሚና በተገቢው በመወጣት ለጥሩ ውጤት እንዲበቁ ያደርጋል፡፡

4. በመማሪያው ክፍል ውስጥ በመምህሩ አጋዥነት በተማሪዎች ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት ሁሉ የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ስልትን የተከተሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ የማስተማሪያ ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል መማሪያ ክፍል ውስጥ ሊተገበር የሚችልና ተማሪዎችን ውጤታማ የሚያደርግ ነው፡፡

በመጨረሻም መምህሩ የመማሪያ ክፍሉን በሚገባ መቃኘት አለበት፡ በተመሳሳይ መምህሩ ትምህርቱ በሚያቀርብበት ጊዜ ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ የመፃፍ ክሂል በየትምህርት ቤቶች ተቀባይነት እንዲኖረው አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ ይህንን ዘዴ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ በመተግበር  በቀጣይ መሻሻሎች እንዲኖር ዕድል ይፈጥራል፡፡

የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ የበለጠ ተግባራዊ እንዲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ መማሪያ ክፍላቸውን ከመምህር ተኮር አቀራረብ ወደ ተማሪ ተኮር አቀራረብ መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ለማከናወን በመማር ማስተማሩን ሂደት የተማሪዎችና የመምህራን ሚና ሊታሰብበት ይገባል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎች እንዲማሩ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹና አቅጣጫ የሚያሳዩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በአንጻሩ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ለራሳቸው ስራ፣ ዕቅድ አውጪ፣ ተቆጣጣሪና ገምጋሚ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የሂደተዘውጋዊ ዘዴ በተገቢ ሁኔታ እንዲተገበር መምህራን የቀረቡትን ንድፈ ሀሳቦችና አካሄዶች በሚገባ ማጤን አለባቸው፡፡ በመጨረሻም መምህራን  ከዚህ ቀደም ስለትምህርት አቀራረብ ያላቸው እውቀት እንዲጎለብትና በበቂ ሁኔታ እንዲያስተምሩ በመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዙሪያ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎችም ስለሂደተዘውጋዊ ዘዴ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ትርጉም ያለው ትምህርት እንዲማሩ ስለሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ግንዛቤ ኖሯቸው በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመጨረሻም በክፍል ውስጥ የሚኖረው መስተጋብር ሁልጊዜ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ብቻ መሆን የለበትም ይልቁንም በተማሪዎችም መካከል የእርስ በርስ ግንኙነት ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገር በመነሳት የፈጠራ አስተሳሰብና የነቃ የትምህርት ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 6.1.5 የመፍትሔ ሀሳቦችና አስተያየቶች

ይህ ጥናት የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል መሆኑን አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ውጤት በመነሳት አቀራረቡ ተግባራዊ መሆን ይችል ዘንድ በተመራማሪው እይታ መተኮር አለባቸው የተባሉ ነጥቦች ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

1. የሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ጥሩ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከአተገባበር አኳያ የተማሪዎችን የመማር ሂደት ባልገደበ ሁኔታ መተግበር ስላለበት መምህራን ከአተገባበር አኳያ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ሊያጤኑት ይገባል፡፡ Adeyem (2003) እንደጠቆሙት የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን መምህራን በነጻነት የመማርን አተገባበር ሊያስቡበት ይገባል፡፡ ስለዚህ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት በመምህራን የሚያቀርበው ትምህርት፣ የተማሪዎችን ምርጫ መሰረት አድርጎ በፍላጎትና በነፃነት እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ሊሆን ይገባል፡፡

2. መምህራን የሂደተዘውጋዊ አቀራረብን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የሚጠበቀው ትምህርታዊና ማህበራዊ ስኬት እንዲመጣ ተማሪዎች አዲሱን አቀራረብ በሚገባ እንዲረዱት እና በትምህርቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ በቂ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

3. መምህራን ጥሩ ግንዛቤ ኖሯቸው በክፍል ውስጥ በተገቢው ሁኔታ መተግበር እንዲችሉ የሚያደርጋቸው በቂ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

4. የመማሪያ እና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች የይዘት ምርጫውን እና አደረጃጀቱን ለሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትግበራ በሚያመች ሁኔታ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

5. የመምህራንን አፈፃፀም በመከታተል ሙያዊ እገዛ ለማድረግ የሚሹ አካላት ለዚህ የሚያበቃቸው ግንዛቤ ያላቸው እና የሠለጠኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡

### 6.1.6 የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ መፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያሳየ ነበር:: ይሁን እንጂ ጥናቱ ሲካሄድ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመቀነስ አንዳንድ እርምጃዎች ቢወሰዱም ጥናቱ ውሱንነት ታይቷል::

ይህ ጥናት በተለያዩ ተፅዕኖዎች የተነሳ ውሱንነት ታይቶበታል:: ውሱንነት ከታየባቸው ነገሮች መካከል የጊዜ እጥረት በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን ተመራማሪው በዚህ አጭር ጊዜ ለጥናቱ ሰፊ ሽፋን ለመስጠት ውሱንነት ታይቷል::

የጊዜ እጥረት በመኖሩ ምክንያት የናሙናዎቹ መጠን አነስተኛ እንዲሆን ተወስኗል:: የጥናቱን ተሳታፊዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ከዘጠነኛ ክፍሎች ሁለት ክፍሎች ተመርጠዋል:: የተመረጡትም ከአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት ብቻ ነው:: እነዚህ ሁለት ክፍሎች አንደኛው ለሙከራ ቡድኑ ሌላኛው ደግሞ ለቁጥጥር ቡድኑ ተመርጠዋል:: በእያንዳንዱ ቡድን አርባአምስት ተማሪዎች ብቻ ተመድበውለታል:: አንድ መምህር ለጥናቱ ተመድቧል:: በበጥናቱ ውሱንነት የተነሳ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በማስተማር ውጤቱን ማረጋገጥ አስቸጋሪ በመሆኑ በጥናቱ መጠን አነስተኛነት የተነሳ የውጤቱ አጠቃላይነት ወሱንነት አለበት::

### 6.1.7 ለቀጣይ ጥናቶች አስተያየት

1. የሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በየጊዜው ድጋፍና ማብረታቻን ለሚሹ ዝቅተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎችም አስፈላጊ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ እንደዚህ አይነት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲያካፍሉ ክሂላቸውን ሊያሳድጉ ይገባል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በዚህ ምርምር በሂደተዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ የበለጠ ተነቃቅተዋል፡፡ ዓላማቸውን ለማሳካት ያቀዱትን ተግባር በራሳቸው ለማከናወን ያላቸው ፍላጎት መጨመሩ ተስተውሏል፡፡

2.ይህ ሁኔታ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተጠኚዎችም በተመሳሳይ ተስተውሏል። በመሆኑም የሂደዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ዝቅተኛና ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ዓላማቸውን ለማሳካት የሚደግፋቸው መሆኑን ነው። በመሆኑም ተመራማሪው በቀጣይ የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ አንድ አይነት ደረጃ ባላቸው ተማሪዎች ላይ የሚያመጣው ተጽህኖ ቢመረመር በሌላ አባባል በቀጣይ በመፃፍ ረገድ ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎችን ችሎታ በማሻል ረገድ የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ሂደት የሚኖረው ተጽህኖ ቢፈተሽ።

2. ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተዘውጋዊ ዘዴን መተግበር አስፈላጊነት አሳይቷል። ይህም በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መተግበር ስለመቻሉ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ይህ ማለት የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ከአንድ ክፍል በዘለለ በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች ላይ መተግበሩ በተለይም በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ ጥናት መካሄድ እንዳለበት የሚጠቁም ነው። በመሆኑም በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ቢማሩ ሊያስመዘግቡ በሚችሉት ውጤት ላይ ጥናት ቢደረግ።

3. ይህ ጥናት አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ከልማዳዊው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ጋር ሲነጻጸር የተሻለ መሆኑን አሳይቷል። ይሁን እንጂ በሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ዙሪያ ባለሙያዎች ሁለቱ አቀራረቦች በተለያዩ ክሂሎች ላይ የሚኖራቸው ውጤት ቢፈተሽ። በአጠቃላይ ይህንን ጥናት ወደ አጠቃላይነት ለማምጣት እነዚህ ሁለት አቀራረቦች በሌሎች ተላውጦዎች ይኸውም መነቃቃትና የግል ውጤታማነት አንጻር ጥናት ቢከናወን፡

4. በመጨረሻም በሙከራ ጥናት ወቅት ተመራማሪው በሚፈትሻቸው ተላወጦዎችና ግንኙነት ላይ ተፅህኖ የሚፈጥሩ ተላውጦዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። በዚህ አይነት ሁኔታ የሚከሰቱ ተላውጦዎች የጥናቱ ፍላጎት ባይሆኑም በውጤቱ ላይ ተፅህኖ ከማሳደራቸው በላይ ስህተትን ይጨምራሉ (Martyn, 2008, Richards 1998)

ከዚህ አንፃር ምናልባት ከሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብና ከልማዳዊው አቀራረብ የተለዩ የጥናቱን ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ ተላውጣዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። በሌላ አባባል እነዚህ ተላውጦወዎች ያልታቀዱና በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅህኖ የሚያሳርፉ ናቸው። እነዚህ ተለውጠዎች ተማሪዎች፣ መምህሩና ጊዜ ሊሆኑ

ይችላሉ፡፡ እነዚህ የማይፈለጉ ተለውጦዎች ለመቆጣጠር በጥናቱ ትውረታዊ ማዕቀፍ ሊታዩ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በዚህ መሰረት ጥናት ለማካሄድ ንድፍ ሲወጣ ተላውጠዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

## ዋቢ ፅሑፎች

ሀና ታምራት:: (2003):: "በሆሳህና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ጽህፈት ክሂል ኮርስ የአቀራረበና የአተገባበር ፍተሻ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ማረው አለሙ::(1887):: "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ሰለሞን ዩሐንስ:: (1991):: "የተማሪዎች የአማርኛ ደርሰት የመፃፍ ስትራቴጂና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞሽ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ስዩም ከበደ:: (1988):: "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ሰይድ ይመር:: (1993):: "በ9ኛ ክፍል ለአማርኛ መማሪያ መፃህፍት የቀረቡት የጽህፈት ትምህርቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ በሰባት አዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት::"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ሶፊያ ሙሀመድ:: (2002):: "በዳሞት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ድርሰትን ለማስተማር ስልት ያለውን ተግባራዊነት መፈተሽ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/::

በድሉ ዋቅጅራ:; (1996):: *በስነፅሁፍ ቋንቋን ማሰተማር::* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ባየ ይማም:: (1987):: *የአማርኛ ሰዋስው::* አዲስ አዲስ አበባ ት.መ.ማ.ደ::

ተመስገን ፈቀደ:: (2001):: “የ11 ክፍል መምህራን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ::” (በሃዲያ ዞን በሾኔ መሰናዶ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ (የተካሄደ ጥናት):: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/::

ተስፋዬ ሸዋዬ:: (1986):: *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር*:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ደ::

ትምህርት ሚንስቴር:: (2004):: *የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ::* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ ማህበር::

አለም እሸቱ::(1995):: ”በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር:: ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ/ም ለአማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርዐ ትምህርቶች ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ::“ (ያልታተመ)::

አለማየው ፀጋዬ:: (1986):: “የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፅሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምንጮች ትንተና::” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/::

አስቴር ሳሙኤል:: (1998):: የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

አስቻለው ቦጋለ:: (2000):: “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጽህፈት ክሂል ትምህርት የአቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴዎች ፍተሻ::” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

አንለይ አዳነ:: (2000):: “ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ውስጥ የጽህፈት ክሂል የማስተማር ስነ ዘዴዎች

አተገባበር::” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ክፍሌ ሀብተማሪያም:: (1986):: “የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታ::” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ፅጌ ታደሰ:: (1992):: “ለፅህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል በአዲስአበባ ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መፃህፍት ላይ የተካሄደ የይዘት ትንተና ግምገማ::“ አዲስአበባ ዩንቨርሲቲ፣ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ /ያልታተመ/::

Atkinson, D. (2003). ‘’L2 Writing in the post process era, Introduction on.’’ *Jornal of Second Language Writing* .12.3-15.

Babalola, H.A.L. (2011). “ Relative Effects of Task-Based and Process-Genre Instructional Approaches on Written English performance of polytechnic students” partial Fulfilment of the Degree of Doctor of Philosophy University of Ilorin Nigeria.

Badger, R. and White, G. (2000) ‘’Product, Process and Gener: Approaches to Writing in EAP.’’ (Electronic Version). *ELT Jornal*, 54(2), 153-160.

Bawarshi, A.(2003) . *Gener &the invention of the writer ፡ Reconsidering the place of invention in compostion.* Logan Utahi utah State.Up

Bernstein, B. (1990). *The structuring of pedagogic discourse,* vol IV,‘Class, codes and control’. London: Routledge Kegan Pau.

Berlin, J (1984). Writing instruction in nineteen-century America college.USA: conference on college composing & communication.

Brakus,P. (2003). "A product /process/ gener approach to teaching writing: a synthesis of approach in a letter writing course non-native English speaking administrative personnel". Un puplished Dissertation, university of Surrey. M.A, Allyn and Bacon.

Best,J.W and Khan,J.V.(1993). Reaserch in education. Needham heights,

Brandly.S.(1994). *Teaching English*. London: Rutledge

Brown (2001). *Teaching by Principle: An Interactive Approach to Language Pedagogy*. (2nd ed), New York: Addison wesly Longman,

Brown. H.D (2000). *Principles of Language Learning and Teaching* (4te ed), white plawns, NY: Addison wesley longman.

Burden and Larson and Toonen (2005) Gaining In Dependence Through Collaboration: Using Partner or Small Group Conferences to Discuss Students' Drafts.

Burgss, R.G. (Ed). (1989) *strategies of Educational Research*: Qualitative Method. London and Philade/Phia: The Falmer Press.

Burns, A. (2001). Gener- based approach to Writing and Biginning adult ESL Learners. In C,Candlin & N,Mercer(Eds). English Language Teaching in Social Context: A reader (pp.200-207). London: Routledge.

Byram, M. (2004). *Gener and Gener- based Teaching*. The Routledg Encyclopidia of Language Teaching and Learning(pp.234-237).

Byrne, D. (1990).*Teaching Writing Skills*. London: London: Routledge

Callaghan,Mike,C, Peter Kanappad ,Greg ,Nobel(1993). *The power of literary: Agener approach to teaching writing* (eds),Bill ,Cope& Msrry Kalantzis pittsburg university press.

Carson, Joan and gayle Nelson. (2012). Chiness students perception of ESL peer response group ".*Jornal of second language writing*. 1-19.

Caudery, T. (1998). "Increasing Students Awareness of Gener Through Text Transformation Exercises: an Old Class Room Activities revised." TESC-EJ./ 3.3. A2. pp., 1-15 Retrieved December 31, 2006 From http://www.latrobe.du.au/education/celia/test-ej/ej11/a2.htm

Celce Murcia, M. (ed).(1991). *Teaching English as a second or foreign language.* Bosten: Heinle and heinle publisher.

Cheng,A. (2006). Understanding learners and learning in ESPgener based writing instruction. English for specific purpose, 25(1),76-89.

________ (2007). Simulation-based L2 writing instruction: enhacment through gener analysis. Simulation and Gaming, 38,(1),67-82.

________(2008). Analizing gener examplars in preparation for writing. Th case on L2 graduate student in the ESP gener based instructional frame work of Academic Litracy, Applied Linguistics, 29(1):50-71,1.

Christine ,F. (1987). *Gener as a choice*. I Reid (ed). "The place of ghener in learning current dibates". Deakin :Deakin University Press.

Conner,U &Karen,A .(1997). "Peer response group in ESC Writing class. how much impaction revition? "*jornal of language writing*. 3(3).257-276.

Cope, B and M.Kalantzis. (1993). 'Background to gener teaching' in B, cope and M.Kanntzis (eds). *The power of Literacy*: A gener Approach to Teaching Writing. London: Falmer Press.

Davies,F (1988)." Designing a writing syllabus in English for academic purposes: process and product ".In Robinson (p.c) .ed . Academic writing: process and product (London: modern English production —British council, "ELT Document, 129". pp.130-142.

Degi,Z.(2005). "The process oriented approach to ESL./EFL writing instruction and research. " *ELEA Jornal (Biononthly)*. South east missouth state university.

Derewianka, B. (2003). "Trends and issues in gener based approach" .*RELC Jornal.* 34 (2).133-54.

Devit, A. (2003). "Generalizing about gener : New conception of an old concept : College Compositin & Communication. " *ELT Journal*. vol .44,573-86

Emig,J.(1971). *The writing process of twelfth graders*. Urbana: IL,NCTE.

Feez ,S. (2002). "Hertage and innovation in second language education. "Gener in the classroom: Multiple perspective .ED. Ann Johns Newjersy: Lawrence Eribaum Association, 43-69 .print.

FeeZ, S. Dan H. Joyce. (2002). *Text-based Syllabus Design*. Sydney: NCELTR. Mac Quarie University.

Ferris, D .(1995). "Student reaction to teacher response in multiple draft compostion class rooms. "*TESOL. Quarterly*. 29

Flore,L.S (Ed). (1998).Reading- to-Write: Expioring aCognitive and Social Process,Oxford.England: Oxford University Press.

Foley,J.A.(2005) . “English in Thailand”. *RELC Journal* , 36(2),223-234.

Frankel, J. and Norman, E. Wallen (1990). *How to Design and Evaluate Research in Education.* New York: McGraw Hill inc.

Gabrielatos,C.(2002). EFL.Writing:Product and Process. retrived on ougust 25 2015 from <http://wwwgabrielates. com/Writing. pdf›

Gallaghan, Mike, C, Peter Knapp and Greg Noble.(1993). “The power of literacy: A Genre approach to teaching writing”.(Eds) Bill Cope & Msrry Kalantzis Pittsburgh : University press, 179-202.

Gao, J. (2007). Teaching writing in Chinese universities: finding an eclectic approach. *Asian EFL Journal (Teaching articles)*, 20 (2), 285-297.

Gibbons, P. (2002). *Scaffolding Language, Scalffolding Learning*: Teaching Second Language Learners in the Mainstream Class Room. Portsmouth, NH: Heineman

Graim,M. (2005). “The effect of teacher written feed back on ESL students perception: A study A Jaudi ESL university- level content” *ARECLS Journal.* 2(4),76-12

Halliday, M. A. K. (1978). *Language as a social semiotic*: The social interpretation of language and meaning. London: Edward Arnold.

Hammond, J. (1992*). English for social purposes: A handbook for teachers of adult literacy*. Sydney, Australia: National Centre for English Language Teaching and Research.

Harmer,J.(1998).The Practice of English Language. London: Longman.

Harmond.J and Drewianka,B (2001).Gener in R.Carter& D.Nunan (eds).*The Cambridge guied to teaching English to speakers of other language*. Cambridge: Cambridge university press.

Heaton, J.D. (1988). *Writing English Language* **Tests.** (2nd Ed). London: Longman.

Hedge, T. (1988) *Writing Resource Book for Teachers*. Oxford: Oxford University Press.

Henry, A. and Roeberry, r.L. (1998). “An Evaluation of a Gener- Based Approach to the Teaching of EAP/ESP Writing”. *TESOL Quarterly*, 32(1), 147-156.

Horowitz, D.(1986), “process not prouct: Less than meets the eye” *TESOL Quarterly,*20,141-144 .

Hyland, K. (2002). “Gener in Primary Classrooms: The New Souther Wales (NSW) k-6 Syllabus”. Inc N. Candlin and D.R. Hall (Eds). Teaching and Researching (pp. 96-103) Harlow. ESSEX.

__________(2003a). “Gener based pedagogy :A social response to process.” *Jornal of seconed language writing* . 12(1),17_25 .

__________ (2003b). *Second Language Writing*. New York: Cambridge University Pre

__________(2004). *Gener and second language writing* Ann,Arober,MI:The university of Michigan press.

__________(2007). “Gener pedagogy :Language,Literacy and L2 writing instruction”. *Jornal of seconed language writing* . 16(148)_164.

Hyon, S. (1996). “Gener in Three traditions’ Implication for ESL”. *TESOL Quarterly.* 30(4), 693-7022.

Janet,E.(2003). “Writing as model of learning“ *TESOL QUARTWRLY*. Vol.37/21,p(345-351)

Johns.A.(1997). *Text, Roll and Context; Developing Academec Literacies*. Cambridge: Cambridge university press.

______(2003). "Gener room & ESL/EFL. Compostion instruction". In B kroll (ed) *Exploring the Dynamics of Second Language Wriing*. Cambridge. Cambridge university press.pp.195-21

Kaur, S. & Chan, P. S. (2005)."Towards a process-genre based approach in the teaching of writing for business English." [Online]. Available: http://www.esp-world.info/Articles_11/Sarjit-poon2.htm. [28 October 2012

Kay, H., & Dudley-Evans, T. (1998). Genre :What teachers think [Electronic version]. ELT Journal, 52(4), 308-314.

Kim, M.S. (2007). *Gener Based Approach to Teaching Writing*. Hawai: Pacific University.

Kimg, and Kim, J. (2005). "Teaching Korean University Writing Class: Balancing the Process and the Gener Approach" (Electronic Version) Asian EFL Jornal. 7(2)-1-15.

Kongpetch, S. (2006). "Using A Gener- Based Approach to Teach Writing to Thai Students"; A Case Study Prospect Vol. 21. No.2.

Koul, C. (1996). *Methodology of Educational Research*. (2nd Revised Ed). New Delh: Hindustan Offset Printers

Kroll, B.(1990).''What does Time Buy? ESL Student Performance on Home versus Class Compositions." In Second Language Teaching.

Leedg, P.D. and Ormorod, J.E. (2005) *Practical Research: Planning and Design.* (8th ed). New Jersey: Pearson Prentice Hail.

Leki, I. (1992). Understanding ESL writers: A guide for teachers. Portsmouth, NH: Boynton/Cook.

Lin,B (2003). "English in Singapor: An in siders perspective of syllabus renewal through a gener based approach". *RELC Journal*,34(2), 223-246 Gner in the

Macken- Horarik.M. (2001). Something shoot for:a systemic functional approach to teachjng gener in secondary school Science. in A.M, Johnes (ed).Genre in the Classroom,pp.17-42, Mahwah: Erlbaum.

Matsuda,P.K.(2003). "Process and post process": A discursive history. *Journal of Second Language Writing*. (12).63-85

McLaughlin, B. (1990). "Conscious versus Unconscious learning." *TESOL Quarterly* 24:

Miller, C.R. (1984). "Gener as Social Action" (Electronic Version) *Quarterly Journal of Speech.* 70, 151-167. 617-34.

Muncie,J. (2002). Process writing and vocabulary lexical frequency orfile drafts.system.30(2), 225-235.

Muray,D.(1982).*Learning by Teaching: Selected Articles on Writing and Teaching* Performance. London :OUP.

Nordin, S. &Norhisham, M. (2006). "The best of two approaches: Process-genre approach to teaching writing". *The English Teacher,* **35**, 75-85.

Nunan, D. (1999). *Design Tasks For the Communicative Classroom*. Cambridge: Cambridge University Pres

Paltridge,B. (2000). Gener analysis. In B, Paltridge (ed). Making sense of discourse analysis. Goldcost, QLD: Anti podean educational enterprise.pp.105-126.

_________(2001).Gener and the language learning classroom. Ann Arbor: University of Michigan Press.pp.

_________(2002). Gener, text, type and English for academic purpose(EAP).In A.M, Johns(ed). Gener in the class room: Multiple perspective. Mahwah, N.J:L .Erlbaum.pp.73-93.

_________(2007).Approch to gener in ELT.In J. Cummins & C,Davison (eds). International handbook of English language teaching .vol.15, 931-943. Springer US.

Pianko, S. (1979). A description of the Composing Proceses of college Fresh man writers

Pica, T.(1986). "Interactional Aproach to the Teaching Writing" *English Teaching Forum.* 24/3,6-10.

Pincas, A. (1982). Teaching English Writing. London: Rergman Press Ltd. Vol. 23 No 3. PP. 359-360.

Raimes, A. (1983). *Techniques in the Teaching writing*. New York: Oxford University Press.

Reid, J. (1993). *Teaching ESL Writing* .New Jersy: Regents / Prentice Hall

_________(2001).*The Cambridge guied to teaching English to speaker of other language*. In R.Carter & Nunan (Ed),writing (p.23-33).Cambridge: Cambridge university press.

Richards, J.C. (1990). *The Language Teaching Matrix*. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards,J.C. & Renanday,W. (2002). *Teaching writing .In language teaching: An anthology of current practice*. (pp.303-305).Cambridge, England: Cambridge University Press.

Seow,A. (2002). "The writing process and process writing" .In Jackc. Richards, Willy,A,Renandya (Eds). *Methodology of Current Practice* (pp.315-320). Cambridge. New York: Cambridge university press.

Silva, T. (1990) "Second Language Composition Instruction: Development Issues and Directions in ESC." *Second Language Writing*. In Barbara Kroll (ed) Cambridge: Cambridge University Press.

Simpson, p(1997). *Language through literature*. London & Newyork :Routledge.

South Africa Ministry of Basic Education (2010). Curriculum Assessment Policy Statement. RSANIED.

S. Rodgers (2001). *Approaches and Methods in Language Teaching* (2nd edition) Cambridge University Press

Stan, R. (2000). *Film Theory*. Oxford: Black Well.

Standley,G. (2007). "Approaches to Process Writing". www.teaching english.net/think/write/processwrite.shtm/

Swales, J. (1990). *Gener Analysis*. UK: Cambridge University Press.

Swami, J.A .(2008). "Senstizing ESL Learners to gener". TESL- EJ, 13(3).1-13.

Tompkins, G. (1997) *Teaching and Writing: Balancing Process and Product*. Columbus. OH: Merrill Publishing Co.

Tribble, C. (1996). *Writing.* Oxford: Oxford University Press.

Ur, P. (1996). *Course in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Vygotsky, L.S. (1978). *Mind in Society: The Development of Higher Psychological Process.* Cambridge. MA.: Cambridge University Pres.

Walter-Echols,E. (2009). 'Teaching Writing by modeling geners through the teaching learning cycle", cam *TESOL.* Confrence on English language teaching ;Selected papers . ,230-238.

Weigle,S.C(2002).Assessing Writing.Camridge:CPU.

White,R.and Arned ,V(1991). *Process writing* .Harold :Long man.

Widdowson, H (1990). *Aspects of language teaching.* Oxford: Oxford University Press

Willson,G .(2003). *Learning through interaction*. Cambridge: Cambridge University press.

Yan, G. (2005) A Process Gener Model for Teaching Writing English Teaching Forum. 43(3),18-26.

Zamel, V. (1982). "Writing the Process of Discovery Meaning". *TESOL Qurterly.* 16, 195-209.

_________ (2011). "The Composing Process of Advanced ESL Students Six Class Studies" *TESOL Quarterly* 17, PP, 179-180.

__________ (2012). "Responding to student writing " *TESOL Quarterly*. 19.1: 79-101.

Zeng,D.(2005). The process oriented approach to ESL-EFL. Writing instruction and research, Teaching English in China. 28(5).66-77.

Zinser, D. (1984). *Basic Principle of Experimental Psychology* New York: MC.Graw- Hill.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

## የስልጠና ማኑአል (Traing Manual)

## የሂደተዘውጋዊ ዘዴ አተገባበር

# በተካልኝ ለማ የተዘጋጀ

መስከረም 2007 ዓ,ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

**ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ ......................................................................156**

1.1. ለሰልጣኝ መምህሩ የተፃፉ ደብደቤ ......................................................156

1.2. የስልጠናው ስምምነት ፎርም ..............................................................157

1.3. የስልጠና ማኑኣል አጠቃላይ ገፅታ ........................................................158

1.4. ለስልጠናው የተመደበ ጊዜ ..................................................................158

1.5. ለስልጠናው የተመደበው ጊዜ ክፍፍል (Breakdown to Each lesson) .........................................................................................159

**ምዕራፍ ሁለት:- በስልጠናው ጊዜ የሚሸፈኑ ይዘቶች ...................................159**

2.1. ብያኔዎች .........................................................................................159

2.2. የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ .............................................................................................160

2.3. የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ጠቀሜታዎች ...............................................161

2.4. በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተዘውጋዊ ዘዴ አተገባበር ...............................................................................................162

2.5. የመምህሩ እና የተማሪው ሚና ............................................................168

2.5.1. የመምህሩ ሚና ...........................................................................168

2.5.2. የተማሪው ሚና ...........................................................................170

**ምዕራፍ ሶስት፡- የሙከራወን ሂደት ማከናወን ..........................................170**

3.1 የመማር ማስተማር ሂደቱን ማከናወን ......................................................171

3.2 የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብን መለማመድ .................................................172

3.3 የሚያጋጥሙ ችግሮችን መቆጣጠር ..........................................................173

## ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ

የዚህ ጥናት አላማ የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ችሎታን ማሻሻል አለማሻሻሉን መመርመር ነው:: ይህንን አላማ ለማሳካ፦ ሁለት ክፍሎች የሚመረጡ ሲሆን አንደኛው ለሙከራ ቡድን ሌላኛው ደግሞ ለጥብቅ ቡድኑ ይሆናል:: እነዚህን ሁለት ክፍሎች እምዲያስተምር አንድ መምህር ተመድቧል:: ይህ መምህር የጥብቅ ቡድኑን ክፍል መፃፍን በልማዳዊ አቀራረብ /Traditional approach/ የሚያስተምር ሲሆን የሙከራ ቡድኑን ደግሞ በሂደዘውጋዊ ዘዴ አስተምሯል:: የሙከራ ክፍሉን ለማስተማር ይረዳው ዘንድ መምህሩን የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ አቀራረብን ግንዛቤ ለማሳደግ ከልምምዱ በፊት በተመራማሪው ስልጠና ተሰጥቶታል::

ይህ የስልጠና ማኑአል ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከተለያዩ ንውሳን ርዕሶች ጋር አሉት:: የመጀመሪያው ክፍል መግቢያውን የተመለከተ ሲሆን በዚህ ርዕስ ስር ለሰልጣኙ መምህር የተፃፈ ደብዳቤ፣ የስልጠናው ስምምነት ፎርም አጠቃላይ የስልጠናው ሂደት እና ለስልጠናው የተመደበውን ጊዜ ያጠቃልላል:: ከዚህም በተጨማሪ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚኖረውን እረፍት እና ለስልጠናው የሚሆን ቼክሊስት ይዟል::

በሁለተኛው ምዕራፍ ስለሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ንድፈ ሀሳብ የሚነሳ ሲሆን ይህም ለሰልጣኝ መምህሩ ትምህርቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ስለሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ እውቀት እንዲያገኝ ያግዘዋል::

በመጨረሻው ምዕራፍ መምህሩ በሙከራው ትምህርት ወቅት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ነገሮች ተጠቃለዋል::ይህንን ስልጠና ከወሰደ በኋላ የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብን ተግባራዊ እንዲያደርግ የማስተማሪያ ፅሁፍ ተሰጥቶታል(አባሪ ሁለትን ይመለከቷል)::

### 1.1. ለሰልጣኝ መምህሩ የተፃፋ ደብደቤ

ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ሙከራዊ ሂደት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረውን ፈቃደኝነትህን ሰላሳየኸኝ ያለኝን አድናቆት መግለፅ እውዳለሁ:: ይህ ስልጠና ስለሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ ሀሳቦችን ለማጋራት ይሞክራል:: በተመራማሪው

የተሰጠውን ሰልጠና በተገቢ ሁኔታ መከታተልህ በጽሁፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሂደተዘውጋዊ አቀራረብን ለመተገበር አስችሏል::

ከስልጠና በኋላ በወቅቱ አቀራረቡን ለመተግበር ለሚካሄደው ጥናት ከዘጠነኛ ክፍል ለሚመረጠው አንድ ክፍል የምትመደብ በመሆኑ ስልጠናውን በሰዓቱ በመገኘት በተገቢው ሁኔታ እንደትከታተል በትህትና እጠይቅአለሁ:: ይህንን ስልጠና በክፍል ውስጥ ስራ ላይ ለማዋል ይረዳህ ዘንድ ይህ የስልጠና ማኑአል ይሰጥሃል::

## 1.2. የስልጠናው ስምምነት ፎርም

ይህ ፎርም በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ስልጠና ከመጀመሩ በፊት መሞላት አለበት::

የሰልጣኝ መምህሩ አድራሻ

ስም ---------------------------------

አድራሻ ----------------------------

ስልክ ቁጥር ----------------------

ኢ-ሜል--------------------------------

የአሰልጣኝ አድራሻ

ስም -----------------------------------

አድራሻ ------------------------------

--------------------------------

ስልክ ቁጥር --------------------------

ኢ-ሜል--------------------------------

ስልጠናው የሚካሄደው ከ ------------------ እስከ --------------- ነው::

ሰልጣኝ መምህሩ በተመራማሪው የቀረበውን የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ስልጠና ይከታተላል:: ስልጠናውን ከተከታተልክ በኋላ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይህንን

አቀራረብ ለመተግበር ፈቀደኝነቴን አረጋግጣለሁ:: በተጨማሪም እንዳከናውን የተፈለገውን አካሄድ እከተላለሁ::

የሰልጣኙ ፊርማ --------------------------- ቀን ------------------------

የአሰልጣኙ ፊርማ ------------------------ ቀን -----------

## 1.3 የስልጠና ማኑኣል አጠቃላይ ገፅታ

የዚህ ምርምር አላማ የሂደተ ዘውጋዊ የትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ያሳድግ እንደሆነ መመርመር ነው:: ይህንን አላማ ለማሳካት የሙከራ ቡድኑ መምህር ስለሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ይህ የስልጠና ማኑአል የታቀደው መምህሩ ስለዚህ አቀራረበ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው::

ይህ የስልጠና ማኑኣል የተዘጋጀው ለሙከራ ሂደቱ መምህር ከሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ንድፈ ሀሳብ ጋር ለማለማመድ ሲሆን በተለይም በሂደተዘውጋዊ አቀራረብ እና በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል መሻሻል መካከል ያለውን ግንኙነት ታሳቢ ያደረገ ነው:: በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ለ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የቀረቡ የጽሁፍ ርዕሶችን ይገለገላል::

## 1.4 ለስልጠናው የተመደበ ጊዜ

በስልጠናው ጊዜ ለሰልጣኙ አመቺ የሆነ ጊዜ ይመቻቻል:: ስልጠናው በየቀኑ ለ2ሰዓት የሚካሄድ እና ለ8 ሰዓታት የሚሰጥ ይሆናል:: በተሰጠው ጊዜ የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ንድፈ ሀሳብና ልምምድ ጋር የምትተዋወቅበት ሲሆን በልምምዱ ወቅት ለማመሳከሪያነት እንዲያገለግልህ ይህ የስልጠና ማኑአል ይሰጥአል:: በሙከራ ልምምዱ ወቅት እና ከዚያም ውጪ ባለው ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና አስተያየቶችን መስጠት ይቻላል::

### 1.5 ለስልጠናው የተመደበው ጊዜ ክፍፍል ( Breakdown to Each lesson)

ይህ ሰንጠረዥ በስልጠናው ጊዜ የተመደበውን የጊዜ ክፍፍል የሚያሳይ ነው::

| ተ.ቀ | የትምህርቱ ይዘት | ሰዓት |
|---|---|---|
| 1 | የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ብያኔዎች እና ገለፃዎች | 1 ሰዓት |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የክፍል ትምህርት አቀራረብ | 1 ሰዓት |
| 3 | የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ጠቀሜታዎች | 1 ሰዓት |
| 4 | በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ አተገባበር | 1 ሰዓት |
| 5 | የሂደተዘውጋዊ ዘዴ ማቅረቢያ ቴክኒኮች | 1 ሰዓት |
| 6 | የመምህሩ እና የተማሪው ሚና | 1 ሰዓት |
| 7 | የሙከራ ሂደቱን መለማመድ | 2 ሰዓት |

## ምዕራፍ ሁለት:- በስልጠናው ጊዜ የሚሸፈኑ ይዘቶች

በዚህ ምዕራፍ በስልጠናው ወቅት የሚቀርቡ ይዘቶች ይብራራሉ:: ስልጠናው በተግባር ከመሰጠቱ በፊት ስለ ሂደተዘውጋዊ አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦች ውይይት ይደረጋል:: በሂደቱ ተመራማሪው እና መምህሩ በስልጠናው ጊዜ በሚነሱ ይዘቶች እና ቴክኒኮቹ ውይይት ይደረግባቸዋል:: በመሆኑም የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብን ተግባራዊ ከማድረግ አስቀድሞ የሚከተሉትን ይዘቶች ማወቅ ይኖርብሃል::

### 2.1. ብያኔዎች

**አላማ**:- የዚህ ትምህርት አላማ ሰልጣኙ መምህር ከሂደተ ዘውጋዊ እና ልማዳዊ /Traditional Approach / አቀራረቦች ጋር ያሉ ፅንሰ ሀሳቦችን እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው::

**ዘውግ ተኮር አቀራረብ:-** ዘውግ በተለየ ማህበራዊ ዐውድ ውስጥ ለተግባቦታዊ ተግባር የተፈጠረ በመሆኑ ተለይቶ ይታወቃል:: ስነትምህርታዊ ዘውግ ተማሪዎች መፃፍን ሲማሩ የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ስለቋንቋ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሲኖራቸው ነው የሚለውን ሀስተሳሰብ መሰረት ያደርጋል:: ዘውግ የሚለው ቃል ሰፊ የሆነ የጽሁፍ ስራዎችን ይኸውም የንግድ ውል፣ ገላጭ ፣ተራኪ እና አከራካሪ ጽሁፎችን የሚያጠቃልል ሲሆን በአንድ ባህል ውስጥ ባሉ አባላት ተቀባይነት ያለው መዋቅርና ስነልሳናዊ ገፅታ ነው::

**ሂደት ተኮር:-** ድርሰት በሚፃፍበት ጊዜ ደጋግሞ ርዕሰ ጉዳዩን ማሰላሰል በተደጋጋሚ የማርቀቅ እና የመከለስ ስራ ነው::

ውጤት **ተኮር**: በተጠናቀቀው የተማሪዎች ጽሁፍ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ተማሪዎች ከሰዋስዋዊ፣ ከስርዓተ አፃፃፍ ፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ከፊደላትና ሆሂያት አጣጣል ወዘተ አኳያ ስህተቶች ሳይፈፀሙ እንዲጽፉ የሚያግዝ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ነው::

**ቅንጅታዊ አቀራረብ** በዚህ ጥናት የሂደተዘውጋዊ አቀራረብን ፅንሰሀሳብ መሰረት አድርጎ የሁለቱን ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመፈተሽ ጠንካራ ጎኖቻቸውን በመውሰድ የማቅረብ ተግባር ያለው መሆኑን ያሳያል::

## 2.2. የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ

**ዓላማ**:- የዚህ ትምህርት አላማ በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ስለሚደረገው የሂደተዘውጋዊ አቀራረብ መርህ እና ህሳቤዎች ግልፅ ለማድረግ እና እንዲሁም በአቀራረቦች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ግልፅ ለማድረግ ነው:: የተለያዩ የመፃፍ ትምህርት አቀራረቦች ቢኖሩም የዘውግ ተኮር አቀራረብ እና ልማዳዊ / traditional approach / አቀራረቦች ቀጥሎ ይብራራሉ::

| ዘውግ ተኮር አቀራረብ | ልማዳዊ (traditional approach) አቀራረብ |
|---|---|
| መሰረት የሚያደርገው ተማሪው በበቂ ሁኔታ ስለቋንቋው ከተጋለጠ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ እና በአጋጣሚ ቋንቋን ይማራል::<br>የቋንቋ እውቀት ከማህበራዊ አላማ ጋር የተሳሰረ እና ከፀሀፊው ይልቅ በአንባቢው ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋል::<br>ትምህርትየሚከናወነው በመቅዳት እና የተለያዩ ሞዴሎችን በማሰስ ነው<br>ተማሪዎች ለተለያዩ የዘውግ ሞዴሎች በመጋለጥ የተለየ ዘውግ በመፃፍ የጽሁፍ ችሎታቸው ያድጋል<br>ተደጋጋሚ ሞዴል በጋራ መገንባት እና በግል ጽሁፍን ማደራጀት ላይ ያተኩራል<br>የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የበለጠ ውጤታማ ነው | ትኩረት የሚያደርገው በመፃፍ ወቅተ በሚከናወኑት ተግባራት ወይም ወደ ውጤት ለመድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ እንጂ በመጨረሻው ውጤት ላይ አይደለም::<br>በዚህ ደረጃ የድርጊቶች ቅደም ተከተል በአራት ደረጃዎች ማለትም ቅድመ ጽህፈት (pre writing) ማደራጀት /መንደፍ/ (composing, drafting) መከለስ (Rivising) እና ማረምን ያጠቃልላል |

## 2.3. የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ጠቀሜታዎች

**ዓላማ**:- የዚህ ትምህርት አላማ ሰልጣኙን በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴን ጠቀሜታዎች ማስተዋወቅ ነው:: እነዚህ ጠቀሜታዎች ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ጥናቶች የተጠቆሙ ሲሆን ለግንዛቤ እንዲረዳቸው ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ጥናቶች ከተጠቆሙት መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን እንመልከት::

በማህበረሰቡ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶች በዘውግ አቀራረብ ላይ ትኩረት ሊደረግ ችሏል:: ዘውግ ማንኛውንም በባህል ውስጥ ተቀባይነት ያለው ተግባር ለምሳሌ ገለፃ፣ የዜና ዘገባ፣ ግጥም እና ትረካ የመሳሰሉትን በማህበረሰቡ ውስጥ ዕውን የሚሆን ድርጊቶችን ይመለከታል::

ከዘውግ ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታዎች መካከል ለተለያዩ አካዳሚያዊ ሁኔታዎች ያለው አስተዋጽኦ ነው:: ዋነኛው ጠቀሜታው ተማሪዎች የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን እና የጽሁፍ ሞዴሎች ተገንዝበው በመጨረሻም የራሳቸውን ተመሳሳየ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያግዛቸዋል::

ከዚህም ሌላ ዘውግ ሁልጊዜ የተለያዩ ነገሮችን ድምፆችን፣ ስልቶችን ፣የንግግር ገለፃዎችን እና አለመለካከቶችን በማጣመር የሚያቀርብ ነው:: በመሆኑም የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ለተለያዩ ዘውጎች እንዲጋለጡ በማድረግ በዘውግ አቀራረብ ተጠቅመው የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል:: ስለዚህ የዘውግ አቀራረብ በዘውግ መሰረታዊ ሀስተሳሰብ እውነት እንዲሆን በመጨረሻው ደረጃ ተማሪዎች በዘውግ ውስጥ የሚገኘውን ስልት እንዲገነዘቡት እና እንዲገለገሉበት ያስችላል::

Devit (2003) ባቀረቡት ማብራሪያ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የዘውግን ስነትምህርታዊ ፋይዳ እንደሚከተለው አብራርተውታል::

የዘውግ ስነ ትምህርታዊነት መምህሩ ትኩረቱን በቀረበው ጽሁፍ ላይ እንዲያደርግ ተማሪዎችም በታለመላቸው ዐውድ እንዲጽፉ ያስችላቸዋል:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ባለው አለም ውጤታማ የሆነ ተሳተፎ እንዲኖራቸው ያግዛል:: የዘውግ ንድፈ ሀሳብና ምርምር ግለሰቦችን በሁለተኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ለማዘጋጀት ለጽሁፍ መማሪያ የሚሆኑ የማስተማሪያ

መሳሪያዎች እና የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲያዘጋጁ ለመምከር ለትምህርት ባለሙያዎች የተገደበ ሚና ይሰጣል::

ከዚህም በተጨማሪ የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የመምህሩን ግንዛቤ ማለትም ተማሪዎቹ የሚጽፉትን እንዲገመግም እና ምን ማድረግ እንዳለበት ግንዛቤ ይፈጥርለታል::

## 2.4. በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሂደተዘውጋዊ ዘዴ አተገባበር

የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የማስተማር ሞዴልን በክፍል ውስጥ ስራ ላይ የሚውልበት አቀራረብ የFeez እና Joce's (1998) የመማር ማስተማር ውህደት ከአምስት ደረጃዎች ማለትም አውድን መገንባት ፣ጽሁፍን በጋራ መገንባት፣ ጽሑፍን በግል መጻፍ፣ ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሑፎች ማገናኘት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው:: ይህ የጽህፈት ሞዴል መሰረት የሚያደርገው በመማር ማስተማር ሂደት ዘውግን መሰረት ከሚያደርገው የአውስተራሊያው የዘውግ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለማስተማር መሰረት ከሚያደርገው መርህ ነው::

የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ ማስተማሪያ ሞዴል በአምስት ደረጃዎች ማለትም ጽሑፍን መገንባት፣ የጽሁፍን ሞዴል መተንተን ፣ጽሑፍን በጋራ መገንባት እና በጽሑፍ ላይ ጽብረቃ መስጠትን ያካተተ ነው:: ይህ ሞዴል ተማሪዎች የዘውግን ውስብስብ እይታ እንዲያሳድጉና በጽሑፍ ወቅት እንዲጠቀሙበት የማድረግ አላማ አለው::

### 1. ዐውድን መገንባት

ዐውድን በምንገነባበት ደረጃ የአራቱ ተላውጦዎች ማዕቀፍ ማለትም (Gener, Field, tenor and mode) በአውስትራሊያ የዘውግ ትምህርት ቤት በማህበራዊ አውድ ውስጥ ታላሚው ዘውግ ይኸውም የታላሚው ጽሁፍ ማህበራዊ አላማ ፣ታላሚው ጽሁፍ ሲፃፍ ማህበራዊ ተግባሩ፣ በተግባቦታዊ ተሳትፎ የተሳታፊዎች ግንኙነት እና ተግባቦት የሚገኝበትን ሁኔታ መመርመር ለተማሪዎች እንደመመሪያ ያገለግላል::

ለተማሪዎች ዐውድን መገንባት በጣም አስፈላጊው ደረጃ ሲሆን መምህራን ለትምህርቱ ጠንካራ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በዚህ ደረጃ ጠቃሚው መርህ ተማሪዎች ጽሑፍ ከማህበራዊ አውድ እንደሚገኝ እና በድርጊቱ ውስጥ ማህበራዊ

ግንኙነትን እንደሚያካትት እንደገነዘቡት ማድረግ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች የዘውግን አላማ ለመረዳት በተፈጠረው ግንኙነት ዐውድን መረደታቸው አስፈላጊ ነገር ነው (Cllaghan 1993:181) በዚህ ደረጃ በቋንቋ አገልግሎት እና በዐውድ ውስጥ ፍቺ እንዴት እንደሚፈጠር ትኩረት ይደረጋል (Feez 2002 Hyland 2004)::

በዚህ ደረጃ በክፍል ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል በአውዱ ላይ ውይይት እንዲደረግ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ ፣ማቅረብ ፣ስለፅሁፍ በስዕል መግለፅ፣ እንግዳ ተናጋሪዎችን መጋበዝ እና የመሳሰሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ (Hyland 2004 130-131)::

## 2. ሞዴል ጽሑፍን መገንባት

በዚህ የሞዴል ጽሑፍ ትንተና ደረጃ መምህሩ ያለውን ግንኙነት በጠንካራ ሁኔታ ይመራል:: በዚህ የሞዴል ጽሑፍ ታላሚው ዘውግ በአውዱ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: (Feez 2002:66) :: መምህሩ እና ተማሪው ስለጽሁፉ አደረጃጀት፣ ሰዋስዋዊ ገጽታው በተለየ አውድ ውስጥ የጽሑፍን አገልግሎት በተመለከተ እና የቃላት ምርጫ ላይ መነጋገር አለባቸው::

Hyland (2004) ባቀረቡት ሀሳብ ትንተናው ከታች ወደ ላይ ከሚሆን ይልቅ ጽሁፍ ሙሉ በሙሉ ቢሆን ይሻላል:: ብለዋል:: ከተለየ አንባቢና መልእክት ጋር አለማን ለማሳየት ጽሁፍ እንዴት እንደተደራጀ ግምት ውስጥ መግባት አለበት:: በመሆኑም ሁሉም የጽሁፍ አካል የተግባቦትን አላማ ለማሳካት እንዴት መፃፍ እንዳለበት ለምሳሌ አንቀፅ እና አረፍተ ነገር እንዴት እንደሚደራጅ፣ እንደሚዋቀሩና በስርዓት እንደሚፃፉ መገንዘብ ያስፈልጋል:: በሌላ በከል መምህራን ለተማሪዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ ሰዋስውን በግልፅ እንዲጠቀሙ ማሳየት ያለባቸው ሲሆን ይህም ለተማሪዎቹ ጠቃሚ ነው:: (Hyland: 2004)::

በሞዴል ጽሑፍ ትንተና ወቅት በመዋቅር ላይ መነጋገር፣ በሰዋስው፣ ከማህበራዊ አላማ ጋር በተገናኘ ልምምድ ማድረግ ጠቃሚ የክፍል ውስጥ ተግባራት ናቸው (Pallridse 2001)::

### 3. ጽሑፍን በጋራ መገንባት (Collaborative Construction of the text)

በዚህ ደረጃ መምህሩ ሚናውን በመቀነስ ሁኔታዎችን ወደማመቻቸት ይሄዳል (Hyland 2004፣134):: ተማሪዎች በማርቀቅና በማዘጋጀት ደረጃዎች ላይ እያሉ በግልፅ መነጋገር እና በፍቺ ላይ መስማማት እንዲኖር መደገፍ ያስፈልጋል:: በጽሑፋቸው ላይ ቁጥጥር ለማድረግና አጠቃላይ የሆነ የዘውግ ምሳሌ እንዲሰጡ በአነስተኛ ቡድኖች እንዲደራጁ ይደረጋል:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች በጽሁፍ አደረጃጀት ላይ ችግር ካለባቸው ወደቀደመው ደረጃ ስለአውድና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ዳግመኛ ሊመለከቱት ይችላሉ:: (Callaghan 1993)::

የዚህ ደረጃ ጠቃሚ ገፅታው መምህር የጽሑፍ ሂደት የሆኑትን ሀሳብ እና ተማሪዎች ጽሑፍ በሚያጠናቅሩበት ጊዜ የዐውድ የዘውግ እና በጽሑፍ ሂደት እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ መሆኑ ነው:: ተማሪዎች ካለፉት ደረጃዎች ያገኙትን የዘውግ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ተከታታይ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የመፃፍ ሂደት እንዴት እንደሆነና የጽሁፍ ክሂላቸው እንዲዳብር በጽሑፋቸው ይዘት ጽሑፍ፣ መንደፍ እና መከለሰን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል:: (Hyland 2004):: በክፍል ውስጥ ጽሑፍን በጋራ የመገንባት ተግባር በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ሊከናወን ይችላል::

- **በአግባቡ ላይ መነጋገር**

ተማሪዎች በሚፃፈው ጽሁፍ አገባብ ላይ ንግግር ማድረግ ያላቸው ሲሆን በተጨማሪም ጽሁፍ የሚገነባበት ሁኔታ አላማው የፀሀፊው እና የአንባቢውን ሚና መለየት ይኖርበታል:: ይህ አይነቱ ጽሁፋዊ ገፅታ ለማህበራዊ ሁኔታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መለየት አለበት::

- **ይዘትን ማሳደግ**

ተማሪዎችን የሚያነቃቃቁ ስልቶችን ተጠቅሞ የሚቀርቡ ጽሁፎች ይዘትን ያጎለብታሉ:: በዚህ መሰረት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማስቀረት ተገቢነት ያላቸውን ይዘቶች ለማሳደግ ስለአውድ ያላቸው እውቀትና በአውድ ላይ ለመነጋገር እንደ ማዕቀፍ መጠቀም አለባቸው::

- **ጽሑፍን ማደራጀት**

በዚህ ተግባር ተማሪዎች ያገኙትን ሀሳብ ያደራጃሉ:: ከዚህ አንፃር መዋቅርን መሰረት አድርገው ጽሁፍ ስለሚፈጠርበት የቋንቋ ገፅታ ይነጋገራሉ::

- **ራስን በመገምገም ንድፍን መከለስ**

ተማሪዎች የንድፍን ይዘትና አደረጃጀት በዐወዱ ውስጥ ዓላማውን ማሳካቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ግምገማ ያካሂዳሉ ::

- **ንድፍ ማዘጋጀት**

በቅድመ መፃፍ ተግባራት ወቅት የተፃፈወን ንድፍ መሰረት በማድረግ የፅሁፍን ንድፍ የዘጋጃሉ::

- **ራስን መገምገምና ንድፍን መከለስ**

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ራሳቸውን መገምገምና ፅሁፍን የመከለስ ተግባር ያከናውናሉ:

- **የብጤ ግምገማ**

ተማሪዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ በተማሩት የዘውግ ዕውቀት አማካይነት የፅሁፍን ውጤታማነት ይገመግማሉ:: በዚህ መሰረት መምህራን ተማሪዎች ንድፍን ለመገምገም የሚያስችል መመሪያ ያዘጋጃሉ:: ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው ጋር ንድፋቸውን በመለዋወጥ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የቢጤዎቻቸውን ንድፍ አርመው ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ:: ከዚህ በኋላ ሁለቱም በጋራ በንድፎቻቸው ላይ ይነጋገራሉ:: መምህሩም በውይይቱ በመሳተፍ ተጨማሪ አስተያየት ሊሰጥ ይችላል::

- **ከቢጤ በተሰጠ አስተያየት ንድፍን መከለስ**

በንድፍ ላይ ከቢጤ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ተማሪዎች ከውይይትና ከምጋቤ ምላሽ በመነሳት ንድፋቸውን ይከልሳሉ::

## 4. ፅሁፍን በራስ መገንባት

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን እና የፅሁፍ ክሂላቸውን ተጠቅመው ዐውድን በመመርመር የራሳቸውን ፅሁፍ በግላቸው ይፅፋሉ:: ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ቢጤዎቻቸውን  እና መምህራንን ሀሳብ መጠየቅ ይችላሉ:: እንዲሁም ባለፈው ፅሁፍን በጋራ የመገንባት ደረጃ የአገባብ ዕውቀት ፣የዘውግ እና ሂደት ጥምረትን የመተቀሙ ልምድ የራሳቸውን ፅሁፍ በነፃነት እንዲፅፉ ያግዛቸዋል::

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በየግላቸው የመፃፍን ተግባር የሚያከናውኑ ከመሆኑም በላይ የዘውግን ዕውቀት ማቀናጀታቸውን ለማረጋገጥ መምህሩ የተለያዩ ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያበረታታቸዋል:: ተማሪዎች ግላዊ የፅሁፍ ተግባር እንዲያከናውኑ ከተነገራቸው በኋላ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ይመከራሉ::

- **የይዘት ትንተና**

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የጽሁፉን አገባብ እንዲተነትኑት የሚጠየቁ ሲሆን ፅሁፍ የተፃፈበት ሁኔታና ዓላማውን እንዲለዩ ይጠበቃሉ:: የፅሀፊዎችን እና የአንባቢን ሚና የተፃፈው የፅሁፍ ዓይነት እና ማህበራዊ ሁኔታ ለፅህፈት ገፅታ ያበረከተው አስተዋፅኦ ይታያል::

- **ይዘትን ማሰሳደግ**

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የፅሁፍ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉና መነሳሳት እንዲፈጥሩ ይበረታታሉ:: ከዚህም ሌላ የማይፈለጉ መረጃዎችን በመተው ተፈላጊ ይዘቶችን እንዲያሳድጉ የማህበራዊ ዕውቀትን እንደመመሪያ እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ::

- **ፅሁፍን ማደራጀት**

ተማሪዎች ያገኟቸውን ሀሳቦች የሚያደራጁ ሲሆን የታላሚውን ዘውግ መሰረት በማድረግ ንድፍ ያዘጋጃሉ:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዝርዝር መረጃዎች ሀሳባቸውን የበለጠ ማሳደግ ወይም የማይፈለጉ መረጃዎቸን ያስወግዳሉ::

➢ **ራስን መገምገምና ረቂቅን መከለስ**

ተማሪዎች ይዘት እና አደረጃጀት የጽሁፍን ማህበራዊ ዓላማ የሚያሳኩ መሆናቸው ከመምህራቸው በተሰጣቸው መገምገሚያ አማካይነት ፅሁፋቸውን ይገመግማሉ::

➢ **ንድፍ መፃፍ**

የቅድመ የመፃፍ ግባራትን መሰረት አድርገው ንድፍ ያዘጋጃሉ::

➢ **ራስን መገምግምና ንድፉን መከለስ**

ተማሪዎች ራስን መገምግመና የዘውግን ዕውቀት እንደመመሪያ ተጠቅመው የፃፉቸውን ፅሁፎች የይዘት ምርጫ በማድረግ ሰዋስውና ቃላት በማህበራዊ ዐውድ ውስጥ ዓላማቸውን አስተካክለዋል? የሚለውን ሀሳብ ሊያጠየኑት ይገባል:: ራስን የመገምገሚያ መስፈርት በመምህሩ ሊዘጋጅ ይገባል::

➢ **የብጤ ግምገማ**

ተማሪዎች አስተያየት ለመቀበል ከቢጤዎቻቸው ጋር ንድፉቸውን ይለዋወጣሉ :: በመቀጠልም ፀሀፊውና ቢጤው በንድፉ ላይ ለመነጋገር ይገናኛሉ ::ተማሪዎች ለግምገማው መስፈረት የሚሆነው በአገባብ እና በፀሀፊው ገፅታ የዘውግን ዕውቀት መሰረት እንደሚያደርግ ተማሪዎችን ማስታወስ ያስፈልጋል::

➢ **የቢጤ አስተያየትን መሰረት ያደረገ የንድፍ ክለሳ**

ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ ጋገኙ በኋላ በተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ አማካይነት ንድፉቸውን ይከልሳሉ:: በመቀጠልም ተማሪዎች የመጨረሻውን ንድፍ ከመጀመሪያው ንድፍና የማነቃቂያ ማስታወሻቸውን ለመምራቸው ያቀርባሉ::

➢ **ለንድፍ የመምህሩ ምላሽ**

መምህሩ ንድፉ ከማህበራዊ አውድ አንፃር ተገቢ በሆነ ሁኔታ ተፅፏል? ዓላማው መሳካቱን ለማረጋገጥ ቤማሪዎቹ ንድፍ ላይ ምልክት በማድረግ አሰተያየት

ያቀርባል:: አስተያየት የመስጫ መስፈርት መሰረት የሚያደርገው መምምሩ በንድፍ ላይ የሚሰተው አስተያየት ነው::

- **ከመምሩ በሚሰጠው ምላሽ ንድፍን መከለስ**

ተማሪዎች ከመምህሩ ባገኙት ምላሽ እና አስተያየት ንድፋቸውን ይከልሳሉ::

5. **በጽሁፍ ላይ ፅብረቃ** (Reflecting on writin)

ተማሪዎች ንድፍ ፅፈው ከጨረሱ በኋላ በፃፉት ፅሁፍ ላይ ፅብረቃ እንዲያደረጉ ይጠበቃል:: ይህ ሁኔታ የፅሁፍን አገባብ፣ ማህበራዊ ዐውድ ላይ የሚያሳርፈውን ተፅህኖ እንዲገነዘቡ ይረዳል::ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በአገባብ ላይ ያለን ተመሳሳይነትና ሌሎች ያጠኗቸውን ፅሁፎች እንዲያጤኑት ያበረታታል:: በፅብረቃ አማካይነት በተግባ ላይ ያለው ፅሁፍ ላይ ተፅህኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ሁኔታዎች እና ተግባራትን ለማጠናቀቅ ስለሚከተሉት ስልት በፅብረቃ እንዲገልፁ ይበረታታሉ (Johans፣1997፣134)::

በአጠቃላይ በፅሁፎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲያጤኑት ይህም በፅሁፍ ውስጥ የታለመው ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ዕድል ይፈጥርላቸዋል::

### 2.5. የመምህሩ እና የተማሪው ሚና

**ዓለማ**:- የዚህ ትምህርት አላማ ሰልጣኙን መምህር በሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ወቅት የመምህሩን እና የተማሪውን ሚና እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው:: እንደሚታወቀው እና አንተም እንደመምርነትህ እንደምትረዳው በልማዳዊው / traditional approach / አቀራረብም ቢሆን መምህሩ እና ተማሪው የሚጫወቱት የተለየ ሚና ይኖራል:: እንደሙከራ ክፍል መምህርነትህ እነዚህ ነገሮች በሚገባ ልታጤናቸው ይገባል:: በመሆኑም ይህ ንዑስ የትምህርት ክፍል በዘውግ ተኮር አቀራረብ በመምህሩ እና በተማሪው መካከል ያለውን ሚና በግልፅ ያሳይሃል::

#### 2.5.1. የመምህሩ ሚና

በሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህሩ ሚና ከፍ ያለ ሲሆን ትምህርቱ የተሻለ የሚሆነው መምህሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች

የሚፈልጉትን በሚያቀርብበት ጊዜ ነው:: በመሆኑም መምህሩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በመፃፍ ሂደት ይሳተፋል::

መምህሩ አውቀቱን በቀጥታ ወይም በተማሪዎች መፃፍ የሚታየውን ስህተት በማሳየት ሊያቀርብ ይችላል:: ከዚህም ሌላ መምህሩ ተማሪዎች መፃፍ ያለባቸውን ነገር እስኪረዱ ድረስ የታለመላቸውን ጽሁፍ እንዲቃኙ ሊፈቅድላቸው ይችላል:: በተጨማሪም መምህሩ የተማሪዎችን ፍላጎት ባጤነ መልኩ በጽህፍት ሂደቱ ሚና ይኖረዋል::

በሂደ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ወቅት መምህሩ የሚጫወተው ሚና ይኖረዋል:: በዚህ ረገድ በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህሩን ሚና አስመልክቶ /Devit ፣2003/ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል::

- በመፃፍ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያፈልቁ ማገዝ፣
- የመፃፍ ሞዴል ማቅረብና ጥሩ የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው ማበረታተት
- ዕቅድ እንዲያወጡ ማገዝ እና
- ከክፍል ውጪ የሚሰሩ የጽሁፍ መልመጃዎችን ማቅረብ ናቸው::

በሌላ በኩል የመምህሩን ሚና አስመልክቶ የሚነሳው ጥያቄ በተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል ጣልቃ ይገባል የሚለው ጥያቄ ነው:: ከዚህ አንፃር መምህሩ ለተማሪው ምንም አይነት ነፃነት ሳይሰጥ በቀጥታ ትምህርቱን የሚያቀርብ ከሆነ የተማሪውን በራስ የመተማመን ስሜት እንዳይጎለብት የሚያደርግ ይሆናል:: በዚህ የተነሳ በመፃፍ ወቅት ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አይበረታታም::

በተቃራኒው መምህር ለተማሪው ሙሉ ነፃነት ከሰጠ እና ስለሚጽፉት ጉዳይ ተገቢውን ማብራሪያ የሚያቀርብ ከሆነ ችሎታቸው ከፍ ያለ ተማሪዎች ብቻ የተፈለገውን ግብ ያሳካሉ:: በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የበዛ ነፃነት የሚኖር ከሆነ አነስተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ወደተሳሳተ አቅጣጫ ከመውሰዱም በላይ ተስፋ ያስቆርጣቸዋል::

በመሆኑም በሂደተ ዘውጋዊ ትምህርት ወቅት መምህሩ የተማሪዎቹን ችሎታ እና ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል:: ከዚህም ሌላ

መምህሩ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መፃፍ በሚማሩበት ክፍል ውስጥ ተጨባጭ ሚና ሊኖረው ይገባል::

በአጠቃላይ መምህሩ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማመቻቸቱም ባሻገር ተማሪዎች ወደተሻለ የመፃፍ ስልት ላይ እንዲደርሱ ልምዱን ያካፍላል:: በተጨማሪም የተሻለ አቀራረብ እንዲኖር ውይይቶችን ያካሂዳል ፣የተለያዩ የጽህፈት ሂደቶችን ይከተላል ::

### 2.5.2. የተማሪው ሚና

መፃፍን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ዋነኛው ተተኳሪ ናቸው::የሂደ ዘውጋዊ ተኮር አቀራረብን ተጠቅሞ ተግባቦትን በመፍጥር መፃፍን ለማስተማር የሚያስችሉ የንድፈ ሀሳብ ድጋፎች አሉ:: ተማሪው ለተለያዩ ፅሁፎች መጋለጡ ብቻ ሳይሆን ፅሁፉ የተደራጀበት ሞዴል ያሰፈልገዋል:: ከዚህ በዋላ የሚፅፉ ሲሆን በሚፅፉበት ጊዜ የሚከተሉትን ማለትም ማቀድ፣መንደፍ፣መከለስ እና ማስተካከያ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ መዋቅሩ ትክክለኛ የሆነ እና የፅሁፉን ዓላማ የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል::

በሂደዘውጋዊ ዘዴ ወስጥ ውጤታማ የሆነ ምላሽ እንዲኖር ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያመነጩ እና ይህንን ያመነጩትን ሀሳብ ማቅረብ ይገባቸዋል:: ይሁን እንጂ ይህ ብቻ በቂ ላይሆን ስለሚችል ሚና ጫወታ ሊኖር ይገባል:: በዘውግ ፅሁፍ ውስጥ የሚኖርን ሚና ጫወታ ለመተርጎም፣ለመተንተን እና ሀሳብን ከራስ አመለካከት አንፃር ለመግለፅ ሰፋ ያለ ዕውቀት ይጠይቃል::

በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ማለትም ተማሪዎች ሚና ጫወታ ሲኖራቸው ፅሁፉ ፍንጭ እንዲሰጥ ያስፈልጋል ::በመጨረሻም የቀረበው ፅሁፍ በተማሪዎች በራሳቸው እንደተፃፈ የሚያሳምን መሆን አለበት::

### ምዕራፍ ሶስት፡- የሙከራወን ሂደት ማከናወን

በዚህ ምህራፍ ስር በሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ መፃፍን ስታሰተምር የምትከተለው አካሄድ ቀርቦልሃል:: በክፍል ውስጥ ሁለት ተግባራትን የምታከናውን ሲሆን የመጀመሪያው ተግባር ተማሪውን በሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ማስተማር ነው:: ሁለተኛው ተግባር ደግሞ ተማሪዎች የመፃፍን ተግባር እንዴት እንደሚያከናወኑ ማስተማር ነው::ይህንን የስለጠና ማኑአል በተገቢው ሁኔታ ተከታትለህ

በመተግበር ሙከራው ውጤታማ እንዲሆን የበኩልህን ድርሻ እንድትወጣ በትህትና እጠይቅአለው::

## 3.1 የመማር ማስተማር ሂደቱን ማከናወን

ከዚህ ቀደም ውጤት፣ ሂደት እና ዘውግ ተኮር አቀራረቦችን ትኩረት አድርገን ተመልክተናቸዋል:: እያንዳንዱ አቀራረብ የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት:: ሂደት ተኮር አቀራረብ ፈጠራ የሚያነሳውን የጽህፈት ሂደት ችላ የሚል እና ብዙ ጊዜ ተቀባይነት ያለው መሳሪያ እና ትኩረት የሚያደርገው በመጨረሻው ውጤት ላይ ነው:: እንደዚህ አይነቱ አቀራረብ መርሀ ትምህርት ሲነደፍ፣ የትምህርትን ሂደት ለመቆጣጠር ስህተትን እና ፈተናዎችን ለመገምገም ይጠቅማል::

በሌላ በኩል ሂደት ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር አቀራረብ በተፃራሪ በጽህፈት ፈጠራዊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይሁን እንጂ የመፃፍ ድርጊቶችን እንደመቅዳት ቀላል አይደደለም:: ነገር ግን ሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ሲያቅዱ የበለጠ የማብራራት፣ የመከለስ እና በተለያየ ደረጃ ማረምን የሚያጠቃል ሲሆን አንባቢው እና የጽሁፍ አላማ የበለጠ ጠቃሚ ሲሆኑ የጽሁፉ የተግባቦት ሀይል ዋነኛው አንቀሳቃሽ ነው:: ይሁን እንጂ የክፍል ውስጥ ተግባራት ግልፅነት የሚጎድላቸው እና ተማሪዎች መፃፍን በተለያየ ደረጃ ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል:: የሂደት ተኮር ዋነኛው ችግር የማህበረሰቡን ጽሁፍ በመተውና የጸሀፊዎችን ፅሁፍ ከማህበረሰቡ አንፃር የሚመለከትበትን ሁኔታ ችላ በማለት የግለሰብን የመፃፍ ችሎታ በማሳደግ ላይ ያተኩራል::

በአንፃሩ የዘውግ አቀራረብ ሀሳብ ወይም ንድፍ ከመሆን ባለፈ ገላጭ መሆኑ ጠቀሜታ አለው:: ዘውግን በመግለፅ እና በመተንተን ዘውግ እንዴት እንደሚገነባ እና ወደተማሪዎቹ እንደሚተላለፍ በግልፅ ያሳያል:: በዚህ መሰረት ተማሪዎች በንግግር ተግባቦት ተቀባይነት ያለውን በዘውግ ምሳሌ የተገኙትን እውቀቶች ይጋራሉ::

የእያንዳንዱ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ሁለት ጠቃሚ ነገሮችን ማለትም ተማሪውን እና የክፍል ውስጥ ልምምድን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል:: ማንኛውም መርሃ ትምህርት እና የማስተማር ዘዴ ሲመረጥ

ከተማሪው ፍላጎትና የቀደመ ታሪክ ይኸውም የቀደመ የተማሪዎች የትምህርት ታሪክ፣ ፍላጎት እና ግብ ጋር የተገናኘ መሆን ይኖርበታል:: ዝርዝር እና የተለዩ ፍላጎቶችን ለመለየት የዘውግ  አቀራረብ አቅም አለው::

ቀላል እና ውጤታማ የሆኑ ሞዴሎችን ወደ ተማሪዎች ማሸጋገር ቀላል ጉዳይ አይደለም:: እንደ Swales (1990) አገላለፅ በመማረያ ክፍል ውስጥ ልምምድ ሲደረግባቸው ጥሩ ፅሁፎች እንዴት በትክክል እንደሚሰሩ እርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው:: የገላጭነት ሀይል እና አንዳንድ የመመሪያ መለኪያዎች ተመጣጣኝነት መኖር አለበት::

አገባብ፣ መዋቅር፣ አላማ እና ስነልሳናዊ ገፅታዎች እንደ ዘውጋቸው በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ መንፀባረቅ ያለባቸው ሲሆን ተማሪዎች የራሳቸውን ድርሰት ሲፅፉ ይህንን ሁኔታ መገመት አለባቸው (Harwood ፣2005:3):: እንደ Kin (2007) አስተያየት በዘውግ አቀራረብ ለአንባቢው እና ለፅሁፉ ትኩረት መስጠት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: በሌላ በኩል Kim (2005) እንደገለፁት የዘውግ አቀራረብ እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስናስተምር እንደ ድጋፍ ሰጪ ሆኖ ያገለግላል ::

የተማሪዎችን ስነልሳናዊ ገፅታ እና መዋቅራዊ ደንቦች የተለያዩ ዘውጎችን መሰረት አድርገው የሚፈጥሩት ተግባቦቶች ብዙ ጊዜ ውሱንነት አለባቸው በመሆኑም የመፃፍ መምህሩ ተማሪዎችን በመምራት ፣በመደገፍ እና በመረዳት በኩል በተለያዩ ዘውጎች መነሻነት ከፅሎቶቻቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛል::

## 3.2 የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብን መለማመድ

1. የሂደተዘውጋዊ  አቀራረብን ለተማሪዎች ካስገነዘብክ በዋላ በየክፍለጊዜው የሚቀርቡ    ፅሁፎችን ማስተዋወቅ አለብህ::
2. ተማሪዎች በቡድን ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው መንገር ::
3. ተማሪዎች ስራቸውን በየራሳቸው እንዲሰሩ እና ያላቸውን መረጃ ለየቡድኑ እንዲያካፍሉ ንገራቸው፡፡ተማሪዎቹ ይህንን ተግባር ሲያከናውኑ በክፍሉ ውስጥ ዞር ዞር እያለክ ያንተን እገዛ እንዲፈልጉ አድርግ::

### 3.3 የሚያጋጥሙ ችግሮችን መቆጣጠር

የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ስራ ላይ በሚውለበት ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎች  ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል:: አንዳንድ ተማሪዎች ስለአቀራረቡ ጥሩ ስሜት ላይሰማቸው ይችላል:: ወይም ስለአቀራረቡ አውንታዊ የሆነ አስተሳሰብ ሊያሳድሩ ይችላሉ:: በዚህም የተነሳ  የሂደተዘውጋዊ አቀራርብን ላይቀበሉት ይችላሉ::

በልምምዱ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት በስልጠና ማኑዋሉ ከቀረበልህ ንድፈሀሳባዊ እና ተግባራዊ ሁኔታዎች ጋር በሚገባ መተዋወቅ ይኖርብሃል:: ስልጠናውን በተገቢ ሁኔታ መከታተል ትምህርቱን ተግባራዊ በምታደርግ ጊዜ የሚያግጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ያግዝሃል::

የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ስራ ላይ በሚውለበት ጊዜ ስለሚኖረው መሰረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ልታስጨብጣቸው ይገባል:: ይህ ማለት ስለሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብ ያለህ ዕውቀት የሚያጋጥሙህን ችግሮች ለማቃለል እና አቀራረቡን ስራ ላይ ለማዋል ያግዝአል:: ስለጠናው ከተጠናቀቀ በዋላ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሂደት ዘውጋዊ  አቀራረብ ታካሂዳለህ:: በዚህን ጊዜ ተመራማሪው አካሄዱ በትክክል ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ምልከታ ያካሂዳል::

አባሪ ሁለት

# የሂደት ዘውጋዊ የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር

## ዘጠነኛ ክፍል(የተማሪው)

ጥር 2007

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


መግቢያ......................................................................................................174
ክፍል አንድ………………… .................................................................. 176
ፈሪው ወታደር……………................................................................... 176
ክፍል ሁለት.................... ..................................................................... 185
ዲን፡ ሱዊፍት………….......................................................................... 185
ክፍል ሶስት………………. ..................................................................... 193
አይናለም………….................................................................................. 193
ክፍል አራት……………… ..................................................................... 199
ለወሬ ሞትኩ ይበሉ………………………………………………………………199
ክፍል አምስት……………. ...................................................................... 206
ግርግር …………………… .................................................................. 206
ክፍል ስድስት……………....................................................................... 212
ሰብለወንጌል……………….................................................................... 212
ክፍል ሰባት………………. ..................................................................... 217
ሱጴ……………………… ...................................................................... 217
ክፍል ስምንት……………. ......................................................................222
በሰርጉ ማግስት………….. ...................................................................... 222

## መግቢያ

ተማሪዎች በዘጠነኛ ክፍል ከሚማሯቸው የቋንቋ ክሂሎች መካከል መፃፍ አንዱ ነው:: መፃፍ የፊደልን ቅርፅ ለይቶ ከመፃፍ ጀምሮ አዲስ ሀሳብን በማፍለቅ ቃላትን እና ሀረጋትን አቀናጅቶ አረፍተ ነገርን አረፍተ ነገሮችን አቀናጅቶ አንቀጽን በማዋቀር ሀሳብን በተደራጀ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ የሚያስችል ሂደታዊ ተግባር ነው::

በዚህ የ9ኛ ክፍል ትምህርት ደረጃ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል በተለይም ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ ይዘቶች ተመርጠው በስምንት ክፍሎች ተመድበው የቀረቡ ሲሆን ከተለያዩ ምንጮች የተወሰዱ ምንባቦች ናቸው:: ምንባባቱ ከተማሪዎች እድሜ ችሎታ  እና ደረጃ ጋር የተገናዘቡ እና ከመርሐ ትምህረቱ ጋር የተገናዘበ ነው ተብሎ ይታሰባል:: ምንባባቱን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች አስቀድመው ከተነሱት ነጥቦች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ሙከራ ተደርጓል::

ሀ. የትምህርቱ አላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተከታተላችሁ በኋላ:-

- ለቃላት ቀጥተኛና አግባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፣
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፣
- አንቀጽ ትፅፋላችሁ፣
- ተራኪ ድርሰቶች ትፅፋላችሁ፣
- ሀይለ ቃልንና መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፣
- ሀረጎችን መነሻ በማድረግ በራሳችሁ አበባል ትፅፋላችሁ::
- ሀሳቦችን በአንድ ቃል ትገልፃላችሁ::
- አረፍተ ነገሮችን ታሟላላችሁ::

ለ. ተግባራት

- ለቃላት ቀጥተኛ እና አገባባዊ ፍቺ መስጠት::
- ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም::
- አንቀፅ መጻፍ::
- ተራኪ ድርሰት መፃፍ::

- የአንቀፅን ሀይለቃልና መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን መለየት::
- አንቀፅና ተራኪ ድርሰት መፃፍ::

ሐ. ዘዴዎች

- ❖ ገለፃ
- ❖ የጥንድና የቡድን ውይይት
- ❖ የሂደ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ
- ❖ መ. ግምገማ

- ✓ በየግል የሚፅፏቸውን አንቀፆችንና ተራኪ ድርሰቶች መተራረም ተማሪዎች የሚያከናውኑት
- ✓ አዘጋጅተው የሚፅፏቸውን አንቀፆች እና ተራኪ ድርሰቶች መተራረም በቡድን የሚከናወን
- ✓ ተማሪዎች የሚፅፉትን አንቀፅና ተራኪ ድርሰት የመፃፍ ሙከራዎች መምህሩ የሚያካሂደው
- ✓ ሠ. ማጣቀሻ መፃፍ

ሀዲስ አለማየሁ:: /1958/:: ፍቅር እስከመቃብር:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

በዓሉ ግርማ:: /1993/:: ከአድማስ ባ ሻገር:: አዲስ አበባ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

----------------- :: /1975/ :: ሀዲስ:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

ደረጀ ገብሬ:: /1996/:: ተግባራዊ የጽህፈት ማስተማሪያ:: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት::ዳኛቸው ወርቁ:: /1988/:: የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ:: አዲስ አበባ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ /2ኛ ዕትም/:ማረው ዓለሙ:: /1996/:: በሳል ድርሰት ማስተማሪያ:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

## ክፍል አንድ

## ፈሪው ወታደር

### መመሪያ ለተማሪዎች;-

### ናሙና አንቀፅ፡-1

### ተግባር አንድ:-

*ያለፈው መልካም ጊዜ*

*ብዙዎቻችን የዛሬ አምሳ እና ስድሳ ዓመት ወይም ከዚያ በፊት ስለነበረው ስለሰው የኑሮ እና ስሜት፣ በጠቅለቀለቀው እነደዛሬው ስላልተከላለሰው ያገራችን ባዕል፣ ስላልተወሳሰበው የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ስርዓትና ዝንባሌ ሳናሰማ አለቀረንም:: ልብ አድርገው የሚያዳምጡት ወጣቶችስ ፣በ20ኛው መቶ ዘመን ስለመፈጠራቸው ምን ይሰማቸዋል ?በበኩሌ ሁኔታዎችን በማሰብና በመመኘት ብቻ ለማማሻል በመሞከር የገዛ ጭንቅላቴን ለማዞር በማልቃጣበት፣ተፈጥሮን ከፍጥረቱ ጋር አስማምቶ ለመኖር በምችልበት በድሮ ዘመን ተፈጥሬ ብሆን ኖሮ እንዴት በወደድኩ ነበር:*

1.*ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::*

- *የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?*
- *ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?*
- *ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?*
- *ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?*

**ተግባር ሁለት:-**

- በቡድን አራት አራት ሆናችው "**ያለፈው ዓመት ትዝታዬ**" በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ::

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

____________________________________________________________

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

**ተግባር ሶስት:-**

**በቡድን በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

**አንቀጽ**

አንቀጽ ማለት አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለጽ ሲባል በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሀሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርጽ ነው:: አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ሀይለ ቃል /መንደርደሪያ አረፍተ ነገር/ እና ከአንድ በላይ መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን ሊይዝ ይችላል:: የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት:-

ምሳሌ

የተምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል:: ከሁለት አመት በፊት በእግር ኳስና በመረብ ኳስ ስፖርቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በነበሩ ተማሪዎች መካከል ውድድሮች ተካሂደው ነበር:: ባሳለፍነው የትምህርት ዘመንም የውድድር አይነቶቹን ከሁለት ወደ አራት በማሳደግ በእግር በመረብ በእጅና በቅርጫት ኳስ የውስጥ ውድድሮችን አካዷል:: በያዝነው የትምህርት ዘመን ደግሞ በአራቱም የውድድር አይነቶች የውስጥ ውድድሮች ከማካሄዱም በላይ የከተማው ባህልና ስፖርት መምሪያ ባዘጋጀው የዘመኑ ውድድር ላይ በአግር ኳስና በመረብ ኳስ በመሳተፍ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል::

በዚህ ምሳሌ እንደሚታየው በአንቀጹ ሀይለ ቃል የትምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል:: በሚል የሰፈረው ዋና ሀሳብ ከሱ በኋላ በመጡት መዘርዝር አረፍተነገሮች ተብራቷል:: በመዘርዝር አረፍተነገሮቹ በመጀመሪያ የስፖርት እንቅስቃሴው በሁለት የውድድር አይነቶችና በውስጥ ውድድር ጀምሮ በየጊዜው ባደረገው መ ሻሻል የውድድር አይነቶቹን ወደ አራት እንዴት እንዳሳደገና ከውስጥ ውድድሮች በተጨማሪ የውጪ ውድድሮችንም መሳተፍ እንደጀመረ ደረጃ በደረጃ ተብራርቷል::

(9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ፣2004፣45)

ቀጥሎ ፈሪው ወታደር በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድረሰት ቀረቦላቸዋል::

## ፈሪው ወታደር

አንድ ትልቅ ጦርነት ሲካሄድ ተካፋይ የነበረ አንድ ፈሪ ወታደር ነበር:: በጦርነቱ አብረውት የተሰለፉ ጓደኞቹ ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተው በጀግንነት ተዋጉ:: እየተመቱም አንዳቸው ባንዳቸው ላይ እየተደራረቡ ወደቁ:: ይህንን ያየው ቡቡው ወታደር ሆዱ ተሸበረበት ጉልበቱም ቄጤማ ሆነበት:: ከዚያ ስፍራ ከሬሳ በስተቀር አንድም የሚያውቀው ወታደር ማየት አልቻለም ነበር::

ጦርነቱ እሱ ባለበት በኩል እያደር እየተፋፋመና እየተጋጋለ መጣ:: በዚህ ጊዜ መክቶ መቋቋም እሩጦም ማምለጥ እንደማይችል ተገነዘበ እንግዲህ ከዚህ በቀር ሌላ ነገር የሚያድነኝ የለኝ አለና የተደራረቡትን እሬሳዎች ፈነቃቅሎ ገባ:: አንዱን እሬሳ በላዩ ላይ ጭኖ ትንፋሹን አሳጥሮ ተኛ::

የወዲያኛውም የወዲያኛውም ወገን በሾተል እየተጠዛጠዘ በፎቄ እየተጓመደ እያወከ እየተዋጋ እየተተራመሰ እሱ ወደ ተሸሸገ በት በጣም እየቀረበ መጣ:: አጠገቡ በደረሰ ጊዜ የፈረሰ አጓዳ ከአሁን አሁን ያደባየኛል ሲል ሲፈራ ቆይቶ እንደምንም እግሩን ይሰበስባል:: ወዲያው እንደ ተዋጊ ፈረሰኛ አየው ከፈረሱ ላይ እንደሆነም የዚያን ሳይቆስል የሞተ ሰው እግር በቀጭን ሹልጦሩ ጠቆም ጠቆም እያደረገ ይሄስ የሞተ አይመስልም አለ በዚህ ጊዜ ያ በውሸት የሞተው ወታደር አይ አይ:: እያለና እግሩን እያንፈራገጠ እሺ ተወኝ ሞቻለሁ አለ አፉን በእጁ እየተመተመ::

/ዳኛቸው የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ 1977 ፣178-179 ተሻሽሎ የቀረበ/

**ተግባር አራት:-**

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማሰብ ዕሁፉን ደጋግመው ያነባሉ::

1. ዕሁፉ የሚጀምረው እና የሚያልቀው እንዴት ነው?
2. የዕሁፉ ቅደምተከተላዊ አካሄድ ምን ይመስላል ?
3. ዕሁፉ ምን ያህል ደረጃዎችነ አልፏል?
4. የእያንዳንዱ የዕሁፍ ደረጃ ምን ጥቅም አለው?

**ተራኪ ድርሰት**

ተራኪ ድርሰት በጣም ከተለመዱት አራት ዋና ዋና የድርሰት አይነቶች አንዱ ነው:: የቀሩት ሶስቱ ስዕላዊ ድርሰት ገላጭ ድርሰትና አመዛዛኝ ድርሰተ በመባል ይታወቃሉ::

ተራኪ ድርሰት ድርጊቶችን እና ሰንሰለታዊ እውነቶችን የድርጊት የጊዜ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ እንግዲህ እንዲህ ሆና እንግዲህ እንዲህ ተደረገ:: እያለ የሚተርክልን ጽሁፍ ነው:: ታሪኩን የሚነግረንም ራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ሊሆን ይችላል:: አለበለዚያም ድርጊቱን የተመለከተ የደረሰበት በልምድ ያገኘው ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል:: ከላይ የቀረበው ተራኪ ድርሰትም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል::

**ተግባር አምስት:-**

ዓላማ:-የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን መልሶ ማደራጀት

<u>አካሄድ</u>

1. ፅሁፉን መልሳችሁ አደራጁ፣
2. ለፅሁፉ ተስማሚ ርዕስ ስጡ፣
3. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ በቀረበው ፅሁፍ ላይ ተነጋገሩ፣
4. በተገኘው ውጤት ላይ በመወያየት አቃሚ ነጥቦችን ማብራራት

i. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከል አንድ ተራኪ አንቀጽ ይወጣቸዋል:: አረፍተ ነገሮቹን በጥንቃቄ መርምራችሁ ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሉ:: ለድርሰቱም ርዕስ ስጡ::
   1. በክረምት ለእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቼለት ነበር::
   2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ አክስቴ ብቻዋን እንደምትኖር የነገረችኝ ትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብዬ አሳብ ገባኝ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝም ማሰላሰል ቀጠልኩ::

3. በልጅነቴ የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ወደፍቼ ከተማ በሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም::
4. ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ ባረጀውና ቁመቱ ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጥራት ወሰንኩ::
5. የአክስቴን አይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህር ዛፍ ጫካ ውስጥ ጥቂት መጓዝ ነበረብኝ::
6. እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብቀኝ ጉቶ ላይ አረፍኩ:: ከዚያ በኋላማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው አክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር በመካከል የሆነውን ነገር ሁሉ አላስታውስም::
7. ድካሜን ሁሉ ረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጪው በር እንደደረስኩ በሩን ቶሎ ቶሎ አንኳኳሁ:: ነገር ግን ማን ነህ የሚለኝ አጣሁ::
8. እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ::
9. የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርባት የገጠር መንደር ከአዲስኌ ግማሽ ቀን ተጉዤ ስድስት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ::
10. እንደገናም በሩን ደጋግሜ ደበደብኩት ምንም መልስ የለም:

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ii. ድርሰታችሁን ከሌላ ቡድን ጋር በመለዋወጥ ከሐሳብ ፍሰቱ፣ ከድርጊትና ጊዜ ቅደም ተከተል አጠባበቁ፣ ከስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀሙ አንጻር መርምራችሁ የቡድናችሁን አስተያየት ስጡ::

**የትረካ ንድፍ**

ጭብጥ ------------------------------------------------------------------------------------------

ማስተዋወቂያ -------------------------------------------------------------------------------------

ፀባህረና ገለፃ ----------------------------------------------------------------------------------

- ------------------------------ ------------------------------------
- --------------------------------- -----------------------------------
- ---------------------------------- ----------------------------------

የት -----------------------------------------------------------------

መቼ------------------------------------------------------------------

ውስብስብነት -----------------------------------------------------

ድርጊቶች

- ----------------------------------- ------------------------------
- --------------------------------------- ------------------------------
- ---------------------------------------- -------------------------------

መፍትሄ --------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

III. የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ

<table>
<tr><td colspan="2">ርዕስ:- ሰነፉ ገበሬ<br><br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________</td><td rowspan="3">የመምህሩ<br>አስተያየት</td></tr>
<tr><td>የብጤ አስተያየት</td><td>ቡደን</td></tr>
<tr><td>/ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br><br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር</td><td></td></tr>
</table>

# ክፍል ሁለት

## ዲን: ሱዊፍት

### ናሙና አንቀፅ:-2

*ፅልመት የመሰለው ጠጉሩ አድጎ ጎፍሯል፣ የሶስት ወይም የአራት ቀን ዕድሜ ያለው ጢሙ ጉንጮቹና አራት ማዕዘን አገጩ ላይ ሲታይ አጥንት ላይ የሚተራመስ ጉንዳን ይመስላል:: ጠይም ፊቱ ላይ ስጋ አይታይም፣ ጉንጮቹ ላይ ያሉት አጥንቶች እንደአለት ቆመው ሰው ላይ ያፈጣሉ:: ድፍጥጥ ብሎ ወርዶ ቀዳዳዎቹ ሰፋፊ የሆኑትን አፍንጫውን እንደወናፍ ከፍዝቅ እያደረገ፣ ወፍራም ከንፈሮቹን ገጥሞ፣ ከማነበብ ብዛት ደካክመው የቀሉትን መካከለኛ ዓይኖቹን ውልብ ውልብ እያደረገ ያነባል::*

## ተግባርአንድ:-

*መመሪያ ለተማሪዎች;-*

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ገላጭ  ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::

- የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
- ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
- ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
- ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

## ተግባር ሁለት:-

- በቡድን አራት አራት ሆናችው "ኢስ ሜዳ" በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ::

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

__________________________________________________

## ዲን: ሱዊፍት

ዲን ሲዊፋት የሚባለው የእንግሊዝ ደራሲ አዲስ አሽከር በቀጠረ ቁጥር እንዲህ ይለው ነበር:: እንድትፈፅማቸው የምለምንህ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው:: አንዱ የምለምንህ ነገር ምን ጊዜም ቢሆን በቤትህ ውስጥ ስትተላለፍ ከአንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ አንደኛው ክፍል ስትገባ በሩን እንድትዘጋ ነው:: ሁለተኛው የምለምንህ ነገር እንደዚሁ ሁሉ ካንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ ደጅ ስተሄድ የከፈትከውን ቤት ዘግተህ እንደትሄድ ነው::

አንዱ አገልጋይ ከእለታት አንድ ቀን ወደእሱ ዘንድ ቀርቦ እህቴ ልትዳር ነውና ለሰርግዋ እንድሄድ ፍቀድልኝ አለው:: ዲንሱዊፍትም ደስ እያለው ፈቀደለትና እሱ ከሚቀመጥባቸው ፈረሶች አንደኛው ተጭኖበት አንድ ሌላ አገልጋይ ተከትሎት ሄዶ ከቤቱ አድርሶት እንዲመለስ አዘዘ:: አገልጋይም ከደስታ ብዛት ጌታው ያስጠነቀቀውን ትእዛዝ ዘንግቶ በሩን ከፍቶ ሳይዘጋው ሄደ:: ከሄደ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ዲን ሌላ አገልጋይ ጠራና ፈረስ ጭነህ ጋልበህ ድረስባቸውና ምንም ያህል ርቀው ቢሄዱ ከደረሱበት ቦታ ተመልሰው በፍጥነት እንዲመጡ ንገራቸው ብሎ ላከው::

የተላከው አገልጋይ በፈረስ ጋልቦ ግማሽ መንገድ እንደ ሄዱ ደረሰባቸውና የጌታቸውን ትዕዛዝ ነገራቸው:: ፈቃደ ተቀብሎ የነበረው አገልጋይ ምክንያቱ ምን ይሆን እያለ ደንግጦ እየሰጋ ተመልሶ መጣ ከጌታው አጠገብ ቀረቦ እነሆ ተመልሼ መጣሁ ትዕዛዙን ይሰጡኝ አለው:: ዲንሱዊፍት አይ የጠራሁህ ለሌላ ነገር አይደለም:: ከፍተህ ትተኸው የነበረውን በር ዘግተህ እንድትሄድ ነው:: ብሎ መለሰለት::

(9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ፣2004፣154)

## ተግባር ሶስት :-

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
   - ❖ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?

- ❖ ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
- ❖ ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
- ❖ ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

3. በትረካው የተገለፁት ድርጊቶች የከናወኑት የት ነው?
4. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
5. ትረካውን የተረከልን ማን ነው

**ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ**

በጽሁፉ ውስጥ በስርዓተ ነጥቦች ዋነኛ ተግባር የፅሁፉ መልእክት ሳይድበሰበስ በአፍታ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰት ማገዝ ነው:: በጽሁፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የስርዓተ ነጥብ አይነቶች መካከል ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ ተጠቃሽ ናቸው::

/…/ ነጠብጣብ

1. ከጽሁፍ ወይም ከጥቅስ ውስጥ የተወሰነውን ቃል ወይም ክፍል ያስቀረነው መሆኑን ለማመልከት
   ምሳሌ አባቷን አታውቅ….. እንዲሉ
   
   አባቷን አታውቅ አያቷን ትናፍቅ::
2. በፈጠራ ድርሰት ውስጥ አንባቢ የቀረውን በሀሳቡ እንዲሞላና የሚሆነውን እንዲረዳ ሲፈልግ
   ምሳሌ
   
   አልቀመጥም እኔ የመጣሁት ካንተ አንዲት ቃል ተንፈስልኝ::
   
   ስትለው….

/፦/ ድርብ ሰረዝ

/ሲሳይ ንጉሱ ፦ሰመመን፦ 1996 183/

የሀሳብ ቁርኝት ያላቸውን አረፍተነገሮች አጣጥሞ ለማቅረብ ያገለግላል:: ድርብ ሰረዝ ነገ መቋጫነት ከምንጠቀምበት አራት ነጥብ የሚለየው ደግሞ አራት ነጥብ አረፍተ ነገሩ ማለቁን ከሚጠቁመን በስተቀር በሱና ከኋላው በተሰለፉት ሌሎች አረፍተነገሮች መካከል ያለውን የሐሳብ

## ተግባር አራት :-

**የሚከተለው አንቀጽ ስርዓተ ነጥቦች የሚገቡባቸው 14 ክፍት ቦታዎች አሉት**:: የቀረበውን ታሪክ በጥንቃቄ በማንበብና የተሰጡት 4 ስርዓተ ነጥቦች የት ቦታ እንደሚገቡ በማጤን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በክፍት ቦታዎች ላይ ሙሉ::

1. አራት ነጥብ /:: /
2. ነጠላ ሠረዝ / ፣/
3. ቅንፍ ( )
4. ትዕምርተ ጥቅሰ / /

በጣሊያን ወራራ ዘመን ለሀገራቸው ነፃነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር 1 ዘርጋናጂ 2 ቁመቱ ረጅም 3 አጥንቶቹ ሰፋፊ 4 መልከ ቀይ 5 ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሶስትዮሽ የተሸረበ ነበር6 ያ ፀጉሩ በጀርባውና በትከሻው ላይ ተንዥርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናፅፈዋል 7 ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆን 8 ጠቅላላ ገፅታው የሰው አይን የሚማርክ ሸበላ 9 ቆንጆ 10 ነበር ዘርጋ ለአራት ዓመታተ ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖር 11 ሹርባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታቻ ወርዶ ይታይ ነበር 12 በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሟት ያየችው ሴት ሁሉ 13 አይኔ ይፍሰስልህ ሳትል አታልፍም ነበር 14

/ዓለም እሸቱ አለማየሁ ኑራን በመጥቀስ 1999 24/

## ተግባር አምስት :-

***የታሪክ ትንበያ***

*ጀቡዱ ከዕለታት አንድ ቀን ከጎሮቤቶቹ አንዱ ቢዙ የተቀበረ ገንዘብ እንዳገኘ ሰማ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጀቡዱ እየከፋው ሄደ:: ይህን ያህል እየለፋ እሱ ያላገኘውን ሀብት ምንም ያልደከመ ያልለፋ ሰው ሲያገኘው ፣ጌትንት ተከታትሎ ሲመጣለት ሰምቶ ነገሩ አልገባህ አለው፣ ብስጭት አደረበት፣ በወፍጮው ላይ ያውለው የነበረ የስራ ትጋት እያነሰ ሄደ፣ይህም ቸልታው ሲጠራቀም የቆየውን ሀብቱን ይጎዳው ጀመር::*

***ለተማሪዎች መመሪያ:-***

*ይህ ጥያቄ በቃል የሚደራጅ ተግባር ሊሆን ይችላል:: ተማሪዎች ለመምህሩ ታሪኩ የሚቀጥልበትን አማራጭ ይነግሩታል:: ተማሪዎች ታሪኩን የሚጨርሱበት ሁኔታ በመቅዳት በመፃፍ እና በስዕል ሊቀርብ ይችላል::*

- *የቀረበውን ታሪክ በጥሞና አንብብ*
- *ታሪኩን የምታሳድግበት የተለያዩ መንገዶችን አስብ*
- *በደንብ የወደድከውን ሀሳብ ምረጥና ታሪኩን ጨርስ*

***የቀረበው ታሪክ የሚያልቅበትን ሁኔታ ተንብየህ በፅሁፍ አቅርብ::***

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

# የፅሁፍ ማዕቀፍ

| | |
|---|---|
| ዓላማ | ሀሳባዊ ታሪክን መናገር/በዕውነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል/ |
| | |
| ማዕቀፍ | |
| ርዕስ | |
| መቼት | ማን? የት? መቼ? |
| የድሪጊቶች መሆን | ገፀባህሪው እንዴት ይሳተፋል? |
| ችግር | ግጭቱ /ችግሩ/ ምንድን ነው? |
| መፍትሔ | ችግሩ እንዴት ተቃለለ? |
| ምሳሌ | |
| የቋንቋ ገፅታ | የኃላፊ ጊዜ<br>ገፀባህሪን መግለፅ<br>ክርክር<br>ምናባዊ ፈጠሪ ለማካሄድ ገላጭ ቋንቋ መጠቀም |

**የትረካ ንድፍ**

**ጭብጥ** ------------------------------------------------------------------------------

**ማስተዋወቂያ** ---------------------------------------------------------------------------

**ገፀባህረና ገለፃ** ----------------------------------------------------------------------

- ---------------------------  ------------------------------------------
- ----------------------------  ------------------------------------------
- -----------------------------  ------------------------------------------

**የት** -------------------------------------------------------

**መቼ**--------------------------------------------------------

**ውስብስብነት** ---------------------------------------------

**ድርጊቶች**

- --------------------------------  ----------------------------------------
- ---------------------------------  ---------------------------------------
- ----------------------------------  -----------------------------------------

**መፍትሄ** ---------------------------------------------------------------------------------

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

| | **የመምህሩ አስተያየት** |
|---|---|
| ርዕስ:- አብዲሳ አጋ | |

| **የብጤ አስተያየት** | **ቡደን** |
|---|---|
| /ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር | |

# ክፍል ሶስት

# አይናለም

**ናሙና አንቀፅ፡-2**

…ትንሽ ፀጥ ብላ እንደቆየች አንድ ድምፅ በሩቅ እነደሚሰሙት የብዙ ንብ መዝሙር የሚዝገመገም ድምፅ የሰማች መሰላት እና አንገትዋን ወደ ላይ ሳብአድርጋ፣ አንድ ጆሮዋ ድምፁን ወደሰማችበት ወገን ደቅና ብታዳምጥ ጠፋ:: የለም ብላ አንገትዋን ስትሰበስብና ጆሮዋን ከደቀነችበት ስትመልስ ደግሞ መጣና ለትይዘው ስትል ደግሞ ጠፋ:: እንዲሁ እየሄደ ከሚመለሰው የአየር ማዕበል ጋር ድምፁም እየሄደ ሲመጣ ፣እሷም ጨብጣ ለማስቀረት አንድ ጊዜ ቀኝ አንድ ጊዜ ግራ ጆሮዋን እየደቀነች ሲያመልጣት ቆየና በሁዋላ መሄዱን ትቶ መምጣቱን ቀጠለ:: ሰብለወንጌል ያን ተንኮለኛ ድምፅ ከሚሸሽበት በጆሮዋ አባራ ይዛ እንዳመጣችው ሁሉ በጣም ደስ አላት:: ያ ከትንሽ ጊዜ በፊት ጠልሞ፣ከስሎ የነበረ ፊትዋ እንደንጋት ሰማይ ወገግ አለ::ያዘችው፣ ማረከችው፣ ምን እንደሆነ እስታውቅ ቸኮለች ፣እሱም ትንሽ በትንሽ እየቀረበ እየጎላ

## ተግባርአንድ:-

***መመሪያ ለተማሪዎች;-***

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
    - የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
    - ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
    - ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
    - ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

## ተግባር ሁለት:-

በቡድን አራት አራት ሆናችው **“ፀጥ ባለው ሌሊት”** በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ::

## ተግባር ሶስት:-

**በቡድን በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1) ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::
2) የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
3) አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
4) አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
5) አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::

## አይናለም

ቀደም ሲል አይናለም ከሰገነቱ ላይ ቆማ በምሽት  ጀንበር ብርሃን ጋዜጣ ስታነብ አያት ልቡ ካለችበት ዘላ ከጉሮሮው ላይ የተወተፈች ይመስል ትንፋሹ ታነቀ:: ጀንበሯ ሳትጠልቅ ትንሽ እንድትቆይ ሊማለድዋት የሚፈልጉ ይመስል ርግቦች ከጣራው ላይ እየተነሱ ወደ ጀንበርዋ አቅጣጫ ይበሩ ነበር:: አይናለም ነጭ ጉም በመሰለው የሃገር ልብስም ነጠላዋን ክንፍ አድርጋ እያውለበለበች የምትበር መስላ ትታየው ነበር:: ነፍስ የበተነው ጠጉርዋ የምሽት ጀንበርዋን ብርሃን እየጋረደ:: በደኑ ነበር ያንን ስሞተኛ የእንጨት ደረጃ የወጣው:: ደረጃው ሳይሆን ልቡ የሚያቃስት ነበር የሚመስለው::

ፊታውራሪ አሉ የሉም::

የት እንደሄዱ ለመጠየቅ አልፈለገም:: ፊቷ ላይ የሚተረማመሰው ደም ልቡን አተረማመሰበት:: በሚንቀጠቀጡት ከንፈሮቹ ምንድን ነው የምታነቢው አላት አሮጌ የአዲስ ዘመን  ጋዜጣ ቅጂ መሆኑን እያወቀ አሮጌ ጋዜጣ አለም ሁሉ ወደ ሙዚቃ ተለውጦ የእለቴ ወንዝ እየተዘፈነ የሚወርድ ዛፎች ሁሉ እየዘፈኑ ዳንኪራ የሚረግጡ ይመስለው ነበር::

አዲስ ጋዜጦች አምጥቼልሻለሁ... እ.... ጥቂት መጻህፍት ይገፎልሽ መጥቼ ነበር ብሎአት ጋዜጦቹንና መፃህፍቱን ሊሰጣት እሱ ሁለት እጆቹን ሲዘረጋ እርስዋም ለመቀበል እጆቿን ስትዘረጋላት ድንገት እጆቻቸው ተያያዙ::

/በዓሉ ግርማ ሐዲስ 1982 ገጽ 12

## ተግባር:- አራት

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
    - የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
    - ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
    - ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
    - ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?
3. በትረካው የተገለፁት ድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
4. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
5. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

II. ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች የያዙት ፅንሰ ሀሳብ ሳይዛባ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር ጎን የተሰጡትን ሀረጎች መነሻ በማድረግ በራሳችሁ አባባል ጻፏቸው::

1 -በድንገት ጉሮሮው ላይ… /ልቡ ካለችበት ዘላ ከጉሮሮው ላይ የተወተፈች ይመስልትንፋሹ ታነቀ/

-------------------------------------------------------------------------------------------------

2- ልቡን ያተረማመሰበት…. /ፊትዋ ላይ የሚተረማመሰው የምሽት ጀንበር ብርሃን ልቡን አተረማመሰበት/

-------------------------------------------------------------------------------------------------

3-እየዘፈኑ ዳንኪራ……… /ዛፎች ሁሉ እየዘፈኑ ዳንኪራ የሚረግጡ ይመስለው ነበር::/

-------------------------------------------------------------------------------------------------

4-በድንገት እጆቻቸው የተያያዙት….. /እርስዋ ለመቀበል እጆቿን ስትዘረጋለት ድንገት እጆቻቸው ተያያዙ::

## የትረካ ንድፍ

ጭብጥ ---------------------------------------------------------------------------------------

ማስተዋወቂያ ---------------------------------------------------------------------------

ገፀባህረና ገለፃ ---------------------------------------------------------------------------

- ---------------------------- ---------------------------------------------
- ------------------------------ ---------------------------------------------
- ------------------------------- ---------------------------------------------

የት -----------------------------------------------------------

መቼ-------------------------------------------------------------

ውስብስብነት -------------------------------------------------

ድርጊቶች

- -------------------------------- ---------------------------------------
- ------------------------------------ -----------------------------------------
- ------------------------------------- ---------------------------------------------

መፍትሄ ---------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ:- በመስቀል ዋዜማ<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________ | | **የመምህሩ**<br><br>**አስተያየት** |
| **የብጤ አስተያየት** | **ቡደን** | |
| /ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br><br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር | | |

# ክፍል አራት:

## ለወሬ ሞትኩ ይበሉ

***ናሙና አንቀፅ** :-4*

> ፀዳለ ሀብቷ የተፈጥሮ ውበቷ ብቻ ነው:: ጫማ የላትም ፣እግሯ ግን እንሶስላ ይመስላል፣ተረከዟ ከሎሚ ያምራል::ፀጉሯን ውሃ የሚነካው ዝናብ ሲደበድበው ብቻ ነው ፣ሽቶና ዘይት አያወቅም ፣በሳሙና ለመታጠብ እንኳእድል አላገኘም ፣ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዷል ::የተከበረውን ትከሻዋን አጥለቅልቆታል ፣ጫፉም ሀረጉን ሽንጧን አልፎታል:: መዘናፈሉም መላልሶ ያጠፉት ይመስላል::ዓይኖቿ ኩል አያወቁም፣ነገር ግን እንደንጋት ኮከብ ያበራሉ::ጥርሶቿ ብርሃን ያስተጋባሉ ፣የሚፋቁትም አልፎአልፎ ነው:: ጥፍሮቿ ቀለም አላዩም ፣ሆኖም ውበታቸው ዕፁብ ድንቅ ነው:: ድህነትና ውበት በአንድ አካል ላይእንደዚህ ያለ ህብር ሲኖራቸው በፀዳለ ላይ ብቻ ነው::
>
> (ዳኛቸው ወርቁ፣1989፣168-169)

## ተግባርአንድ:-

***መመሪያ ለተማሪዎች**;-*

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
   - ✓ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
   - ✓ ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
   - ✓ ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
   - ✓ ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

## ተግባር ሁለት:-

በቡድን አራት አራት ሆናችው "**ፀጥ ባለው ሌሊት**" በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ::

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

____________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

____________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________

## ተግባር ሶስት:-

**በቡድን በመሆን የጻፉችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

## ለወሬ ሞትኩ ይበሉ

ጢት ማታ ከመኝታዬ ተነስቼ ፊቴንና እጆቼን ታጥቤ ወደ ሳሎን እንደገባሁ ሬዲዮኔን ከፍቼ ዜና መስማት የቆየ ልማዴ ሆኗል:: የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን እንዲሁም ሌሎች የሀገራችን ሬዲዮ ጣቢያዎችን ቢቢሲንም ሆነ ቮይስ ኦፍ አሜሪካን ዶቼቬሌንም ሆነ ሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናልን ወይም ሌላ ሬዲዮ ጣቢያ ስከፍት አሜሪካን አገር ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት የሚገሰግሰው አውሎነፋስ ከባድ ጉዳት አደረሰ.....

ጃፓን ከፍተኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ደረሰበት የመሬት መንቀጥቀጡ ሱናሚም ያስከተለ ነበር

ሕንድ አገር ውስጥ የመሬት ነውጥ ተከስቶ ብዙ ህዝብ አለቀ....

ቻይና ውስጥ በተወሰነ አካባቢ ርእደ መሬት ደረሰ::

የሚሉ እና ሌሎችም የተለያዩ ዜናዎች በየጊዜው አገኛለሁ:: ለኔም ይሁን እንደኔ ላሉት እንዲህ አይነት ዜናዎችና ሌሎችም ምን ይረቡ ይሆን?

የሰው ልጅ ሕይወት ተመሳሳይነት ስላለው ይሆን በሌሎች አገሮች የተከሰተውን ዜና ለመስማት ጉጉት የሚያድርብን ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለው አደጋ ወይም ጉዳት በኔም አገር ሊከሰት ይችላል በሚል ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ፍራቻ የዓለምን ዜና የምንከታተል ይመስለኛል::

በተጠቀሰው ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት እኔ ብቻ ሳልሆን የመላው ዓለም ህዝብ ወሬ ፍለጋ በነጋ በጠባ ሬዲዮ እንደሚነረጉር ቴሌቪዥን እንደሚከፍት ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ገዝቶ እንደሚያነብ አውቃለሁ:: የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንደሚከፍት ጋዜጦችነ መፅሔቶችን ገዝቶ እንደሚያነብ አውቃለሁ:: የሰው ልጅ

የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን መቼ በተፈጠሩ ነበር ጋዜጠኝነትስ መቼ በተጀመረ ነበር

ስለ ሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ሳነሳ አንዲት ሴት ወይዘሮ ትዝ ይሉኛል:: እኚህ የመስሪያ ቤት ባልደረባዬ ቀልደኛ ብጤ ነበሩ:: ሁለታችንም እየተከባበርን የምንጠራው በአንቱታ ነበር::

ታዲያ እኚህ ቀልደኛ ሴት ወይዘሮ አልፎ አልፎ ቢሮዬ ድረስ ይመጡና እየሳቁ ለወሬ ሞትኩ ይበሉ::... የምነግሮት አለኝ ይሉኛል:: እኔም ፈገግ ብዬ የሚነግሩኝ ካለዎት እንዲሁ ይንገሩኝ እንጂ እኔስ ለወሬ ምትኩ አልልም እላቸዋለሁ:: ወሬያችንን እንዲህ

በሳቅ ከጀመርን በኋላ አንዳንድ አዳዲስ የሰሙትን ነገር አውግተውኝ እኔም ስለአጫወቱኝ ነገር አመስግኛቸው እሳቸውም ወደ ቢሮአቸው ይመለሳሉ::

እንደጥንቱ አባባል እንኳ ለወሬ የለውም ፍሬ ይባል ነበር ነገር ግን ይህ አባባል በዛሬው ዘመን ተቀባይነት አይኖረውም:: ይልቁንስ በዘመናችን የተለያዩ ወሬዎች መረጃዎች ስለሆኑ ያ ለመረጃ ያለ ወሬ መኖር የለም ቢባል ተቀባየነት ይኖረዋል::

በኢትዮጵያ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ዮናታን ዲምብልቢ የተባለው ዜና አቅራቢ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወሎ ውስጥ በድርቅ ምክንያት እንደቅጠል ሲረግፉ የነበሩትን አዛውንቶች ጎልማሶች ወጣቶችና ህፃናትን ፊልም አንስቶ ተደብቆ የነበረውን የረሃብ ዜና ይፋ ባያወጣው ኖሮ የ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የኢትዮጵያ አብዮት ይከሰት ነበር ብሎ መገመት አይቻልም:: በእርግጥ ለአብዮቱ መቀጣጠል ሌሎች በርካታ ምክንያቶች ነበሩ:: ለወሬ የለውም ፍሬ የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጊዜ ያለፈበት መሆኑን የሚያስረዳን ይህ የተጠቀሰው ሌሎች እርምጃዎችን ያስከተለ ዜና ነው::

/ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም 1992 102-104 ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ/::

(9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ፣2004፣134-136)

## ተግባር አራት:-

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
    - ✓ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
    - ✓ ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
    - ✓ ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
    - ✓ ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?
3. በትረካው የተገለፁት ድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
4. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
5. .ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

1-በምድብ “ሀ” ለተዘረዘሩት ቃላት/ሐረጎች ከምድብ “ለ” የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ::

ሀ ለ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| --------- 1. ነጋጠባ | ሀ. አንዳንድ ጊዜ |
| --------- 2. መቼ በተፈጠረ ነበር | ለ. የማይረባ |
| --------- 3. በአንቱታ | ሐ. በብዛት ሲሞቱ |
| --------- 4. አልፎ አልፎ | መ. ተጫዋች |
| --------- 5. ቀልደኛ ብጤ | ሠ.በተሰራ |
| --------- 6. አውግተውኝ | ረ. ሽማግሌዎች |
| --------- 7. ለወሬ የለውም ፍሬ | ሰ. ሁል ጊዜ |
| --------- 8. እንደቅጠል ሲረግፉ | ሸ. አጫወተውኝ |
| --------- 9. ይፋ ባያወጣ | ቀ. ባይገልፅ |
| --------- 10. አዛውንቶች | በ. በመከባበር |

**የትረካ ንድፍ**

ጭብጥ ------------------------------------------------------------------------------

ማስተዋወያ --------------------------------------------------------------------------

ገፀባህሪና ገለፃ ----------------------------------------------------------------------

- ---------------------------          -------------------------------------------
- -----------------------------          -------------------------------------------
- ------------------------------          -------------------------------------------

የት ---------------------------------------------------------

መቼ---------------------------------------------------------

ውስብስብነት ----------------------------------------------

ድርጊቶች

- --------------------------------          -----------------------------------------
- ---------------------------------          -----------------------------------------
- ----------------------------------          -----------------------------------------

መፍትሄ ----------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

3- የገጠሯ ኮረዳ በሚል ርዕሰ ከ70 ቃላት ያልበለጠ አንድ ተራኪ ድርሰት ፃፍ::

<table>
<tr><td colspan="2">ርዕስ:- የገጠሯ ኮረዳ<br><br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________</td><td rowspan="3">የመምህሩ አስተያየት</td></tr>
<tr><td>የብጤ አስተያየት</td><td>ቡድን</td></tr>
<tr><td>/ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br><br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር</td><td></td></tr>
</table>

# ክፍል አምስት

## ግርግር

***ናሙና አንቀፅ*** :-5

ሣር አምባ ውስጥ ዝምድናው ገና ከቅድመ አያት ለዘለለና የወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ዋና ተቆርቋሪ መሳይ ምስጢረኛ ፣አፈሳ ማንያዘዋል ነው::የሴትየዋን ፍየሎች በድብቅ ከፍየሎቹ ጋር ቀላቅሎ ያረባላቸዋል::ከገዛ ቤታቸው እየሰረቀ የሚያወጡትን ልዩ ልየ እህል ያስቀምጥላቸዋል::በቀኛዘማች ዓይንና ግምት ቀና ዘመድ መስሎ ስለሚታይ እሳቸአውን ተጠግቶ በሚኖር ቤተኛ ወይም ሎሌ ላይ መሰሪ ነገር አውጠንጥኖ ጥፋት ይሸርባል ተብሎ አይታሰብም::

### ተግባርአንድ:-

***መመሪያ ለተማሪዎች;-***

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::

- የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
- ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
- ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
- ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

### ተግባር ሁለት:-

ዓላማ :- ተማሪዎች የተማሩትን መሰረት አድረገው በግላቸው አንቀፅ ይፅፋሉ::

- ተማሪዎች በአንድ ዓይነት ርዕስ እዲፅፉ መመርያ ይሰጣል::
- እያንዳነዱ ተማሪ የራሱን ፅሁፍ ያነባል::
- መምህሩ ድጋፍና ምክ ይሰጣል::

**የእህቴ ልጅ በሚል ርዕስ አንቀፅ ፃፍ::**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

___________________________________________________________

## ተግባር ሶስት:-

**በየግል የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

## ግርግር

በዚህ ግርግርና ውዥንብር ውስጥ ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው? ጢት ባህር ላይ ተንሳፊፊ መገኘት አልፈልግም:: እንደ መጽሀፍ ለህይወቱ የሚጨነቅ እና የሚሰጋ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም:: የጠጣሁት ሁለት ቢራ ስራውን ሰራ መሰለኝ አድሮብኝ የነበረው ድካም ለቀቀኝ:: ምሽቱ ገና ለጋ ነበር:: ምፅዋ ላይ ሲመሽ ነውና የሚነጋው በጊዜ ሂዶ መተኛት ሀጢያት መስሎ ስለታየኝ መፅሀፊ ዳንኤልን ትቼ ጋዜጤኞችን ፍለጋ ወጣሁ::

እየዞርኩ በየቡና ቤቱ ፈለኳቸው:: ጋዜጠኞች የትም አልነበሩም በመቶ የሚቆጠሩ መኪናዎች ወደ ጉርጉሱም ባህርዳርቻ ሲሄዱም ከዚያም ሲመለሱም መንገዱ ላይ ይታይ ነበር:: የድንኳን ከተማው ሺ ደመራ ተደምሮ የተቀጣጠለበት መስሏል:: ጭፈራውና ዘፈኑ ይቀልጣል:: ቀዝቀዝ ያለው አየር ከጭፈራው እና ከዘፈኑ ጋር ተደማምሮ መንፈስ ያድሳል:: ቅርብ መስሎ ከሚታየው ጥቁር ሰማይ ላይ የፈሰሱት ከዋክብት በደስታ

የሚደንሱ ይመስላሉ:: እና የተይባህር ማዕበሎችም ያረግዱ ነበር:: አንዳንዴ ማእቦሎቹ ፀጥ ሲሉ በየቦታው የሚነደው እሳት ነፀብራቅ ዘመነዊ ሰዓሊ የሳለው የህይወት ጥላ የሚመስሉ ዝብርቅርው ጥላዎች ባህሩ ወለል ላይ ይፈጠራል::

በዚህ ግርግርና ውዥንብር ውሰጥ ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው?

አሁን እንዲያው ከተፈጥሮ የበለጠ ስዕል የት ይኖራል? እያልኩ የባህሩን ጠርዝ ይዤ እየተከዝኩ ሳዘግም አንዲት ልጅ ብቻዋን ካንድ ጠርብ ድንጋይ ላይ ቆማ ማዶ- ሰማይና ባህሩ የሚመሳሰሉበትን አድማስ ስትመለከት አየሁ:: ባህሩ የቆመችበትን ድንጋይ እያጠበ ይመልሳል:: ከባህር የሚመጣው ቀዝቃዛ አየር ጠጉሯን እያነሳ አየር ላይ ይነሰንሰው ነበር:: በቁጭን መያዣ ክብ ትከሻዋ ላይ ተንጠልጥሎ ጀርባዋን ገልጦ የሚያሳይ ነጭ አጠር ያለ የበጋ ቀሚስ ለብሳለች:: የባህርን አምላክ የምታመልክ ነጭ ርግብ መስላ ታየችኝ:: ፎቶግራፍ ማንሻ ምነው በያዝኩ ኖሮ አልኩ:: ከድንኳኖቹ መንደር የተተከሰው ርችት ጥቁር ሰማይ ላይ ድንገት ሲፈነዳ በሺ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ አበባዎች ጨለማላይ ረገፉ:: ደንግጣ ዞር ስትል መልኳ ታየኝ:: ከሩቅ ተወርውሮ የሚመጣው የኤሌክትሪክ ብርሃን ትንሽ ትንሽ ያሳያል እሷ ትሆን ወይስ አይደለችም እያልኩ ተጠጋኋት እሷ ነበረች:: /በዓሉ ግርማ ኦሮማይ 2001:199-200/

## ተግባር አራት

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
    - የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
    - ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
    - ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
    - ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?
3. በትረካው የተገለፁት ድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
4. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
5. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

**ተግባር አምስት:-**

**መልመጃ**

1. የቀረበውን ጽሁፍ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በሰንጠረዥ ለተቀመጡት የተለያዩ ቃላት ወይም አገላለፆች ከተሰጡት ሁለት ሁለት ፍቺዎች መካከል ትክክለኛውን አውዳዊ ፍቺ ከስሩ በማስመር አመልክቱ፡ በመቀጠል እያንዳንዳችሁን መልስ በቡድን ተነጋገሩበት::

| ቃላት/ሀረጎች/ | ፍቺ /አገላለፅ |
|---|---|
| ውኸርንብር | የተሳሳተ እምነት ሐቅ |
| ለጋ | መታ ቀለል ያለ |
| መንሳፈፍ | መዋኘት መሞት |
| አረገደ | አናጠረ አረገ |
| ግርግር | ወከባ ሁከት |

2. **የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን አለባቸው**::

1. ጭፈራውና ዘፈኑ --------------------------/ቀለጠ/::
2. ከዋክብት በደስታ ------------------------- ይመሰላሉ /ደነሱ/::
3. ማዕበሎቹ ፀጥ ሲሉ ---------------- የሚነደው እሳተ ነፀብራቅ ልብን ያስደስታል:: /ቦታ/
4. በዚህ ግርግር እና ውኸርንብር ውስጥ ምን --------- ነገር አለ /ሆን/
5. የቀይ ባህር ማዕበሎችም ---------- ነበር:: /ያረግዱ/
6. አጠር ያለ የበጋ ቀሚስ --------------- /ለበሰ/
7. የባህርን አምላክ ---------------- ነጭ እርግብ መስላለች:: /አመለከ/
8. የተተኮሰው ርችት ድንገት ------------- ደነገጥኩ:: /ፈነዳ/
9. የሰማዩን አድማስ -------------- አያት:: /መመልከት/
10. ልዩ ልዩ አበባዎች -----------------ላይ አብበው ይታያሉ:: /መስክ/

**የትረካ ንድፍ**

**ጭብጥ --------------------------------------------------------------------------------**

**ማስተዋወያ ---------------------------------------------------------------------------**

**ገፀባህሪና ገለፃ -----------------------------------------------------------------------**

- **---------------------------    -------------------------------------------**
- **-----------------------------    -------------------------------------------**
- **------------------------------    -------------------------------------------**

**የት ---------------------------------------------------------**

**መቼ---------------------------------------------------------**

**ውስብስብነት ----------------------------------------------**

**ድርጊቶች**

- **-------------------------------    -------------------------------------**
- **----------------------------------    ---------------------------------------**
- **-----------------------------------    ----------------------------------------**
  **--**

**መፍትሂ -----------------------------------------------------------------------------------**

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

| | **የመምህሩ አስተያየት** |
|---|---|
| ርዕስ:- ትምህርት ቤቴ<br><br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________<br>____________________________________________________________ | |

| **የብጤ አስተያየት** | **ቡደን** |
|---|---|
| /ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር | |

# ክፍል ስድስት

## ሰብለወንጌል

**ናሙናአነቀፅ**:-6

ወ/ሮ አምሳለ እንደልማዳቸው ምሽቱ ሳይገፋ በጊዜ ፣ሁለት ብርጭቆ የአጃ አጥሚታቸውን ጠጥተው ፣ሊጋ ቅቤአቸውን በሰርናቸው አንቆርቁረውና እንደጨረቃ ክብ የሆነች ፊታቸውን በቀዝቃዛ ወተት ከወለወሉበኋላ ከፊታቸው ላይ ጤዛ መስሎ የሚያብረቀርቅ ቅባት ተቀብተው ሲያበቁ ሻሻቸውን እስከ ጆሮ ግንዳቸው ድረስ ዝርግድ አድርገው አልጋ ላይ ከወጡ የቆዩ ቢሆንም እንደፈርጥ የሚንገበገበው ትላልቅ ዓይናቸው እንቅልፍ የሚሉት ጣዕመ ነገር ከቶውንም አልዞረም:: እንደጉርድ በርሜል ከአልጋ ውስጥ ይገላበጣሉ::

## ተግባር አንድ:-

- በቡድን አራት አራት ሆናችሁ በሚከተሉት ርዕሶች አንቀፅ ፃፉ::

**ቆሞቀር በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

## ተግባር ሁለት:-

**በቡድን በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

## ሰብለወንጌል

ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩ አይነት እንደዚህ እየተወያዩ እውነትሽ እውነትህ ሲባባሉ ልጃቸው አስራ ስድስት አመት እስኪሆናት ድረስ ጠያቂዋ አባት እናትዋን እረፍት ከልክሎአቸው ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን ትንሽ በትንሽ እየተረሳች ሄደች:: አንዳንድ ጠያቂዎች እንኳዋ አልፈው አልፈው ቢመጡ አንዳንድ ጊዜ እንደሚደርገው ቆሞ ቀር ከሚባሉት ተቆጥራ በፈትነት እንጂ በልጃገረድ ስራት ለማግባት የሚጠይቅ ጠፉ::

ሰብለ ወንጌል ባል ሳታገባ ጊዜም በማለፉ የመንደሩ ሰው ሽሙጥና ሀሜት በሄደችበት ሁሉ አንገቷን ቀና አድርጋ ሰው ለማየት ያሳቅቃት ነበር:: አንድ ቀን ከእናትዋ ጋር እቤተክርስቲያን ቆማ ስታስቀድስ:

እባክሽ እባክሽ እይልኝ የጌቶችን ልጅ እናትዋን እኮ አከለች:: አለች ደብሪቱ የምትባለዋ ከመንደሩ አሽማጣጮች አንድዋ::

ምነው እናቷን አከለች ትያለሽ ከናትዋ በለጠች በይ እንጂ ዳሌዋንና ደረትዋን አታይም አስር የወለደች መሰለች:: አለች ጓደኛዋም ስንዱ

እኚህ አባትዋ ምን ሊያደርጓት ነው አስረው የሚያወፍሯት አርደው ይበሏት ይመስል ወዲያ ላንዱ አይሰጧትም እንዴ

አሁን እማ ለማን ይስጡዋት ጠያቂ ሲጠፋ የጠየቋቸውን ሁሉ አታክሉንም አትመስሉንም እያሉ ሲያባርሩ ኖረው አሁን ጠያቂ አጡ::

ኸረ ፊታውራሪ አሰጌ ጠይቀዋል አሉ አለች ደብሪቱ የሽሙጥ ሳቅ እየሳቀች::

የትኛው አሰጌ?

እኚህ የቢቸናው ፊታውራሪ አሰጌ::

ምን ልጅ አላቸው?

ለራሳቸው ነው እንጂ ምን ልጅ አላቸው::

ለራሳቸው ኸረ የዲማው አባቴ የልጅ ልጃቸው አትሆንም

እንዲያውም ይግረምሽ በልጃገረድ ስም አላገባም ብለው ሳያፈርሱ አይቀርም ይባላል::

/ሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከመቃብር 2001 ገፅ 87-88/

## ተግባር ሶስት:-

*ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::*
*ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ ::*

1. *ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::*
2. *ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::*
    - ✓ *የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?*
    - ✓ *ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?*
    - ✓ *ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?*
    - ✓ *ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?*
3. *በትረካው የተገለፁትድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?*
4. *በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?*
5. *ትረካውን የተረከልን ማን ነው?*

## ተግባር አራት:-

***የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ:: የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል***

***የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን ይኖርባቸዋል::***

1. *ልጃቸው ------------ ብዙ አመት አለፋት:: /አገባ/*
2. *በልጃገረድ ስም አላገባም ብለው ---------------- አይቀርም:: /አፈረሰ/*
3. *አስራስድስት አመት እስኪሆናት ድረስ ---------- ቤተሰቦቿን እረፍት ነስተው ነበር:: /ጠየቀ/*
4. *ሰብለ ወንጌል በትንሽ በትንሹ ----------- ሄደች /ተረሳ/*
5. *አንድ ቀን እቤተክርስቲያን ቆማ --------------- የሁለት ሴቶች ሀሜት ከጆሮዋ ደረሰ ደረሰ:: /ቀደሰ/*
6. *ሰብለወንጌል አንገቷን ቀና አድርጋ ሰው ለማየት----------- ነበር:: /መሳቀቅ/*
7. *ሳታገባ ከመቆየቷ የተነሳ አስር -------------- ትመስላለች:: /ወለደች*
8. *የጠየቃቸውን ሁሉ ------------------ እያሉ ሲመልሱ ከረሙ:: /መጠነ/*
9. *ልጅቱ ቆሞቀር ከሚባሉት ---------------- ጠያቂም ጠፋ:: /ቆጠረ/*
10. *ልጅቱ ለሰውየው የልጅ ልጃቸው -------------- /ሆና*

**የትረካ ንድፍ**

ጭብጥ ----------------------------------------------------------------------------

ማስተዋወያ ------------------------------------------------------------------------

ገፀባህረና ገለፃ ----------------------------------------------------------------------

- ---------------------------     -------------------------------------------
- -----------------------------     -------------------------------------------
- ------------------------------     -------------------------------------------

የት ---------------------------------------------------------

መቼ----------------------------------------------------------

ውስብስብነት ---------------------------------------------

ድርጊቶች

- ------------------------------     ------------------------------------
- ---------------------------------     --------------------------------------
- ----------------------------------     -----------------------------------------

መፍትሄ ---------------------------------------------------------------------------------

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ:- ያላቻ ጋብቻ<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________<br>______________________________ | | **የመምህሩ አስተያየት** |
| **የብጤ አስተያየት** | **ቡደን** | |
| /ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር | | |

# ክፍል ሰባት

## ሱጴ

*ናሙና:-7*

የሱጴ ለልጃገረዶች ጎረምሶች ከፊታውራሪ ግቢ በየቀኑ እየተሰበሰቡ የሰርግ ዋዜማ መዝፈን ከጀመሩ ቆይተዋል:: ሰውም በየቤቱ ቡና የሚያከትመው በዓይናለም ተካና ሀዲስ ሳህሌ ሰርግ ወሬ ነበር:: እንደወጉ ከሆነ በእሱም ቤት መዘፈን ነበረበት ግን ምንም ዓይነት ዝግጅት አላደረገም:: ፊታውራሪ ምንም ዓይነት ዝግጅት እንዲያደርግ አልፈለጉም:: ከእሱ ይጠበቅ የነበረው የሰርጉ ዕለት ዕድምተኞቹን እና ሚዜዎቹን ይዞ መምጣት ብቻ ነበር:: ቤትም ሳይቀር እዚያው ፊታውራሪ ጊቢ ውስጥ እንደሚዘጋጅለት ተነግሮታል:: ነገሩን ባይወደውም ምረጫ አልነበረውም ችግር የፈጠረበት ነገር ቢኖር እድምተኞቹን እና ሚዜዎቹን በመመልመል ላይ ነበር:: ብዙ ሰው አያውቅም:: ጓደኞችም አላፈራም:: ሱጴ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጊዜውን ያሳለፈው በቁም ነገር ብቻ እንደመሆኑ መጠን ሀዘኑንም ሆነ

## ተግባር አንድ:-

- በቡድን አራት አራት ሆናችው ከሰባት ዐረፍተ ነገሮች ባላነሰ አንድ አንቀፅ ፃፉ::

" የምኖርባት ከተማ "

-ህዝቡ ምን ይሰራል ?

-ለስራ ያላቸው ሁኔታ ምን ይመስላል?

-ህዝቡ በትርፍ ጊዜው ምን ይሰራል?

-ለየትኛው የስፖርት ዓይነት የተመቸ ሁኔታ አለ?

## ተግባር ሁለት:-

**በቡድን በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

## ሱጼ

ጥር ላይ ከቡና ዑደት ጋር የሱጼ ስልት ህይወት ይለወጣል:: ቡና ለመሸምጠጥ ለመልቀም ለማድረቅ ለመፈልፈል ለማጠብና ለመጫነ የደቦ ስራ አይበቃም:: በሺ የሚቆጠሩ ሰራተኞች ያስፈልጋሉ:: ይህንኑ የሚያውቁ በዘኔዎች ከሰባትቤት ጉራጌ እና ከወሎ እና ከትግራይ በቡድን መጥተው ጊዜያዊ ስፍራ በማበጀት ስራ መጫረት ይጀምራሉ:: ቃላቸው ህግ ስለሚሆን በዋጋ የሚከራከራቸው የለም:: ያሉትን ዋጋ አሜን ብሎ ከመቀበል ሌላ አያዋጣም:: ቡና በጊዜ ተለቅሞ በጊዜ ገብቶ በጊዜ መሸጥ አለበት:: የጥር ቡና ገበያ ቆሞ ማንንም አይጠብቅም::

ዘላን ኮማሪዎች እና ሴተኛ አዳሪዎችም የቦዘኔዎችን እግር ተከትለው መጥተው የሻማ የኩራዝና የፋኖስ ሰፈር ያበጃሉ:: ያምቡላና ያተላ ሽታ ሶጼን ማወድ ይጀምራል:: እነዚህ ቤት ጠላ አለ በማለት የሚያመላክቱ በእንጨት ላይ የተሰኩ የተጨረማመቱ ጣሳዎች በየደጃፉ ሰልፍ ይቆማሉ:: ጠጅቤቶች እና ጠላቤቶች ካፍ እስከ ገደፋቸው በሰው ጢም ብለው ይሞላሉ:: ያተረፈው ተደስቶ ይጠጣል:: ሁሉም ይጠጣል ቡና ጀባ ቀሀጀባ የቡና ሼህ ዘንድ አደራ እያለ ከዘንድሮ የቡና ሰብል መጠንና ዋጋ ሌላ ወሬ አይሰማም:: ሁሉም ስለቡና ያወራል:: ሁሉም ስለቡና ይጠጣል::

ጉሮሮአቸው የሽሪሪት ድር አድርቶ ዝጎ ለደግ ቀን የመሰንቆዎቻቸውን ጭራዎች በባህር እጣን ሲያሙዋሹ የከረሙት አዝማሪዎች ጉሮሮአቸው በጠጅርሶ ግንባራቸው በአረንጓዴና በቀይ ብር አጊጦ እንዲያው ማቅራራት ማስካካት ይጀምራሉ::

ያገዳ ጥንቅሽ መጠው ያደጉ ቅልብ የሀረር ሰንጋዎች የሚመስሉ የቡና መሬት ባለርስቶች በቡና ንግድ የከበሩና የወፈሩ ቱጃሮች ቱባ ቱባ ብር ተሸክመው ገንዘብ የተቸገረውን ሰው ከሩቁ የሚያሸቱ አራጣ አበደሪዎች ከዝናሽ ቡናቤት ይሰበሰባሉ::

/በዓለ ግርማ ሐዲስ 1982 ገጽ 122-123

## ተግባር ሶስት:-

ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::

ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ ::

1. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
2. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
   - ✓ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?
   - ✓ ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?
   - ✓ ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?
   - ✓ ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?
3. በትረካው የተገለፁትድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
4. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
5. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

## ተግባር አራት:-

**I- በምድብ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት /ሐረጎች ከምድብ "ለ" የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ**

| | |
|---|---|
| ------- 1. ይለወጣል | ሀ. ከጠጅ የሚቀር ዝቃጭ |
| ------- 2. ያበጃሉ | ለ. የሚያሳዩ |
| ------- 3. አምቡላ | ሐ. በደንብ ጠጥተው |
| ------- 4. ማወድ | መ. ጢም ብሎ |
| ------- 5. የተጨረማመተ | ሠ. የመሬት ባለቤት |
| ------- 6. ካፍ እስከገደፍ | ረ. ከፍተኛ ወለድ |
| ------- 7. ባለርስት | ሰ. ይቀየራል |
| ------- 8. አራጣ | ሸ. መሽተት |
| ------- 9. ጉሮሮአቸው በጠጅ ርሶ | ቀ. የተተጣጠፈ |
| ------- 10. የሚያመላክቱ | በ. ይሰራሉ |

**የትረካ ንድፍ**

ጭብጥ ------------------------------------------------------------------------------------

ማስተዋወቂያ ----------------------------------------------------------------------------

ገፀባህረና ገለፃ ---------------------------------------------------------------------------

- ----------------------------- ----------------------------------------------
- ------------------------------- ----------------------------------------------
- -------------------------------- ----------------------------------------------

የት --------------------------------------------------------------

መቼ---------------------------------------------------------------

ውስብስብነት --------------------------------------------------

ድርጊቶች

- --------------------------------- ----------------------------------------
- ------------------------------------ ------------------------------------------
- ------------------------------------- ---------------------------------------------

መፍትሄ -----------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

<table>
<tr><td colspan="2">ርዕስ:- በምሽት ጨረቃ<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________<br>________________________________________</td><td rowspan="3">የመምህሩ አስተያየት</td></tr>
<tr><td>የብጤ አስተያየት</td><td>ቡደን</td></tr>
<tr><td>/ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br><br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር</td><td></td></tr>
</table>

# ክፍል ስምንት

## በሰርጉ ማግስት

ናሙና ድርሰት:-8

አንድ ጫማ ሰፊ

"አንድ ጫማ ሰፊ ከጧት እስከማታ በእጁ ጫማ ሲሰፋ ባፉ ሲዘፍን ይውል ነበር:: በጎረቤቱም አንድ ባለጠጋ ነበረና አንድ ቀን ወደርሱ መጥቶ ወዳጄ ሆይ ፣እንዲህ ሌት ተቀን ስትደክም ባመት ምን ያህል ታተርፋለህ አለው:: ጫማ ሰፊውም እየሳቀ መለሰ::ጌታዬ እኔ ያመት ትርፍ አላስብም:: ነገር ግን ሀሳቤ ሁሉ እጄ ወደ አፌ የሚያቀርበው የዕለት ምግብ እንዳልቸገር ብቻ ነው አለው::

ባንድ ቀን ምን ያህል ታተርፋለህ አለው:: ጌታዬ ሆይ አንድ ቀን ብዙ ፣አንድ ቀን ጥቂት እሰራለሁ:: ትርፉ በምን ይታወቃል አለው ፡፡ባለጠጋውም እንግዲህ እኔ ያለችግር አኖርሃለሁና ከኔ ዘንድ መቶ ምዝምዝ ወርቅ ውሰድና በጥንቃቄ ጠብቀህ አኑር:: በቸገረህም ጊዜ የሚበቃህን ያህል እንጂ አታባክን ብሎ ሰጠው::

እረሱም ይህን ያህል ገንዘብ ባይኑ እንኳ አይቶ አያውቅም ነበረናደስ እያለው ተቀብሎ ወደ ቤት ሄደ:: ነገር ግን ይጠፋብኛል ብሎ ሲዐነቅ ሌሊቱን ሁሉ ካይኑ እንቅልፍ ሸሸ:: በሌሊትም የሰው ድምፅ በሰማ ጊዜ ገንዘቡን የሚቀማ ወንበዴ የመጣ ይመስለዋል:: ነፋስም ቤቱን ባነቃነቀ ጊዜ ገንዘቡንየሚሰርቅ ሌባ የመጣ እየመሰለው ይጨንቅ ጀመረ:: እንዲህ እየሆነ ብዙ ቀን ተቀመጠ:: ነገር ግን ልቡ የዚህን ሀሳብ የማይችል ሆነ:: ከዕለታት ባንድ ቀን እንዲህ ሰጨነቅ አደረና በማግስቱ በማለዳ ተነስቶ ወደዚያ ባለጠጋ ቤት እየሮጠ ሄዶ ለኔስ የቀድሞ ኖሮዬእጅግ የሻለኛል:: አሁንም የሰጠኸኝን መቶ ምዝምዝ ወርቅ ተቀበለኝ:: ቀን ስሰራ እየዋለሁ ሌሊት እንቅልፍ ቢወስደኝ ለኔ እጅግ መልካም ነውብሎ በትኖለት ሄደ::"

## ተግባር አንድ:-

- በቡድን አራት አራት ሆናችሁ በሚከተሉት ርዕሶች አንቀፅ ፃፉ::

ሀ. ስስታሙ ሀብታም

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ለ. ታታሪው ገበሬ-

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**ተግባር ሁለት ፡- በቡድን በመሆን የጻፉችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. አንቀፁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

## በሰርጉ ማግስት

ጋሼ ፍሬ ነገሩ ይህ አይደለም:: አስቀድሜ ሰርግና ድግስ የሚባል ነገር አልፈልግም ብዬ ነግሬህ ነበር:: እኔ በህይወቴ እያለሁ ሉሊት የምትባል አታገባም ስትለኝ ከርመህ ቆርጨ መነሳቴን ስታውቅ ካልደገስኩ ሞቼ እገኛለሁ ብለህ ገንዘብ እንዳለው ሰው ደገስክ:: ከቶ አይገባኝም ጨርሶ አይገባኝም....

ምኑ ይገባሀል የናቴ ልጅ አይገባህም:: ባህላችንንና አስተሳሰባችንን  አታውቀውማ አንድ ታናሽ ወንድሜ አበራ ሲያገባ እንዴት አንደባእድ ከዳር ቁጭ ብየ ልመልከት ጎረቤት ምን ይለኛል የፊታውራሪ ወርቁ ልጅ የአባቱ ወንድም የእመት ባፈና ባንት ይርጉ ልጅ ያለሰርግ ያለድግስ እንዲሁ አገባ ቢባል.... ጎረቤት እድርተኛውና የሚያውቀት ሰው ሁሉ ምን አይነት ትዝብት ላይ ይጥለናል ምን አይነትስ ግምት ይወስድብናል አባታችን በንፉግነት ተጠርተው ስማቸው በየመንደሩ የቡና ቁርስ ከሚሆን ሞቼ መቀበሬን እመርጣለሁ:: አባታችን በህይወተ ሳሉ በሰርግ ቀን ይቅርና በሌላውም ቀን ከሰው ተለይተው መብላትን አይወዱም ነበር:: እስከ እለተ ሞታቸው በክብር ጠብቀው ያቆዮን ስም እንዴት በልጃቸወ ምክንያት ይበላሽ?..." አበራ "ከእዳ ሌላ ምን ተረፈኝ?" ከማለት ሌላ በተጨማሪ የሚናገረው ነገር አልነበረውም::

/በዓሉ ግርማ ከአድማስ ባሻገር 1962 96-97 ለማሰተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተዘጋጀ/::

## ተግባር ሶስት:-

ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::

1. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ ::
2. ተማሪዎች የቀረበላችሁን ሞዴል ተራኪ ፅሁፍ በጥሞና አንብቡ::
3. ፅሁፉን ስታነቡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልብ በሉ::
   - ✓ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?

✓ ስለታላሚው አንባቢ ምን ታስባላችው?

✓ ፀሀፊው ዓላማውን አሳክቷል?

✓ ስለፅሁፉ አሳማኝ መሆን እና አለመሆን ምን ትላላችው ?

4. በትረካው የተገለፁትድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
5. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
6. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

## ተግባር አራት:-

I. በቀረበው ፅሁፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ትክክለኛ ፍቺያቸውን ምረጡ::

| | | |
|---|---|---|
| 1. ቆርጦ መነሳት | ሀ. መወሰን | ለ. መዋለል |
| | ሐ. መደናበር | መ. መግደርደር |
| 2. ባእድ | ሀ. ዘመድ ያልሆነ | ለ. ዘመድ የሆነ |
| | ሐ. ጠላት | መ. ለ ና ሐ መልስ ይሆናሉ |
| 3. ንፉግነት | ሀ. ደግነት | ለ. ለጋስነት |
| | ሐ. መስጠት ያለመፈለግ | መ. ቸር የሆነ |
| 4. ያለሰርግ | ሀ. ያለግብዣ | ለ. ያለድግስ |
| | ሐ. ሰርግ ሳይኖር | መ. ሁሉም |

5. ምንተረፈኝ ሀ. ምን አገኘሁለ. ምን አጣሁ ሐ.ምን ጨመርኩ

**የትረካ ንድፍ**

**ጭብጥ ----------------------------------------------------------------------------------**

**ማስተዋወቂያ -----------------------------------------------------------------------------**

**ገፀባህረና ገለፃ ---------------------------------------------------------------------------**

- **---------------------------- ---------------------------------------------**
- **------------------------------ ---------------------------------------------**
- **------------------------------- ---------------------------------------------**

**የት ------------------------------------------------------------**

**መቼ-------------------------------------------------------------**

**ውስብስብነት ------------------------------------------------**

**ድርጊቶች**

- **-------------------------------- ---------------------------------------**
- **----------------------------------- -----------------------------------------**
- **------------------------------------ ----------------------------------------------**

**መፍትሂ ----------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------**

**የራሳችሁን ተራኪ ድርሰት ጻፉ**

<table>
<tr><td colspan="2">

ርዕስ:- **የሰርጌ ዕለት**

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

</td><td rowspan="3">የመምህሩ አስተያየት</td></tr>
<tr><td>የብጤ አስተያየት</td><td>ቡደን</td></tr>
<tr><td>/ግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦች/<br><br>ፈጠራ<br>አደረጃጀት<br>ትክክለኛ አረፍተ ነገር</td><td></td></tr>
</table>

አባሪ ሶስት

# በሂደት ተኮር የቀረበ የመፃፍ ትምህርት

## ዘጠነኛ ክፍል

(የተማሪው)

ጥር

2007

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


መግቢያ………………….. ..........................................................................228
ክፍል አንድ……………… ........................................................................230
ፈሪው ወታደር…………… .........................................................................230
ክፍል ሁለት……………..............................................................................237
ዲን: ሱዊፍት…………….............................................................................237
ክፍል ሶስት………………...........................................................................240
አይናለም………………….........................................................................240
ክፍል አራት……………….........................................................................242
ለወሬ ምትኩ ይበሉ……….........................................................................242
ክፍል አምስት……………...........................................................................246
ግርግር ………………… .........................................................................246
ክፍል ስድስት……………. .........................................................................249
ሰብለወንጌል……………… .........................................................................249
ክፍል ሰባት……………….........................................................................252
ሱጴ……………………….........................................................................252
ክፍል ስምንት…………...........................................................................255
በሰርጉ ማግስት………….........................................................................255

## መግቢያ

የጽሁፍ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቀዳሚ ትኩረት ከሚሰጣቸው መሰረታዊ የክሂል ዘርፎች መካከል አንዱ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚታሰበው የተግባቦት እውቀት እንዲኖራቸው በሚያስችል ሁኔታ መማር አለባቸው::

ተማሪዎች በዘጠነኛ ክፍል ከሚማሯቸው የቋንቋ ክሂሎች መካከል መፃፍ አንዱ ነው:: መፃፍ የፊደልን ቅርፅ ለይቶ ከመፃፍ ጀምሮ አዲስ ሀሳብን በማፍለቅ ቃላትን እና ሀረጋትን አቀናጅቶ አረፍተ ነገርን አረፍተ ነገሮችን አቀናጅቶ አንቀጽን በማዋቀር ሀሳብን በተደራጀ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ የሚያስችል ሂደታዊ ተግባር ነው::

በዚህ የ9ኛ ክፍል ትምህርት ደረጃ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል በተለይም ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ ይዘቶች ተመርጠው በስምንት ክፍሎች ተመድበው የቀረቡ ሲሆን ከተለያዩ ምንጮች የተወሰዱ ምንባቦች ናቸው :: ምንባባቱ ከተማሪዎች እድሜ አካባቢ ፍላጎት እና ደረጃ ጋር የተገናዘቡ ናቸው ተብሎ ይታሰባል:: ምንባባቱን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች አስቀድመው ከተነሱት ነጥቦች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ሙከራ ተደርጓል::

ሀ. የትምህርቱ አላማ

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተከታተላችሁ በኋላ:-

- ለቃላት ቀጥተኛና አግባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፣
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፣
- አንቀጽ ትፅፋላችሁ፣
- ተራኪ ድርሰቶች ትፅፋላችሁ፣
- ሀይለ ቃልንና መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፣
- ሀረጎችን መነሻ በማድረግ በራሳችሁ አበባል ትፅፋላችሁ::
- ሀሳቦችን በአንድ ቃል ትገልፃላችሁ::
- አረፍተ ነገሮችን ታሟላላችሁ::

ለ. ተግባራት

- ለቃላት ቀጥተኛ እና አገባባዊ ፍቺ መስጠት::
- ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም::
- አንቀፅ መጻፍ::
- ተራኪ ድርሰት መፃፍ::
- የአንቀፅን ሀይለቃልና መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን መለየት::
- አስተዋጽኦ ነድፎ አንቀፅና ተራኪ ድርሰተ መፃፍ::

ሐ. ዘዴዎች

- ገለፃ
- የጥንድና የቡድን ውይይት
- ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ

መ. ግምገማ

- በየግል የሚፅፏቸውን አንቀፆችንና ተራኪ ድርሰቶች መተራረም ተማሪዎች የሚያከናውኑት
- አስተዋጽኦ ነድፈው ረቂቅ አዘጋጅተው የሚፅፏቸውን አንቀፆች እና ተራኪ ድርሰቶች መተራረም በቡድን የሚከናወን
- ተማሪዎች የሚፅፉትን አንቀፅና ተራኪ ድርሰት የመፃፍ ሙከራዎች መምህሩ የሚያካሂደው

ሠ. ማጣቀሻ መፃፍ


ሀዲስ አለማየሁ:: /1958/:: ፍቅር እስከመቃብር:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

በዓሉ ግርማ:: /1993/:: ከአድማስ ባ ሻገር:: አዲስ አበባ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

---------------- :: /1975/ :: ሀዲስ:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

ደረጀ ገብሬ:: /1996/:: ተግባራዊ የጽህፈት ማስተማሪያ:: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት::

ዳኛቸው ወርቁ:: /1988/:: የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ:: አዲስ አበባ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ /2ኛ ዕትም/::

ማረው ዓለሙ:: /1996/:: በሳል ድርሰት ማስተማሪያ:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

# ክፍል አንድ

## ፈሪው ወታደር

**1. ከዚህ በታች ስለአንቀፅ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ- ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀፅ ፃፉ::**

1. ማርፈድ

2. ከትምህርት ቤት መቅረት

3. የጥናት መርሀ ግብር

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**2. በጥንድ በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ሀይለ ቃልንና መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን ለዩ::
2. አንቀጹ የያዛቸው አረፍተ ነገሮች የሀሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በሀይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሀሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ::
3. አረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ::
4. ጓደኛችሁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ::
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኛችሁ አስተያየት ስጡ::

**አንቀፅ**

አንቀጽ ማለት አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለጽ ሲባል በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሀሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርጽ ነው:: አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ሀይለ ቃል /መንደርደሪያ አረፍተ ነገር/ እና ከአንድ በላይ መዘርዘር አረፍተ ነገሮችን ሊይዝ ይችላል:: የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት:-

ምሳሌ

የተምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል:: ከሁለት አመት በፊት በእግር ኳስና በመረብ ኳስ ስፖርቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በነበሩ ተማሪዎች መካከል ውድድሮች ተካሂደው ነበር:: ባሳለፍነው የትምህርት ዘመንም የውድድር አይነቶቹን ከሁለት ወደ አራት በማሳደግ በእግር በመረብ በእጅና በቅርጫት ኳስ የውስጥ ውድድሮችን አካዷል:: በያዝነው የትምህርት ዘመን ደግሞ በአራቱም የውድድር አይነቶች የውስጥ ውድድሮች ከማካሄዱም በላይ የከተማው ባህልና ስፖርት መምሪያ ባዘጋጀው የዘመኑ ውድድር ላይ በአግር ኳስና በመረብ ኳስ በመሳተፍ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል::

በዚህ ምሳሌ እንደሚታየው በአንቀጹ ሀይለ ቃል የትምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል:: በሚል የሰፈረው ዋና ሀሳብ ከሱ በኋላ በመጡት መዘርዝር አረፍተነገሮች ተብራቷል:: በመዘርዝር አረፍተነገሮቹ በመጀመሪያ የስፖርት እንቅስቃሴው በሁለት የውድድር አይነቶችና በውስጥ ውድድር ጀምሮ በየጊዜው ባደረገው መ ሻሻል የውድድር አይነቶቹን ወደ አራት እንዴት እንዳሳደገና ከውስጥ ውድድሮች በተጨማሪ የውጪ ውድድሮችንም መሳተፍ እንደጀመረ ደረጃ በደረጃ ተብራርቷል::

3. **ከዚህ በታች በቀረበው አንቀጽ ውስጥ በተጓደሉ ስርዓተ ነጥቦች ምትክ ቁጥሮች ሰፍረዋል:: በቁጥሮቹ ቦታ መግባት ያለበትን ስርአተ ነጥብ ግለጹ::**

መጠጥ አካልና መንፈስን ያዳክማል:: በአኗኗሩ ጠንቃቃ 1 በአስተሳሰቡ በሳል 2 በስራወም ክቡር የሆነ ሰው በጠጣ ጊዜ መንፈሱ ይደክማል አካሉ ይዝላል 3 ምላሱ ይተሳሰራል:: ስካሩ የፀና ከሆነም እግሩ እየከዳው... እግሮቹ ተሳስረው እየወደቀ 4 ለመነሳት እየቧጠጠ 5 ባለበት ይዳክራል 6 ያለበት ዝላይ አይችልም እንዲሉ ሳይጠይቁት ይመልሳል 7 ሳያናግሩት ያናግራል::

**ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ**

በጽሁፉ ውስጥ በስርዓተ ነጥቦች ዋነኛ ተግባር የፅሁፉ መልእክት ሳይድበሰበስ በአፍታ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰት ማገዝ ነው:: በጽሁፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የስርዓተ ነጥብ አይነቶች መካከል ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ ተጠቃሽ ናቸው::

/…/ ነጠብጣብ

1. ከጽሁፍ ወይም ከጥቅስ ውስጥ የተወሰነውን ቃል ወይም ክፍል ያስቀረነው መሆኑን ለማመልከት

ምሳሌ አባቷን አታውቅ….. እንዲሉ

አባቷን አታውቅ አያቷን ትናፍቅ::

2. በፈጠራ ድርሰት ውስጥ አንባቢ የቀረውን በሀሳቡ እንዲሞላና የሚሆነውን እንዲረዳ ሲፈልግ

ምሳሌ

አልቀመጥም እኔ የመጣሁት ካንተ አንዲት ቃል ተንፈስልኝ::

ስትለው….

/ሲሳይ ለመመን 1996 183/

**/፤/ ድርብ ሰረዝ**

የሀሳብ ቁርኝት ያላቸውን አረፍተነገሮች አጣጥሞ ለማቅረብ ያገለግላል:: ድርብ ሰረዝ ለአረፍተ ነገር መቋጫነት ከምንጠቀምበት አራት ነጥብ የሚለየው ደግሞ አራት ነጥብ አረፍተ ነገሩ ማለቁን ከሚጠቁመን በስተቀር በሱና ከኋላው በተሰለፉት ሌሎች አረፍተነገሮች መካከል ያለውን የሐሳብ መያያዝ አያመለክትም::

**ቀጥሎ ፈሪው ወታደር በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድረሰት ቀረቦላቸዋል:: ድርሰቱን በጥንቃቄ ካነበባቸው በኋላ በስተመጨረሻ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ::**

## ፈሪው ወታደር

አንድ ትልቅ ጦርነት ሲካሄድ ተካፋይ የነበረ አንድ ፈሪ ወታደር ነበር:: በጦርነቱ አብረውት የተሰለፉ ጓደኞቹ ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተው በጀግንነት ተዋጉ:: እየተመቱም አንዳቸው ባንዳቸው ላይ እየተደራረቡ ወደቁ:: ይህንን ያየው ቡቡው ወታደር ሆዱ ተሸበረበት ጉልበቱም ቁጤማ ሆነበት:: ከዚያ ስፍራ ከሬሳ በስተቀር አንድም የሚያውቀው ወታደር ማየት አልቻለም ነበር::

ጦርነቱ እሱ ባለበት በኩል እያደር እየተፋፋመና እየተጋጋለ መጣ:: በዚህ ጊዜ መክቶ መቋቋም እሩጦም ማምለጥ እንደማይችል ተገነዘበ እንግዲህ ከዚህ በቀር ሌላ ነገር የሚያድነኝ የለኝ አለና የተደራረቡትን እሬሳዎች ፈነቃቅሎ ገባ:: አንዱን እሬሳ በላዩ ላይ ጭኖ ትንፋሹን አሳጥሮ ተኛ::

የወዲያኛውም የወዲያኛውም ወገን በሾተል እየተጠዛጠዘ በፎቁ እየተጓመደ እያወከ እየተዋጋ እየተተራመሰ እሱ ወደ ተሸሸገ በት በጣም እየቀረበ መጣ:: አጠገቡ በደረሰ ጊዜ የፈረሰ አንዳ ከአሁን አሁን ያደባየኛል ሲል ሲፈራ ቆይቶ እንደምንም እግሩን ይሰበስባል:: ወዲያው እንደ ተዋጊ ፈረሰኛ አየው ከፈረሱ ላይ እንደሆነም የዚያን ሳይቆስል የሞተ ሰው እግር በቀጭን ሹልጦሩ ጠቆም ጠቆም እያደረገ ይሄስ የሞተ አይመስልም አለ በዚህ ጊዜ ያ በውሸት የሞተው ወታደር አይ አይ:: እያለና እግሩን እያንፈራገጠ እሺ ተወኝ ሞቻለሁ አለ አፉን በእጁ እየተመተመ::

/ዳኛቸው የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ 1977 ፣178-179 ተሻሽሎ የቀረበ/

1. በትረካው የተገለፁት ድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
2. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭሩ ባጭሩ ዘርዝሩ:: በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
3. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

**ተራኪ ድርሰት**

ተራኪ ድርሰተ በጣም ከተለመዱት አራት ዋና ዋና የድርሰት አይነቶች አንዱ ነው:: የቀሩት ሶስቱ ስዕላዊ ድርሰት ገላጭ ድርሰትና አመዛዣኝ ድርሰተ በመባል ይታወቃሉ::

ተራኪ ድርሰት ድርጊቶችን እና ሰንሰለታዊ እውነቶችን የድርጊት የጊዜ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ እንግዲህ እንዲህ ሆና እንግዲህ እንዲህ ተደረገ:: እያለ የሚተርክልን ጽሁፍ ነው:: ታሪኩን የሚነግረንም ራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ሊሆን ይችላል:: አለበለዚያም ድርጊቱን የተመለከተ የደረሰበት በልምድ ያገኘው ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል:: ከላይ የቀረበው ተራኪ ድርሰትም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል::

**የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከል አንድ ተራኪ አንቀጽ ይወጣቸዋል:: አረፍተ ነገሮቹን በጥንቃቄ መርምራችሁ ቅደም ተከተላቸውን አሰተካክሉ:: ለድርሰቱም ርዕስ ስጡ::**

1. በክረምት ለእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቼለት ነበር::

2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ አክስቴ ብቻዋን እንደምትኖር የነገረችኝ ትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብዬ አሳብ ገባኝ:: ምን ማድረግ እንዳለብኝም ማሰላሰል ቀጠልኩ::

4. በልጅነቴ የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ወደፍቼ ከተማ በሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም::
5. ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ ባረጀውና ቁመቱ ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጥራት ወሰንኩ::
6. የአክስቴን አይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህር ዛፍ ጫካ ውስጥ ጥቂት መጓዝ ነበረብኝ::
7. እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብቀኝ ጉቶ ላይ አረፍኩ:: ከዚያ በኋላማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው አክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር በመካከል የሆነውን ነገር ሁሉ አላስታውስም::
8. ድካሜን ሁሉ ረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጪው በር እንደደረስኩ በሩን ቶሎ ቶሎ አንኳኳሁ:: ነገር ግን ማን ነህ የሚለኝ አጣሁ::
9. እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ::

10. የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርባት የገጠር መንደር ከአዲስኜ ግማሽ ቀን ተጉዤ ስድስት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ::
11. እንደገናም በሩን ደጋገሜ ደበደብኩት ምንም መልስ የለም::

**በቡድን ሆናችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንድትችሉ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል አከናውኑ:-**

1. እየተወያያችሁ ርዕስ ምረጡ::
2. በርዕሱ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ::
3. በሐሳብ የሚቀራረቡ ዝርዝሮችን እየለያችሁ ባንድ ላይ መድቡ::
4. ስለአንቀጽ በተማራችሁት መሰረት የድርሰቱን የመጀመሪያ ረቂቅ ጻፉ::
5. የጻፋችሁትን የድርሰት ረቂቅ አንብባችሁ የስርዓተ ነጥቦችና የሰዋስው 6. ግድፈቶችን በማረም እንደገና ጽፋችሁ አቅርቡ::
6. ድርሰታችሁን ከሌላ ቡድን ጋር በመለዋወጥ ከሐሳብ ፍሰቱ ከድርጊትና ጊዜ ቅደም ተከተል አጠባበቁ ከስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀሙ አንጻር መርምራችሁ የቡድናችሁን አስተያየት ስጡ::

## ማጠቃለያ

ስለአንቀፅ ምንነት ባየንበት ክፍል አንቀፅን  በማዋቀር ሂደት ልናውቃቸው የሚገቡ ነጥቦች ለይተናል:: አንቀፅ ጽፈንም እርስ በርስ ተራርመናል:: በጽሁፋችን ውስጥ የስርዓተ ነጥቦችን ጠቀሜታ በተለይም በድርብ ሰረዝና በነጠብጣብ ላይ አተኩረን ተመልክተናል:: በጽሁፋችንም ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም ችለናል:: በመጨረሻም የተራኪ ድርሰት ምንነትን አወቀን ተራኪ ድርሰተ መፃፍ ችለናል::

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ስለ አንቀፅ ምንነትና ባህሪ በተማራችሁት መሰረት በመረጣችሁት ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ::
2. ከዚህ ቀደም በራሳችሁ ወይም በጓደኞቻችሁ የደረሰ አንድ ገጠመኝ በማስታወስ አንድ ተራኪ ድርሰተ ጻፉ::
3. ለጻፋችሁት ድርሰተ ርዕስ ስጡ::

/አንቀፅ/

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

/ተራኪ ድርሰት/

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# ክፍል ሁለት

## ዲን: ሱዊፍት

ዲን ሲዊፋት የሚባለው የእንግሊዝ ደራሲ አዲስ አሽከር በቀጠረ ቁጥር እንዲህ ይለው ነበር:: እንድትፈፅማቸው የምለምንህ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው:: አንዱ የምለምንህ ነገር ምን ጊዜም ቢሆን በቤትህ ውስጥ ስትተላለፍ ከአንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ አንደኛው ክፍል ስትገባ በሩን እንድትዘጋ ነው:: ሁለተኛው የምለምንህ ነገር እንደዚሁ ሁሉ ካንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ ደጅ ስተሂድ የከፈትከውን ቤት ዘግተህ እንደትሄድ ነው::

አንዱ አገልጋይ ከእለታት አንድ ቀን ወደእሱ ዘንድ ቀርቦ እህቴ ልትዳር ነውና ለሰርግዋ እንድሄድ ፍቀድልኝ አለው:: ዲንሱዊፍትም ደስ እያለው ፈቀደለትና እሱ ከሚቀመጥባቸው ፈረሶች አንደኛው ተጭኖበት አንድ ሌላ አገልጋይ ተከትሎት ሄዶ ከቤቱ አድርሶት እንዲመለስ አዘዘ:: አገልጋይም ከደስታ ብዛት ጌታው ያስጠነቀቀውን ትእዛዝ ዘንግቶ በሩን ከፍቶ ሳይዘጋው ሄደ:: ከሄደ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ዲን ሌላ አገልጋይ ጠራና ፈረስ ጭነህ ጋልበህ ድረስባቸውና ምንም ያህል ርቀው ቢሄዱ ከደረሱበት ቦታ  ተመልሰው በፍጥነት እንዲመጡ ንገራቸው ብሎ ላከው::

የተላከው አገልጋይ በፈረስ ጋልቦ ግማሽ መንገድ እንደ ሄዱ ደረሰባቸውና የጌታቸውን ትዕዛዝ ነገራቸው:: ፈቃደ ተቀብሎ የነበረው አገልጋይ ምክንያቱ ምን ይሆን እያለ ደንግጦ እየሰጋ ተመልሶ መጣ ከጌታው አጠገብ ቀረቦ እነሆ ተመልሼ መጣሁ ትዕዛዙን ይሰጡኝ አለው:: ዲንሱዊፍት አይ የጠራሁህ ለሌላ ነገር አይደለም:: ከፍተህ ትተኸው የነበረውን በር ዘግተህ እንድትሄድ ነው:: ብሎ መለሰለት::

**የሚከተለው አንቀጽ ስርዓተ ነጥቦች የሚገቡባቸው 14 ክፍት ቦታዎች አሉት:: የቀረበውን ታሪክ በጥንቃቄ በማንበብና የተሰጡት 4 ስርዓተ ነጥቦች የት ቦታ እንደሚገቡ በማጤን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በክፍት ቦታዎች ላይ ሙሉ::**

1. አራት ነጥብ /:: /　　　　3. ቅንፍ (   )

2. ነጠላ ሠረዝ / ፣/　　　　4. ትዕምርተ ጥቅሰ /   /

በጣሊያን ወራራ ዘመን ለሀገራቸው ነፃነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር 1 ዘርጋናጂ 2 ቁመቱ ረጅም 3 አጥንቶቹ ሰፋፊ 4 መልከ ቀይ 5 ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሶስትዮሽ የተሸረበ ነበር6 ያ ፀጉሩ በጀርባውና በትከሻው ላይ ተንዥርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናፅፈዋል 7 ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆን 8 ጠቅላላ ገፅታው የሰው አይን የሚማርክ ሸበላ 9 ቆንጆ 10 ነበር ዘርጋ ለአራት ዓመታተ ያህል በዋሻና

በጫካ ውስጥ ሲኖር 11 ሹርባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር 12 በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሟት ያየችው ሴት ሁሉ 13 አይኔ ይፍሰስልህ ሳትል አታልፍም ነበር 14

/ዓለም እሸቱ አለማየሁ ኑራን በመጥቀስ 1999 24/

**በቀረበው ፅሁፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ትክክለኛ ፍቺያቸውን ምረጡ::**

1. አገል.ጋይ ሀ. ሰራተኛ ለ. ተቀጣሪ
   ሐ. ጡረተኛ መ. ሀ ና ለ መልስ ይሆናሉ::
2. አዘዘ ሀ. መመሪያ ሰጠ ለ. አዘነ
   ሐ. ተቆጣ መ. ሄደ
3. ዘንግቶ ሀ. አስታውሶ ለ. ረስቶ
   ሐ. አስተውሎ መ. ተገንዝቦ
4. እየሰጋ ሀ. እያሰበ ለ. እየተጨነቀ
   ሐ. እየፈራ መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ
5. እንድትፈፅማችው ሀ. እንድታከናውናቸው ለ. እንድትፈራቸው
   ሐ .እንድትተዋቸው መ. እንድትነግራቸው

**ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ አንቀጽ ፃፉ**

ሀ. ፈረስ ግልቢያ

ለ. የምሳ ግብዣ

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

**የእህቴ ሠርግ በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰት ፃፉ**

# ክፍል ሶስት

# አይናለም

ቀደም ሲል አይናለም ከሰገነቱ ላይ ቆማ በምሽት ጀንበር ብርሃን ጋዜጣ ስታነብ አያት ልቡ ካለችበት ዘላ ከጉሮሮው ላይ የተወተፈች ይመስል ትንፋሹ ታነቀ:: ጀንበሯ ሳትጠልቅ ትንሽ እንድትቆይ ሊማለድዋት የሚፈልጉ ይመስል ርግቦች ከጣራው ላይ እየተነሱ ወደ ጀንበርዋ አቅጣጫ ይበሩ ነበር:: አይናለም ነጭ ጉም በመሰለው የሃገር ልብስም ነጠላዋን ክንፍ አድርጋ እያውለበለበች የምትበር መስላ ትታየው ነበር:: ነፍስ የበተነው ጠጉርዋ የምሽት ጀንበርዋን ብርሃን እየጋረደ:: በደኑ ነበር ያንን ስሞተኛ የእንጨት ደረጃ የወጣው:: ደረጃው ሳይሆን ልቡ የሚያቃስት ነበር የሚመስለው::

ፊታውራሪ አሉ የሉም::

የት እንደሄዱ ለመጠየቅ አልፈለገም:: ፊቷ ላይ የሚተረማመሰው ደም ልቡን አተረማመሰበት:: በሚንቀጠቀጡት ከንፈሮቹ ምንድን ነው የምታነቢው አላት አሮጌ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቅጂ መሆኑን እያወቀ አሮጌ ጋዜጣ አለም ሁሉ ወደ ሙዚቃ ተለውጦ የእለቁ ወንዝ እየተዘፈነ የሚወርድ ዛፎች ሁሉ እየዘፈኑ ዳንኪራ የሚረግጡ ይመስለው ነበር::

አዲስ ጋዜጦች አምጥቼልሻለሁ… እ…. ጥቂት መጻህፍት ይገፍልሽ መጥቼ ነበር ብሎአት ጋዜጦቹንና መፃህፍቱን ሊሰጣት እሱ ሁለት እጆቹን ሲዘረጋ እርስዋም ለመቀበል እጆቿን ስትዘረጋላት ድንገት እጆቻቸው ተያያዙ::

/በዓሉ ግርማ ሐዲስ 1982 ገጽ 126/

I. በቀረበው ጽሁፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ትክክለኛ ፍቺዎቻቸውን ምረጡ::

1. ማለዳ ሀ. ለመነ ሐ. በጣም ጣት
   ሐ. ጠጅ ጠና መ. ሀ ና ለ መልስ ይሆናሉ::
2. ሰገነት ሀ. የፎቅ ቤት በረንዳ ለ. ባለአንድ ፎቅ የገጠር ቤት
   ሐ. ከፍ ብሎ የተሰራ ቦታ መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ::
3. መንቀጥቀጥ ሀ. መርበድበድ ለ. መራድ
   ሐ. መፍራት
4. መወተፍ ሀ. መሸጥ ለ. አስገባ

ሐ. ቀረቀረ መ. መወርወር

5. ተተረማመሰ ሀ. ሁከት ለ. ግርግር

ሐ. ሽብር መ. ደብልቅልቅ

II. ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች የያዙት ፅንሰ ሀሳብ ሳይዛባ በእያንዳንዱ አረፍተ ነገር ጎን የተሰጡትን ሀረጎች መነሻ በማድረግ በራሳችሁ አባባል ጻፏቸው::

1. በድንገት ጉሮሮው ላይ… /ልቡ ካለችበት ዘላ ከጉሮሮው ላይ የተወተፈች ይመስል ትንፋሹ ታነቀ/

-----------------------------------------------------------------------------------------------

2. ልቡን ያተረማመሰበት…. /ፊትዋ ላይ የሚተረማመሰው የምሽት ጀንበር ብርሃን ልቡን አተረማመሰበት/

-----------------------------------------------------------------------------------------------

3. እየዘፈኑ ዳንኪራ……… /ዛፎች ሁሉ እየዘፈኑ ዳንኪራ የሚረግጡ ይመስለው ነበር::/

-----------------------------------------------------------------------------------------------

4. በድንገት እጆቻቸው የተያያዙት….. /እርስዋ ለመቀበል እጆቿን ስትዘረጋለት ድንገት እጆቻቸው ተያያዙ::/

-----------------------------------------------------------------------------------------------

5. የምሽት ጀንበርዋ ብርሃን…….. /ነፋስ የበተነው ፀጉሯ የምሽት ጀንበሯ ብርሃን እየጋረደ::/

---

III.ቀጥሎ የተሰጡትን አያያዦች በመጠቀም የቀረበውን ጽሁፍ ከ60 ቃላት ባልበለጠ ማጠቃለያ ጻፉ::

| | | |
|---|---|---|
| ወዲያውኑ | | |
| በዚህ ሳቢያ | በተለይ | ይሁን እንጂ |
| በዚህ ሁኔታ ሳሉ | በመጨረሻው | እንዲያውም |
| ከፍ ሲል | | |
| ይሁን እንጂ | አሁኑኑ | እንዲሁም |
| ከሁሉም በላይ | በእርግጥም | ዛሬ ግን |

## ክፍል አራት

## ለወሬ ምትኩ ይበሉ

ጢት ማታ ከመኝታዬ ተነስቼ ፊቴንና እጆቼን ታጥቤ ወደ ሳሎን እንደገባሁ ሬዲዮኔን ከፍቼ ዜና መስማት የቆየ ልማዴ ሆኗል:: የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን እንዲሁም ሌሎች የሀገራችን ሬዲዮ ጣቢያዎችን ቢቢሲንም ሆነ ቮይስ ኦፍ አሜሪካን ዶቼቬሌንም ሆነ ሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናልን ወይም ሌላ ሬዲዮ ጣቢያ ስከፍት አሜሪካን አገር ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት የሚገሰግሰው አውሎነፋስ ከባድ ጉዳት አደረሰ…..

ጃፓን ከፍተኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ደረሰበት የመሬት መንቀጥቀጡ ሱናሚም ያስከተለ ነበር

ሕንድ አገር ውስጥ የመሬት ነውጥ ተከስቶ ብዙ ህዝብ አለቀ….

ቻይና ውስጥ በተወሰነ አካባቢ ርእደ መሬት ደረሰ::

የሚሉ እና ሌሎችም የተለያዩ ዜናዎች በየጊዜው አገኛለሁ:: ለኔም ይሁን እንደኔ ላሉት እንዲህ አይነት ዜናዎችና ሌሎችም ምን ይረቡ ይሆን?

የሰው ልጅ ሕይወት ተመሳሳይነት ስላለው ይሆን በሌሎች አገሮች የተከሰተውን ዜና ለመስማት ጉጉት የሚያድርብን ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለው አደጋ ወይም ጉዳት በኔም አገር ሊከሰት ይችላል በሚል ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ፍራቻ የዓለምን ዜና የምንከታተል ይመስለኛል::

በተጠቀሰው ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት እኔ ብቻ ሳልሆን የመላው ዓለም ህዝብ ወሬ ፍለጋ በነጋ በጠባ ሬዲዮ እንደሚጎረጉር ቴሌቪዥን እንደሚከፍት ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ገዝቶ እንደሚያነብ አውቃለሁ:: የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንደሚከፍት ጋዜጦችነ መፅሔቶችን ገዝቶ እንደሚያነብ አውቃለሁ:: የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን መቼ በተፈጠሩ ነበር ጋዜጠኝነትስ መቼ በተጀመረ ነበር፡፡

ስለ ሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ሳነሳ አንዲት ሴት ወይዘሮ ትዝ ይሉኛል:: እኚህ የመስሪያ ቤት ባልደረባዬ ቀልደኛ ብጤ ነበሩ:: ሁለታችንም እየተከባበርን የምንጠራው በአንቱታ ነበር::

ታዲያ እኚህ ቀልደኛ ሴት ወይዘሮ አልፎ አልፎ ቢሮዬ ድረስ ይመጡና እየሳቁ ለወሬ ሞትኩ ይበሉ::… የምነግሮት አለኝ ይሉኛል:: እኔም ፈገግ ብዬ የሚነግሩኝ ካለዎት እንዲሁ ይንገሩኝ እንጂ እኔስ ለወሬ ምትኩ አልልም እላቸዋለሁ:: ወሬያችንን እንዲህ

በሳቅ ከጀመርን በኋላ አንዳንድ አዳዲስ የሰሙትን ነገር አውግተውኝ እኔም ስለአጫወቱኝ ነገር አመስግኛቸው እሳቸውም ወደ ቢሮአቸው ይመለሳሉ::

እንደጥንቱ አባባል እንኳ ለወሬ የለውም ፍሬ ይባል ነበር ነገር ግን ይህ አባባል በዛሬው ዘመን ተቀባይነት አይኖረውም:: ይልቁንስ በዘመናችን የተለያዩ ወሬዎች መረጃዎች ስለሆኑ ያ ለመረጃ ያለ ወሬ መኖር የለም ቢባል ተቀባየነት ይኖረዋል::

በኢትዮጵያ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ዮናታን ዲምብልቢ የተባለው ዜና አቅራቢ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወሎ ውስጥ በድርቅ ምክንያት እንደቅጠል ሲረግፉ የነበሩትን አዛውንቶች ጎልማሶች ወጣቶችና ህፃናትን ፊልም አንስቶ ተደብቆ የነበረውን የረሃብ ዜና ይፋ ባያወጣው ኖሮ የ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የኢትዮጵያ አብዮት ይከሰት ነበር ብሎ መገመት አይቻልም:: በእርግጥ ለአብዮቱ መቀጣጠል ሌሎች በርካታ ምክንያቶች ነበሩ:: ለወሬ የለውም ፍሬ የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጊዜ ያለፈበት መሆኑን የሚያስረዳን ይህ የተጠቀሰው ሌሎች እርምጃዎችን ያስከተለ ዜና ነው::

/ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም 1992 102-104 ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ/::

1. ጽሁፉን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በሰንጠረዥ ለተቀመጡት የተለያዩ ቃላት ወይም አገላለጾች ከተሰጡት ሁለት ሁለት ፍቺዎች መካከል ትክክለኛውን አውዳዊ ፍቺ በስሩ በማስመር አመልክቱ:: እያንዳንዳችሁ የሰጣችሁትን መልስ በጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩበት

| ቃላት/ሐረጎች | ፍቺ አገላለፅ |
|---|---|
| ሳሎን | የማረፊያ ቤት ፣ የመኝታ ቤት |
| ርዕደ መሬት | የመሬት መንቀጥቀጥ የመሬት መንሸራተት |
| የተከሰተው | ያጋጠመው ፣የኮሰሰው |
| መላው | ብልጠቱ፣ አጠቃላይ |
| ባልደረባዬ | የስራጓደኛ ፣የትዳር ጓደኛ |
| አውግተውኝ | ሞግተውኝ ፣ነግረውኝ |
| መቀጣጠል | መነሳሳት ፣መያያዝ |
| የሚገሰግሰው | የሚጣደፈው ፣የሚባክነው |
| ምን ይረቡ ይሆን | ምን ያስደስቱ ይሆን፣ ምን ያሳዝኑ ይሆን |
| የማወቅ ፍላጎት | ጉጉት ፣ተስ ፋ |

1. **በምድብ "ሀ" ለተዘረዘሩት ቃላት/ሐረጎች ከምድብ "ለ" የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ::**

| ***ሀ*** | ***ለ*** |
|---|---|
| --------- 1. ነጋጠባ | ሀ. አንዳንድ ጊዜ |
| --------- 2. መቼ በተፈጠረ ነበር | ለ. የማይረባ |
| --------- 3. በአንቱታ | ሐ. በብዛት ሲሞቱ |
| --------- 4. አልፎ አልፎ | መ. ተጫዋች |
| --------- 5. ቀልደኛ ብጤ | ሠ.በተሰራ |
| --------- 6. አውግተውኝ | ረ. ሽማግሌዎች |
| --------- 7. ለወሬ የለውም ፍሬ | ሰ. ሁል ጊዜ |
| --------- 8. እንደቅጠል ሲረግፉ | ሸ. አጫወተውኝ |
| --------- 9. ይፋ ባያወጣ | ቀ. ባይገልፅ |
| --------- 10. አዛውንቶች | በ. በመከባበር |

3. ለወሬ የለውም ፍሬ በሚል ርዕሰ ከ70 ቃላት ያልበለጠ  አንድ ተራኪ ድርሰት ፃፍ::

# ክፍል አምስት

## ግርግር

*በዚህ ግርግርና ውዥንብር ውሰጥ ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው? ጧት ባህር ላይ ተንሳፊፌ መገኘት አልፈልግም:: እንደ መጽሀፍ ለህይወቱ የሚጨነቅ እና የሚሰጋ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም:: የጠጣሁት ሁለት ቢራ ስራውን ሰራ መሰለኝ አድሮብኝ የነበረው ድካም ለቀቀኝ:: ምሽቱ ገና ለጋ ነበር:: ምፅዋ ላይ ሲመሽ ነውና የሚነጋው በጊዜ ሄዶ መተኛት ሀጢያት መስሎ ስለታየኝ መፅሀፊ ዳንኤልን ትቼ ጋዜጤኞችን ፍለጋ ወጣሁ::*

*እየዞርኩ በየቡና ቤቱ ፈለኳቸው:: ጋዜጠኞች የትም አልነበሩም በመቶ የሚቆጠሩ መኪናዎች ወደ ጉርጉሱም ባህርዳርቻ ሲሄዱም ከዚያም ሲመለሱም መንገዱ ላይ ይታይ ነበር:: የድንኳን ከተማው ሺ ደመራ ተደምሮ የተቀጣጠለበት መስሏል:: ጭፈራውና ዘፈኑ ይቀልጣል:: ቀዝቀዝ ያለው አየር ከጭፈራው እና ከዘፈኑ ጋር ተደማምሮ መንፈስ ያድሳል:: ቅርብ መስሎ ከሚታየው ጥቁር ሰማይ ላይ የፈሰሱት ከዋክብት በደስታ የሚደንሱ ይመስላሉ:: እና የተይባህር ማዕበሎችም ያረግዱ ነበር:: አንዳንዴ ማእቦሎቹ ፀጥ ሲሉ በየቦታው የሚነደው እሳት ነፀብራቅ ዘመነዊ ሰዓሊ የሳለው የህይወት ጥላ የሚመስሉ ዝብርቅርው ጥላዎች ባህሩ ወለል ላይ ይፈጠራል::*

*በዚህ ግርግርና ውዥንብር ውሰጥ ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው?*

*አሁን እንዲያው ከተፈጥሮ የበለጠ ስዕል የት ይኖራል? እያልኩ የባህሩን ጠርዝ ይዤ እየተከዝኩ ሳዘግም አንዲት ልጅ ብቻዋን ካንድ ጠርብ ድንጋይ ላይ ቆማ ማዶ- ሰማይና ባህሩ የሚመሳሰሉበትን አድማስ ስትመለከት አየሁ:: ባህሩ የቆመችበትን ድንጋይ እያጠበ ይመልሳል:: ከባህር የሚመጣው ቀዝቃዛ አየር ጠጉሯን እያነሳ አየር ላይ ይነሰንሰው ነበር:: በቁጭን መያዣ ክብ ትከሻዋ ላይ ተንጠልጥሎ ጀርባዋን ገልጦ የሚያሳይ ነጭ አጠር ያለ የበጋ ቀሚስ ለብሳለች:: የባህርን አምላክ የምታመልክ ነጭ ርግብ መስላ ታየችኝ:: ፎቶግራፍ ማንሻ ምነው በያዝኩ ኖሮ አልኩ:: ከድንኳኖቹ መንደር የተተኮሰው ርችት ጥቁር ሰማይ ላይ ድንገት ሲፈነዳ በሺ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ አበባዎች ጨለማው ላይ ረገፉ:: ደንግጣ ዞር ስትል መልኳ ታየኝ:: ከሩቅ ተወርውሮ የሚመጣው የኤሌክትሪክ ብርሃን ትንሽ ትንሽ ያሳያል እሷ ትሆን ወይስ አይደለችም እያልኩ ተጠጋኋት እሷ ነበረች::*

/*በዓሉ ግርማ ኦሮማይ* 2001:199-200/

**መልመጃ**

1. **የቀረበውን ጽሁፍ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በሰንጠረዥ ለተቀመጡት የተለያዩ ቃላት ወይም አገላለፆች ከተሰጡት ሁለት ሁለት ፍቺዎች መካከል ትክክለኛውን አውዳዊ ፍቺ ከስሩ በማስመር አመልክቱ፡ በመቀጠል እያንዳንዳችሁን መልስ በቡድን ተነጋገሩበት::**

| ቃላት/ሀረጎች/ | ፍቺ /አገላለፅ |
|---|---|
| ውዥንብር | የተሳሳተ እምነት ሐቅ |
| ለጋ | መታ ቀለል ያለ |
| መንሳፈፍ | መዋኘት መሞት |
| አረገደ | አናጠረ አረገ |
| ግርግር | ወከባ ሁከት |

2. **የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን አለባቸው::**

1. ጭፈራውና ዘፈኑ -------------------------/ቀለጠ/::
2. ከዋክብት በደስታ ------------------------ ይመስላሉ /ደነሱ/::
3. ማዕበሎቹ ፀጥ ሲሉ --------------- የሚነደው እሳተ ነፀብራቅ ልብን ያስደስታል:: /ቦታ/
4. በዚህ ግርግር እና ውዥንብር ውስጥ ምን --------- ነገር አለ /ሆን/
5. የቀይ ባህር ማዕበሎችም ---------- ነበር:: /ያረግዱ/
6. አጠር ያለ የበጋ ቀሚስ -------------- /ለበሰ/
7. የባህርን አምላክ --------------- ነጭ እርግብ መስላለች:: /አመለከ/
8. የተተኮሰው ርችት ድንገት ------------ ደነገጥኩ:: /ፈነዳ/
9. የሰማዩን አድማስ ------------- አያት:: /መመልከት/
10. ልዩ ልዩ አበባዎች ---------------- ላይ አብበው ይታያሉ:: /መስክ/

አበባ በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፍ

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

11. የገበያ ግርግር በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰተ ፃፉ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

# ክፍል ስድስት

## ሰብለወንጌል

ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩ አይነት እንደዚህ እየተወያዩ እውነትሽ እውነትህ ሲባባሉ ልጃቸው አስራ ስድስት አመት እሰኪሆናት ድረስ ጠያቂዋ አባት እናትዋን እረፍት ከልክሎአቸው ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን ትንሽ በትንሽ እየተረሳች ሄደች:: አንዳንድ ጠያቂዎች እንኩዋ አልፌው አልፌው ቢመጡ አንዳንድ ጊዜ እንደሚደርገው ቆሞ ቀር ከሚባሉት ተቆጥራ በፈትነት እንጂ በልጃገረድ ስራት ለማግባት የሚጠይቅ ጠፉ::

ሰብለ ወንጌል ባል ሳታገባ ጊዜም በማለፉ የመንደሩ ሰው ሽሙጥና ሀሜት በሄደችበት ሁሉ አንገቷን ቀና አድርጋ ሰው ለማየት ያሳቅቃት ነበር:: አንድ ቀን ከእናትዋ ጋር እቤተክርስቲያን ቆማ ስታስቀድስ:

እባክሽ እባክሽ እይልኝ የጌቶችን ልጅ እናትዋን እኮ አከለች:: አለች ደብሪቱ የምትባለዋ ከመንደሩ አሽማጣጮች አንድዋ::

ምነው እናቷን አከለች ትያለሽ ከናትዋ በለጠች በይ እንጂ ዳሌዋንና ደረትዋን አታይም አስር የወለደች መሰለች:: አለች ጓደኛዋም ስንዱ እኚህ አባትዋ ምን ሊያደርጓት ነው አስረው የሚያወፍሯት አርደው ይበሏት ይመስል ወዲያ ላንዱ አይሰጧትም እንዴ አሁን እማ ለማን ይስጡዋት ጠያቂ ሲጠፋ የጠየቋቸውን ሁሉ አታክሉንም አትመስሉንም እያሉ ሲያባርሩ ኖረው አሁን ጠያቂ አጡ::

ኸረ ፊታውራሪ አሰጌ ጠይቀዋል አሉ አለች ደብሪቱ የሽሙጥ ሳቅ እየሳቀች::

የትኛው አሰጌ?

እኚህ የቢቾናው ፊታውራሪ አሰጌ::

ምን ልጅ አላቸው?

ለራሳቸው ነው እንጂ ምን ልጅ አላቸው::

ለራሳቸው ኸረ የዲማው አባቴ የልጅ ልጃቸው አትሆንም

እንዲያውም ይግረምሽ በልጃገረድ ስም አላገባም ብለው ሳያፈርሱ አይቀርም ይባላል::

/ሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከመቃብር 2001 ገፅ 87-88/

**መልመጃ**

I. የሚከተሉትን ሀሳቦች በምሳሌው መሰረት ጽሁፍን በመንተራስ በአንድ ቃል ገልጿቸዋል::

ምሳሌ: በፈጣን ሩጫ አመለጠ ----------- ፈረጠጠ

1. የወለዱትን ልጅ ለቤተክርስቲያን አሳልፎ መስጠት---------
2. ሰብለወንጌል 24 ዓመት ሳታገባ መቅረቷ ምን ያሳስባታል-------------
3. ከባለቤቷ ጋር ተለያይታ ብቻዋን የምትኖር ሴት----------
4. እባክሽ እባክሽ እይልኝ እናቷን አከለች::--------------
5. ቀና ብሎ ሰውን ለማየት ግራ መጋባት ---------------
6. አስር የወለደች መሰለች:: አለች -----------------
7. ሰብለወንጌልን ለጋብቻ ጠየቀዋል::-------------
8. ፊታውራሪ መሸሻ እና ወ/ሮ ጥሩ ዓይነት::-------------
9. ከዚያ በኋላ ግን ትንሽ በትንሽ እየተረሳች ሄደች--------------
10. የትኛውን አሰኜ-------------

**II. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ:: የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን ይኖርባቸዋል::**

1. ልጃቸው ------------ ብዙ አመት አለፉት:: /አገባ/
2. በልጃገረድ ስም አላገባም ብለው ---------------- አይቀርም:: /አፈረሰ/
3. አስራስድስት አመት እስኪሆናት ድረስ ---------- ቤተሰቦቿን እረፍት ነስተው ነበር:: /ጠየቀ/
4. ሰብለ ወንጌል በትንሽ በትንሹ ----------- ሄደች /ተረሳ/
5. አንድ ቀን እቤተክርስቲያን ቆማ -------------- የሁለት ሴቶች ሀሜት ከጆሮዋ ደረሰ:: /ቀደሰ/
6. ሰብለወንጌል አንገቷን ቀና አድርጋ ሰው ለማየት----------- ነበር:: /መሳቀቅ/
7. ሳታገባ ከመቆየቷ የተነሳ አስር ------------- ትመስላለች:: /ወለደች/
8. የጠየቃቸውን ሁሉ ----------------- እያሉ ሲመልሱ ከረሙ:: /መጠነ/
9. ልጅቱ ቆሞቀር ከሚባሉት ---------------- ጠያቂም ጠፋ:: /ቆጠረ/
10. ልጅቱ ለሰውየው የልጅ ልጃቸው ------------- /ሆና/

III. ቆሞቀር በሚል ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ

IV. ያላቻ ጋብቻ በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰተ ፃፉ::

# ክፍል ሰባት

## ሱቄ

ጥር ላይ ከቡና ዑደት ጋር የሱቄ ስልት ህይወት ይለወጣል:: ቡና ለመሸምጠጥ ለመልቀም ለማድረቅ ለመፈልፈል ለማጠብና ለመጫነ የደቦ ስራ አይበቃም:: በሺ የሚቆጠሩ ሰራተኞች ያስፈልጋሉ:: ይህንኑ የሚያውቁ በዘኔዎች ከሰባትቤት ጉራጌ እና ከወሎ እና ከትግራይ በቡድን መጥተው ጊዜያዊ ስፍራ በማበጀት ስራ መጫረት ይጀምራሉ:: ቃላቸው ህግ ስለሚሆን በዋጋ የሚከራከራቸው የለም:: ያሉትን ዋጋ አሜን ብሎ ከመቀበል ሌላ አያዋጣም:: ቡና በጊዜ ተለቅሞ በጊዜ ገብቶ በጊዜ መሸጥ አለበት:: የጥር ቡና ገበያ ቆሞ ማንንም አይጠብቅም::

ዘላን ኮማሪዎች እና ሴተኛ አዳሪዎችም የቦዘኔዎችን እግር ተከትለው መጥተው የሻማ የኩራዝና የፋኖስ ሰፈር ያበጃሉ:: ያምቡላና ያተላ ሽታ ሶቄን ማወድ ይጀምራል:: እነዚህ ቤት ጠላ አለ በማለት የሚያመላክቱ በእንጨት ላይ የተሰኩ የተጨረማመቱ ጣሳዎች በየደጃፉ ሰልፍ ይቆማሉ:: ጠጅቤቶች እና ጠላቤቶች ካፍ እስከ ገደፋቸው በሰው ጢም ብለው ይሞላሉ:: ያተረፈው ተደስቶ ይጠጣል:: ሁሉም ይጠጣል ቡና ጀባ ቀሀጀባ የቡና ሼህ ዘንድ አደራ እያለ ከዘንድሮ የቡና ሰብል መጠንና ዋጋ ሌላ ወሬ አይሰማም:: ሁሉም ስለቡና ያወራል:: ሁሉም ስለቡና ይጠጣል::

ጉሮሮአቸው የሸሪሪት ድር አድርቶ ዝጎ ለደግ ቀን የመሰንቆዎቻቸውን ጭራዎች በባህር እጣን ሲያሙዋሹ የከረሙት አዝማሪዎች ጉሮሮአቸው በጠጅርሶ ግንባራቸው በአረንጓዴና በቀይ ብር አጊጦ እንዲያው ማቅራራት ማስካካት ይጀምራሉ::

ያገዳ ጥንቅሽ መጠው ያደጉ ቅልብ የሀረር ሰንጋዎች የሚመስሉ የቡና መሬት ባለርስቶች በቡና ንግድ የከበሩና የወፈሩ ቱጃሮች ቱባ ቱባ ብር ተሸክመው ገንዘብ የተቸገረውን ሰው ከሩቁ የሚያሸቱ አራጣ አበደሪዎች ከዝናሽ ቡናቤት ይሰበሰባሉ::

/በዓለ ግርማ ሐዲስ 1982 ገጽ 122-123/

I. በምድብ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት /ሐረጎች ከምድብ "ለ" የሚስማማቸውን በመምረጥ አዛምዱ

------- 1. ይለወጣል　　　ሀ. ከጠጅ የሚቀር ዝቃጭ

------- 2. ያበጃሉ　　　ለ. የሚያሳዩ

------- 3. አምቡላ　　　ሐ. በደንብ ጠጥተው

------- 4. ማወድ　　　መ. ጢም ብሎ

------- 5. የተጨረማመተ　　　ሠ. የመሬት ባለቤት

